ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ኢየሱስ መሲሕ
ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ
<u>ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u>

የይሁዳው አንበሳ፡ ድል ነሣ!
እርሱም፡ በኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ፡ የአጼነት ሹመት ሥርዓት፡
የጽዮን ንጉሥ፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች ንጉሥ ኾኖ፡
በዘለዓለማዊው ክህነት የሚኖረው፡ ኢየሱስ መሲሕ ነው።

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
ድንግል ማርያም
እሙ ለአምላክነ፥ ወእምነ ዘዚአነ
<u>ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u>

በእግዚአብሔርነቷ፡ እጆቿን ዘርግታ የምትኖረው ኢትዮጵያ፣
የአምላክ እናትና የእኛም እናት፣
የጽዮን ንግሥት፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች
ንግሥት፡ እግዚአብሔር እም፥ ድንግል ማርያም ናት።

---

**ቍጥር ፲፪/፳፻፫ ዓ. ም.**

# ቃለ ዐዋድ!

## እምኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር።

# የዐዋጅ ቃል!

## ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

በስመ እግዚአብሔር አብወእም፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ
ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፤

በስመ እግዝእትነ፥ ወእምነ፥ ወሃይማኖትነ፥ ወሀገሪትነ፥
ወንግሥትነ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤

በኃይለ መስቀሉ፡ ዘእግዚእነ፥ ወአቡነ፥ ወመድኃኒነ፥
ወካህንነ፥ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ፡
ወልደ-እግዚአብሔር ሕያው፥ ወወልደ-ማርያም ሥግው።

ማለትም:-

በልዩ ሦስትነት፡ አንድ አምላክ በኾነው፡
በእግዚአብሔር አብወእም፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም፤

እናታችንና ሃይማኖታችን፥ አገራችንና ንግሥታችን፥
መድኃኒታችንም በኾነችው፡ አምላክን በወለደችው፡
በእመቤታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ስም፤

በአምላክነቱ እና በሰውነቱ፡ የእግዚአብሔር አብ እና
የእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ልጅ፥
አባታችንና ጌታችን፥ ካህናችንና ንጉሣችን፥ ሰላማችንም
በኾነው፡ በኢየሱስ መሲሕ፡ በመስቀሉ ኃይል።

\+ \+ \+

# ይድረስ፡-

በጌታዬ በፍቅሬ በእግዚአብሔር አብ፥
በልጇ በወዳጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፥
በሕይወቴ በመድኃኒቴ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡
የኹለንተና ልጆቼ ለኾናችሁት፥

ስሜ በተጠራባት፡ በኢትዮጵያ ምድር ላላችሁትና
በመላው ዓለም ለተበተናችሁት፥
በልዩ ልዩ ተግባርና ሙያም ለምታገለግሉ፥
በተለያየ የኑሮ ኹኔታና የሥራ መስክ ለምትገኙ፥

ይልቁንም፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ከሚለው፡
የመጀመሪያ መታወቂያችሁ ጋር፡
"የኢትዮጵያ ልጆች" የሚለውን የመጨረሻ ስም በመቀዳጀት፡
በቅዱሱ ኪዳን፡ ርስት ጒልቴ ለኾናችሁት፥

በአጠቃላይ፡ እንደኢትዮጵያ ሥርዓተ-መንግሥት፡
የቤተ-ሕዝቡ፥ የቤተ-ክህነቱና የቤተ-ምልክናው አባሎች ለኾናችሁት፡
ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያን እና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት ልጆቼ!

እንዲሁም፡
የሚሰማ መንፈሳዊ ጆሮና የሚያይ መንፈሳዊ ዓይን ላላችሁ፡
በምድር ላይ ለምትኖሩ፡ ለመላው የዓለሙ የሰው ወገኖች ፍጡሮቻችን፥
ለወንዶቹም፡ ለሴቶቹም፥ ለአዛውንቱም፥ ለወጣቶቹም፥
በየግላችሁም፥ ለኹላችሁም!

በአንድ አምላካዊ ፈጣሪነቱ፥ በሥላሴነት መለኮታዊ ቸርነቱም፡ ሙሽራውና እናቱ፥ መቅደሱም ባደረገኝ፡ በልዑል እግዚአብሔር ስም፡ ዘለዓለማዊው፡ የእናትነት ጸጋዬ፡ ፍቅሬና ሰላሜ፥ በረከቴና ረድኤቴ፡ በያላችሁበት ይድረሳችሁ!

እንዳለፈው፡ እንደ፲፩ኛው መለኮታዊ የዐዋጅ ቃሌ፡ ዛሬም፡ የምናገራችሁና የማናግራችሁ፡ እግዚአብሔር እናታችሁና ሃይማኖታችሁ፥ አገራችሁና ንግሥታችሁ፥ ክህነታችሁና መቅደሳችሁ፥ እመ-ቤታችሁና ምድረ-ርስታችሁ የኾንሁት፡ እኔው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ድንግል ማርያም ነኝ።

## መቅድም

በዚህ የዐዋጅ ቃሌ፡ "አዳም" ብዬ የምጠራው ወንድ፡ እንደአግባቡ፡ "ቀዳማዊ" የኾነውንና የሚባለውን፡ የመጀመሪያውን ሰብኣዊ ወንድ ፍጡር ብቻ አይደለም፤ ወይም፡ "ዳግማዊ" የኾነውንና የሚባለውን፥ በወንድነት ጾታ የተገለጠውን፡ የመጨረሻውንና ዘለዓለማዊውን፥ እውነተኛውንና መልካሙን፥ መለኮታዊውንና ትስብእታዊዉን ልጄን ወዳጄን፡ ኢየሱስ መሲሕን ብቻም አይደለም፤ ነገር ግን፡ እናንተን፡ እያንዳንዳችሁን ወንዶች ጭምር ነው።

እንዲሁም፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ፡ "ሔዋን" ብዬ የምጠራት ሴት፡ እንደአግባቡ፡ "ቀዳማዊት" የኾነችውንና የምትባለውን፡ የመጀመሪያዋን ሰብኣዊት ሴት ፍጡር ብቻ አይደለም፤ ወይም፡ "ዳግማዊት" የኾንሁትንና የምባለውን፥ በሴትነት ጾታ የተገለጥሁትን፡ የመጨረሻዋንና ዘለዓለማዊቷን፥ እውነተኛዋንና መልካሚቱን፥ መለኮታዊቷንና ትስብእታዊቷን፡ እኔን ራሴን፡ ድንግል ማርያምን ብቻም አይደለም፤ ነገር ግን፡ እናንተን፡ እያንዳንዳችሁን ሴቶች ጭምር ነው።

* መሲሕ (ግእዝ) = ክርስቶስ (ፅርዕ=ግሪክ)።

በቅድሚያ፡ ይህን ቍም-ነገር ካሳወቅኋችሁ በኋላ፡ ቀጥዬ ደግሞ የምገልጥላችሁ፡ ይህ መልእክት፡ በኣኹኑ ጊዜ እንዲተላለፍ፡ አስፈላጊ የኾነበትን ምክንያት ነው፤ እርሱንም፡ እንዲህ በሚል አጭር ሓተታ አሳውቃችኋለሁ፡-

በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ኢትዮጵያኛ ቋንቋ፡ "ጒድ!" የተሰኘው፥ በፈረንጆቹ፡ የእንግሊዝኛ ቋንቋም፡ "good" የሚለው፡ የሙገሳ ቅጽል ቃል የተሰጠው፡ "ግብረ-ሰዶም" ተብሎ የተሰየመው፡ ፀያፍ የሙስና ግብር ያመጣው፥ የወንድና ወንድ፥ የሴትና ሴት ኢ-ተፈጥሮአዊ የኾነው፡ እስከጋብቻ ያደረሰ፡ ሰይጣናዊው የመወዳጀትና የሩካቤ-ሥጋ ግንኙነት፥ ፅንሰ-አሳቡና አኗኗሩ ጭምር፡ "መልካምና ተገቢ፥ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው!" ተብሎ፡ "ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ" በምትባለው አገር፡ በመንግሥታዊ ዐዋጅ፡ ሕግ ኾኖ፡ በቅርቡ፡ በይፋ መጽደቁን፥ በገሃዳዊ ደረጃም፡ በተግባር ላይ መዋል መጀመሩን፡ በዚያው አገር የምትኖር፡ "ኅሪተ-ገብርኤል" ብለን የሰየምናት፡ አንዲቷ ኪዳናዊት ኢትዮጵያዊት የኾነች፡ ካህኒት ልጃችን፡ በአግራሞት ኾና፡ ስልክ ደወለች።

የደወለችውም፡ አዳምና ሔዋን በተፈጠሩባት፥ ከዚህ የተነሣም፡ እስከዛሬ፡ "**ኢትዮጵያ**" በምትባለው ምድር ወደሚኖረው፡ አንዱ፡ **የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ** አገልጋይ ልጃችን ወደኾነው፡ ወደኪዳናዊው ኢትዮጵያዊ ወንድሟ ወደኤርምያስ ነው።

አዎን! እኒህ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ልጆቻችን የኾኑት አገልጋዮቻችን፡ ኪዳናዊት እኅትና ኪዳናዊ ወንድም፡ በስልኩ ጥሪ አማካይነት፡ በጒዳዩ ላይ፡ በቃል መወያየታቸውን ከመጀመራቸው በፊት፡ ኤርምያስ፡ ይህን፡ የ"ግብረ-ሰዶም"ን አርእስተ ነገር በሚመለከት፡ ይህ፡ መልእክታዊ ዐዋጅ ተጽፎ ይታወጅ ዘንድ፡ መመሪያው፡ እንደተለመደው፡ ከ**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን**፡ በመንፈስ ቅዱስ ደርሶት፡ ይህን ዐዋጅ እያዘጋጀ በሚገኝበት ጊዜ፡ ይህንኑ፡ መንፈስ ቅዱሳዊውን መመሪያ የተከተለ ተጨማሪ መልእክት፡ ከዚህችው ኪዳናዊት ልጃችንና አገልጋያችን አንደበት ደግሞ፡ በስልክ ንግግራቸው መዝጊያ ላይ ተነገረው።

የእርሷም ቃል፡ "ወንድም ጋሼ! እባክህ! ይህንኑ የግብረ-ሰዶምን ነገር በሚመለከት፡ በጎዋ ሰሌዳችንና በፌስቡክ መድረካችን ላይ፡ ለኪዳናውያንና ለኪዳናውያት ብቻ ሳይኾን፥ ለመላዎቹ አንባቢዎቻችንና በመላው ዓለም ላይ ለሚኖረው የሰው ዘር ኹሉ ጭምር፡ ሊሠራጭና ሊደርስ የሚችል፡ በይፋ ምንባብነት የሚቀርብ፡ አንድ ዓይነት መግለጫ፥ ማብራሪያ፥ ወይም መልእክት፡ በአንተ በኩል፡ መዘጋጀት የሚኖርበት ይመስለኛል!" የሚል ነው።

የኹለቱ የስልክ ውይይት ካበቃ በኋላ፡ ኤርምያስ፡ ይህን የእርሷን ማሳሰቢያ፡ እንዳለፉት ጊዜያት ኹሉ፡ አኹንም፡ ከእኔ እየተቀበለ በመጻፍ ላይ ላለው፡ የዐዋጅ ቃሌ፡ ማጠናከሪያ መመሪያ መኾኑን ተገንዝቦ፡ ተልእኮውን እያካኼደ ባለበት፡ በዚሁ ጊዜ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ እንዲህ የሚለውን ቃል አስታወሰው፡-

"ጸሓፍ፡ ለዛቲ ቃል ዘነገሮ ለዮሓንስ ዘበዓለራእዩ፡ አሓዱ፡ እምነ እልክቱ ሰብዓቱ መላእክት፡ እለ ይፀውሩ ሰብዓተ ጽዋዓተ ዘመቅሠፍት፡ በዘቦቱ የኀልቅ መዓቱ ለእግዚአብሔር!

"የእግዚአብሔር ቍጣ፡ በእነርሱ ከሚፈጸመው፥ ሰባቱንም ጽዋዎች ከያዙ፥ ከሰባቱ መላእክት፡ አንዱ መጥቶ፡ ለባለራእዩ ለዮሓንስ የተናገረውን ቃል ጻፍ!"

መልአኩ፡ ለባለራእዩ ለዮሓንስ የተናገረውም ቃል፡ እንዲህ የሚል ነው፡- "ወይቤለኒ፡- 'ነዓ! አርኢከ ደይና፡ ለእንታክቲ ዘማ ዐባይ፡ እንተ ትነብር ውስተ ማያት ብዙኅ። እንተ ምስሌሃ ዘመዉ፡ ነገሥተ ምድር፤ ወሰክሩ፡ እለ ይነብሩ ዲበ ምድር፡ እምነ ወይነ ዝሙታ።'"

"'ና! በብዙ ውኆች ላይ የተቀመጠችውን፡ የታላቂቱን ጋለሞታ ፍርድ አሳይሃለሁ። የምድርም ነገሥታት፡ ከእርስዋ ጋር ሴሰኑ፤ በምድርም የሚኖሩ፡ ከዝሙቷ ወይን ጠጅ ሰከሩ!' ብሎ ተናገረኝ!" የሚለው ነው።
(ራእ. ፲፯፥ ፩፤ ፲፯፥ ፩-፪።)

አዎን! የምድር ነገሥታት፡ ከእርሷ ጋር እንዲሴስኑ፥ በምድርም የሚኖሩ ኹሉ፡ ከዝሙቷ ወይን ጠጅ እንዲሰክሩ ያደረገች፥ ከዚህ የተነሣም፡ እነሆ፡ የግብረ-ሰዶምን ሥራ፡ እንዲህ፡ በአገሯ፡ በመንግሥታዊ ዐዋጅ፡ ሕግ ኾኖ፡ በይፋ እንዲጸድቅ፥ በተግባርም ላይ እንዲውል ያደረገች፡ ይህችው፡ "ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ" የምትባለው አገር መኾኗ፡ ይኸው፡ በገሃድ እየታየና እየተረጋገጠ ነው።

ፀረ-እግዚአብሔርና ፀረ-ክርስቶስ፥ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ማርያም የኾነው፡ ይህ ዓይነቱ፡ የዚች አገር፡ አሳፋሪና አስነዋሪ ተግባር፡ በራሷ፡ በ"ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ" ምድር ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይኾን፡ ዋና ግቡ፡ ይኸው ቀሣፌ-ሕይወት የኾነው የኃጢአት ተግባር፡ "ሕዝባዊ አገዛዝ" (Democracy) በሚለው፡ አረማዊ ፍልስፍናቸው ሽፋን፡ በመላው የዓለም አህጉራትም ዘንድ ኹሉ፡ በዚሁ መልኩና ይዘቱ፡ እንዲስፋፋና እንዲሰፍን ለማድረግ ጭምር መኾኑ፡ በይፋ በሚነገር ቃላቸው ብቻ ሳይኾን፡ በይፋ ድርጊታቸውም ጭምር እየተረጋገጠ ያለ እውነታ መኾኑ፡ በኹሉ ዘንድ ይታወቃል።

ለዚህ ርኵስ ዓላማቸው፡ የተሳካ ውጤትን ለማስገኘት ደግሞ፡ ይህችው አገር፡ የምትጠቀምበት መሠሪ ዘዴ፡ ሎሌዎቿ ባለሥልጣናት፡ በየአገሩ በመሠረቱት ተቀማጭነታቸው ብቻ ሳይኾን፡ ርእሰ ብሔሮቿ ጭምር፡ በኢትዮጵያ ሳይቀር፡ ካገር ወዳገር እየተዘዋወሩ በሚያካኺዱት፡ የይፋ ጕብኝታቸው አማካይነት፡ የሚፈጽሙት ታላቅ የደባ ዘመቻ መኾኑን፡ አዎን! ዓለሙ ኹሉ ተገንዝቦ የተቀበለው እውነታ ነው።

*"ሕገ መንግሥቴ፡ በክርስትና ሃይማኖት ላይ የተመሠረተ ነው! የዚሁ ሕገ መንግሥቴ አመንጪዎችና አዘጋጆች፥ አጽዳቂዎችና ዐውዋጇዎች የኾኑት፡ የአገርነቴና የመንግሥትነቴ መሥራቾችም፡ ስለእውነተኛዋ የክርስትና እምነት ብለው፡ ከጨቋኞቹ፡ የአውሮጳ፡ የክርስቲያን አገሮች፡ የተሰደዱ ሰማዕታት ናቸው!"* እያለች፡ በግብዝነት የምትመጻደቀው፡ ይህችው፡ "ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ" የምትባለው አገር፡ በዚህ ረገድ ያላትን የማንነትና የምንነት ባሕርይ፡ እስኪ፡ በጥቂቱ ጠለቅ ብላችሁ እንድትመለከቷት ላድርጋችሁ!

"የእኔ አገሬ፥ ግዛቴ ነው!" በምትለው፡ በዚያ፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ምድር ላይ፡ በዚችው፡ **በእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ፡** የተፈጠሩ ብቻ ሳይኾኑ፡ ልጆቿና ነጋሢዎቿ፥ አገልጋዮቿና ዜጎቿም በኾኑት፡ የሕዝብና የአሕዛብ ወገኖች ላይ፡ ይህችው፡ "ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ"፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ከቶ ምን እያደረገች ነው? ምን እያደረገች እንደኾነማ፡ በማስተዋል ስሙ! እዩም!

በነገረ ቀደም፡ እግዚአብሔር፡ ሰውን የፈጠረው፡ በአንድነት መልኩና በሥላሴነቱ አርአያ መኾኑን፥ ይኸውም፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስም መኾኑን የማያውቅና የማያምን፥ በተለይ፡ ራሱን፡ ክርስቲያን ያደረገ ሰብአዊ ፍጡር፡ በአኹኑ ጊዜ፡"ይኖራል!" ብላችሁ አታስቡ ይኾናል። ነገር ግን፡ እውነታው ይህ አይደለም።

ይህን መለኮታዊ ሕያው ሕንጻ የኾነውን፡ አንዱን ሰው ነው፡ ፩ኛ፡ ከሦስቱ አካላትና ባሕርያት መካከል፡ ሉዓላዊ የኾነው <u>መንፈስ</u> እንደሌለው፥ "በነፍስና በሥጋ" ብቻም እንደተፈጠረ፤ ፪ኛ፡ እነዚሁ ነፍስና ሥጋም፡ ከኹለት እንደተከፈሉ በመቁጠር፡ "ይህ፡ የሥጋ ነው! ይህ ደግሞ፡ የነፍስ ነው!" እያለች፡ እነዚያ፡ "ፍትሓ ነገሥት" የተባለው መጽሓፍ አዘጋጆች ካህናት፡ በ፬ኛው ምእት ዓመተ-ምሕረት፡ ለቄሣሩ ቆስጠንጢኖስ የሰጡትን ፀረ-እግዚአብሔርና ፀረ-ክርስቶስ፥ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ማርያም የኾነውን ሓሳዊ መመሪያ በማጽናት፡ የለያየችው፡ ይህችው፡ "ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ"፡ ናት።

ከዚሁ፡ ከ"ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ"፡ ስሑት አቋም የተነሣም፡ ከእርሷ ቀደምት ኾነው የተቋቋሙትን፡ የመሰሎቿን ሰብአውያን መንግሥታት፡ ክፉና ጥፉ አርአያነት በመከተል፡ የእኛ፡ የፈጣሪ ብቸኛ ሀብት የኾነችውና በምሥጢረ ተዋሕዶ ሥላሴነታችን የተከወነችው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን** እንኳ ሳትቀር፡ መንፈሳዊ አገልግሎቷን፡ ለሕዝቦቻችን የምታበረክትባትን፡ የቤተ ክህነት ዘርፏን፡ ከቤተ-ሕዝቧና ከቤተ ምልክናዋ ለይታ በማስወገድ፡ "Church and State"፡ ማለትም፡ "ቤተ-ክህነት እና ቤተ-መንግሥት" ብላ፡ ከኹለት የከፈለችው፡ ይህችው፡ "ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ" ናት።

***ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡*** "እኒህ ሰብኣውያን ፍጡሮቻችን፡ ሕይወታቸውን ጠብቀውና አንከባክበው፡ በመልካም እያካኼዱ ሊኖሩ የሚያስችላቸው፡ ተገቢውና እውነተኛው ሥርዓት፡ በዚህ፡ በእግዚአብሔራዊው የተዋሕዶ ሥላሴነታቸው ተፈጥሮ፡ ማለትም፡ በአንድነታቸውና በሦስትነታቸው ህላዌ ጸንተውና እርሱን ተከትለው ሲገኙ ብቻ ነው!" ስትል፡ ይህችው፡ "ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ" ግን፡ "የለም! አይደለም! እንዲህ ሳይኾን፡ በዲያብሎሳዊው ሰው-ሠራሽ ኹለትነት ተከፍለው ነው፡ ሊኖሩ፥ ሊካኼዱም የሚገባቸው!" እያለች ነው፡ በሓሳዊው ዕውቀቷ፥ ትምህርቷና ስብከቷ፥ በዕዳ በማሰነ ገንዘቧ፥ ቈሳቍሷና የጥበብ መሣሪያዋ፥ በኪነት በተራቀቀው፡ የምድር፥ የባሕርና የአየር ጦር ኃይሎቿ በመመካትና በመጠቀም፡ ይህን፡ የሓሳዊ መሲሕ ዓላማዋን እያወጀችና እያስፋፋች ያለችው።

ይህም እውን ኹኔታ፡ በአጠቃላይና በመላው ዓለም፥ በተለይ ግን፡ "ክርስቲያን ነኝ!" በሚለው በግብዙ ዓለም ዘንድ፡ በይፋ መታወቁ ብቻ ሳይኾን፡ በይፋም እየተሠራበት መኾኑ ጭምር፡ ከማንም የተሠወረ አይደለም። አንድ ሰብኣዊ ፍጡር፡ በሕያው ህልውናው፡ በዚህ ኹኔታና ድርጊት፡ ለአንዲት ቅጽበት እንኳ ሊቀጥል እንደማይችል እየታወቀ፡ "ሥጋህን እና ነፍስህን፡ ለያይተህ ለመኖር በመሞከር፡ ህልውናህን ለማራዘም፡ ጣር! ጋር!" የማለት ያህል መኾኑ፡ ግልጽ ነው።

ይህችው፡ "ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ"፡ መላዋ ምድራዊት ዓለም፡ ***የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ*** መኾኗን፡ እንዲህ፡ ፈጽማ ክዳ፥ "አምንበታለሁ! እመራበታለሁ! የሃይማኖቴ መሠረትና መገለጫም ነው!" በምትለው፡ በቅዱሱ መጽሓፍዋ ውስጥ የተመዘገበውን፡ ***"እስመ ለእግዚአብሔር መንግሥት"፡*** ማለትም፡ ***"መንግሥት፡ የእግዚአብሔር ብቻ ናት!"*** የሚለውን፡ የእግዚአብሔርንም ቃል አፍርሳ፡ "ሕዝባዊ አገዛዝ" (Democracy) በሚለው፡ አረማዊ ፍልስፍናዋ እየተከራራችና እየደነፋች፡ "የለም! መንግሥትማ፡ የእኛ የሰዎች ነው እንጂ፡ የእግዚአብሔር አይደለችም!" የሚል፡ የማናለብኝ ድፍረቷን፡ እነሆ፡ አጽንታው እንደቀጠለችበት፡ ይኸው፡ በገሃድ ድርጊቶቿ ይታያል።

በእርሷ ዘንድ፡ "ቀይ ሕንዶች" (Red Indians) የሚባሉት፥ ***በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ ግን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ፡*** ሰብኣውያን ፍጡራን፥ ልጆችና ነጋሢዎች፥ አገልጋዮችና ዜጎችም በኾኑት የሰው ወገኖች ላይ ስትፈጽም የኖረችው፥ ዛሬም እያካኼደች ያለችው፡ ግፍና በደል፡ በዓለሙ ኹሉ ዘንድ የታወቀ ነው። የገዛ እምነታቸውን አጽንተውና ተከትለው፡ በሰላምና በሥርዓት ይኖሩ የነበሩትን፡ እነዚህኑ የሰው ወገኖች የኾኑ ፍጡሮቻችንን፡ ከባለመብትነታቸው ብቻ ሳይኾን፡ ከህልውናቸው ጭምር ለማስወገድ ተብሎ፡ በተራቀቀ ስልት፡ የደረሰባቸው፥ አኹንም እየደረሰባቸው ያለው ሥቃይና ዕልቂት፡ ምንጊዜም የሚዘነጋ አይደለም።

በአኹኑ ጊዜ፡ ከዚያ የጭካኔ ጥቃት በተረፉት፡ በእነርሱ ወገኖችና በቀሩትም፡ የመልክና የዘር ጠንቀኛ ጥቃት ሰለባዎች በኾኑት፡ **የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ** ፍጡሮች ላይ፡ ይህችው፡ "ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ"፡ በኢፍትሓዊነትና በግልጽ ድፍረት የምታካኺደውን፥ ከዚህም ርእሰ-ነገር ጋር ነክነት ያለውን፡ አንዱን፡ ፀረ-እግዚአብሔርና ፀረ-ክርስቶስ፥ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ማርያም ድርጊቷን፡ እዚህ ላይ ማውሳቱ፡ አግባብ ይኾናል።

ይህም፡ እርሷ፡ በቀጥታ በምታስተዳድራቸውና የራሷ ግዛቶቿ በኾኑት ዘንድ ብቻ ሳይኾን፡ የእርሷ ጥገኞች በኾኑትና በእጃዙር በምትቆጣጠራቸውም፡ "ነጻ-ተብዬ" አገሮች ዘንድ፡ የሚሠራበት መንግሥታዊ መመሪያዋ  ነው። አዎን! በዓለም-ዐቀፍ ደረጃ፡ የነጻው ሕዝባዊ አገዛዝ ፍልስፍና፡ "አምበል ነኝ!" በምትለው፡ በዚህችው፡ በ"ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ"፡ በተግባር ውሎ እየተሠራበት ባለው፡ በዚህ መንግሥታዊ መመሪያ መሠረት፡ ትምህርት ቤቶችን በመሰሉ የመንግሥት ተቋማትና ብዙኃን መገናኛን በመሰሉ፡ የሕዝብ ድርጅቶች ዘንድ፡ ብቻ ሳይኾን፡ "ከዚህ ውጭ ናቸው!" በሚባሉት፡ በማናቸውም አውታሮቻቸውም ዘንድ፡ በተለይ፡ በሃይማኖቱ ኾነ በንግግሩ፥ በሌላውም፥ በሌላውም ዓይነት የነጻነት መብት ረገድ፡ ሙሉውን ሥልጣንና ልቅ የኾነው የነጻነት መድረክ የተሰጠው፥ ያገኘውም፡ ያው፡ ፀረ-እግዚአብሔርና ፀረ-ክርስቶስ፥ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ማርያም የኾነው ወገን ኾኖ ይታያል።

ይህን እውነታ ለማረጋገጥ፡ ወደሩቅ መኼድ፥ ወይም፡ ወደጥልቅ መውረድ፥ ወይም፡ ወደጠፈር መምጠቅ አያስፈልጋችሁም፤ እውነታው፡ እዚሁ፡ ገሃድና ተጨባጭ ኾኖ፡ በቅርባችሁ ይገኛልና። ለዚህም፡ እጅግ ብዙት ካላቸው፡ የተለያዩ ማስረጃዎች መካከል፡ ለአብነት ያህል፡ ኹለቱን ብቻ እገልጥላችኋለሁ።

**የመጀመሪያው ማስረጃ፡-** በአንድ በኩል፡ "ዳርዊን" የተባለ፡ አንድ እንግሊዛዊ፡ *"የዛሬው ሰብኣዊ ፍጡር፡ ከዚህ የሰውነት ብቅዓት የደረሰው፡ ከዝንጀሮ የዘር ሥር በቅሎ፡ የዕድገትና የለውጥ ኺደቱን ስለፈጸመ ነው!"* ሲል፡ በጥንተ አረማዊነቱ የፈጠረው፡ ይህ ሓሳዊና ሓሳባዊ መላምት፡ "ክርስቲያን ነኝ!" በሚለው ሕዝባዊ መንግሥቷ ዘንድ፡ የይፋ ተቀባይነትንና ሕጋዊ ዕውቅናን አግኝቶ፡ ይህ፡ ፀረ-እግዚአብሔርና ፀረ-ክርስቶስ፥ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ማርያም የኾነው፡ የዳርዊን መላምት፡ ለምሳሌ፡-

- በትምህርት ረገድ፡ በሥርዓተ ትምህርቷ ውስጥ ተካትቶ፡ ከሕፃናት ክፍል አንሥቶ፡ እስከመጨረሻው መካነ-አእምሮ ድረስ፡ በትምህርት መልክ እንዲሰጥ፥
- በዕውቀትም ረገድ፡ ለመላው ሕዝቧ፡ በኹሉም የብዙኃኑ መገናኛ አማካይነት፡ በዜና መልክ፡ ልቅ ኾኖ እንዲናኝ መደረጉ ነው።

በሌላው በኩል ግን፡ "የለም! ሰው፡ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረ፥ ፈጣሪውም፡ ‹ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!› በማለት፡ ለፍጹም አምላክነት ያበቃው፡ ቅዱስና ክቡር ፍጡር ነው!" የሚለው፡ እግዚአብሔራዊውና ክርስቲያናዊው፥ ኢትዮጵያዊውና ማርያማዊው ትምህርት፡ "ክርስቲያን ነኝ!" በሚለው፡ በዚሁ ሕዝባዊ መንግሥቷ ዘንድ፡ እንኳንስ፡ ተቀባይነትንና ሕጋዊ ዕውቅናን ሊያገኝ፥ በሥርዓተ ትምህርቷም ውስጥ ሊካተት ይቅርና፡ እንዲያውም፡ ‹መጽደቁ ቀርቶ፡ በወጉ በኮነነኝ!› እንደምትሉት፡

- ይኸው፡ እግዚአብሔራዊውና ክርስቲያናዊው፥ ኢትዮጵያዊውና ማርያማዊው ትምህርት፡ በማናቸውም፡ መንግሥታዊና ሕዝባዊ ትምህርት ቤቶቿ እንዳይሰሰጥ፡ በሕግ ተከለከለ።

- በዕውቀትም ረገድ፡ ለመላው ሕዝቧ፡ በኹሉም የብዙኃኑ መገናኛ አማካይነት፡ ምናልባት፡ ዐልፎ፡ ዕልፎ፡ በዜና መልክ ካልኾነ በቀር፡ እንደትምህርት እንዳይሰሰጥ ተደረገ።

- ጭርሱኑም፡ ይግረማችሁ ተብሎ፡ የፍጥረተ ዓለማቱ ፈጣሪና ባለቤት፥ ጠባቂና መጋቢ የኾንነው፡ እኛ እግዚአብሔር፡ ስማችንም እንኳ፡ በጸሎት መልክም ቢኾን፡ በየትኛውም መንግሥታዊና ሕዝባዊ ክልል ውስጥ፡ ፈጽሞ እንዳይነሣ፡ በሕግ፡ ታገደ።

ኹለተኛው ማስረጃ፡- በአንድ በኩል፡ እግዚአብሔራዊ ሥርዓት የኾነውን፡ የወንድ እና የሴት ጋብቻን በመፃረር፡ ለማፍረስ፥ ተፈጥሮአዊ የኾነውንም፡ የሴትንና የወንድን ሩካቤ-ሥጋ፡ በተቃውሞ በማዛባት፡ ወደኢተፈጥሮአዊነት ለመለወጥ፡ በፀረ-እግዚአብሔርና በፀረ-ክርስቶስ፥ በፀረ-ኢትዮጵያና በፀረ-ማርያም የሰይጣን ወገኖች ለሚካኼደው፡ ወንድ ከወንድ፥ ሴትም፡ ከሴት ጋር፡ የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን እንዲፈጽሙ የሚያደርገውን፡ ስሑት የግብረ-ሰዶምን ድርጊት፡ አኹንም፡ "ክርስቲያን ነኝ!" በሚለው ሕዝባዊ መንግሥቷ ዘንድ፡ እንዲህ፡ የይፋ ተቀባይነትንና ሕጋዊ ዕውቅናን በመስጠት፡ ኢተፈጥሮአዊ ብቻ ሳይኾን፡ ፀረ-እግዚአብሔርና ፀረ-ክርስቶስ፥ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ማርያም የኾነው፡ ይህ፡ ርኵሰት፡ አኹንም፡ እንደገና፡ ለምሳሌ፡-

- በትምህርት ረገድ፡ በሥርዓተ ትምህርቷ ውስጥ ተካትቶ፡ ከሕፃናት ክፍል አንሥቶ፡ እስከመጨረሻው መካነ-አእምሮ ድረስ፡ በትምህርት መልክ፡ በልቅነት እንዲሰሰጥ፥

- በዕውቀትም ረገድ፡ ለመላው ሕዝቧ፡ በኹሉም የብዙኃኑ መገናኛዎች አማካይነት፡ በዜናነት ብቻ ሳይኾን፡ በትምህርት መልክ ጭምር እንዲናኝ፡ በሕጋዊ ዐዋጁ መፈቀዱ ነው።

በሌላው በኩል ግን፡ "የለም! ሰው፡ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረ፥ ፈጣሪውም፡ ‹ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!› በማለት፡ ለፍጹም አምላክነት ያበቃው፡ ቅዱስና ክቡር ፍጡር ስለኾነ፡ በዚህ ዓለም፡ በምድር ላይ ሳይቀር፡ በሥጋዊውና በነፍሳዊው፥ በመንፈሳዊዉና በኹለንተናዊው ህልውናው፡ እግዚአብሔርን ለመምሰል በሚያበቃው፡ በመልካሙና በጤናማው የቅድስና ሕይወት፡ ለዘለዓለም፡ ደስ ብሎት፡ በፍጹም ተድላ እንዲኖር ወደዚህ ዓለም የመጣ እንጂ፡ ይህን በመሰለው፡ ከእንስሳትና ከአራዊት፥ ከአዕዋፋትና ከዓሣትም እንኳ በታች፡ እጅግ አዋርዶና አሳንሶ፡ ሰይጣናዊ እስከመኾን በሚያደርሰው፡ በክፉው የርኵሰት አኗኗር፡ ለዘለዓለም እንዲሠቃይ አይደለም!"

ደግሞም፡ "እግዚአብሔራዊው ሥርዓት የኾነው፡ የወንድ እና የሴት ጋብቻ፡ ከግዙፉና ከሥጋዊው የአዳምና የሔዋን ሥነ ፍጥረት በፊት እንኳ ሳይቀር፡ ልጃቸውን እግዚአብሔር ወልድን ለመውለድ፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስንም፡ ለማሥረፅ፡ በእግዚአብሔር አብ እና በእግዚአብሔር እም፡ መለኮታዊ ፈቃድ የተመሠረተና በዘለዓለማዊ ፍሬያማነቱ ሲሠራ የኖረ በመኾኑ፥

እንዲሁም፡ ሊጸና የሚገባው፡ እግዚአብሔራዊውና ተፈጥሮአዊ የኾነው፡ የሴትና የወንድ ሩካቤ-ሥጋ የሚፈጸምበት፥ መሰሎቻቸውን፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆችንም፡ በሥጋ ልደት የሚያፈሩበት፡ ቅዱሱ ጋብቻ እንጂ፡ ኢተፈጥሮአዊ የኾነው፥ በፀረ-እግዚአብሔርና በፀረ-ክርስቶስ፥ በፀረ-ኢትዮጵያና በፀረ-ማርያም የሰይጣን ወገኖች የሚካኼደው፡ ወንድ፡ ከወንድ፥ ሴትም፡ ከሴት ጋር፡ የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን እንዲፈጽሙ የሚያስተው፡ ርኩሱ የግብረ-ሰዶም ድርጊት አይደለም!" እየተባለ፣

አኹንም፡"ክርስቲያን ነኝ!" በሚለው ሕዝባዊ መንግሥቷ ዘንድ፡ እንዲህ፡ የይፋ ተቀባይነትንና ሕጋዊ ዕውቅናን በመስጠት፡ ኢተፈጥሮአዊ ብቻ ሳይኾን፡ ፀረ-እግዚአብሔርና ፀረ-ክርስቶስ፥ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ማርያም የኾነው፡ ይህ፡ ርኵሰት፡ አኹንም፡ እንደገና፡ ለምሳሌ፡-

- በትምህርት ረገድ፡ በሥርዓተ ትምህርቷ ውስጥ ተካትቶ፡ ከሕፃናት ክፍል አንሥቶ፡ እስከመጨረሻው መካነ-አእምሮ ድረስ፡ በትምህርት መልክ ሊሰጥ አይገባም፤

- በዕውቀትም ረገድ፡ ለመላው ሕዝቧ፡ በኹሉም የብዙኃኑ መገናኛዎች አማካይነት፡ በዜና መልክ እንዲናኝ፡ በሕጋዊ ዐዋጁ መፈቀዱ አግባብና ትክክል አይደለም!" የሚለው እግዚአብሔራዊውና ክርስቶሳዊው፥ ኢትዮጵያዊውና ማርያማዊው የቅዱሱ ኪዳን ቃል፡ በምንም መልኩና ይዘቱ፡ ፀረ-እግዚአብሔርና ፀረ-ክርስቶስ፥ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ማርያም ለኾነው፡ ለሰይጣናዊው ግብረ-ሰዶም የተሰጠውንና ያገኘውን የይፋ ተቀባይነቱንና የሕጋዊው ዕውቅናውን ዕድል ማግኘቱ ቀርቶ፡ በተቃራኒው፡ ሕጋዊው ክልከላው እንዲጸናበት ተደርጓል።

"ክርስቲያን ነኝ!" የሚለው፡ የ"ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ" ሕዝብ፡ እንደሌሎች መሰሎቹ አህጉርና መንግሥታት ኹሉ፡ ራሱን፡ ከክርስቲያናዊነትና **ከእግዚአብሔር** ***መንግሥት ኢትዮጵያ*** ውጪ በማድረግ፡ (Democracy በሚለው) በአረማዊው ሕዝባዊ አገዛዝ ፍልስፍናው፡ ባቋቋማቸው በሰብአዊው መንግሥቱና የኅብረተሰብ ዘርፎቹ፥ በተለያዩት አያሌ የቤተ ክርስቲያን ድርጅቶቹም አማካይነት ሲያካኺዳቸው የኖሩት ተግባሮች፡ እንግዴህ፡ እነዚህና እነዚህን የመሰሉ ናቸው።

ከዚህ የተነሣ ነው፡ ያ፡ የግብረ-ሰዶሙ ኃጢአት ጽዋ፡ ሞልቶ የመፍሰሱ ነገር፥ ይልቁንም፡ ሞልቶ የመፍሰሱ ኹኔታ፡ የሚያስከትለውን መቅሠፍታዊ ጥፋት፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ በመልአኩ አማካይነት፡ ለባለራእዩ ዮሓንስ፡ እንዲህ በሚል ቃል ያሳየው። ይህን እውነታ መመልከቱ፡ ለዛሬው አስተዋይ ሰብአዊ ልቡና፡ የሚያበረክተው ምስክርነት፡ የሚበቃ ይኾናል! ይበጀዋልም።

ያም ቃል፡ ከዚህ የሚከተለው ነው፡- **"ወይቤሎሙ፡ ቃል እምሰማይ፡ እምነ መቅደሱ፡ ለእልክቱ ሰብዓቱ መላእክት፡- 'ሑሩ! ወከዐዉ! ጽዋዐ መዓቱ ለእግዚአብሔር፡ ውስተ ኵላ ምድር።'"**

**"ለእነዚህ፡ ለሰባቱም መላእክት፡ ከሰማይ፥ ከመቅደሱ የመጣው ቃል፡ 'ኺዱ! የእግዚአብሔርን የቍጣ ጽዋዎችንም፡ በምድር ኹሉ ላይ አፍስሱ!' አላቸው።"** (ራእ. ፲፮፥፩።)

እንግዴህ፡ ለዚህ ነው፡ ይህ መልእክት፡ በዚህ ጊዜ፡ በዚህ መልክና በዚህ ይዘት፡ እንዲህ ኾኖ እንዲቀርብ አስፈላጊ የኾነው።

## ስለሰዶማውያንና ስለሰዶማውያት (ስለሰዶሞች)

ይህን የዐዋጅ ቃሌን እንዳስተላልፍላችሁ ስላስፈለገበት ምክንያት፡ ይህን ያህል ከገለጽሁላችሁ፡ ከዚህ በኋላ ደግሞ፡ በዚሁ መልእክት ውስጥ፡ ባጠቃላይ፡ "ሰዶሞች" ስለሚባሉት፡ የዚሁ ግብር ፈጻሚዎች የኾኑት ወንዶች እና ሴቶች ማንነትና ምንነት፡ በጥቂቱ አሳውቃችኋለሁ።

እኒህ ወገኖች፡ እንደመጀመሪያዎቹ የሰው ግንዶቻቸው፡ እንደአዳም እና እንደሔዋን፥ ከእነርሱ እንደተገኙት፡ እንደማንኛዎቹም የሰው ፍጡሮች፡ እኩል በኾኑት፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታዎች፡ የሰውነት ማዕርግ ተሰጥቷቸው፡ እንዲህ፡ በእኛ፡ **በእግዚአብሔር መልክ ተፈጥረው፡** በመለኮታዊው ቃላችን፡ **"ከእኛ፡ እንዳንዱ ኹኑ!"** የተባሉበትን፡ ደጉንና ክፉውን አውቀው የመምረጡንና ወስነው የማድረጉን፡ አምላካዊ ክብር እና ሰብአዊ ሥልጣን፡ ያገኙ ናቸው።

መነሻውን ልታውቁት ከማይቻላችሁ ጊዜ አስቀድሞ ካለው እግዚአብሔርነታችን፥ እርሱም፡ የተባዕታይ [የወንድነት]፥ እና/ወይም፡ የአንስታይ [የሴትነት] ጾታ ከሌለው፡ ከዚሁ፡ ከአንዱው ራሳችን፡ በፍጹም ፈቃዳዊው ስምምነታችን፡ "እግዚአብሔር አብ እና እግዚአብሔር እም" ተብለን፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታ፡ በእኩያነት ለኹለት ተከፍለን፡ አንዱን ተወዳጁን ልጃችንን፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ ከፍጥረት መጀመሪያ በፊት፡ በመለኮታዊው አካላችንና ባሕርያችን፡ በፈጣሪ ማንነቱ፥ በኋላ ዘመን ደግሞ፡ በፍጥረት መጨረሻ፡ ከተዋሓድናት፡ ከድንግል ማርያም፡ በሰብአዊው አካላችንና ባሕርያችን፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ በፍጡር ምንነቱ እንደወለድነው፥ በእግዚአብሔር መንፈስ-ቅዱስነትም እንዳሠረፅነው ታውቃላችሁ።

እነዚህ "ሰዶሞች"፥ እናንተም ሰብአውያን ፍጡሮቻችን ኹላችሁ፥ እያንዳንዳችሁ፡ እንዲህ፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታዎች የተገኛችሁት፡ አስቀድሞ፡ "አዳም" ብለን የጠራነውን ሰብአዊ ፍጡራችንን፡ እንደእኛው፡ የወንድነትና የሴትነት ጾታ ሳይኖረው፡ በአንድያው አርአያችንና ምሳሌያችን፡ አንድ አካልና አንድ ባሕርይ ብቻ አድርገን ከፈጠርነው በኋላ፡ ያንኑ፡ የአንድነት አካሉንና ባሕርዩን፡ እንደእኛው፡ እኩል ከፍለን፡ በወንድነትና በሴትነት ብልትና ጾታ፡ ተባዕትና አንስት አድርገን የሠራናቸው፡ እንደኛው፡ መሰሎቻቸውን፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆችን እየወለዱ፡ በመራባት እንዲበዙ፥ ምድሪቱንም መልተው እንዲኖሩባት ነው።

እንግዴህ፡ እነዚህን "ሰዶሞች"ን፥ እናንተን ሰብአውያን ፍጡሮቻችንንም ኹላችሁን፥ ወንድ እና ሴት አድርገን፡ በእኛ መልክና አርአያ፡ እኛም የፈጠርናችሁ፥ እነርሱም፥ እናንተም የተፈጠራችሁት፡ በወንድነታችሁ እና በሴትነታችሁ እየተጋባችሁ፡ መሰሎቻችሁን ሰብአውያን ወንዶች እና ሴቶች ልጆችን እየወለዳችሁና እየተዋለዳችሁ እንድትበዙ፡ ሙላዋ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ የኾነችውን ምድርንም እንድትመሏት፡ በፍጹም ገነታዊ ተድላ ደስታ፥ በፍቅርና በሰላም፡ ለዘለዓለም እንድትኖሩባት ነው። የሥነ-ፍጥረታችን፡ አንዱና ብቸኛው ዓላማ፡ ይኸው ብቻ ነው፤ ሌላ የለም።

ይህንኑም እውነታ፡ እንዲህ የሚሉት፡ በቅዱሳት መጻሕፍታችሁ ውስጥ የተመዘገቡት ቃሎቻችን ያረጋግጡታል፡- "ወይቤ እግዚአብሔር፡ 'ንግበር ሰብአ፡ በአርአያነ፥ ወበአምሳሊነ፡ ከመ ይኰንን ዓሣተ-ባሕር፥ ወአዕዋፈ-ሰማይ፥ ወአራዊተ-ምድር፥ ወእንስሳሂ፥ ወኵሎ ምድረ፥ ወኵሎ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር። ወገብሮ እግዚአብሔር፡ ለዕጓለ-እመሕያው፡ በአምሳለ-እግዚአብሔር። ተባዕተ፥ ወአንስተ፡ ገብሮሙ። ወባረኮሙ እግዚአብሔር፤ ወይቤሎሙ፡- 'ብዝኁ! ወተባዝኁ! ወምልእዋ ለምድር! ወቅንይዋ!

"እግዚአብሔርም አለ፦ 'የባሕር ዓሦችን፥ የሰማይ ወፎችን፥ የምድር አራዊትን፥ እንስሶችንም፥ ምድርንም ኹሉ፥ በምድርም ላይ የሚንቀሳቀሰውንና የሚላወሰውንም ኹሉ ያስተዳድር ዘንድ፡ ሰውን፡ በመልካችንና በአምሳያችን እንፍጠር!' ይህንም ብሎ፡ እግዚአብሔር፡ የሕያው-ልጅን፡ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረ። ወንድ እና ሴትም አደረጋቸው። '<u>ብዙ! ተባዙም! ምድርንም፡ ሙሏት!</u> አቅኗትም!' አላቸው።" (ኦሪት ዘልደት፡ ፩፥ ፳፯-፳፰።)

እነዚሁ "ሰዶሞች"፡ አዎን! እንደማንኛዎቹም ወንዶችና ሴቶች ሰብኣውያን ፍጡሮቻችን፡ እንዲህ ኾነው የተፈጠሩ እንደመኾናቸው፡ በዚሁ መለኮታዊና ተፈጥሮኣዊ ሥርዓት፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታቸው እየተጋቡ፥ ልጆችንም እየወለዱ ሊኖሩ ይገባቸው ነበር። ከዚያም ቢያልፍ፡ በዚያው፡ በወንድና በሴትነት ጾታቸው፡ ከሥነ-ፍጥረት ባልደረባቸው ጋር፡ የፍትወተ-ሥጋ ፍላጎታቸውን፡ በሩካቤ ሥጋ እየፈጸሙ፡ የሕይወተ-ሥጋ ህልውናቸውን፡ እንደማንኛውም ፍጡራችን፡ በተድላና በደስታ ማሳለፍ ይቻላቸው ነበር።

ነገር ግን፡ የእነዚሁ "ሰዶሞች" አስተሳሰብና አድራጎት፡ ባለመታደል፡ እንዲህ ሳይኾን ቀረ። እንዲያ በመልካሙ የሕይወት ጸጋ መኖር ሲገባቸው፥ ሲቻላቸውም፡ ያን በማድረግ ፋንታ፡ እኛ ፈጣሪያቸው፡ በሰፊው ቸርነታችንና ልግሥናችን፡ በጥንተ ተፈጥሮአቸው፡ እንዲያ አድርገን፡ ባጎናጸፍናቸውና ባቀዳጀናቸው፡ አምላካዊና ሰብኣዊ አካላቸውና ባሕርያቸው፥ በዚህ ዓለም፡ በምድር ላይ፡ በዚህ፡ የዕውቀትና የምርጫ፥ የመወሰንና የማድረግ፡ ግላዊ ሥልጣናቸው፡ በፍጹም ነጻነት ተጠቅመው፡ "የለም! ልንኖርበት የምንፈልገውና የሚገባን፡ ይህን ሳይኾን፡ የዚህ ተቃራኒ የኾነውን፡ ኢተፈጥሮኣዊውንና ሓሳዊዉን የግብረ-ሰዶም ሰይጣናዊ ልማድ ነው!" አሉ።

ይህንም ብለው ከወሰኑ፡ ይህንኑ ክፉና ጥፉ ልማዳቸውን ይዘው የመኖር ተፈጥሮአዊ መብታቸው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ዘንድ፡ የተከበረላቸውና የተጠበቀላቸው መኾኑ፡ በቅድሚያ መታወቅ ያለበት፡ ከፍተኛ ቍም ነገር ነው። የዚህ ቍም-ነገር ዘይቤ፡ ምን ማለት ነው? ይህማ፡ "ራሱን፡ ከመልካሙ፡ ወደክፉው ባሕርይ በመለወጥ፡ የሓሰት አባት እስከመኾን የተዋረደው ዲያብሎስ፡ ህልውናውና የጨለማ አገዛዙ፥ በሰዎች ላይ፡ ሞትን እያስከተለ ያለው፡ የክፋትና የኃጢኣት ምግባሩም፡ ምንጊዜም፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ቍጥጥር ሥር እንደመኾኑ መጠን፡ ይህን ዓይነቱ፡ የሰዶሞችም አኗኗር፡ ከእርሷ የጥበቃ ክልል ውጪ ሊኾን፡ ከቶ አይችልም!" ማለት ነው።

እንዲያውም፡ እግዚአብሔራዊዋ መንግሥታችን የኾንሁት፡ እኔው ራሴ ኢትዮጵያ፡ ለእነዚሁ፡ ለሰዶሞች፡ ለወንዶቼም፥ ለሴቶቼም ፍጡሮቼ፥ ልጆቼም፡ በእናትነት ፍቅሬ፡ የርኅራኄና የምሕረት ጥሪዬን፡ አኹንም፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ፡ እንዲህ እያልሁ፡ ያለማቋረጥ አቀርብላቸዋለሁ፦

"እኔ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር ሙሽራ፥ የእግዚአብሔር እናትና የእግዚአብሔር መቅደስ የኾንሁት፡ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴነቴና በእግዚአብሔር መንግሥትነቴ፡ በሃይማኖትነትና በአገርነት፥ በእናትነትና በንግሥትነት ዙፋኔ ላይ ተቀምጬ የማናግራችሁ፡ ድንግል ማርያም ነኝ!

"ኢትዮጵያዊው ኢየሱስ መሲሕ የኾነው፡ ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድም፡ ከእግዚአብሔር አብ አባቱ እና ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሕይወቱ ጋር፡ ኹላችንም፡ በተዋሕዶ አንድ ኾነን በተገኘንበት፡ ይኸው፡ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ፡ ዐብሮኝ ያናግራችኋል!

"እርሱ እና እኔ፡ የዛሬ ፪ሺ፰ (ኹለት ሽህ ስምንት) ዓመት፡ ለእናንተ እና ለመላው ፍጥረታችን፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፥ ለዘለዓለሙም፡ በፈጸምነው መሥዋዕትነታችንና በከፈልነው ቤዛነታችን፡ ከክፉት፥ ከኃጢአትና ከሞት፡ ፈጽማችሁ ስለዳናችሁ፡ እጅግ ደስ ሊላችሁ ይገባል።

"እኛ፡ ይህን የመሰለውንና ወደር ሊኖረው የማይቻለውን፡ ፍጹም ቸርነት ስላደረግንላችሁ፡ እናንተ ደግሞ፡ በእኛ መልክና 'ከእኛ እንደአንዱ ኾናችሁ!' በተባላችሁበት አምላካዊ ሰውነታችሁ፡ ይህ ለእናንተ የተደረገው የቸርነት ጸጋችን፡ ምን ዓይነት እንደኾነ፡ በማስተዋል አመዛዝናችሁና ተቀብላችሁ፥ ለእየራሳችሁ ደኅንነትና ጥቅም ስትሉ፡ በዚህ፡ የኪዳነ ምሕረት ትድግናችን፡ ከአኹን ጀምራችሁ፡ የዲያብሎስ ከኾነው፥ አዎን! ከዚህ ከምትገኙበት፡ ፀረ-እግዚአብሔርና ፀረ-ክርስቶስ፥ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ማርያም ከኾነው፡ ኢተፈጥሮአዊና ርኵሰት፥ አስነዋሪና አሳፋሪ ከኾነው፡ የባርነት ቀንበርና የጕሥቍልና አኗኗራችሁ፡ እየራሳችሁን፡ በእውነተኛ ንስሓ፡ ነጻ ማውጣት ያስፈልጋችኋል።

"በገዛ ፈቃዳችሁና ምርጫችሁ፡ ይህን፡ 'እየራሳችሁን፡ በእውነተኛ ንስሓ፡ ነጻ የማውጣት' መልካም ሃይማኖታዊ ምግባር ፈጽማችሁ በምትገኙበት ጊዜ፡ እንደገና እጅግ ደስ ብሏችሁ፡ የበለጠ ሐሤትን የምታደርጉበት፡ መለኮታዊውን የምሥራች የዐዋጅ ቃል ትሰማላችሁ፤ ይኸውም፡- «እናንት ሰብኣውያን ወንዶችና ሰብኣውያት ሴቶች ፍጡሮቻችን! በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ በእየራሳችሁ፡ የእኛ ዜጎች በመኾን ብቻ አይደለም፤ በይበልጥ ግን፡ ቅዱሳንና ቅዱሳት ልጆቻችን፥ የመንግሥታችን፡ ወራሾች ነጋሢዎቻችንና ታማኞች ካህናቶቻችን በመኾን ጭምር፡ ዛሬ፡ በምድር ላይ፡ በሥጋ እያላችሁ፡ እየራሳችሁን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት አብቁ! እየራሳችሁን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት በማብቃታችሁም፡ እንዲህ፡ በኪዳናዊነትና በኪዳናዊትነት፡ በዘላለማዊቷ የሰንበት ዓለም፡ የቅድስቲቱ የትንሣኤ ሕይወት ነዋሪዎች ኹኑ!» የሚለው ነው።

## ስለ"ግብረ-ሰዶም"፡ አጠያያቂው ነገር፤

እንግዴህ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ ሰዶሞችን በሚመለከት፡ ስላላት አቋም፡ በመጠኑ፡ ለማስታወቅ በማለት፡ ይህን ያህል ካልኋችሁ፡ አኹን ደግሞ፡ ልገልጥላችሁ ስለተነሣሁበት፡ ስለዋናው፡ ስለ"ግብረ-ሰዶም" ነገር ወደማብራራቱ አመራለሁ።

ይኹን እንጂ፡ ወደዚያ ከማምራቴ በፊት፡ አኹንም፡ ሳላወሳላችሁ የማላልፈው፡ አንድ አጠያያቂ ቍም-ነገር ስላለኝ፡ እዚህ ላይ፡ እርሱን፡ ለመንደርደሪያ ያህል እንድንጠቅስላችሁ ያስፈልጋል፤ እርሱም፡ እንዲህ በሚል አጭር ቃል፡ ሊጠቃለል ይቻላል።

«የግብረ-ሰዶሙ ርእሰ-ነገር፡ በመላው የዓለሙ ኅብረተሰብ ዘንድ፡ በይፋ ታውቆ፡ ዜናው፡ እጅግ የተስፋፋና የሰፈነ መኾኑ፡ እነሆ በግልጽ ይታያል። ያ ሳይበቃ፡ የዓለሙ ኹሉ ሰዎች፡ ለዚህ ስሑት-ግብር ምንጭ ለኾነው፥ በመለኮታዊውም ቃል፡ ለክፋትና ለሓሰት፥ ለአምልኮ ምንዝርናና ለሞት፥ እነዚህን ለመሰሉ ኃጢአቶች ኹሉ፡ "አባት" ለኾነው፡ ለቀንደኛው ለዲያብሎስና ለጭፍሮቹ፡ ያቀዳጁት፡ ምትሓታዊ የኾነው፡ የፍርሃት አክብሮትና የመውደድ አምልኮ፡ የቱን ያህል የላቀ እንደኾነ፡ ከማንም የተሠወረ አይደለም።

«እውነታው፡ ይህ ኾኖ ሣለ፡ ታዲያ! እስካኹን ድረስ፡ በሌላው ዘንድ እንኳ ቢቀር፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ኀዋ ሰሌዳ ላይ ኾነ፥ በፌስቡክ መድረካችን ላይ፡ ከሰዎች፡ ስንት ዓይነት የተለያዩ አርእስተ-ነገሮችን በሚመለከት፡ አያሌ ጥያቄዎች፥ በርካታ ትችቶችና ብዙ አስተያየቶች ሲቀርቡ፡ በዚህ፡ በ"ግብረ-ሰዶም" ረገድ ግን፡ ለምንና እንዴት፡ አንድም ጥያቄ፥ ትችትና አስተያየት ሳይቀርብበት ቆየ?" የሚያሰኘው ጉዳይ ነው።

«ስለዚህ፡ ይህን የመሰለውን ኹኔታ ያስከተለው፡ ከላይ የተጠቀሰው፡ ያ፡ በዓለሙ ሰዎች ዘንድ፡ ለዲያብሎስና ለጭፍሮቹ የሚበረከትላቸው፡ ምትሓታዊው፡ የፍርሃት አክብሮትና የመውደድ አምልኮ፡ ጸንቶ እየሠራ ከመኾኑ የተነሣ ነው!" ብሎ መደምደሙ፡ የሚያስኬድ ይኾናል።»

ከዚህ ኹሉ ይልቅ፡ እጅግ የሚያስገርመው ኹኔታና ድርጊት፡ በጠቅላላ፡ በዓለም ላይ ያሉት፡ የሃይማኖቶች ተቋማት፥ በተለይም፡ "ክርስቲያን ነን!" በሚሉ ሕዝቦች የተቋቋሙት፥ እየራሳቸው፡ መንግሥቶቻቸው ሳይቀሩ፡ የዚሁ፡ የግብረ-ሰዶሙ ዓላማና ተግባር፡ መፈልፈያ ጎሬዎች መኾናቸው ብቻ ሳይኾን፥ አዎን! ቀደምት ደጋፊዎችና ግብረ-ዐበሮች፥ አራማጆችና አስፈጻሚዎች መኾናቸውም ብቻ ሳይኾን፡ ከዚህ ይባስ፥ በይበልጥም፡ ይህንኑ ማንነታቸውንና ምንነታቸውን፡ እየራሳቸው፡ በራሳቸው፡ ገሃድ አድርገው፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ እያሳወቀ መኾናቸው ጭምር ነው።

መንግሥታቱ ይቅሩና፡ "ቤተ ክርስቲያን ነን!" የሚሉት ድርጅቶች፥ የኦርቶዶክሱ ኾነ የካቶሊኩ፥ የጵሮቴስጣንቱ ኾነ፥ በተለያየ ስም የሚጠራው የሃይማኖት ድርጅት ኹሉ፥ በኢትዮጵያ፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክህነት ቅርንጫፍ የኾነችው፡ የኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጭምር፡ እስካኹን፡ ግብረ-ሰዶምን በሚመለከት፡ ሥውር የኾነ፥ ወይም፡ ገሃድ የኾነ መግለጫንና ማብራሪያን፡ በይፋ አውጥተው፡ ለምእመኖቻቸው፥ ለሕዝባዊም ምንባብ ያበቁ መኖራቸው ያጠራጥራል። የለምማ! ሳይኖር!? ለምን? ለምን? ለምን? የለም።

ይህን፡ ብርቱ ጥያቄ፡ ምናልባት፡ ከዚህ ቀጥሎ ያለው አጭር ሓተታ፡ በመጠኑ ይገልጠው ይኾናል፡-

## *"ግብረ-ሰዶም" ምንድር ነው?*

"ግብረ-ሰዶም"፡ ተብሎ የተሰየመው፡ ፀያፍ የሙስና ግብርማ፡ ቀደም ብዬ፡ በዚህ የዐዋጅ-ቃሌ መግቢያ ላይ እንዳመለከትኋችሁ፡ ሰዎች፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታቸው፡ በተፈጥሮአዊው መልኩና ይዘቱ፡ ተገቢውን የሩካቤ-ሥጋ ግንኙነት በመፈጸም፡ በእኛ አርአያና አምሳያ፥ ከእኛ እንደአንዳችን በሚያደርግም፡ የአካልና የባሕርይ ብቅዓት፡ መሰሎቻቸውን፡ የሰውን ልጆች፡ በልደት እንዲያስገኙበት፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታ ለፈጠርናቸው ሰብአውያን ፍጡሮቻችን፡ በጋብቻ ተክሊል አሳምረንና አንጽተን፥ አመልክመንና ቀድሰን የሠራነውን፡ እግዚአብሔራዊና ተፈጥሮአዊ የኾነውን ሥርዓት፡ ጨርሰው አማስነው [አበላሽተው] እና ለውጠው፡ የወንድና ወንድ፥ የሴትና ሴት ኢ-ተፈጥሮአዊ የኾነው፡ እስከጋብቻ ያደረሰ፡ ሰይጣናዊው የመወዳጀትና የሩካቤ-ሥጋ ግንኙነትን የሚያደርጉ ወንዶችና ሴቶች ሰብአውያን ፍጡሮቻችን፡ በእየራሳቸውና በየእርስ በርሳቸው የፈጠሩት የጽኑ ኃጢአት ዓይነት ነው።

በጥንቱና በቀድሞው፥ በመካከለኛውና በዚህም ዘመን፥ ወይም፡ ምንጊዜም ቢኾን፡ በምንም መልኩ፡ ሃይማኖታዊ እይታና ምግባራዊ ምዘና ሳያስፈልገው፡ በምድር ላይ፡ በማንኛውም ጤናማና አስተዋይ ሰብአዊ ፍጡር፡ ርትዓዊ መሥፈርት ፊት፡ የ*"ግብረ-ሰዶም"*፡ ኢ-ተፈጥሮአዊነትና ርኵስነት፥ ነውርነትና ፀያፍነት፥ ኃጢአትነትና ሰይጣናዊነት፥ በገመና የሚደበቅ ክፉ ዐመልነት፥ ከዚህ የተነሣም፡ የፀረ-እግዚአብሔርነቱና የፀረ-ክርስቶስነቱ፥ የፀረ-ኢትዮጵያነቱና የፀረ-ማርያምነቱ ግልጽ ባሕርያዊ ምንነት፡ እንዲህ፡ በገሃድ ሊታወቅ ከቶ አይከብድም።

ከፍጥረት ጀምሮ፡ ይኼው ግብር፡ ከሓሰተኞች ሰዎች መካከል ፈጽሞ ያልተወገደ፥ ሊወገድ ያልቻለም በመኾኑ፡ በኢትዮጵያ ልጆቼ ዘንድ እንኳ ሳይቀር፡ እንደሌላው ክፉ ልማድ ኹሉ፡ ይኼም ግብረ-ሰዶም፡ በገመና የሚደበቅ ክፉ ዓመልነቱ ታውቆ፡ ሕዝቤ፡ ላገሩ የጥበቃ አገልግሎት ግዳጅ፡ "ክተት!" ተብሎ፡ ባዋጅ፡ ወደዐደባባይ ሲጠራ፡ "ዐመልህን በጉያ! ስንቅህን ባህያ!" የሚባለው፡ በዚህ ምክንያት መኾኑን ብዙዎቻችሁ ታውቃላችሁ።

ይኸው ግብረ-ሰዶም፡ በነውረኝነቱና በአሳፋሪነቱ፥ በኃጢአትነቱና በሰይጣናዊነቱ እንዲህ፡ በገመናነት ተፈርጆ፡ በድብቅ የኖረ ሲኾን፡ በአኹኑ ዘመናችሁ ግን፡ በየአህጉራቱ ሕዝቦችና በሰብአውያኑ መንግሥታት፥ በሃይማኖት ድርጅቶችም ዘንድ ሳይቀር፡ ይህን የመሰለው የይፋ ዕውቅናና ሕጋዊ ጽናት እንዲያገኝ ተደርጎ፡ በጋብቻ ደረጃ እስከመፈጸም በሚያደርስ ይዘት ሲካኬድ መታየቱ፡ የጥፋት ውኃንና የሰዶምን እሳተ-ገሞራ ያስከተሉትን፡ የኖኅንና የሎጥን የቅጣት ዘመናት በሚያዘክረውና የዚያን ጊዜዎቹን የመቅሠፍት ዓይነቶች በሚጋብዘው፡ የዕልቂትና የድምሳሴ ቀናት ውስጥ መገኘታችሁን፡ ለእየራሳችሁ ጭምር ማረጋገጣችሁ መኾናችሁን ልትገነዘቡት ይገባችኋል።

አዎን! ይህ ኹሉ እውነታ፥ ይልቁንም፡ በኖኅና በሎጥ የተለያዩ ዘመናት፡ በዚሁ፡ በግብረ ሰዶሙ ጠንቅ፡ የደረሰው የጥፋት ውኃና የወረደው ደምሳሽ እሳተ-ገሞራ ተዘንግቶና ተክዶ፡ ግብረ-ሰዶም፡ ዛሬ እንደገና፡ እንዲህ በይፋ አቈጥቍጦና ተንሠራፍቶ፥ እየሠለጠነና እየገነነ፥ ሕጋዊ ዕውቅናንና ሕዝባዊ ቅበላንም ሳይቀር እንዲያገኝ ተፈቅዶለት፡ እነሆ ሲጐመራ ይታያል።

ለመኾኑ፡ ግብረ-ሰዶምን፡ ለዚህ የምንነቱ ደረጃ ያበቁት፡ እነማን ናቸው? ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ በመጀመሪያ፡- ለሥጋዊውና ለምድራዊው የዓለም ኅብረተሰብ ተጠሪና መሪ፥ የአገልግሎትም ዘርፍ የኾነው፡ "ቤተ መንግሥት" የምትሉት፡ የአገዛዝ ድርጅት ነዋ! ይህ አካል፡ ራሱ፡ የዚሁ፡ የግብረ-ሰዶም ተቀባይና አቀነባባሪ፥ ግብረ-ዐበርና አስፈጻሚ በመኾን፡ ይህን ልቅ የኾነ የአሥረኸ-ምቿው ፈቃድን የሰጠ ስለኾነ፡ ከባድ ኀላፊነትና ተጠያቂነት ይጠብቀዋል።

ቀጥሎ፡ ለሚመጣው መለኮታዊ ፍርድ፡ ተጠያቂነቱና ኀላፊነቱ፡ በዚህ አካል ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም፤ በተለይ፥ በይበልጥም፡ "ክርስቲያን ነኝ!" እያለ፡ በግብዝነት የሚመጻደቀው፡ ለመንፈሳዊውና ለሃይማኖታዊው የዓለም ኅብረተሰብ ተጠሪና መሪ፥ የአገልግሎትም ዘርፍ የኾነው፡ "ቤተ ክህነት" የምትሉት የጭቆና ተቋም፡ ከቀደመው "ቤተ-መንግሥታዊ" አካል የባሰ፡ እጅግ ከባድ የኾነ፡ ኀላፊነትና ተጠያቂነት ይጠብቀዋል።

ስለዚህ፡ ለእናንተ ኹለት ሥጋውያንና መንፈሳውያን አካላት፥ ማለትም፡ ለቤተ-መንግሥቱ ኾነ፡ ለቤተ-ክህነቱ፥ "ከእነዚህ ውጪ ነን!" ለምትሉ፡ ለቀራችሁት፡ ለመላው የዓለሙ ኅብረተሰብ ጭምር በሙሉ! አዎን! *"ግብረ ሰዶም"* ስለሚባለው አስተሳሰባችሁና አድራጎታችሁ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ የምትለውን ስሙ፡-

የሰውነት ክብር ተሰጥቷቸው ባጠቃላይ፡ "ሰዶሞች" የተባሉት፡ የዚሁ ግብረ-ሙስና ፈጻሚዎች የኾኑት ወንዶች እና ሴቶች፥ ደጋፊዎቻቸው ጭምር፡ ይህ ሙሱን አስተሳሰባቸው፡ "ከዝንጀሮ የተገኘን ነን!" ከሚለው የራቀ ሊኾን እንዳልቻለ፡ ጤናማ አእምሮ ባለው ፍጡር ዘንድ፡ ግልጽ ኾኖ ይታያል።

ዝንጀሮም እኮ፡ ይህን የመሰለውን ኢተፈጥሮአዊ የኾነ፡ ፀያፍ ድርጊት፡ ስለማይፈጽም፡ እነዚሁ የሓሰት ባርያዎች የኾኑ ባለጌዎች፡ ለዚያ ዓይነቱም ስሑት መላምት እንኳ ሊበቁ አይችሉም ማለት ይኾናል። ከዚህ የተነሣ፡ ምናልባት፡ ልቡሳነ ሥጋ አጋንንት እንጂ፡ "ሰዎች" ተብለው ሊጠሩም እንኳ ያዳግታል። ምክንያቱም፡ ይህንኑ፡ ግብረ ሰዶምን፡ እንስሳትና አራዊት፥ አዕዋፋትና ዓሣት፡ በሥነ ተፈጥሮ ጠባይዓቸው፡ ሊያደርጉት ቀርቶ፡ ሊያስቡት እንኳን የማይቃጡት፡ ኢተፈጥሮአዊ ስለኾነ ነው።

ስለዚህ፡ "ሰዶሞች"፡ በዚህ ኹሉ ምክንያት፡ በአስተሳሰባቸውም ኾነ በግብራቸው ብቻ ሳይኾን፡ በተፈጥሮአቸውም ጭምር፡ እየራሳቸውን፡ ከሰውነት ብቻም አይደለም፡ ከእንስሳቱና ከአራዊቱ፥ ከአዕዋፋቱና ከዓሣቱም ሳይቀር ያሳነሱትና ያዋረዱት፤ ከሰውነት ውጪ፡ ወደሰይጣናዊነቱም የለወጡ በመኾናቸው፡ "ልቡሳነ ሥጋ አጋንንት" መባላቸው፡ የሚያስኬድ ኾኖ ይገኛል።

በመሲሑ ኢየሱስ ቃል፡ "ክፉና ከሃዲ፥ ዐመፀኛና አመንዝሪ" ለተባለው፥ ይህንኑ፡ "ግብረ ሰዶም" የተባለውንም ሰይጣናዊ ልማድ ላስገኘው፥ ለዚህ፡ ለዓለሙ፡ የሰው ልጆች ትውልድ፥ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" ለሚለው ጭምር፡ ሰዎች ከጻፉት መጽሓፍ ካልተጠቀሰለት በቀር፡ ፈጣሪው ባጐናጸፈው የተፈጥሮና የመንፈስ ዕውቀት በመጠቀም፡ ምንም ነገር ተረድቶ ሊቀበል ቀርቶ፡ ሊሰማም እንኳ እንደማይፈልግ፡ ይኸው ይታያል።

ከዚህ የተነሣ፡ ይኸው ትውልድ፡ አይቀበላቸውም እንጂ፡ የሚቀበላቸው ከኾነ፥ እንዲያው ለምናልባቱ፡ ቢኾንለት እንኳ፡ አምኖ የሚፈጽመውም ከኾነ፡ እኔም፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ፡ ስለዚሁ፡ ስለግብረ ሰዶም ምንነት፡ በቀላሉ ለማስረዳት፡ በሰዎች እጅ፡ በብራናና በክርታስ ከተጻፉት፡ ከቅዱሳት መጻሕፍታችሁ፡ ስለዚሁ ርእሰ-ነገር ከሚናገሩት ከእግዚአብሔር ቃላት መካከል፡ በቅድሚያ፡ በብሉይ ኪዳኑ ክፍል፥ ቀጥሎም፡ በአዲስ ኪዳኑ ያሉትን፡ አንዳንዶቹን፡ እያከታተልሁ በመጠቃቀስ፡ እንደሚከተለው አቅርቤላችሁና፡ አዳምጧቸው!

ይህ እንዲኾን፡ በግድ ያስፈለገው፡ በቀጥታ፡ ከእኛ ከፈጣሪያችሁ፡ በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖታቸው ተቀብለው፥ በምግባር እየፈጸሙ የሚኖሩት፡ "የኢትዮጵያ ልጆቼ" እንደሚያደርጉት ኹሉ፡ እኛ እግዚአብሔር፡ በተፈጥሮ፡ ለሰው ኹሉ፡ ለየራሱ በማስተማር፡ በየልቦናው ላይ በጻፍነው፥ በየኅሊናውም ባሳደርነው፡ የዕውቀት ጸጋ መጠቀሙ የሚበቃ ሲኾን፡ ይኸው ከላይ የተጠቀሰው፡ የዓለሙ ሥጋዊ ትውልድ ግን፡ ይህን፡ እግዚአብሔራዊ የኾነውን ፍጹም ሥርዓት፡ ለመቀበል ባለመፍቀዱ መኾኑ፡ ሊታወቅ ይገባል።

## ከብሉይ ኪዳኑ ክፍል

፩፡ «ወምስለ ተባዕት፡ ኢትስክብ ከመ አንስት! እስመ ርኵስ ውእቱ። ...እስመ ኵሉ ዘገብረ፡ እምዝንቱ ኵሉ ርኵስ፡ ትሠሮ፡ ይእቲ ነፍስ፡ እምሕዝባ እንተ ገብረቶ።»

«ከሴት ጋር እንደምትተኛ፡ ከወንድ ጋር አትተኛ! ጸያፍ ነገር ነውና። ...ከዚህ ርኵሰት ኹሉ፡ ማናቸውን የሚያደርግ፡ ያ ሰው፡ ከሕዝቡ መካከል ተለይቶ ይጠፋል።» (ዘሌዋ. ፲፰፥ ፳፪።)

፪፡ «ወይቤሎ እግዚአብሔር፡ ለአብርሃም፦ "ጽራሖሙ፡ ለሰዶም፥ ወለገሞራ፡ በጽሓ ኀቤየ፤ ወኃጣውኢሆሙኒ፡ በዝኃት ጥቀ። እረድ እንከሰ! ወእርአይ፡ ለእመ በከመ ጽራሖሙ፡ እንተ ትመጽእ ኀቤየ፡ ይፌጽምዋ፤ ወእመ አኮሰ፡ አአምር።"

«ወሶበ ተመይጡ እምህየ፡ እልክቱ ዕደው፡ መጽኡ ውስተ ሰዶም። ወአብርሃምሰ፡ ሀሎ ዓዲ ይቀውም፡ ቅድመ እግዚአብሔር። ወቀርበ አብርሃም፤ ወይቤ፡ "ኢታማስን እግዚኦ ጻድቃነ፡ ምስለ ኃጥኣን! ወኢይኩን ጻድቅ፡ ከመ ኃጥእ! ...ለእመኬ ተረክቡ በህየ፡ ፲ቱ (ዐሠርቱ) ጻድቃን፡ ታማስኖሙኑ፥ ወኢታሐዩኑ፡ በእንተ ፲ቱ ጻድቃን፡ ኵሎ ብሔረ?" ወይቤሎ፡ "ኢያማስን፡ በእንተ ፲ቱ። ወሶበ አኅለቀ ተናግሮቶ ለአብርሃም፡ ኀለፈ እግዚአብሔር፤ ወአብርሃምኒ ገብአ፡ ኀበ ምንባሪሁ።

«ወበጽሑ፡ እልክቱ ክልኤቱ መላእክት፡ ውስተ ሰዶም፡ ፍና ሠርክ፤ ወሎጥኒ፡ ሀሎ ይነብር፡ ውስተ አንቀጸ ሰዶም። ወሶበ ርእዮሙ፡ ተንሥአ፤ ወተቀበሎም፤ ወሰገደ ሎሙ። ወይቤሎሙ፦ "አጋእዝትየ! ገኃሡ ኀበ ቤተ ገብርክሙ! ወኅድሩ! ወተሓፀቡ እገሪክሙ! ወትጊሡ! ወትሑሩ ፍኖተክሙ!"

«ወይቤልዎ፦ "አልቦ! አላ ነኀድር ውስተ መርኅብ።"

«ወሰገደ ሎሙ በገጹ፤ ወአገበሮሙ፤ ወግኅሡ ኀቤሁ፤ ወቦኡ ውስተ ቤቱ፤ ወገብረ ሎሙ፡ ዳፍንተ ናእተ፤ ወበልዑ፤ ወሰትዩ።

«ወእንበለ ይስክቡ፡ ሰብኣ፡ ለይእቲ ሀገር፡ ዐገትዋ ለቤቶሙ፡ ኵሉ ሰብኦሙ ኅቡረ፣ ንኡሶሙ፤ ወዐቢዮሙ። ወጸውዕዎ ለሎጥ፤ ወይቤልዎ፦ "አይቴ፡ እሙንቱ እደው፡ እለቦኡ ኀቤከ፡ ሌሊተ? አውጽዕዎ ኀቤነ፡ ከመ ንሑሮሙ!"

«ወወጽአ ኀቤሆሙ ሎጥ፡ ኀበ ኆኅት ቅድሜሆሙ፤ ወዐፀወ ኆኅተ፡ ድኅሬሁ። ወይቤሎሙ፦ "ሓሰ ለክሙ፡ አኀውየ! ኢታኅሥሙ ላዕለ እሉ። ወናሁ ብየ፡ክልኤ አዋልድ፡ ዘኢያእመራ ብእሴ፤ ወአውፅአን ለክሙ፤ ወግበርዎን፡ ዘከመ ይኤድመክሙ፤ ወባሕቱ፡ ላዕለ እሉ እደው፡ ኢትግበሩ፡ ምንተኒ ዐመፃ፣ እለ ቦኡ፡ ታሕተ ጽላሎተ ቤትየ።"

«ወይቤልዎ፡- "ሑር ከሐከ! ቦእከ፡ ከመ ትኀድር፤ ወአኮ ከመ ትኰንነነ፤ ወይእዜኒ፡ ኪያከ ነሣቂ ፈድፋደ እምኔሆሙ።" ወተኀየልዎ ሎቱ ፈድፋደ፤ ወቀርቡ ከመ ይስብርዋ ለኆኅት።

«ወአውጽኡ እደዊሆሙ፡ እልክቱ እደው፤ ወሰሓብዎ፡ ለሎጥ፤ ወአብእዎ ኀቤሆሙ፡ ውስተ ቤት፤ ወዐፀዉ ኆኅተ። ወለእልክቱሰ እደው፡ እለ ሀለዉ ቅድመ ኆኅቱ፡ ለውእቱ ቤት፡ አፆርዎሙ አዕይንቲሆሙ፡ ለንኡሶሙ፥ ወለዐቢዮሙ።

«ወሠርሑ፡ እንዘ የኀሥሥዎ፡ ለውእቱ ኆኅት፤ ወኀጥእዎ።

«ወይቤልዎ ለሎጥ፡ እልክቱ መላእክት፡- "ቦኑ ዘብከ፡ በዝየ፡ ታእኃ፥ አው ታሕማ፥ ወእመሂ፡ ደቂቅ፥ ወአዋልድ? ወለእመ ዘብከ ዐርከ፡ ዘተአምር ውስተዝ ሀገር፡ አውፅኦሙ፡ እምነ ዝንቱ መካን። እስመ ናማስና ንሕነ፡ ለዛቲ መካን፣ እስመ ዐብየ ገዐሮሙ፡ በቅድመ እግዚአብሔር፤ ወፈነወነ፡ ከመ ንደምስሳ።"

«ወወፅአ ሎጥ፡ ኀበ ታሕማሁ፡ እለ ይነሥእዎን፡ ለክልኤሆን አዋልዲሁ፤ ወይቤሎሙ፡- "ተንሥኡ! ወፃኡ፡ እምዝንቱ ሀገር፣ እስመ ይደመስሶ እግዚአብሔር!" ወመሰሎሙ፡ ለታሕማሁ፡ ከመ ዘበሥላቅ ይቤሎሙ።

«ወሶበ ኮነ፡ አፈ ጽባሕ፡ አኀዙ ያጐጕእዎ መላእክት፡ ለሎጥ፤ ወይቤልዎ፡- "ተንሥእ! ወንሣእ! ክልኤሆን አዋልዲከ፥ ወብእሲተከ፤ ወፃእ! ከመ አንተኒ ኢትሙት በኃጢአቶሙ ለሰብአ ዝንቱ ሀገር።" ወአኀዝዎ እዴሁ፡ እልክቱ እደው፣ ወእደ ብእሲቱ፣ ወክልኤሆን አዋልዲሁ፣ እስመ ምህኮሙ እግዚአብሔር።

«ወይቤልዎ፡ ሶበ አውጽእዎ አፍአ፡- "አድኅን ነፍሰከ! ወኢትነጽር ድኅሬከ! ወኢትቁም ውስተ አድያሚሃ፥ ወውስተ ደብራ፡ ለዛቲ ሀገር፡ ከመ ኢትርከብከ ለከኒ፡ እኪት።"

«ወይቤሎሙ ሎጥ፡ "ብቍዑኒ አጋእዝትየ! እመ ረከብኩ ምሕረተ፡ በቅድሜክሙ፥ ወአዕበይኮ ለምሕረትከ ምስሌየ፡ ከመ ታሕይዋ ለነፍስየ። አንሰ ኢይክል፡ አድኅኖ ርእስየ ውስተ ደብር፡ ከመ ኢትርከበኒ እኪት፤ ወኢይመውት። ወናሁ ዛቲ ሀገር ቅርብት ይእቲ፤ ወንስቲት፤ እሩጽ ህየ፤ ወአድኅን ርእስየ። ወኢኮነት ንስቲተ፡ እምከመ ድኅነት ነፍስየ።"

«ወይቤሎ፡ "ናሁ አድኀንክዋ ለገጽከ፤ ወበከመ ትቤ፡ ኢይገፈትኣ ለይእቲ ሀገር፡ እንተ በእንቲአሃ ነበብከኒ። አፍጥን እንከ! ወአድኅን ርእሰከ በህየ!" በእንተ ዝንቱ፡ ተሰምየት፡ ይእቲ ሀገር፡ "ሴጎር".

«ወአዝነመ እግዚአብሔር፡ ላዕለ ሰዶም፥ ወገሞራ፡ እሳተ፥ ወተየ፡ እምኀበ እግዚአብሔር፡ እምሰማይ። ወገፍትኦን፡ ለእማንቱ አህጉር፥ ወለአድያሚሆን፡ ምስለ ኰሎሙ፡ እለ ይነብሩ ውስቴቶን፥ ወለኵሉ ዘርአ ምድሮሙ።

«ወነጸረት፡ ብእሲተ ሎጥ፡ ድኅሬሃ፤ ወኮነት ሓውልተ ጼው።

«ወጌሠ አብርሃም፡ ውስተ ዝኩ መካን፡ ኀበ ቆመ ቅድመ እግዚአብሔር፤ ወነጸረ ላዕለ ገጸ ሰዶም፥ ወገሞራ፥ ወላዕለ ኵሉ አድያሚሃ፤ ወሶበ ርእየ፡ ናሁ የዐርግ ነድ፡ እምድር፡ ከመ ጢሰ እቶን።

«ወኮነ፡ ሶበ ደምሰሶን እግዚአብሔር፡ ለእማንቱ አህጉር፥ ወለኵሉ አድያሚሆን፡ እለ ውስቴቶን የኀድር ሎጥ፡ ተዘከሮ ለአብርሃም፤ ወአውጽኦ ለሎጥ፡ እማእከለ ሙስና።

«ወዐርገ ሎጥ፡ እምነ ሴጎር፤ ወኀደረ ውስተ ደብር፣ እስመ ፈርሀ ነቢረ ውስተ ሴጎር፤ ወነበረ ውስተ በዓት፣ ውእቱ፥ ወክልኤሆን አዋልዲሁ።

«ወትቤላ፡ እንተ ትልህቅ፡ ለእንተ ትንእስ፡ ‹ናሁ አቡነ አረጋዊ ውእቱ! ወአልቦ ሰብእ፡ ዘይበውእ ኀቤነ፡ ከመ ይትዋለድ ውስተ ኵሉ ምድር። ንዒ! ናስትዮ ወይነ፡ ለአቡነ! ወንስክብ ምስሌሁ! ወናቅም ዘርአ፡ እምአቡነ!› ወአስተያሁ ወይነ፡ ለአቡሆን። ወበይእቲ ሌሊት፡ ቦአት፡ እንተ ትልህቅ፤ ወሰከበት ምስለ አቡሃ፤ ወኢያእመረ፡ በሰኪቦታ፥ ወበተንሥአታ።

«ወእምዝ ትቤላ፡ እንተ ትልህቅ፡ ለእንተ ትንእስ፡ ‹ናሁ ሰከብኩ፡ ትማልም፡ ምስለ አቡነ፤ ካዕበ ናስትዮ ወይነ፤ ወስክቢ ምስሌሁ፡ በዛቲ ሌሊት፤ ወናቅም ዘርአ እምአቡነ።› ወአስተያሁ ወይነ፡ በይእቲ ሌሊት፤ ወቦአት እንተ ትንእስ፤ ወሰከበት ምስለ አቡሃ፤ ወኢያእመረ፡ በሰኪቦታ፥ ወበተንሥአታ።

«ወፀንሳ ክልኤሆን አዋልዲሁ ለሎጥ፡ እምአቡሆን። ወወለደት፡ እንተ ትልህቅ፡ ወልደ፤ ወሰየመቶ ስሞ፡ ‹ሞአብ›፣ ‹ዘእምአቡየ› ብሂል፤ ወውእቱ፡ አቡሆሙ፡ ለሞአባውያን። ወወለደት ወልደ፡ እንተ ትንእስኒ፤ ወሰየመቶ፡ ‹አሞን›፡ እንዘ ትብል፡ ‹ወልደ ሕዝብየ›፤ ወውእቱ አቡሆሙ፡ ለአሞናውያን።»

«እግዚአብሔርም፡ ለአብርሃም አለው፡- "የሰዶምና የገሞራ ጩኸት፡ እጅግ በዝቷልና፥ ኃጢአታቸውም፡ እጅግ ከብዳለችና፡ እንግዴህስ፡ ወደእኔ እንደመጣች፡ እንደጩኸቷ አድርገው እንደኾነ፡ ወርጄ አያለሁ፤ እንዲሁም ባይኾን፡ አውቃለሁ።"

«ሰዎቹም፡ ከዚያ ፊታቸውን አቀኑ፤ ወደሰዶምም ኼዱ። አብርሃም ግን፡ በእግዚአብሔር ፊት፡ ገና ቆሞ ነበር። አብርሃምም ቀረበ፤ አለም፡- "አቤቱ! በአንተ ዘንድ እውነተኛ፡ እንደሓሰተኛ አይቆጠር! እውነተኞችን፡ ከሓሰተኞች [ጻድቃንን፡ ከኃጥአን] ጋር ዐብረህ አታጥፋ! ...በዚያ፡ ፲ (ዓሥር) እውነተኞች ቢገኙሳ፡ ስለእነዚህ፡ ስለ፲ሩ እውነተኞች ስትል፡ ያችን ከተማ አትምርምን? ነገር ግን፡ ዓሥሩን እውነተኞች ጭምር፡ ከኃጢአተኞቹ ጋር ዐብረህ ታጠፋቸዋለህን?" እግዚአብሔርም አለው፡- "የለም! ስለ፲ሩ (ዓሥሩ) እውነተኞች ስል፡ ያችን ከተማ፡ እምራለሁ እንጂ፡ አላጠፋም።" ከአብርሃም ጋር የሚያደርገውን ንግግር፡ እንዲህ እንደጨረሰ፡ እግዚአብሔር ኼደ። አብርሃምም፡ ወደመኖሪያው ተመለሰ።

«እነዚያም፡ ኹለቱ መላእክት፡ ሲመሽ፡ ሰዶም ደረሱ። ሎጥም፡ በሰዶም፡ በከተማዪቱ በር ተቀምጦ ነበርና፡ ባያቸው ጊዜ፡ ተነሥቶ ተቀበላቸው፤ ሰገደላቸውም። እንዲህም አላቸው፦ "ጌቶቼ! እባካችሁ፡ ወደባሪያችሁ ቤት አቅኑ! በዚያም ዕደሩ! እግራችሁንም ታጠቡ! ማልዳችሁም፡ መንገዳችሁን ትኼዳላችሁ!"

«እነርሱም፡ "በአደባባዩ እናድራለን እንጂ፡ አይኾንም!" አሉት።

«እርሱም፡ በግንባሩ ተደፍቶ እየሰገደላቸው፡ እጅግ ስለዘበዘባቸው፡ ወደቤቱ አቀኑ፤ እንደደረሱም፡ ገቡ፤ በዚያም፡ በተጋገረ ኅብስት፡ ማዕድ አቀረበላቸው፤ ያንንም በሉ፤ ጠጡ።

«ገናም ሳይተኙ፡ የዚያች ከተማ ሰዎች፡ ከብላቴናው ጀምሮ እስከሽማግሌው ድረስ ያሉት፡ ያገሩ ሕዝብ ተጠራርተው፡ በአንድነት፡ ያን ቤታቸውን ከበቡት። ሎጥንም ጠርተው፡ እንዲህ አሉት፦ "በዚህ ሌሊት ወደቤትህ የገቡት ሰዎች፡ ወዴት ናቸው? ሩካቤ ሥጋን እንፈጽምባቸው ዘንድ፡ ወደእኛ አውጣቸው!"

«ሎጥም፡ ወደእነርሱ፡ ወደደጅ ወጣ፤ መዝጊያውንም፡ በኋላው ዘግቶ፡ በፊታቸው ቆመ፤ አላቸውም፦ "ወንድሞቼ ሆይ! ይህን ክፉ ነገር፡ በእነዚህ እንግዶቼ ላይ ልታደርጉ፡ ለእናንተ አይገባችሁም። እነሆ! ወንድን ያላወቁ፡ ኹለት ሴቶች ልጆች አሉኝ፤ እነርሱን ላውጣላችሁና፡ በእነርሱ፡ የወደዳችሁትን አድርጉባቸው። በጣራዬ ጥላ ሥር፡ በእንግድነት በገቡት፡ በእነዚህ ሰዎች ብቻ፡ እባካችሁ፡ ምንም አታድርጉ!"

«እነርሱም፡ "ወዲያ ኺድ! አንተ ደግሞ፡ በእኛ ዘንድ፡ በመጻተኛነት ልትኖር እንጂ፡ በእኛ ላይ ልትፈርድ የመጣህ አይደለህም። አለዚያ፡ አኹን፡ ከእነርሱ ይልቅ፡ በአንተ ላይ የባሰ ሥቃይን እናደርስብሃለን።" ብለው፡ እጅግ ተጋፉት፤ አየሉበትም። የደጁንም መዝጊያ ለመስበር ቀረቡ።

«ኹለቱም ሰዎች፡ እጃቸውን ዘርግተው፡ ሎጥን፡ ወደእነርሱ ዘንድ፥ ወደቤት አገቡት፤ በሩንም ዘጉት። በቤቱ ደጃፍ የነበሩትንም፡ እነዚያን ሰዎች፡ ከብላቴኖቻቸው ጀምረው፡ እስከሽማግሌዎቻቸው ድረስ ያሉትን ኹሉ፡ አሳወሩዋቸው። እነርሱም፡ ደጃፉን ለማግኘት፡ እስኪደክሙ ጣሩ፤ ነገር ግን፡ አልኾነላቸውም።

«ኹለቱ መላእክት፡ ሎጥን አሉት፦ "በውኑ፡ በዚህ ከተማ፡ የአንተ የኾኑ፡ ወንድሞች፥ ወይም፡ አማቾች፥ ወንዶችና ሴቶች ልጆችም አሉን? አንተ የምታውቀው ወዳጅ ቢኖርህም፡ ኹሉንም፡ ከዚህ ሥፍራ አስወጣቸው! እኛ፡ ይህን ቦታ ልናጠፋው ነውና። ጩኸታቸው፡ በእግዚአብሔር ፊት፡ ታላቅ ኾኗልና። ስለዚህም፡ እንደመስሳት ዘንድ ሰድዶናል።"

«ሎጥም፡ ወጣ፤ ኹለት ሴቶች ልጆቹን ወደሚያገቡት አማቾቹም ኼዶ፡ "ተነሡ! ከዚህ ከተማም ውጡ! እግዚአብሔር፡ ሊደመስሰው ነውና።" አላቸው። አማቾቹ ግን፡ ይህን ሲላቸው፡ የሚያፌዝባቸው መሰላቸው።

«ኀህም በቀደደ ጊዜ፡ መላእክት፡ ሎጥን፡ "ተነሥ! ኹለቱን፡ ሴቶች ልጆችህንና ሚስትህን ይዘህ፡ ከዚህ በቶሎ ውጣ! የዚህች ከተማ ሰዎች በፈጸሙት ኃጢአታቸው ምክንያት፡ አንተም እንዳትሞት!" እያሉ ያስቸኩሉት ጀመር። እንዳይጠፉ እግዚአብሔር አዝኖላቸዋልና፡ እኒሁ፡ ኹለት ሰዎች፡ የእርሱን እጅ፥የሚስቱንና የኹለቱንም፡ የሴት ልጆቹን እጆች ይዘው፡ ወደውጭ አወጧቸው።

«በሚያወጧቸውም ጊዜ፡ እንዲህ አሉት፡- "እንግዴህ፡ ራስህን አድን! ወደኋላህም አትመልከት! በአንተም፡ ክፉው እንዳያገኝህ፡ በዚች ከተማ፡ በአካባቢያዋም፥ በተራራዋም ላይ አትቁም!

«ሎጥም አላቸው፡ "ጌቶቼ ሆይ! በፊታችሁ፡ እንዲህ፡ ምሕረትን ካገኘሁ፥ ነፍሴንም፡ ታድናት ዘንድ፡ ምሕረትህን በእኔ ላይ አብዝተሃልና፡ ልመናዬን፡ በጄ በሉኝ! ክፉው እንዳያገኘኝ፥ እንዳልሞትም፡ እኔ፡ ወደዚህ ተራራ ሸሽቼ ላመልጥ፥ ራሴንም ማዳን አይቻለኝም። እነሆ፡ ይህች ከተማ፡ ቅርብ ናት፤ ትንሽም ናት። ወደርሷ ሸሽቼ ለማምለጥ፡ ራሴንም ለማዳን፡ ወደዚያ ልሩጥ! ነፍሴን ለማትረፍ፡ ትንሽ አይደለችም።"

«እርሱም አለው፡- "ስለእርሷ፡ የተናገርሃትን ይህችን ከተማ እንዳላጠፋት፡ እነሆ፡ በዚህ ነገር፡ የለመንኸኝን ተቀብዬሃለሁ። እንግዴህ፡ ወደዚያ፡ በፍጥነት ሸሽተህ አምልጥ! በዚያም፡ ራስህን አድን!" ስለዚህም፡ የዚያች ከተማ ስም፡ "ሴጎር" ተባለ።

«እግዚአብሔርም፡ በሰዶም እና በገሞራ ላይ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ፥ ከሰማይ፡ እሳትና ዲን አዘነበ፤ እነዚያንም ከተሞች፥ በዙርያቸው ያለውንም ኹሉ፥ በውስጣቸው የሚኖሩትንም ኹሉ፥ የምድራቸውንም ቡቃያ ኹሉ ገለባበጠ።

«የሎጥም ሚስት፡ ወደኋላዋ ተመለከተች፤ የጨው ሓውልትም ኾነች።

«አብርሃምም፡ በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ወደነበረበት ሥፍራ ለመኼድ ማልዶ ተነሣ። ወደሰዶምና ወደገሞራ፥ በዚያች አገር ወዳለውም ምድር ኹሉ ተመለከተ፤ እነሆም፡ በዚያን ጊዜ፡ እሳት፡ ከምድር፡ እንደምድጃ ጢስ፡ ወደላይ ሲወጣ አየ።

«እንዲህም ኾነ! ሎጥ፡ በውስጣቸው፡ ይኖርባቸው የነበሩትን፡ እነዚያን ከተሞች፥ አካባቢያቸውንም ኹሉ፡ እግዚአብሔር፡ በደመሰሰ ጊዜ፡ አብርሃምን አሰበው፤ ሎጥንም፡ ከዚህ ጥፋት መካከል አወጣው።

«ሎጥም፡ ከሴጎር ወጣ፤ በሴጎር ውስጥ መቆየትን ስለፈራ፡ ወደተራራ ኼዶ፡ ይኖር ጀመረ፤ በዚያም ባለች ዋሻ ውስጥ፡ እርሱና ኹለቱ ሴቶች ልጆቹ ተቀመጡ።

«ታላቂቱም፡ ለታናሽቱ፡ እንዲህ አለቻት፡- "እነሆ አባታችን፡ እየሸመገለ ነው፤ ልጆችን ለመውለድ፡ ከእኛ ጋር ተጋብቶ ሊገናኘን የሚችልና የሚመስለን ወንድ፡ እንግዴህ፡ በምድር ላይ የለም። ስለዚህ፡ ነዪ! አባታችንን፡ ወይን ጠጅ አጠጥተን እናስክረውና፡ ከእርሱ ጋር እንተኛ! ከአባታችንም፡ ዘር እናስቀር!"

«ለአባታቸውም፡ የወይን ጠጁን አጠጡት። በዚያችም ሌሊት፡ ታላቂቱ፡ ወደአባቷ ገባች፤ ከእርሱም ጋር ተኛች። እርሱ ግን፡ ይህን መኘታዋን፥ መነሣቷንም አላወቀም። ከዚህም በኋላ፡ ታላቂቱ፡ ለታናሺቱ፡ እንዲህ አለቻት፡- "እነሆ፡ እኔ፡ ትናንት፡ ከአባታችን ጋር ተኛሁ፤ አኹን እንደገና፡ የወይን ጠጁን እናጠጣውና፡ አንቺ ደግሞ፡ በዚች ሌሊት፡ ከእርሱ ጋር ተኚና፡ ከአባታችን፡ ዘር እናስቀር!" በዚያችም ሌሊት፡ ለአባታቸው፡ የወይን ጠጁን አጠጡት። ታናሺቱም፡ ወደአባቷ ገባች፤ ከእርሱም ጋር ተኛች። እርሱ ግን፡ ይህን መኘታዋን፥ መነሣቷንም አላወቀም።

«ኹለቱም የሎጥ ሴቶች ልጆች፡ ከአባታቸው ፀነሱ። ታላቂቱም፡ ወንድ ልጅን ወለደች፤ ስሙንም፡ "ከአባቴ ያገኘሁት" ስትል፡ "ሞአብ" ብላ ጠራችው፤ እርሱም፡ "የሞአባውያን አባት" ነው። ታናሺቱም ደግሞ፡ ወንድ ልጅን ወለደች፤ ስሙንም፡ "የወገኔ ልጅ" ስትል፡ "አሞን!" ብላ ጠራችው፤ እርሱም፡ "የአሞናውያን አባት" ነው።» (ዘፍጥ. ፲፰፥ ፳-፴፫፤ ፲፱፥ ፩-፴፰።)

## ከአዲስ ኪዳኑ ክፍል።

፫፡ "ወበከመ ኮነ፡ በመዋዕሊሁ ለኖኅ፡ ከማሁ ይከውን፡ በምጽአቱ፡ ለወልደ ዕጓለ-እመሕያው፤ እንዘ ይበልዑ፥ ወይሰትዩ፥ ወያወስቡ፥ ወይትዋሰቡ፡ እስከአመ ቦአ ኖኅ፡ ውስተ ንፍቀ ታቦት፤ ወመጽአ ማየ አይኅ፤ ወአጥፍአ ኵሎ ኀቡረ። ወበከመ ኮነ፡ በመዋዕሊሁ ለሎጥ፤ እንዘ ይበልዑ፥ ወይሰትዩ፥ ወየሐንጹ፥ ወይተክሉ፥ ወይሠይጡ፥ ወይሣየጡ፤ እስከዕለተ ወጽአ ሎጥ፡ እምሰዶም፤ ወአዝነመ እግዚአብሔር፡ እሳተ፣ ወተየ፡ እምሰማይ፤ ወአጥፍአ ኵሎ። ከማሁ ውእቱ፡ ምጽአቱ ለወልደ ዕጓለ-እመሕያው፡ ኢይትዐወቅ። ...ተዘከርዋ፡ ለብእሲተ ሎጥ።"

"የማርያም ልጅ፡ ዳግመኛ የሚመጣበት ጊዜና ኹኔታ፡ ልክ፡ በኖኅ ዘመን እንደኾነው ይኾናል። ይህም፡- 'ኖኅ፡ ከነቤተሰቡ፡ ወደመርከቡ ጒርጅ እስከገባባት ሰዓት ድረስ፡ ሕዝቡ፡ እየበሉና እየጠጡ፥ እያገቡና እየተጋቡ ሣሉ፡ የጥፋቱ ውኃ ማዕበል መጥቶ፡ ኹሉንም አጥለቅልቆ፡ በአንድነት እስካጠፋቸው ድረስ፡ ሳያውቁና ሳይዘጋጁ፡ በድንገት እንደደረሰባቸው ዓይነት ይኾናል!' ማለት ነው።

"ደግሞም፡ "የማርያም ልጅ፡ ዳግመኛ የሚመጣበት ጊዜና ኹኔታ፡ ልክ፡ በሎጥ ዘመን እንደኾነው፡ እንደዚያ ይኾናል። ይህም፡- 'ሎጥ፡ ከነቤተሰቡ፡ ከሰዶም እስከወጣባት ዕለት ድረስ፡ ሕዝቡ፡ እየበሉና እየጠጡ፥ ሕንጻ እየሠሩና አትክልት እየተከሉ፥ ያንንም፡ እየተሻሻጡና እየተገበያዩ ሣሉ፡ እግዚአብሔር ብቻ ባወቀው፡ እሳትና ዲን፡ እንደዝናም፡ ከሰማይ ወርዶ፡ ኹሉን እስካጠፋቸው ድረስ፡ ሳያውቁና ሳይዘጋጁ፡ በድንገት እንደደረሰባቸው ዓይነት ይኾናል።...[በዚያን ጊዜ፡ ከጥፋቱ ለማምለጥ፡ ታድላ የነበረችውን፥ ነገር ግን፡ በድብቅ እምነቷና ግብሯ፡ ሕዝቡን መስላ በመገኘቷ፡ ጨው ኾና የቀረችውን]፡ የሎጥን ሚስት አስቧት!!' ማለት ነው።" (ሉቃ. ፲፯፥ ፳፮-፴፪።)

፬፡ «ወዘኢያስተርኢ እግዚአብሔር፡ እምፍጥረተ-ዓለም፡ ይትዐወቅ በፍጥረቱ፡ በኀልዮ፥ ወበአእምሮ፤ ወከመዝ፡ ይትአመር ኃይሉ፥ ወመለኮቱ፡ ዘለዓለም። ከመ ኢይርከቡ፡ በዘይትዋሥኡ፡ እስመ እንዘ የአምርዎ ለእግዚአብሔር፡ አኮ ከመ እግዚአብሔር፡ ዘአእኰትዎ፥ ወሰብሕዎ፡ ዘእንበለ ዘሓሰውዎ፤ ወረከሱ በኀሊናሆሙ፤ ወተጸለለ ልቦሙ። ወእንዘ ይፈቅዱ ይጥበቡ፡ ዓብዱ፤ እስመ ወለጡ፡ ስብሓቲሁ ለእግዚአብሔር፡ ዘኢይመውት፤ ወአምሳለ ርእየተ ሰብእ መዋቲ፡ ረሰዩ፤ ወከመ እንስሳ፥ ወከመ አራዊት፥ ወከመ አዕዋፍ።

«ወበእንተዝ፡ አግብአሙ፥ ወኀደጎሙ፡ ከመ ያርኵሱ ርእሶሙ፥ ለሊሆሙ፤ ወያኅሥሩ ነፍስቶሙ። እስመ ሓሰተ ረሰይዎ ለጽድቀ እግዚአብሔር፤ ወአምለኩ፤ ወተጸእጽኡ ተግባሮ፤ ወኀደግዎ፡ ለፈጣሬ ኵሉ፡ ዘውእቱ፡ አምላክ ቡሩክ፤ ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

«ወበእንተዝ፡ ወሀቦሙ እግዚአብሔር፡ መቅሠፍተ እኩየ፤ ወአንስትያሆሙኒ፡ ኃደጋ ፍጥረቶን፤ ወተመሰላ፡ በዘኢኮነ ፍጥረቶን። ወከማሁ፡ እደዊሆሙኒ፡ ኀደጉ አንስቲያኒሆሙ፤ ወነዱ፡ በፍትወቶሙ፤ ወገብኡ በበይናቲሆሙ፡ ብእሲ፡ ላዕለ ብእሲ፡ ኀሣሮሙ ገብሩ። ወባሕቱ፡ ይረክቡ ፍዳሆሙ፤ ወይገብእ ጌጋዮሙ ዲበ ርእሶሙ።

«ወበከመ ኢኀለይዎ ለእግዚአብሔር በልቦሙ፡ ከማሁ፡ እግዚአብሔርኒ፡ ወሀቦሙ ልበ ዕበድ፡ ከመ ይግበሩ ዘንተ፡ ዘኢይደሉ። እንዘ እሙንቱ፡ ጽጉባነ ኵሉ ዐመፃ፥ ወእከይ፥ ወዱግ፥ ወትዕግልት፥ ወጽጉባነ ቅንአት፥ ሓማምያን፥ ቀታልያን፥ ጕሕላውያን፥ መስተመይናን፥ ዝጐራን፥ እኩያነ ልማድ ወግእዝ። ሓማይያን፥ መስተሣልቃን፥ መስተሓብባን፥ ዕቡያን፥ ዝሉፋን፥ ዐላውያን፥ ሓሳውያን፥ ጸላእያነ-እግዚእ፥ ሥሑጻን። አብዳን፥ ወዝንጉዓን፥ ወመስተሓሥሣነ ለእከይ። ወአልቦሙ ምሕረት፡ እንዘ ለሊሆሙ፡ የአምሩ ኵነኔሁ ለእግዚአብሔር፡ ከመ ይደልዎ ሞት፡ ለዘገብረ ዘንተ፤ ከመዝ አኮ ባሕቲቶሙ ዘይገብርዎ፤ ዓዲ፡ ለባዕድኒ፡ ይዌሕክዎ ያግብእዎ።»

«በባሕርዩ የማይታየው እግዚአብሔር፡ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ፡ በፍጥረቱ፥ በሰው ኅሊናና ዕውቀትም ይታወቃል፤ ስለዚህም፡ ኃይሉ፥ የዘለዓለም አምላክነቱም፡ ግልጥ ኾኖ ይታያል። እነርሱ ግን፡ እግዚአብሔርን፡ እንዲህ እያወቁት፡ ያከበሩትና ያመሰገኑት፡ በሓሰት እንጂ፡ እንደእግዚአብሔርነቱ ስላልኾነ፡ የሚያመካኙት አጡ። ስለዚህም፡ በአሳባቸው፡ ረከሱ፤ ልቦናቸውም፡ ታወረ፤ ጥበበኞች ሊኾኑ ሲፈልጉ፡ አላዋቂዎች ሞኞች ኾኑ፤ የማይሞት እግዚአብሔርን፡ ክብሩን፡ ሟች በኾነው፡ በሰው፥ በእንስሳ፥ በአራዊትና በአዕዋፍ መልክ መስለው ለወጡ።

«ስለዚህም፡ እርስ በእርሳቸው፡ ሥጋቸውን ሊያዋርዱ፥ እየራሳቸውንም እንዲያረክሱ፡ እግዚአብሔር ተዋቸው፤ ለልባቸውም ፍትወት፡ አሳልፎ ሰጣቸው። የእግዚአብሔርን እውነት፡ በሓሰት ለውጠዋልና፤ በፈጣሪም ፈንታ፡ እርሱ የፈጠረውን አምልከዋልና፤ አገልግለዋልምና፤ የኹሉ ፈጣሪ የኾነውን እርሱን ትተዋልና፤ እርሱም፡ ለዘላለም ሲመሰገን የሚኖረው አምላክ ነው፤ አሜን።

«ስለዚህም፡ እግዚአብሔር፡ ክፉ መቅሠፍትን፡ በላያቸው አመጣባቸው፤ ይኸውም፡ ሴቶቻቸው፡ በሥጋ ፍላጎታቸው፡ የተፈጥሮ ባሕርያቸው የኾነውን፡ ወንዶችን አግብተው፡ በግብረ-ሥጋ መገናኘትን ትተው፡ የተፈጥሮ ባሕርያቸው ያልኾነውን፡ እርስ በእርሳቸው ተጋብተው፥ እንስሳትን ሳይቀር፡ በግብረ-ሥጋ መገናኘትን መምረጣቸው ነው። እንዲሁ ደግሞ፡ ወንዶቻቸው፡ ሴቶቻቸውን አግብተው፡ ተፈጥሮአዊዉን የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ማድረግን ትተው፡ በሥጋቸው ከሚነድደው የሴሰኝነት ቃጠሎ ጽናት የተነሣ፡ እርስ በርሳቸው እየተጋቡ፡ የወንድ ለወንድ፡ የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን በመፈጸም፡ አስነዋሪ ወራዳነታቸውን አረጋገጡ። በዚህም ምክንያት፡ ፍዳቸውን ይቀበላሉ፤ የኃጢአታቸውም ብድራት፡ በእየራሳቸው ላይ ይመጣባቸዋል።

«በውስጥ ሰውነታቸው ያለውን፡ እግዚአብሔርን፡ በየኅሊናቸው መርምረው፡ ሊያገኙትና ሊያውቁት ባልፈለጉ መጠን፡ እንዲሁ፡ እርሱ፡ እግዚአብሔር ደግሞ፡ ይህን፡ የማይገባውን፡ የነውርና የርኵሰት፥ ጸያፍና አዋራጅ ሥራ ያደርጉ ዘንድ፡ ለማይረባ አእምሮ፡ አሳልፎ ሰጣቸው።

«ከዚህ የተነሣ፡ ዓመፃን፥ ክፋትንና ተንኰልን፥ ግፍንም፥ ቅንዓትንም ኹሉ እጅግ የተመሉ ምቀኞች፥ ነፍሰ-ገዳዮች፥ አታላዮች፥ በስስት የተቃጠሉ፥ ትዕቢተኞች፥ ትምክህተኞች፥ የክፉ ልማድና ጠባይ ሱሰኞች፥ ሓሜተኞችና አሾክሿኪዎች፥ በእውነት ላይ የሚሣለቁ፥ ነቃፊዎች፥ ተሳዳቢዎች፥ ከሃዲዎች፥ ሓሰተኞች፥ እግዚአብሔርን የሚጠሉ፥ አሽሟጣጮች፥ አዋራጆች፥ ሰነፎችና ቍም-ነገር የሌላቸው ዝንጉዎች፥ ነገረ-ሠሪዎችም ኾኑ። ደግሞም፡ ይህን ዓይነቱን ኃጢአት የሚያደርግ ኹሉ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ በራሱ ላይ፡ የሞት ፍርድን እንዳመጣ የሚቈጠር መኾኑን፡ እየራሳቸው እያወቁ፡ እነርሱ ግን፡ ለሰው፡ ምሕረት ስለሌላቸው፡ ይህን ማድረጋቸው፡ ለእየራሳቸው፡ የሚበቃቸው ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ ሌላውም ኹሉ፡ የዚህ ክፉ ግብራቸው፡ ተባባሪያቸውና ግብረ-ዐበራቸው እንዲኾን ያነሣሣሉ።» (ሮሜ. ፩፥ ፳-፴፪።)

፯፡ "ወእግዚአብሔርሰ፡ ለመላእክቲሁ፡ ጥቀ አቢሶሙ፡ ኢመሐኮሙ፤ አላ፡ ወደዮሙ ውስተ ጸዕረ-ደይን፡ ዘርሱን፤ ወመጠዎሙ፡ ይትኰነኑ፤ ወይንበሩ ውስተ ጸዕረ-ደይን።

"ወለዓለምሰ ቀደምት፡ ኢምሐኮሙ፤ አላ፡ አትረፈ፡ ሰማኒተ ነፍስ፡ ምስለ ኖኅ፡ ዘዐቀባ ለጽድቅ፣ ከመ ይኩን፡ ዜናዌ በጽድቅ፤ ወለባዕዳንሰ ሰብእ ረሲዓን፡ ፈነወ አይኅ ላዕሌሆሙ።

"ወለአህጉረ ሰዶምኒ፥ ወገሞራ፡ አውዐዮን፥ ወገፍትኦን፤ ወከመዝ ኰነኖሙ፤ ወአርአያ ረሰዮሙ፣ ለእለ በደኃሪ መዋዕል፡ ለኃጥኣን።

"ወለጻድቅሰ ሎጥ፡ ዘይትገፋዕ፡ እምእለ ይኤብሱ፡ በምግባረ ዝሙቶሙ፡ አድኅኖ። ወእንዘ ይሬኢ፥ ወይሰምዕ፥ ወህዱር ምስሌሆሙ፥ ወዕለተ፡ እምዕለት፡ ያጼዕርዋ ለነፍሱ ጻድቅት፡ በእከየ ምግባሮሙ።

"ናሁኬ አእመርነ፡ ከመ እግዚአብሔር ይክል አድኅኖቶሙ፡ እምነ መንሱት፡ ለጻድቃን። ወለኃጥኣንሰ፡ ዕለተ ደይን ትጸንሖሙ፡ ለተጽሕሮ። ወፈድፋደሰ፡ ለእለ ይትልውዋ ድኅሬሃ፡ ለፍትወቶሙ፣ ወያጌምንዎ ለሥጋሆሙ፣ ወያስተሓቅርዎ ለፈጣሪሆሙ፡ ኅቡላን፥ ወዝሉፋን፡ እለ ኢይደነግፁ፡ ከመ ይፅርፉ ላዕለ ስብሓቲሁ።"

"እግዚአብሔር፡ እጅግ ኃጢአትን ላደረጉ መላእክት፡ እንዲህ ካልራራላቸው፥ ነገር ግን፡ ፍጹም የጣር ሥቃይ ወደጸናበት ገሃነም ከጨመራቸው፥ በዚያም፡ በገሃነም ኹነው፡ ፍርዳቸውን እንዲቀበሉ፡ አሳልፎ ከሰጣቸው፣

"እንዲሁም፡ ለቀደመው ዓለም ፍጡሮቹ ካልራራላቸው፣ ነገር ግን፡ [የእግዚአብሔርን] እውነት ጠብቆና ይዞ በመገኘቱ፡ የዚችው እውነት አብሣሪ ምስክር የኾነውን ኖኅን፡ ከነቤተሰቡ ስምንት ነፍሱን አትርፎ በማዳን፡ በቀረው፡ በኃጢአተኛው የሰው ዘር ላይ በሙሉ፡ የጥፋትን ውኃ ካወረደ፣

"የሰዶምንና የገሞራን ከተሞችንም፡ እንዲያ፡ በእሳት ካነደዳቸውና ከገለባበጣቸው፥ ደግሞም፡ በኋለኛው ዘመን ለሚኖሩ፡ ለመሰሎቻቸው ሓሰተኞች፡ ምሳሌ እንዲኾኑ፡ እንደዚህ ከፈረደባቸው፣

"ከሴሰኝነት የኃጢአት ሥራቸው የተነሣ፡ እንዲያ በበደሉ፡ ክፉ ሕዝቦች የተገፋውን፥ በመካከላቸውም ተቀምጦ፡ ይህንኑ ርኩስ ተግባራቸውን፡ ዕለት በዕለት እያየና እየሰማ፡ ለ[እግዚአብሔር] እውነት ያደረችውን ነፍሱን ሲያስጨንቅ የኖረውን፡ የእውነት ሰው ሎጥን፡ እንዲህ፡ ከግፍ እጃቸው ካዳነ፣

"እንግዲህ፡ እግዚአብሔር፡ በእውነት የሚያመልኩትን እውነተኞችን፡ ከፈተናና ከመከራ ጠብቆ እንደሚያድናቸው፥ ሓሰተኞችን ግን፡ ይልቁንም፡ የሥጋ ፈቃዳቸውን፡ ከኋላዋ እየተከተሉ፡ ፈጣሪያቸው፡ በተፈጥሮ ያቀዳጃቸውን ክብር በመናቅና በማዋረድ፡ ሰውነታቸውን የሚያረክሱ፥ በዚህ ድርጊታቸውም፡ የእርሱን ፈጣሪነት መንቀፋቸውና መስደባቸው፥ መቃወማቸውም መኾኑን አስተውለው የማይደነግጡ ደፋሮችና ተሳዳቢዎች ስለኾኑ፡ ቅጣታቸውን ለሚቀበሉበት፡ ለፍርድ እንደሚያቆያቸው፡ እነሆ፡ እናውቃለን።" (፪ጴጥ. ፪፥ ፬-፲።)

፺. "እስመ ተደመሩ ብክሙ ሰብእ ረሲዓን፡ እለ ጽሑፋን ቀዲሙ፡ ለዝንቱ ደይን፡ እለ ይፌልስዋ፡ ለጸጋ እግዚአብሔር፡ ውስተ ዝሙቶሙ፤ ወይሕክድዎ፡ ለዘውእቱ ባሕቲቱ ንጉሥ፡ ውእቱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ።

"ወተአምሩ ምዕረሰ፡ ከመ ኢየሱስ፡ አድኀነ ሕዝብ፡ እምድረ ግብፅ፤ ወበዳግምሰ ለእለ ኢአምኑ አጥፍአሙ።

"ወለመላእቲሁኒ፡ እለ ኢዐቀቡ ፍጥረቶሙ፤ ወኀደግዋ ለሥርዓቶሙ፡ ውስተ ደይን፡ አንበሮሙ፤ ወተዓሥሩ፡ ለዕለት ዓባይ፡ ለዘለሊሆሙ አቅነዩ ርእሶሙ።

"ወከማሁ ሰዶሙኒ ወገሞራ፥ ወአህጉርኒ፡ እለ ምስሌሆን፥ ወበአርአያሆን፡ ዘመዋ፤ ወተለዋሆን፡ በፍትወተ ዝሙት፡ ሜሞሙ ውስተ ደይን፡ ዘለዓለም፤ ወተመጠዋ ኵነኔሆን።

"ወከማሁ እሉኒ፡ እለ በሕልሞሙ፡ ያጌምኑ ሥጋሆሙ፤ ወይክሕድዎ ለእግዚአሙ፤ ወይፀርፉ ላዕለ ስብሓቲሁ።"

"እርሱ ብቻውን፡ ንጉሥ የኾነውን፡ ኢየሱስ መሲሕን የካዱ፥ በሴሰኝነታቸውም፡ የእግዚአብሔርን ጸጋ የለወጡ፥ እነዚህ፡ ለዚህ ኵነኔ፡ አስቀድመው የተጻፉ፡ ክፉዎች ሰዎች፡ በእናንተ ውስጥ ገብተዋልና።

"ኢየሱስ፡ ሕዝቡን፡ ከምድረ-ግብፅ፡ አንድ ጊዜ እንዳዳነ፥ ዳግመኛም፡ ያላመኑትን እንዳጠፋ ታውቃላችሁ።

"መላእክቱም፡ የተፈጥሮ ባሕርያቸውን ጠብቀው ባለመገኘታቸው፥ የተሰጣቸውን ሥርዓታቸውንም ትተው፡ እየራሳቸውን፡ በእየራሳቸው፡ ለኵነኔ ዳርገውና አስገዝተው፡ለታላቁ የፍርድ ቀን በእሥራት አስጠብቀው ይገኛሉ።

"እንደዚሁም ኹሉ፡ ሰዶም እና ገሞራ፥ ከእነርሱም ጋር የነበሩት ከተሞች፡ እነርሱን መስለው አመነዘሩ፤ የአመንዝራነት ፍላጎታቸውንም ተከትለው ስለሴሰኑ፡ እየራሳቸውን ለኵነኔ ዳርገው፡ ዘለዓለማዊዉን የቅጣት ፍርዳቸውን ተቀበሉ።

"በሕልማቸው እየኖሩ ያሉ፡ እነዚህ ደግሞ፡ እንደዚህ፡ ሥጋቸውን በሴሰኝነት እያረከሱ፡ ፈጣሪያቸው እግዚአብሔርን ይክዳሉ፤ በጌትነቱም ላይ፡ የስድብ ቃልን ይናገራሉ።" (የያዕቆብ ወንድም፡የይሁዳ መልእክት ፩፥ ፬-፰።)

*፲: "ብፁዓን፡ እለ አንጽሑ አልባሲሆሙ፡ ከመ ይኩኑ ሥልጣኖሙ ላዕለ ዕፀ-ሕይወት፤ ወይበውእዋ፡ እንተ አናቅጺሃ፡ ላዛ ሀገር።*

*"ወይወፅኡ አፍአ፡ ኀምስቱ አክላብ፡ እለ ሥራይ፥ ወዘማውያን፥ ወቀታልያን፥ ወእለ ያመልኩ ጣዖተ፥ ወኵሎሙ፡ እለ ያፈቅሩ ግብረ-ሐሰት።"*

*"በሕይወት-ዛፍ ላይ፡ ሥልጣን ይኖራቸው ዘንድ፡ ልብሶቻቸውን ያነጹ፥ በደጃፎቿም፡ ወደዚያችም አገር የሚገቡ፡ ብፁዓን ናቸው።*

*"ሥራይን የሚያደርጉ፥ አመንዝራዎች፥ ነፍሰ-ገዳዮች፥ ልዩ ልዩ ጣዖታትን የሚያመልኩና የሐሰትን ሥራ የሚወድዱ ኹሉ፤ እነዚህ አምስቱ ውሾች ግን፡ ወደውጭ ይጣላሉ።"* (ራእ. ፳፪፥ ፲፬-፲፭።)

## ግብረ-ሰዶም፡ እንዴት መጣ?
## ማንስ አመጣው?
## ለምንስ፡ እንዲህ ተስፋፍቶ፡ ከዚህ ደረጃ ደረሰ?

የእኛ፡ የእግዚአብሔር የኾነችውን፥ እርሷም፡ "ኢትዮጵያ" ተብዬ፡ በመላው የሰማይና የምድር ፍጥረታተ ዓለማት ላይ የሰፈንሁትን፡ አንዲቱ፡ ዘለዓለማዊት መንግሥት የኾንሁትን፡ እኔን፡ ሰዎች፡ ከኹለት ከፍለው፥ እየራሳቸውንም፡ የሚቻላቸው መስሏቸው፡ "ከእርሷ፡ ለይተናል!" ብለው፡ እርስ በርሳቸው፡ እየተላለቁ ባሉት፡ በሥጋውያኑ አብያተ መንግሥታትና በመንፈሳውያኑ አብያተ ሃይማኖታት ዘንድ ሳይቀር፡ በዚህ፡ በግብረ-ሰዶም አነሣሥና መስፋፋት ረገድ፡ ይነስም፡ ይብዛም፥ ይቅለልም፡ ይክበድም እንጂ፡ እያንዳንዱና ኹሉም ሰብአዊ ፍጡር፡ በግለሰብና በቤተሰብ፥ በኅብረተሰብና በብሔረሰብ፥ በዓለመሰብ ደረጃ ጭምር፡ አንዳች ዓይነት አፍራሽና አሉታዊ አስተዋጽኦ ያላደረገ የህልውና ዘርፍ፡ ከቶ የለም።

እዚህ ላይ፡ ለዚህ ጠንቅ፡ መነሻ የኾኑትን ግልጽ ምክንያቶች፡ ዘርዝሮ ማቅረብ፡ አስፈላጊ ይኾናል። ይህን ከማድረግ በፊት ግን፡ ከዚሁ፡ ከግብረ-ሰዶም ጠንቅ ጋር የተያያዘ፡ አንድ የማይታለፍ እውነታን፡ ገሃድ ማድረግ ያሻል፤ እርሱም፡ "ይኸው የግብረ-ሰዶም ጠንቅ፡ በሰብአዊው አካልና ባሕርይ ውስጥ ዐብሮ ተፈጥሮ፡ ኋላ፡ ያ፡ የወንድ ኾነ፡ የሴት ሰውነት፡ ለአካለ-መጠን ሲደርስ፡ ሊከሠት የሚችል፡ ጠባይዓዊ ዝንባሌ ነው!" እየተባለ የሚነገርለት ሰብአዊ መላምት፡ ከቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ እምነት አኳያ ሲታይ፡ ፈጽሞ ሓሳዊ፥ የተዛባና የተሳሳተ አስተሳሰብ መኾኑን የሚያረጋግጠው ቍም-ነገር ነው። ይኸውም፡ እንዲህ በሚል ቃል ይገለጣል፦

በመጀመሪያ ነገር፡ ራሱ፡ እጅግ መልካምና ያማረ፥ ጽሩይና ንጹሕ፥ ጣፋጭና ቅዱስ፥ የእነዚህም ኹሉ ምንጭ የኾነው፡ እግዚአብሔር፡ እንኳንስ፡ በመልኩ ፈጥሮ፡ "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ያለውን፥ በመጨረሻውም የሕይወት ዘመን፡ በተዋሕዶ፡ የራሱ አድርጎና ለትንሣኤ አካል አብቅቶ፡ በዘለዓለማዊ ሰንበትነት እየኖረበት ያለውን፡ ፍጥረታዊ ሰውነትን ቀርቶ፡ ሌላውን፡ መላውን የፍጥረቱን አባል፥ ጥቃቅኑንና ረቂቃኑን እንኳ ሳያስቀር፡ ኹሉንም፡ በፍጹም መልካምነትና ውበት፥ ጽርየትና ንጽሕና፥ ጣዕምና ቅድስና የፈጠረ መኾኑ ይታወቃል።

ታዲያ! «"ወገብሮ እግዚአብሔር ለሰብእ፡ እመሬተ ምድር፤ ወነፍሐ በገጹ፡ መንፈሰ ሕይወት፤ ወኮነ እጓለ እመ-ሕያው በመንፈሰ ሕይወት!"

"እግዚአብሔርም፡ ሰውን፡ ከምድር አፈር አበጀው፤ በፊቱም ላይ፡ የሕይወትን መንፈስ፡ እፍ አለበት፤ እርሱም፡ በዚህ የሕይወት መንፈስ፡ የሕያዋን እናት ልጅ ኾነ!" በተባለለት ሰውነት ውስጥ፡ ይኼን የመሰለውን፡ ኢተፈጥሮአዊና ብልሹ የኾነ ክፉ ነገር፡ ያሳድራል!» ብሎ፡ እንኳንስ ሊናገሩትና ከዚያም ዐልፎ ሊያደርጉት፡ ሊያስቡትም እንኳ የማይቃጣ ሓሰት አይኾንምን? አዎን! በእርግጥ፡ ሓሰት ነው። (ዘፍጥ. ፪፥ ፯፤ ፫፥ ፳።)

እንዲህማ ካልኾነ፡ እግዚአብሔር፡ በመልኩ ፈጥሮ፡ "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ለተባለለት አምላካዊ ጸጋ ያበቃው፥ በፍጹም ቅድስናና ንጽሓ ባሕርይም ያከበረው ይኼው ሰውነት፡ <u>የግብረ-ሰዶምን ፍትወተ-ሥጋ</u> ብቻ ሳይኾን፡ አጉል ምኞትን፥ ሓሰተኛነትን፥ ሥርቆትን፥ ምንዝርናንና መግደልን፡ የመሰሉትን፡ የክፋት ዝርያዎች ኹሉ፡ ኋላ፡ ለዓቅመ-አዳምና ለዓቅመ-ሔዋን ሲደርስ፡ በራሱ ምርጫ ፈጥሮ የሚያመጣቸው መኾናቸው ቀርቶ፡ በጥንተ-ተፈጥሮ፡ ከፈጣሪው ያገኛቸው ናቸው!" ሊባል አይደለምን? ነገር ግን፡ ይህ ዓይነቱ ስሑት ይትበሃል፡ ፈጽሞ ሊኾን፥ ሊያስኬድም አይችልም፤ ተቀባይነትም የለውም፤ ሰይጣናዊ ነውና።

አዎን! ይህ፡ <u>የግብረ-ሰዶም ፍትወተ-ሥጋ፡</u> ጠቅላላ ስሜቱ ጭምር፡ ከላይ እንደተጠቀሱት፡ የሥጋን ብቻ ሳይኾን፡ የነፍስ ሞትን ጭምር እንደሚያስከትሉት፡ እንደሌሎቹ፡ ልዩ ልዩ የኃጢአት ዓይነቶች፡ እያንዳንዱ ወንድ እና ሴት፡ ከፈጣሪያቸው በተሰጣቸው፡ የምርጫ ነጻነት፥ የመወሰን ሥልጣንና የመፈጸም ኃይል ተጠቅመው፥ እየራሳቸውም፡ ከእየራሳቸው ሰውነት አፍልቀው፡ በተግባር ላይ የሚያውሉት ኢ-ተፈጥሮአዊና ክፉ ድርጊት እንጂ፡ በጥንተ ተፈጥሮ፡ ከእግዚአብሔር ያገኙት አይደለም። ሊኾንም አይችልም።

ይኸው <u>የግብረ-ሰዶም ፍትወተ-ሥጋ፡</u> እንደማናቸውም ኃጢአት፡ ከእያንዳንዱ ወንድ እና ሴት፡ የግል ፍላጎትና ምርጫ የሚመነጭ፥ በግለሰቡም ዘንድ፡ ተቀባይነትን አግኝቶ፡ በፈቃድ የሚካኼድ፥ እንዲያውም፡ ያው ግለሰብ፡ በዚያው፡ የግል ፍላጎቱና ምርጫው፡ ምንጊዜም፡ ራሱን፡ ለእውነተኛ ንስሓ በሚያበቃበት ሰዓት ደግሞ፡ ሊያስወግደውና ወደተፈጥሮአዊው ሥርዓቱ አስተካክሎ ሊመልሰው እንደሚቻል፡ ልታምኑ ይገባል።

እንግዴህ፡ "ይህንኑ፡ የግብረ-ሰዶምን ጠንቅ በሚመለከት፡ ገሃድ ሊደረግ የሚገባው፡ አንድ የማይታለፍ እውነታ አለ!" ስለተባለው ርእሰ-ነገር፡ እስከዚህ፡ ባጭር ቃል፡ በቅድሚያ፡ ይህን ያህል የተገለጸው፡ እንደሚበቃ በማመን፡ አኹን ደግሞ፡ "ግብረ-ሰዶም፡ እንዴት መጣ? ማንስ አመጣው? ለምንስ፡ እንዲህ ተስፋፍቶ፡ ከዚህ ደረጃ ደረሰ?" ወደሚለው፡ ወደዋናው መጠይቃዊ አርእስት ተመልሼ፡ ከዚህ የሚከተለውን ዝርዝር ሓተታ አሰማችኋለሁ፡-

ይኸውም፡ ቀደም ብሎ እንደተመለከተው፡ "በዚህ፡ በግብረ-ሰዶም አነሣሥና መስፋፋት ረገድ፡ ይነስም፡ ይብዛም፥ ይቅለልም፡ ይክበድም እንጂ፡ እያንዳንዱና ኹሉም ሰብአዊ ፍጡር፡ በግለሰብና በቤተሰብ፥ በኅብረተሰብና በብሔረሰብ፥ በዓለመሰብ ደረጃ ጭምር፡ አንዳች ዓይነት፡ ፀረ-እግዚአብሔራዊና ፀረ-ክርስቶሳዊ፥ ፀረ-ኢትዮጵያዊና ፀረ-ማርያማዊ፥ ኢተፈጥሮአዊና አሉታዊ አስተዋጽኦ ያላደረገ የህልውና ዘርፍ፡ ከቶ የለም።" ለሚለው አስተያየት፡ የቀረበ ማብራሪያ ነው።

ይህ ማብራሪያ፡ "የግብረ-ሰዶም ፍትወተ-ሥጋ፡ እንደማናቸውም ኃጢአት፡ ከእያንዳንዱ ወንድ እና ሴት፡ የግል ፍላጎትና ምርጫ የሚመነጭ፥ ተቀባይነትንም አግኝቶ፡ በፈቃድ የሚካኼድ፥ እንዲያውም፡ ያው ግለሰብ፡ በዚያው፡ የግል ፍላጎቱና ምርጫው፡ ምንጊዜም፡ ራሱን፡ ለእውነተኛ ንስሓ በሚያበቃበት ሰዓት ደግሞ፡ ሊያስወግደውና ወደተፈጥሮአዊው ሥርዓቱ አስተካክሎ ሊመልሰው የሚችል ነው!" በሚለው፡ ተፈጥሮአዊና ሃይማኖታዊ እውነታ ላይ የተመሠረተ መኾኑ እንዳይዘነጋ ያስፈልጋል።

እስኪ፡ እስላሞችንና አሕዛብን፥ አረማውያንንና ሃይማኖተ-ቢሶችን፡ ለጊዜው፡ ከዚህ ርእሰ-ጉዳይ፡ ገለል ላድርጋቸውና፡ በተለይ፡ እየራሳቸውንና ራሳቸውን፡ "አይሁድ ነን!"፥ "ክርስቲያኖች ነን!" በሚሉት ግብዞች ወገኖች ዘንድ ብቻ ያሉትን፡ እነዚህን፡ ጠንቀኞች የኾኑ የአስተዋጽኦ ዓይነቶች እያጠቃለልሁ፡ አንድ በአንድ ላመልክታችሁ!

፩. ለመኾኑ፡ ከኹሉ በቀደመ ነገር፡ በባሕርያችን፡ ቸርና ደግ የኾንነው፡ እኛ ፈጣሪ እግዚአብሔር አምላክ፡ ጥንቱኑ፡ በመልካችንና "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" ብለን፡ እጅግ መልካምና የተቀደሰ፥ ፍጹም ግሩምና ድንቅ፥ ንጹሕና ያማረ፥ የሠመረና የጣፈጠ አድርገን፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታዎች የፈጠርነው፡ ይኼ፡ ራሱ፡ የእኛ፡ የእግዚአብሔር መልክ የኾነው፥ ኋላም፡ በፍጻሜ የሕይወት ዘመን፡ እኔ እግዚአብሔር እም እና ልጃችን እግዚአብሔር ወልድ፡ ፍጥረተ-ዓለሙን፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፡ ከክፋት፥ ከኃጢአትና ከሞት ለማዳን፥ የእነዚህ አበጋዝ ከኾነው፡ ከዲያብሎስ ጋር፡ ለዝንተዓለም ሲካኼድ የኖረውንም፡ ጽኑ ጦርነት፡ በፍቅርና በትሕትና ኃይል፡ ፈጽሞ ድል በማድረግ፡ የዘላለም ሰላምን ለማስገኘት፡ እየራሳችን የለበስነው ሰብአዊው የሥጋ ሰውነት፡ እንዴት ተለውጦ፡ ወደክፋት፥ ወደኃጢአትና ወደሞት ምንጭነትና ማኅደርነት ሊቀየር በቃ?

ከዚህ የተነሣ፡ የወንዱ አባለ-ዘርና የሴቷ አፈ-ማሕፀንስ፡ እንዴት፡ "ኀፍረተ-ሥጋ" የሚል፡ የውርደት ስያሜ ሊጣልባቸው ተቻለ? በዚያም ሰውነት ውስጥ፡ በተፈጥሮ ሥርዓት የሚፈጠረው የሩካቤ ሥጋ ፍትወት [ፍላጎት]፥ ከዚያ ሰውነት የሚፈልቀውም፡ የወንዱ ዘር፡ "ኃጢአት"፥ የሚመነጨውም፡ የሴቷ የወር አባባ፡ "ዐደፍ-ጉድፍ"፥ "ርኵሰት"፥ "መርገም" ተብለው፡ እንዴት፡ በክፉው ወገን እንዲፈረጁ ተፈረደባቸው?

ይህን ያደረገ ማነው? ይህ የርስሓት [የመተዳደፍ] እና የሙስና [የብልሹነት] ጠንቅ፡ ቀድሞ፡ በሰው ጥንተ ተፈጥሮ ውስጥ ያልነበረ ሲኾን፡ ታድያ! ከየት መጣ? ኋላም፡ በዘመነ ኵነኔ፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ በነፍስ ወከፍ፡ ወንዱም፥ ሴቱም፡ ከእየራሱ እያፈለቀ፡ በፈጠረው ተፃራሪ ፅንሰ-አሳብ፡ በእየራሱ ፍላጎትና ፈቃድ፥ ምርጫና ውሳኔ፡ ተቀብሎትና ፈጽሞት ያስገኘው አይደለምን? እንዲያ በተገኘ ጊዜም እንኳ ቢኾን፡ ታላቅ ኃጢአት የኾነውን፡ ያንኑ፡ የርስሓት እና የሙስና ጠንቅ፡ በፍጻሜ ዘመን፡ እኛ፡ እግዚአብሔር፡ ለዚሁ ፍጡራችን፡ ካለን ፍቅር የተነሣ፡ ለዘለዓለም ልናድነውና ሰላምን ልናጎናጽፈው፡ እኔ እግዚአብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን፡ በቅድሚያ ተዋሕጄ፡ ከእርሷ፡ ልጇ ወዳጇን፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ በሰውነት ወልጄ፡ በመለኮት ሴትነትና ወንድነት፡ ሰው በኾንንበት፡ በዘመነ ሥጋዌ፡ በትስብእት ቤዛነታችንና በኪዳነ ምሕረትነታችን፡ ፈጽሞ ደምስሰን፡ ለዘለዓለም ያስወገድነው አይደለምን? አዎን! በእውንና በእርግጥ አስወግደነዋል።

ታድያ! እንደገና ከየት አንሠራርቶ ብቅ አለ? እውነታው፡ ይህ ኾኖ ሣለ፡ ራሳቸውን "ክርስቲያኖች ነን!" ይልቁንም፡ "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ነን!" በሚሉት ወገኖች ዘንድ ሳይቀር፡ ይህ አስከፊ፡ የጥፋት ኹኔታ፡ እስከዛሬ ድረስና ዛሬም፡ ከነጠንቀኛነቱ፡ እንዴትና እንደምን፡ እንዲህ፡ ጸንቶና ተስፋፍቶ ሊቀጥል ቻለ?

እንግዴህ፡ በክፋት ላይ፡ በሉዓላዊነት፡ እጅግ የመጠቀውን፡ እግዚአብሔራዊዉን የአሸናፊነት ሥልጣን፡ በጥንተ-ተፈጥሮው የተቀዳጀው፡ ይህ፡ "የሰው ልጅ" የተባለው ፍጡራችን፡ አምላካዊዉን የሰውነት ተፈጥሮውን አዳክሞና ቀይሮ፡ ራሱን፡ ለክፋቱ ምትሓታዊ የአገዛዝ ኃይል፡ እንዴትና የቱን ያህል አዋርዶ እንደሰጠ እዩት! በማስተዋልም ተመልከቱት!

የክፋቱንና የሓሰቱን፥ የኃጢአቱን እና የሞቱን አበጋዝ ዲያብሎስን፡ እዚህ ላይ ጣልቃ ማግባቱን ልተወውና፡ እስኪ፡ ራሱን፡ ለክፉው ያስገዛው፡ ይኼ፡ "ሰው" የተባለው፡ ወረተኛና ተለዋዋጭ፥ ቅጥ ያጣና ራሱን፡ ወደጉድ ጭራቅነት ለውጦ፡ ለከባድ ጥፋት የዳረገ ፍጡራችን፡ በዚህ፡ ለግብረ-ሰዶም መፈጠር ምክንያት የኾኑትን ጠንቆች በማስገኘቱ ረገድ፡ እስካኹን ያደረገውን፥ አኹንም እያካኼደ ያለውን ግብሩን እየገላለጥሁ ላመላክታችሁ!?

ይህንም የማደርገው፡ ቀደም ብዬ ባሰማኋችሁ፡ በራሳቸው፡ በጥያቄዎቹ ውስጥ፡ መልስ ኾነው የተጠቃለሉትን ቍም-ነገሮች የያዘውን፡ መልእክታዊዉን የእውነታ ዝርዝር አክዬ በማተት ነው፤ ይኸውም፡-

<u>በመጀመሪያ፡</u> እኛ እግዚአብሔር አምላክ፡ ጥንቱኑ፡ በመልካችንና "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" ብለን፡ በቅድስናና በንጽሓ ባሕርይ የፈጠርነው ሰብአዊው ፍጡራችን፡ በጥንተ ተፈጥሮው፡ እንዲህ፡ በፍጹም የጸዳ መልካም መኾኑን የሚያረጋግጠው ነው፤

<u>ቀጥሎ፡</u> በዚሁ፡ እግዚአብሔራዊ በኾነው፡ በንጽሓ ባሕርዩ፡ የቅድስና ሰውነቱ ውስጥ ያልነበረውን፡ ይህን፡ አማሳኝ የኃጢኣት ጠንቅ ያመጣው፡ ራሱ፡ እያንዳንዱ፡ ሰው፡ በነፍስ ወከፍ፡ ወንዱም፥ ሴቱም፡ ከእየራሱ እያፈለቀ፡ በፈጠረው ተቃራኒ ፅንሰ-አሳብ ነው፤

<u>ከዚያም፡</u> ይህንኑ፡ በእየራሱ ያመጣውን አማሳኝ የኃጢኣት ጠንቅ፡ አኹንም፡ ተቀብሎትና ፈጽሞት የተገኘው፡ በእየራሱ ፍላጎትና ፈቃድ፥ ምርጫና ውሳኔ ነው፤

<u>በመጨረሻም፡</u> በዚህ አሠቃቂ ኹኔታ ሲማቅቅ የኖረበት፡ የ፭ሺ፭፻ (የአምስት ሽህ አምስት መቶ) ዓመታት ዘመነ ፍዳ ሲያበቃ፡ ቀደም ብዬ እንደገለጽሁላችሁ፡ እኔ እግዚአብሔር እምና ልጄ እግዚአብሔር ወልድ፡ ለዚሁ፡ ወላዋይ ለኾነውና ለባዘነው ፍጡራችን፡ ካለን ፍቅር የተነሣ፡ ልናድነው፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን ተዋሕደን፡ ሰው በኾንንበት፡ በዘመነ ሥጋዌ፡ በትስብእት ቤዛነታችንና፡ በኪዳነ ምሕረትነታችን፡ ይኸው አማሳኝ የኃጢኣት ጠንቅ ፈጽሞ መወገዱ ነው።

እንግዴህ፡ ይህ ኹሉ ኾኖለትና ተደርጎለት ነው፡ ምርጫው፡ ይህ የኾነው፡ ሰብአዊው ፍጡራችን፡ እስካኹን፡ ለ፪ሺ፰ (ለኹለት ሽህ ስምንት) ዓመታትና አኹንም፡ በዚሁ፡ በግብረ-ሰዶም፡ የሥቃይ ቀንበር ሲረክስና ሲጐሣቈል፥ ሲማስንና ሲማቅቅ የኖረው።

<u>**ለግብረ-ሰዶም መፈጠር፡ አንዱ ዋነኛውና የመጀመሪያው ጠንቀኛ ምክንያት፡ ይህ፡ መኾኑን አስተውሉት!**</u>

፩. ጥንት፡ በዘመነ ፍጥረት፡ ከኪዳነ አዳምና ሔዋን አንሥቶ፡ በኪዳነ ኖኅና ሓይከል፥ በኪዳነ መልከ ጼዴቅና ሳሌም፥ እንዲሁም፡ በኪዳነ አብርሃምና ሣራ በኩል ዐልፎ፡ የአይሁድ፡ የኦሪት (የሕግ) ቀንበር እስከታወጀበት፡ እስከኪዳነ ሙሴ ድረስ ባለው፡ በዘመነ ኪዳነ ልቦና፡ ቀድሞ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች"፥ ኋላም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" የተባላችሁት ታማኞቼ ፍጡሮቼ፡ በመልካምና በቅድስና፥ በእውነትና በሕይወት፡ ትኖሩበት የነበረው ሰውነታችሁ፡ ከማናቸውም ዓይነት የክፋትና የሓሰት፥ የኃጢኣትና የሞት ጠንቅ፡ ነጻ በኾነ ህልውና ይገኝ እንደነበረ ይታወቃል።

ይህ ኹኔታ በጥቂቶቹ ሰውነት ላይ ጸንቶ የቆየው፥ ይህም እውነታ፡ በገሃድ ተገልጦ የታየው፡ የኋላ ኋላ፡ ከአንዱ ኖኅና ሚስቱ፥ ከሦስቱ ልጆቹና ሚስቶቻቸውም በቀር፡ ከእነዚህ፡ ከእኛ፡ የእግዚአብሔር ወገኖች መካከል፡ ብዙዎቹ፡ ዓለማውያኑን፡ የሰውን ሴቶች ልጆች ቆነጃጅት አይተውና በእነርሱ የሥጋዊ ፍቅር ፍላፃ ተነድፈው፡ ከመለኮታዊው የቅድስና ሥርዓት፡ ወደሰይጣናዊው የርኩሰት ግዛት፡ ፈጽመው በመውደቃቸው፡ ኹሉም፡ በጥፋት ውኃ መደምሰሳቸው እስከተከሠተበት ጊዜ ድረስ መኾኑ መዘንጋት የለበትም። (ዘፍጥ. ፮፥ ፩-፰።)

ይህም ማለት፡ በዚያን ጊዜ፡ እኒሁ የእግዚአብሔርና የኢትዮጵያ ልጆች፡ እግዚአብሔራዊ ምንነታቸውንና ማንነታቸውን ሳይለውጡ፥ ንጽሕናቸውንና ቅድስናቸውንም ሳያረክሱ፡ ጠብቀው ይገኙ ዘንድ፡ እንደእግዚአብሔር አብናእም፡ ከአንድ አካልነትና ባሕርይነት፡ ወደኹለትነት ተከፍለው፡ በአምላካዊውና በተፈጥሮአዊው አንድነት፡ በመለኮታዊው የጋብቻ ተዋሕዶ ምሥጢር፡ እንደገና ፍጹም አንድ እንደኾኑት፡ እንደአዳምና ሔዋን ኹሉ፡ ከእነርሱ የተወለዱትና የተዋለዱት፡ ወንዶቹና ሴቶቹ ልጆቻቸውም፡ እንደዚሁ፡ ጋብቻቸውንና ሩካቤ ሥጋቸውን፡ እርስ በርሳቸው ይፈጽሙ የነበሩት፡ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ እንደኾኑት፡ እንደርግቦች፡ በመለኮታዊው ጥበብ፡ መንትዮች፥ ወይም፡ በተለያዩ ጊዜያት፡ ወንድምና እኅት ኾነው በሚወለዱት መካከል ሳይቀር ነበር ማለት ነው።

በዚህ ረገድ፡ ያ ጋብቻቸው፥ ያ የፍትወተ-ሥጋቸው ፈቃድ መነሣሣትና ሩካቤ-ሥጋቸው [የግብረ-ሥጋ ግንኙነታቸው]፡ እግዚአብሔራዊው የቅድስናና የንጽሕና ተፈጥሮአዊ ሥርዓት መኾኑ ታውቆና ተረጋግጦ ስለሚፈጸምና ስለሚካኼድ፡ ከክፋትና ከስሕተት፥ ከኃጢአትና ከሞት ጠንቅ የነጻና የጠራ መኾኑ፡ ከቶ አያጠያይቅም።

ይህም ኹኔታ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ በእነኄኖክና የአክስቱ ልጅ በኾነችው፡ በሚስቱ፡ በአድኒ በኩል ዐልፎ፡ የቅዱሱን ኪዳን እምነትና ሥርዓት ጠብቀው እስከኖሩት፡ እስከኖኅና መንትያው ሓይከል፥ ቀጥሎም፡ እስከልጆቻቸው፡ እስከሴም፥ ካምና ያፌት፡ ከነመንትዮች ሚስቶቻቸው፥ ከዚያም፡ "መልከ-ጼዴቅ" እስከተባለው ኢትዮጲስና ያኅት-አክስቱ ልጅ እስከኾነችው፡ "ሀገረ-ሰላም"፥ "ሳሌም" እስከተባለችው ሚስቱ "እንተላ" ድረስ፡ ሲካኼድ እንደቆየ ይታመናል።

አኹንም፡ ይኸው የህልውና ሥርዓታዊ ምግባር አፈጻጸምና አካኼድ፡ በእነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ብቻ ተወስኖ የቀረ አይደለም። የቅዱሱን ኪዳን እምነት፥ ሕይወትና ሥርዓት፡ ከኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ ተቀብለው፡ ራሳቸውን፡ ለግርዛት ኪዳን ባበቁት፡ በአብርሃምና እኅት-ሚስቱ በኾነችው፡ በሣራ፥ እንዲሁም፡ በልጃቸው፡ በይስሓቅና ያኅቱ ልጅ በኾነችው፡ በሚስቱ፡ በርብቃ፡ ሕያው ኾኖ ቀጠለ እንጂ።

ከዚያም፡ የእነርሱ ልጅ በኾነው፡ በያዕቆብና በኹለቱ፡ ያጎቱ ልጆች በኾኑት እኅትማማች ሚስቶቹ፡ በልያና በራሔል፥ የእነርሱ በኾኑትና እርሱም፡ ሚስቶቹ ባደረጋቸው፡ በኹለቱ አገልጋዮቻቸው፡ በዘለፋና በባላን ዘንድ ጭምር አልተቋረጠም።

ከእኛ ከእግዚአብሔራዊውና ከመልከ-ጼዴቅያዊው፥ ወይም፡ ኢትዮጵያዊው፡ የአንድ ለአንድ፡ አዳማዊና ሔዋናዊው ሥርዓተ-ጋብቻ ውጪ እየተደረገ የቀጠለው፡ ይህን የመሰለው፡ አብርሃማዊው የግብረ-ሥጋ ግንኙነትና ልጅ የመውለድ ግዳጅ መፈጸሙ እንዳልተቋረጠ፡ **"ኢይጠፍእ ምልክና እምይሁዳ! ወምስፍና፡ እምአባሉ! እስከአመ ይረክብ፡ ዘጽኑሕ ሎቱ፤ ወውእቱ፡ ተስፋሆሙ፡ ለአሕዛብ።**

**"ምልክናነት፡ ከይሁዳ፥ አስተዳዳሪነትም፡ ከተወላጁ አይጠፋም!"** ተብሎ፡ በወንድ ወላጁ፡ በያዕቆብ ትንቢት በተነገረለትና ከዐሥራ ኹለቱ ልጆቹ፡ አንዱ በኾነው በይሁዳ አድራጎት ታይቷል፤ ይኸውም፡ ከነዓናዊት በመኾኗ ብቻ፡ ከእርሷ ልጅ መውለድን ስላልፈለጉ፡ ተባዕታዊ ዘራቸውን፡ በምድር ላይ በማፍሰሳቸው፡ በሞት ከተቀሠፉ፡ ከኹለት ወንዶች ልጆቹ ሚስት ከኾነችው፡ ከምራቱ፡ ከትዕማር፡ "ፋሬስ" እና "ዛራ" የተባሉ መንትዮች ወንዶች ልጆችን በመውለዱ ነው።

ከእነዚሁ መንትዮች፡ ከአንዱ፡ ከፋሬስ ዘር የተወለደው፡ ሰልሞንም፡ "ሴማውያን ነን!" በሚሉት፡ በእስራኤላውያን አይሁድ ዘንድ፡ እንደአሕዛብ ከሚቆጠሩት፡ ከካምና ከያፌት ዘሮች ከተገኙት፡ ከጋለሞታይቱ ከራኬብ፡ ቦኤዝን፥ ቦኤዝም፡ ሎጥ፡ ከሴት ልጁ ከወለደው፡ ከሞዓብ ዘር የልጅ ልጅ ከተገኘችው ከሩት፡ ባለቃል-ኪዳናችን ሊኾን የተገባውን፡ ነቢይ ንጉሥ ዳዊትን የወለደውን የእሴይን ወንድ ወላጅ፡ ኢዮቤድን ወለደ። ዳዊትም፡ ከብዙ ሚስቶቹና ቁባቶቹ ከወለዳቸው፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ መካከል፡ ሰሎሞን አንዱ ነው።

ከአባቱ፡ ከዳዊት ይልቅ፡ ጣዖት አምላኪዎች፥ አረማውያንና አሕዛብ የኾኑ፡ እጅግ አያሌ ንግሥታት ሚስቶችና ቁባቶች ከነበሩት፡ ከእስራኤሉ ንጉሥ ሰሎሞን፡ በእኛ በእግዚአብሔር፡ ፈቃድና መለኮታዊ ዕቅድ፡ ኢትዮጵያዊቷ አጼዬት ልጃችን፡ ንግሥት ማክዳ፡ አንድ ልጇን፡ ምኒልክን ወልዳ፤ ከእርሱ፡ የኢትዮጵያዊነትና የእስራኤላዊነት የትውልድ ሐረግ፡ ሲወርድ ሲዋረድ የቀጠለው ዘር፡ በመጨረሻ፡ የእኔን፡ የድንግል ማርያምን ወላጆች፡ ኢያቄምንና ሐናን አስገኘ።

እኒህ ኹሉ፡ የእግዚአብሔር ልጆች የኾኑት፡ የቀደሙት፡ ቅዱሳን ወንዶችና ቅዱሳት ሴቶች፥ ተከታትለው የተጠቀሱት፡ የኋለኞቹም፡ የእስራኤል ልጆች፡ ይህን ያደርጉ የነበረው፡ ከቅዱሱ ፈጣሪያቸው ጋር በቃል ኪዳን የተጋቡትን፡ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸውን፡ በንጽሕናና በቅድስና ለመጠበቅ ሲሉ እንደነበረ፡ ልታውቁት ያስፈልጋል።

ይኸውም፡ የተቀደሰውንና የተባረከውን ጋብቻቸውን ፈጽመው፡ የፈቃደ-ሥጋ ሩካቤያቸውን እያካኼዱ፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን ይወልዱ፥ በነፍሳዊውና በሥጋዊው፥ በመንፈሳዊውም የተዋሐዶ ሰውነታቸው፡ ፍጹም አንድ የኾነውን፡ ሰብአዊ ህልውናቸውንም፡ በምድር ላይ እያካኼዱ፡ ለእውነተኛዋ ሕይወት አብነትና መልካም አርአያ ኾነው መኖራቸው ነው።

በእኛ፡ በፈጣሪያቸው ላይ ካላቸው፡ ፍጹም እምነታቸው፥ በእውነትና በመንፈስ ከሚያቀርቡልንም አምልኮታቸው የተነሣ፡ "**ብፁዓን፡ እለ ተኀድገ ሎሙ ኃጢአቶሙ፤ ወእለ ኢሐሰበ ሎሙ፡ ኵሎ ጌጋዮሙ። ብፁዕ ብእሲ፡ ዘኢኈለቈ ሎቱ፡ እግዚአብሔር፡ ኃጢአቶ። ወዘአልቦ ጽልሑት፡ ውስተ ልቡ።**

"**ኃጢአታቸው [ስሕተታቸው፥ ጥፋታቸው] የተተወላቸው፥ ይቅርም የተባለላቸው፥ በደላቸውም ኹሉ፡ ያልታሰበባቸው ሰዎች፡ ብፁዓን [የተባረኩ፥ የተሞገሱ] ናቸው። አዎን! እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ ኃጢአታቸውን የማይቈጥርባቸው፥ እነርሱም፡ በየልባቸው ውስጥ፡ ክፉ አሳብን ሠውረው፡ ሰውን የማይሸነግሉ፡ ወንድ እና ሴት፡ የተባረኩና የተሞገሱ ናቸው።**" ተብሎ፡ ከቀድሞ ጀምሮ የተነገረላቸው፡ እንግዴህ፡ እነዚህና እነርሱን የመሰሉት ኹሉ ናቸው። (መዝ. ፴፩፥ ፩-፪።)

በመጨረሻም፡ ከዚሁ፡ ሲያያዝ ከቀጠለው፡ ከኢትዮጵያዊነት የዘር ሓረጋቸው፡ እኔ እግዚአብሔር እም ተዋሕጃት፡ ልጄን ወዳጄን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ በሰውነት የወለደች ድንግል ማርያምን በማስገኘታቸው፡ እነሆ፡ ስማቸውና ምግባራቸው፡ በምሳሌነትና በምስክርነት፡ ሲጠቀስ ይኖራል።

እንግዴህ፡ ምርጫው፡ ክፉው የኾነው፡ ይኸው ሰብአዊው ፍጡራችን፡ እስካኹንና አኹንም፡ በዚሁ፡ በግብረ-ሰዶም፡ የሥቃይ ቀንበር ሲረክስና ሲጐሣቈል፥ ሲማስንና ሲማቅቅ የኖረው፤ እየኖረም ያለው፡ እግዚአብሔራዊና ተፈጥሮአዊ የኾነውን፡ ይህን የመሰለውን፡ የቅድስናና የንጽሓ ጠባይዕ መለኮታዊ ሥርዓት፡ "ኃጢአት ነው!" ብሎ፡ በኃጢአትነት በመፈረጁ መኾኑን፡ ልትገነዘቡት ይገባል።

**<u>ለግብረ-ሰዶም መፈጠር፡ ኹለተኛው ጠንቀኛ ምክንያት፡ ይህ መኾኑን አስተውሉት!</u>**

፫. ከተነሣሁበት የሰዶምና የገሞራ ከተሞች ዝክረ-ነገር ጋር፡ በቀጥታ የተያያዘ፥ የበለጠ ነክነትና አግባብነት ያለው፡ የአብርሃም፡ የወንድሙ ልጅ፡ **የሎጥ ቤተሰብ ዜና መዋዕል**፡ እዚህ ላይ፡ በዋናነት ሊወሳ የሚገባው ይኾናል።

አዎን! በሰዶምና በገሞራ ከተሞች ውስጥ ነዋሪ ስለነበረው ስለሎጥና ስለቤተሰቡ የሚናገረውና በቅዱሳት መጻሕፍታችሁ ውስጥ የተመዘገበው፡ ሙሉ ዜና፡ ከላይ ቀደም ብሎ ሠፍሮ ተነብቧል።

በዚያ ምንባብ ውስጥ፡ በግልጽ እንዳስተዋላችሁት፡ ሎጥና ኹለቱ ሴቶች ልጆቹ ብቻ፡ እንደኄኖክና እንደኖኅ ቤተሰቦች፡ **አካኼዳቸውን፡ ከእግዚአብሔር ጋር ያደረጉ ከመኾናቸው የተነሣ**፡ እየራሳቸውን፡ ለእግዚአብሔር ልጅነታቸው ያበቁ ኾነው በመገኘታቸው፡ ከዚያ መቅሠፍታዊ ጥፋት ሊድኑ ሲችሉ፡ የቀሩት፡ የቤተሰቡ አባሎች የኾኑት፡ ሚስቱና ኹለቱ፡ የልጆቹ ባሎች ግን፡ ከዚያ መራራና አሳዛኝ ጽዋ ለመዳን በተሰጣቸው ዕድልና እርዳታ ለመጠቀም ባለመፈለጋቸው፡ ከአጥፊዎቹ ኃጢኣተኞች ጋር ዐብረው ተደምስሰው እንደጠፉ ተመልክታችኋል።

በእነዚህ፡ ሦስት ዕድለ-ቢሶች፡ የሎጥ ቤተሰቦች ላይ፡ ይህን የመሰለው አሠቃቂ ዕልቂት የደረሰባቸው፡ በኹለት ምክንያቶች የተነሣ መኾኑን ለመገመት፡ ለእናንተ የሚያዳግታችሁ አይኾንም፤ ይኸውም፡

<u>አንደኛው</u>፡- ስማቸውን፡ ቀደም ብዬ እንደተጠቀስሁት፡ እንደእውነተኞቹ የእግዚአብሔር ልጆች፡ በቅዱሱ ኪዳን ሥርዓት፡ ከእኛ ከፈጣሪያቸው የተቀበሉትን፡ የተቀደሰ ሃይማኖታቸውንና የተባረከ ምግባራቸውን ላለማርከስ ሲሉ፡ እስካኹን፡ ከአካባቢያቸው አሕዛብ ተለይተው በሚኖሩበት፡ በቤተሰባዊው የቅድስና ጋብቻቸውና በንጽሓ ባሕርዩ፡ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነታቸው ጸንተው መቀጠል ሲገባቸው፡ ያን የመሰለውን አምላካዊ ሕይወት ትተው፡ "የሰው ልጆች" በተባሉት፡ በሰይጣን ወገኖች ከሚካኼደው፡ ከዚያው፡ ከሰዶማዊው ግብር ጋር፡ ተባባሪ መኾንን መርጠው፡ ያንኑ ፀያፍ ግብር፥ ደግሞም፡ እንደአመንዝራ የሚያስቈጥረውን፡ የዝሙት ሩካቤ ሥጋ ግንኙነት፡ ከእነዚሁ ወገኖች ጋር፡ በሥውር መንገድ፡ በመፈጸሙ ልማድ፡ በመጠመዳቸው ነው፤

ከዚህም ጋር፡ በዚህ ረገድ፡ በኖኅ የጥፋት ውኃ ጊዜ እንዳለቁትና መሰሎቻቸው እንደኾኑት፡ ስሑታን የእግዚአብሔር ልጆች፡ እንዲህ፡ ሥርዓቱን ለማርከስ፡ እስከዚህ ድረስ፡ ደፍረው ከኾነ ደግሞ፡ ከሚመጣው የጥፋት ፍዳ፡ እየራሳቸውን ማዳን እንደማይችሉ ዐውቀው፡ በእውነተኛ ንስሓ መመለስ ሲገባቸው፡ ይህን ቀዳሚ የኾነውን፡ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግንም ኾነ፥ ፈውስ የኾነውን፡ የንስሓ ምግባርን መፈጸምን፡ ስላልፈለጉም ነው።

<u>**ኹለተኛውም**</u>፡- ሎጥ፡ በሚስትነት ያገባት፥ ኹለቱንም ሴቶች ልጆች የወለደችለት ሴት፥ እንዲሁም፡ እነዚያ፡ ለኹለቱ ሴቶች ልጆቹ፡ ባሎች እንዲኾኑ የተቀበላቸው ኹለቱ፡ ወንዶች፡ ከእነዚያው፡ ከራሱ፡ ከሎጥ የጥንት ወገኖች፥ ከሰዶምና ከገሞራም አገር ሰዎች ጋር የሚያስተሳስር የዘር ሓረግ ያላቸው በመኾናቸው፡ "ዘር: ከልጓም ይስባል!" እንደምትሉት፡ ይኼ፡ አረማዊ፥ ወይም፡ አሕዛባዊ ጥንተ-ምንነታቸውና ማንነታቸው፡ ሎጥና ሴቶች ልጆቹ፡ ከእኛ አግኝተው ለሚኖሩበት፡ ለእግዚአብሔር ልጅነትና ለቅድስና ሕይወት፡ እየራሳቸውን ለማብቃት ስላላስቻላቸው ነው።

የሰዶምንና የገሞራን ከተሞች፡ እጅግ በከፋው፡ በዚያ ኃጢአታቸው ከተበላሹት ነዋሪዎቻቸው ጋር: ገለባብጦ ከደመሰሰው፡ ከዚያ ታላቅ የቍጣ እሳት የተረፉት፡ ቅዱሱ ሎጥና ቅዱሳቱ፡ ኹለቱ ሴት ልጆቹ፡ ከዚያ አስደንጋጭና አስፈሪ ጥፋት በኋላ፡ በሰዎች መካከል፡ በከተማ፥ ወይም በመንደር፡ ዐብሮ መቀመጥን፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ ትተው፡ ራቅ ብለው፡ እንደአራዊት፡ በምድረ-በዳ በሚገኝ፡ በተራራ ዋሻ ውስጥ፡ በእግዚአብሔር ጥበቃ ሥር፡ ለብቻቸው መኖራቸውን ጀመሩ።

በዚያም ዋሻቸው፡ ቀድሞ ይኖሩት የነበረውን፡ ቤተሰባዊ የቅድስናና የንጽሕና ኑሮአቸውን፡ በዚያው፡ ከፈጣሪያቸው ባገኙት፡ እግዚአብሔራዊና ተፈጥሮአዊ በኾነው ሥርዓታቸው ቀጠሉ፤ ይኸውም፡ የልጆቹ እናት የኾነችውና በእሳተ-ገሞራው ጽኑ ቃጠሎ፡ የጨው ሓውልት ኾና የቀረችው፡ ሚስቱ በሌለችበት የቤተሰብ ህልውና ውስጥ፡ ይኸው ሎጥ፡ ከኹለቱ ሴቶች ልጆቹና ከእነርሱ ከወለዳቸው፡ ከኹለት ወንዶች ልጆቹ፡ ጋር፡ በመልካሙ፡ ነፍሳዊ፥ ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወት ያሳለፈው፡ ቅዱሱ ቤተሰባዊ ኑሮአቸው ነው።

ይኸው ቤተሰብ፡ ለዘለዓለማዊው ቅድስና የበቃው፡ እንዲያው አይደለም፤ ከዚሁ ቤተሰባዊ ዘር የተገኘችውን፡ "ሩት"ን የምታህል ታላቅ የኾነች፡ ቅድስት ሴትን ያፈራ በመኾኑ ነው።

እርሷ፡ ሩት፡ ማን ናት? እርሷማ፡ ኋላ፡ በፍጻሜ የሕይወት ዘመን፡ ከኪዳናውያኑና ከኪዳናውያቱ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ከመልከ-ጼዴቅና ከሳሌም፥ እየራሳቸውንም፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ካበቁት፡ ከዕብራውያኑና ከዕብራውያቱ፡ ከአብርሃምና ከሣራ፡ ሲወርድ ሲዋረድ፡ ከሰልሞንና ከራኬብ ከደረሰው የትውልድ ዘርፍ ለተወለደው፥ ለባለቃል ኪዳኑ ነቢይና ንጉሥ ዳዊትም፡ ቅድመ-አያት ለኾነው፡ ለቦኤዝ ሚስትነት በቅታ፡ በመጨረሻ፡ በዳዊትና በቤትሳባ፥ ከዚያም፡ በሰሎሞንና በማክዳ በኩል ከቀጠለው የዘር ሓረግ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር እም የተዋሓድኋትን ድንግል ማርያምንና አንድ ልጄ ወዳጄን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ ያሠረፀችውና በሰውነት ልደት ያስገኘችው ናት።

ያም፡ "ቅዱስ" የተባለው፡ የሎጥና የኹለት ሴቶች ልጆቹ፡ ቤተሰባዊ ኑሮ፡ መሰሎቻቸው እንደኾኑት፡ እንደቀደሙትና እንደኋለኞቹ የእግዚአብሔር ልጆች እና የኢትዮጵያ ልጆች ኹሉ፡ አምላካዊና ተፈጥሮአዊ፥ ቅዱስ ኪዳናዊና ንጽሓ ጠባይዓዊ የኾነውን፡ የወንድና የሴት ሩካቤ ሥጋ ፈቃዳቸውን፡ በመልካሙ እግዚአብሔራዊውና ተፈጥሮአዊው ሥርዓት፡ እየፈጸሙ መኖርን የመረጡበትና የቀጠሉበት፡ "በዚህ ጊዜ አንቀላፉ!"፥ ወይም፡ "በዚህ ጊዜ፡ በሞተ-ሥጋ ዐረፉ!" ያልተባሉበት፡ ዘለዓለማዊው ህልውናቸው ነው።

አኹንም፡ እዚህ ላይ፡ እነዚህ "የእኛ የእግዚአብሔር እና የኢትዮጵያ ልጆች" የተባሉት ቤተሰብ፡ "መልካሙን፡ እግዚአብሔራዊውንና ተፈጥሮአዊውን ሥርዓት እየፈጸሙ መኖርን ስለመምረጣቸውና ስለመቀጠላቸው ያወሳሁት ቍም-ነገር፡ እንዲያው፡ ያለምክንያት አይደለም፤

ሰብአዊው ፍጡር ኹሉ፡ እግዚአብሔራዊና ተፈጥሮአዊ የኾነውን፡ የፍትወተ-ሥጋ ፈቃዱን ለመፈጸም፡ ካለበት ተፈጥሮአዊ ግዳጅ የተነሣ፡ ከባድ ኃጢአት በኾነው፥ ያን መቅሠፍታዊ ዕልቂትንም ባስከተለው፡ በሰዶማዊነትና እርሱን በመሰለው፡ በሌላው፡ በማናቸውም ዓይነት፡ ኢተፈጥሮአዊ የግብረ-ሥጋ እኩይ ልማድ መጠመድን ካስከተለው፡ ከሰይጣናዊውና ከሓሳዊው፥ ከሰብአዊው የክፋት ውሳኔና ድንጋጌ ነጻ መኾናቸውን፡ አረጋግጬና አብራርቼ ልገልጽላችሁ ብዬ መኾኑን ልትገነዘቡት ያስፈልጋችኋል።

ይኸውም፡ ቀደም ብዬ እንደገለጽሁላችሁ፡ እኛ እግዚአብሔር፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታዎች የፈጠርነው፡ የሰውነት አካልና ባሕርይ፥ የሠራነውም፡ የጋብቻና የቤተሰባዊው፥ የመውለዱና የመዋለዱ ሥርዓት፥ ከፍትወተ-ሥጋው ፍላጎትና ከሩካቤ-ሥጋው ግብር ጋር፡ ጥንቱኑ፡ እንዲህ፡ በቅድስናነትና በንጽሓ ባሕርይነት፡ በእኛ ሃይማኖትና ምግባር፡ ለመልካምነትና ለሕይወትነት፡ ፈጥረን ያዘጋጀነው ሲኾን፡ ነገር ግን፡ የሓሰቱ አበጋዝ ዲያብሎስና በኋላ ዘመን የተነሡ፡ የእርሱ አገልጋዮች የኾኑ ክፉዎች ሰዎች፡ በተለይም፡ ቀደም ብለው፡ አሪታውያኑ አይሁድ፥ ኋላም፡ ይባስ፡ "የአዲሱ ኪዳን አማኞች ክርስቶሳውያኑ ነን!" የሚሉት መነኰሳት ግን፡ ይህንኑ የተቀደሰ ሥነ-ፍጥረታችንንና ሥርዓቱን፡ ለምን ዓይነቱ፡ ሓሳዊና ሙሱን ምንነት እንደዳረጉት፡ ኹላችሁም፡ የምታውቁት እውነታ አይደለምን?

ይኹን እንጂ፡ አንዳንዶቻችሁ፡ በዚህ ረገድ፡ የእየራሳችሁን፡ የሥውር ተባባሪነታችሁንና ግብረ-ዐበርነታችሁን በመሸሸግ ካልኾነ በቀር፡ እኛ በፈጣሪነታችን፡ ለእያንዳንዳችሁ፡ ለወንዶቹም፥ ለሴቶቹም፡ ባቀዳጀናችሁ አምላካዊና ሰብአዊ ተፈጥሮአችሁ፡ በእየራሳችሁ ልታውቁ የምትችሉትን፥ የሚገባችሁንም፡ ይህን እውነታ፡ ያለግብዝነት፡ በእውነት፡ አኹንም "የለም! አናውቅም!" የምትሉ ካላችሁ፡ ይኸው፡ እኔው ራሴ፡ እንዲህ እያልሁ፡ እውነታውን፡ ገሃድ አድርጌ እነግራችኋለሁ፡-

አዎን! እውነታው፡ ከዚህ ቀደም ብዬ የገለጽሁላችሁን፡ ያን፡ በወንድና በሴት ሰብአውያን ፍጡሮቻችን መካከል ስላለው አንድነትና ግንኙነት፡ በጥንተ ተፈጥሮ የመሠረትነውን፡ የተቀደሰ ሥነ-ፍጥረታችንንና ሥርዓቱን፡ አካትተው የያዙት፥ እነዚያን፡ የእኛ የኾኑትን፡ የመለኮት መልካካም ጸጋዎች ኹሉ፡ በአጠቃላይ፡ "ኃጢአት" ለተባለው፡ ለክፋትና ለሓሰት፥ ለስሕተትና ለጥፋት፡ መሣሪያ ይኾኑ ዘንድ እንደተዘጋጁ በማስመሰል፥ ከዚህ የተነሣም፡ እኒሁ የሰውነት አካልና ባሕርይ፡ ለሞት እንደተዳረጉ በመቍጠር፡ <u>እነዚህ ኹሉ፡ የእኛ የመለኮት ደጋግ ሥራዎች፡ ኹሉም፡ በምትሓታዊው የኃጢአት ማንነትና ምንነት መፈረጃቸው ነው።</u>

<u>ለግብረ-ሰዶም መፈጠር፡ ሦስተኛው ጠንቀኛ ምክንያት፡ ይህ መኾኑን አስተውሉት!</u>

፬. እዚህ ላይ፡ የሎጥ፡ ኹለቱ ሴቶች ልጆቹ፡ መሰላቸውን ሰብአዊዉን ዘር፡ በልደት ለማስቀረት ሲሉ፡ በዚህ ረገድ፡ ተማክረውና ተስማምተው፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸው የፈጸሙትን፡ ኪዳናዊ ምግባር፡ በማስተዋል ስሙት!

"የእግዚአብሔር ልጆች!" ኾነው ከሚኖሩበት፡ ከቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታዊና ምግባራዊ ሕይወታቸው፥ ደግሞም፡ እግዚአብሔራዊና ተፈጥሮአዊ ከኾነው፡ ከቤተሰባዊው የጋብቻ ሥርዓት ውጪ የሚያደርጋቸውን፥ ከሌላ ባዕድና አረማዊ ከኾነ ወንድ፡ ተጋብተውም ኾነ፡ ሳይጋቡ፡ ልጅን ከመውለድ ይልቅ፡ ከራሱ፡ ከወላጃቸው፡ ከሎጥ፡ ልጅን ለመውለድ ባሰቡበት ጊዜ፡ ይኸው ወላጃቸው፡ ይህንኑ ዕቅዳቸውን ሊፈጽምላቸው ይቻለው ዘንድ፡ ወይን ጠጅ ሊያጠጡት እንደተስማሙና ይህንኑ እንዳደረጉ፡ ቀደም ብሎ ያዳመጣችሁት፡ የቅዱሳት መጻሕፍታችሁ ጥቅስ ያስረዳችኋል።

ይኹን እንጂ፡ የወይን ጠጅ መጠጥን በሚመለከት የተጻፈውን፡ ይህን፡ የሓሰት ቃል፡ ሥርዋፅ (እመጫት) አድርገው፡ በአሪቱ መጽሓፉቸው ውስጥ፡ በድፍረት የጨመሩት፡ እነማን ይመስሏችኋል? ይህን የድፍረትና የተንኰል ተግባር የሚፈጽም፡ በልጁ በወዳጁ፡ በኢየሱስ መሲሕ አንደበት፡ "አንትሙሰ፡ እምአቡክሙ ሰይጣን አንትሙ! ወፍትወቶ ለአቡክሙ ትፈቅዱ ትግበሩ፤ ...ወውእቱሰ፡ ሓሳዊ ውእቱ፤ ወአቡሓ ለሓሰት!"

"እናንተማ፡ ከአባታችሁ፡ ከዲያብሎስ ናችሁ! ስለዚህ፡ የእርሱን የአባታችሁን ፍላጎት መፈጸምን ነው፡ እናንተ የምትፈቅዱት!" ከተባሉት፡ ከአይሁድ በቀር ሌላ ማን ይኖራል? እነርሱ ናቸው።

ይህም፡ እነርሱው፡ ቀድሞም ቢኾን፡ "ወእምድኅረ ማየ አይኅ፡ አኀዘ ኖኅ ይትገበራ ለምድር፤ ወተከለ ዐፀደ-ወይን። ወሰትየ እምኔሁ፤ ወሰከረ፤ ወተዐርቀ፡ በውስተ ቤቱ።"

"ከጥፋት ውኃ በኋላ፡ ኖኅ፡ ምድርን ማረስ ጀመረ፤ ወይንንም ተከለ፤ ከዚያ ፍሬ የተጠመቀውን የወይን ጠጅ ጠጣ፤ ሰከረም፤ በቤቱም ውስጥ፡ ራቁቱን ኾነ።" ብለው፡ በኖኅ ላይ፥ እርሱም፡ ከዚሁ ስካሩ የተነሣ፡ ምንም በደል በሌለባቸው፥ ከዐፅመ ርስታቸው ሊነቅሏቸው ብቻ ስለፈለጉ፡ በኹለተኛው ልጁ፡ በካምና የእርሱ፡ የካም ልጁ በኾነው በከነዓን ላይ፡ ያን የመሰለ፡ የማያስፈልግ፡ እጅግ ከባድና አሠቃቂ እርግማንን እንዳወረደበት አድርገው፡ በሓሰት እንደጻፉበት ማለት ነው። (ዘፍጥ. ፱፥ ፳-፳፩። ዮሓ. ፰፥ ፵፬።)

ለመኾኑ፡ በእነዚሁ አይሁድ፡ ለእንዲህ ዓይነቱ ውርደት የተዳረጉት፡ ኖኅና ሎጥ፡ ከነቤተሰቦቻቸው፡ እነማን ናቸው? ከልደታቸው ጀምረው፡ በእኛ በፈጣሪያቸው ፊት፡ ፍጹም እውነተኞች ኾነው በመገኘታቸው፥ የሕይወት አካኼዳቸውንም ከእኛ ከእግዚአብሔር ጋር በማድረጋቸው፥ የሚያስቡትንና የሚናገሩትን፥ የሚሠሩትንም ኹሉ፡ በእኛ የመንፈስ ቅዱስ ዕውቀት፡ ተረድተውና ተገንዝበው የፈጸሙ ናቸዋ!

አዎን! እንዲህ እንደመኾናቸው፥ በመጨረሻ፡ ከእኛ ከቸሩ አምላካቸው ለተቀበሉት፡ ለቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸውና ምግባራቸው፡ እየራሳቸውን፡ ፍጹም ታማኞች አድርገው በማቅረባቸው፡ "የእግዚአብሔር ልጆች!" ተብለው ለመጠራት የበቁት ናቸዋ! ከዚሁ ብቅዓታቸውም የተነሣ፡ ከመዓታዊው የጥፋት ውኃ፥ ከመቅሠፍታዊውም፡ የሰዶምና የገሞራ፡ ዝናመ-እሳት፡ እንዲያ ለመትረፍ የቻሉት ናቸዋ!

እንግዴህ፡ በእነዚሁ በክፉዎቹ አይሁድ ዘንድ እንደታሰበው፡ <u>"ሰካራሞች፥ በዚሁ ሰካራምነታቸውም ምክንያት፡ ያን የመሰለ የስሕተትና የኃጢአት ድርጊትን ፈጸሙ!"</u> ተብለው የተወነጀሉት፡ እኒህ ቅዱሳን ኖኅና ሎጥ፥ ቅዱሳት ቤተሰቦቻቸውም ናቸው።

አዎን! ሎጥና ኹለቱ ሴቶች ልጆቹ የኖሩበት፡ መለኮታዊዉና ተፈጥሮአዊው፥ የቅድስናና የንጽሕና የኾነው፡ ይህ፡ ቤተሰባዊው፡ የሩካቤ ሥጋ ሥርዓት፡ ለእየራሳቸው፡ ወደክፉነትና ወደኃጢአትነት፥ ወደርኵሰትና ወደመርገምነት የተለወጠው፡ በይበልጥና በገሃድ፡ የአይሁዳውያኑ ሕገ-ኦሪት ከተመሠረተበት ጊዜ ወዲህ ነው። ይህን እውነታ በሚመለከት፡ ከዚህ በኋላ፡ ወደዚህ የዐዋጅ ቃሌ መደምደሚያ ግድም፡ በማከታተል በማቀርባቸው ሓተታዎች፡ በበለጠ ተብራርቶ ታገኙታላችሁ።

<u>ለግብረ-ሰዶም መፈጠር፡ አራተኛው ጠንቀኛ ምክንያት፡ ይህ መኾኑን አስተውሉት!</u>

፫. ከዚህ አስቀድሞ ግን፡ እዚህ ላይ፡ ይህንኑ ርእሰ-ጉዳይ በሚመለከት፡ ልጠቅስላችሁ የሚያስፈልጉኝ፡ ኹለት ተዛማጅ ዝክረ ነገሮች አሉ፤ እነዚህም፡ ማናቸውም፡ ሰብአዊ አስተሳሰብ፥ ወይም፡ ድርጊት፡ ከእኛ፡ ከእግዚአብሔራዊው የተፈጥሮ ሥርዓት ውጪ እንዲኾን በሚሞከርበት ጊዜ ኹሉ፡ ራሱ፡ ያ አስተሳሰብ፥ ወይም፡ ድርጊት ብቻ ሳይኾን፡ የአስተሳሰቡ ምንጭና ጠንሳሽ፥ የድርጊቱም መሣሪያና ከዋኝ የኾነው፡ ራሱ ሰብአዊው ፍጡርም ጭምር፡ ኹሉም፡ ለዚያ፡ ለጠንቀኛው የጥፋት ፍጻሜ የሚዳረጉ መኾናቸውን የሚያረጋግጡ የኹነት እውነቶች ናቸው።

እነዚህንም፡ ባጭር አገላለጽ፡ እንደሚከተለው አብራራላችኋለሁ:-

<u>አንደኛው:-</u> አዳምና ሔዋን፡ የሚያውቁንንና መልካሙን ኹሉ ያደረግንላቸውን፡ የእኛን፡ የደጋጎቹንና የቸሮቹን አባትና እናት ፈጣሪያቸውን ፈቃድና ቃል ተከትለው፡ የሕይወትን ዛፍ ፍሬ በመብላት፡ ክፋትና ሓሰት፥ ኃጢአትና ሞት የሌለበትን፡ የዘለዓለም ሕይወትን ወርሰው፡ በተድላ በደስታ መኖር ይቻላቸው፥ ይሻላቸውም እንደነበረ፡ እናንተ ዛሬ ያላችሁት መሰሎቻቸው እንኳ ሳትቀሩ፡ ኹላችሁም ትናገሩታላችሁ።

ነገር ግን፡ እነርሱ፡ ቀድሞውኑም ቢኾን፡ ከእኛ፡ በተፈጥሮ ከተሰጧቸው፥ ከአምላካውያቱ የመምረጥ ነጻነቱና የመወሰን ሥልጣኑ፥ የማድረግ ኃይሉም ጋር፡ "ከእኛ እንደአንዳችን ኾኑ!" ባሰኘቻቸው፡ በዚያች፡ የዕውቀት ዛፍ ፍሬ ተጠቅመው፡ ከክፉው ይልቅ፡ መልካሙን ተቀብለው ለመፈጸም ሲችሉ፡ ያን በማድረግ ፋንታ፡ ከዚያ ይልቅ፡ እነርሱ፡ ኹለቱም፡ የማያውቁትን፥ ባለማወቃቸውም፡ ለብዙ መከራና ሥቃይ፥ ጕሥቍልናና ጉዳት የዳረጋቸውን፡ የክፉውን ፍጡር ሓሳዊ ቃል ሰሙ፤ መስማት ብቻም አይደለም፤ ሰምተውም፡ እኩይ ፈቃዱን ተከተሉ፤ ተከትለውም፡ እነዚያኑ፡ ቀድሞ፡ ከእኛው፡ በተፈጥሮ ያገኟቸውን፡ አምላካውያቱን የመምረጥ ነጻነትና የመወሰን ሥልጣን፥ የማድረግ ኃይልም፡ በተግባር ላይ በማዋል፡ ከመልካሙ ይልቅ፡ ክፉውን፡ "አሜን!" ብለው ተቀበሉ።

ከዚህ የተነሣ፡ መራራዪቱን የጥፋትን ፍሬ በመብላታቸው፡ በእየራሳቸው ላይ፡ የክፋት ተገዢነትንና የሓሰት ባርነትን፥ የኃጢአት ሎሌነትንና የሞት ባለዕዳነትን፥ የአጠቃላዩንም ፍዳ ተቀባዮች የመኾንን ከባድ ቀንበር ተሸካሚዎች ኾኑ! ይህም እውነታ፡ በኹላችሁ ዘንድ፡ ገዝፎ ሲሠራ ይታወቃል።

እኒሁ አዳምና ሔዋን፡ በዚህ ዓይነቱ የኵነኔና የመርገም ኑሮ ውስጥ እያሉ፡ ገና በህልውናቸው መነሻ ላይ፡ እኛ እግዚአብሔር፡ በሥነ-ፍጥረት ጥበባችን፡ ከእነርሱ የሚወለዱት ልጆቻቸው፡ ወንድና ሴት እየኾኑ፡ በመንትያነት እየተፀነሱ እንዲወልዷቸው ያስደረግነውን ሥርዓታችንን ማቃወስ ጀመሩ።

ይኸውም፡ ለመጀመሪያዎቹ ወንዶች ልጆች ለኾኑት፡ ለታላቅና ለታናሽ ወንድማማቾቹ፡ ለቃኤልና ለአቤል፡ በዚያው፡ በእኛው፡ በእግዚአብሔራዊው፡ የተፈጥሮ ሥርዓት፡ የእየራሳቸውን መንትዮቻቸውን ሴቶች፡ ማጋባት ሲገባቸው፡ ወላጆቻቸው፡ ከእኛ፡ ከፈጣሪያቸው ፈቃድ ውጪ፡ ያን፡ ሳያደርጉ መቅረታቸው ነው። በዚያ ፋንታ ያደረጉት፡ የእያንዳንዳቸውን መንትዮች፡ ለዋውጠው፡ በአንድ ወገን፡ እናንተ፡ የታላቁ ልጃቸውን፡ የቃኤልን "ቆንጆ" ያላችኋትን መንትያ፡ ለታናሹ ልጃቸው፡ ለአቤል፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ እናንተ፡ የአቤልን "ፉንጋ" ያላችኋትን መንትያ፡ ለቃኤል በመዳራቸው፡ በእኛ ዘንድ ያልተፈጠረና የሌለ፡ የክፉ ቅንዓት ስሜት፡ በቃኤል ውስጥ ተነሣሥቶ፡ ወንድሙን እስከመግደል የመድረሱ ዝክረ-ነገር፡ ይኸው፡ እስካኹን፡ በመካከላችሁ ሲነገር ይኖራል።

ከዚህ የተነሣ፡ የወንድሙ ነፍሰ-ገዳይ ኾኖ የተገኘው፡ የቃኤል መሰል ተከታዮች የኾኑት ሰብአውያን ፍጡሮች ኹሉ፡ "የሰው ልጆች" ተብለው፡ የክፉው ሰይጣን ወገኖች ሲኾኑ፡ የግፍ ተቀባዩ ሟች፡ የአቤል መሰል ተከታዮች የኾኑት ሰብአውያን ፍጡሮች ደግሞ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ተብለው፡ የእኛ፡ የደጉ ፈጣሪ ወገኖች ኾነው፡ እነሆ፡ በኹለቱ ተፃራሪ ቡድኖች መካከል የተመሠረተው ጥላቻ፡ የጸናና የማይበርድ ኾኖ ቀጠለ።

ይኸው፡ በቋሚ ጠላትነት፡ በመካከላቸው የሚካኼደው ጦርነትና የእርስ በርስ መጋደል፡ እጅግ በተጠናከረና በተራቀቀ መልክና ይዘት፡ ያለማቋረጥ መባባሱን ታያላችሁ።

ኹለተኛው፦ ይህን የመሰለው እውነታ ነው፤ ያም፡ በኋላ ዘመን፡ በአብርሃምና በሣራ ዘንድ ተከሥቶ፥ ጠንቁ፡ በልጆቻቸው፡ በእስማኤልና በይስሓቅ መካከል እየተካኼደ ያለው ብርቱ ጠላትነት ነው፤ ይኸውም፡ በአንድ በኩል ያለው፡ "የእስማኤል ልጆች ነን!" የሚሉትንና እስልምናን የተቀበሉትን ፍልስጥኤማውያንን፥ የእነርሱ ደጋፊ ኾኖ የተሰለፈውንም፡ የእስላሙን ዓለም የሚያጠቃልለው ወገን ነው።

በሌላው በኩል ያለው ደግሞ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ራሳቸውን "እስራኤል" ብለው በመጥራት፡ "ክርስቲያን ነኝ!" የሚለውን ምዕራቡን ዓለም ተገን አድርገው፡ ለዝንተ-ዓለም፡ የእኛ የእግዚአብሔር ተቃዋሚዎች ኾነው፡ እርሱን፡ ልጁን ወዳጁን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ በሰውነት እስከመግደል ባደረሳቸው ጥላቻ ብቻ የሚወሰኑ ሳይኾኑ፡ በሰብአውያን ፍጡሮቻችን ላይ ባላቸው ጭካኔ፡ ጸንተው የቀጠሉበት መኾናቸውን፡ እያረጋገጡ ያሉትን፡ የዓለም-ዓቀፉን አይሁድ ያካተተው ወገን ነው።

በዚህ ምክንያት፡ በኹለቱ የቀደሙት ኾነ፡ የኋለኞቹ፥ የዛሬዎቹም የወንድማማች ትውልዶች መካከል የተፈጠረው፡ ይኸው ጠላትነታቸው፥ የእርስ በርስ ዕልቂታቸውም፡ እስከዛሬና ዛሬም፥ ወደፊትም፡ በተባባሰ ኹኔታ እየቀጠለ ኼዶ፡ ወደቋሚ ጦርነት ተሸጋግሮ፡ማብረጃና ማብቂያ ወደሌለው፥ ሰብአዊ ጥፋት የሚያደርስ ከመኾኑ በቀር፡ በሰውኛው መንገድ፡ ምንም ዓይነት መፍትሔ ሊገኝለት የማይቻል መኾኑን፡ እነሆ፡ ዓለሙ ኹሉ በትካዜ ይመለከተዋል።

እዚህ ላይ፡ በዚህ ረገድ፡ ከዓመታት በፊት፡ በዛሬው አገልጋያችን በኤርምያስ የተፈጸመ፡ አንድ የኾነና የተደረገ ቍም-ነገርን አወሳላችኋለሁ፤ እርሱም፡ ይህ ነው፦ በዚያን ጊዜ፥ በአኹኑም ጊዜ፡ የይሁዲው መንግሥት፡ ጠቅላይ ምሉክ ኾኖ ለሚገዛው፡ "ቢንያሚን ናታንያሁ" ለሚባለው፡ የእስራኤል መሪ እና በአኹኑ ጊዜ፡ በሕይወተ-ሥጋ ለሌለው፥ በዚያን ጊዜ ግን፡ የፍልስጥኤማውያን መሪ ለነበረው፡ "ያሲር አራፋት" ለተባለው ታጋይ፡ በመካከላቸው ስላለው፡ ጽኑና ጠንቀኛ ችግር፡ ፍቱንና ፍጹም የኾነው፡ ዘላቂው መፍትሔ ሊገኝ የሚችለው፡ በእኛ፡ በእግዚአብሔሩ መንገድ ብቻ መኾኑን አረጋግጦ በማመልከት፡ ለኹለቱም፡ የሕዝቦቻቸው ተጠሪዎች፡ በየፊናቸው፡ ጽፎላቸው የነበረው አንድ ደብዳቤን ይመለከታል።

እነርሱን በመፍጠር፥ በቃል ኪዳንም፡ ወደእኛ በማቅረብ፡ አንድ አባትና አንድ እናት የኾንናቸው፡ የእኛ፡ የእግዚአብሔር አብወእም ልጆች የኾኑት፡ እኒህ፡ የኹለቱ ወንድማማች፡ የይስሓቅና የእስማኤል ተወላጆች ሕዝቦች፡ በሥጋም፡ የአንድ ወላጃቸው፡ የአብርሃም፥ የኹለቱ ሚስቶቹና እናቶቻቸው፡ የሣራና የአጋር ልጆች መኾናቸውን የማያውቅ የለም።

እነዚሁ፡ ወንድማማች ሕዝቦች፡ ይህን በመሰለ ጠላትነት፡ እንዲህ፡ በማያቋርጥ የእርስ-በርስ ደም መፋሰስ፡ የሚያካኺዱት ፍጅትና ዕልቂት፡ የቀጠለባት የጦር አውድማ፡ እዚያው የመካከለኛው ምሥራቅ መኖሪያ ዓለማቸው እምብርት በኾነችው፡ በኢየሩሳሌም መኾኑን፡ ኹላችሁም ታውቁታላችሁ።

እነዚህ ወገኖች፡ የዘር ግንዶቻቸው የኾኑትን፡ የአብርሃምንና የሙሴን፥ የዳዊትንም ቃል ኪዳናት በማፍረሳቸው፡ እነርሱን፥ በተለይም፡ አይሁድን፡ ከዲያብሎስ ክፋት፥ ከኃጢአት ቀንበርና ከሞት ቍራኝነት ለማዳን ብቻ ሳይኾን፥ በይበልጥም፡ በእርስ በርሳቸው መካከልም ጸንቶ የቆየውን የጥላቻና የጠብ ግድግዳ፡ ለአንዴና ለዘለዓለም በማፈራረስ፡ የመጨረሻውን ዘለዓለማዊ የዕርቅና የሰላም ስምምነት ሊያስገኝላቸው፡ ኢትዮጵያዊው ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡የዛሬ ኹለት ሺሕ ስምንት ዓመታት፡ በዚችው የኢየሩሳሌም ከተማቸው፥ በተለይም፡ "ቀራንዮ" በተባለው ልዩ ቦታ በተተከለ የመስቀል መከራው ላይ ኾኖ፡ ውኃ እንባውን ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን፡ ደም እንባውን፡ እንደጎርፍ እያፈሰሰ፡ በልመናው እንደተማፀናቸው፡ በኹላችሁም ዘንድ ይታወሳል።

አገልጋያችን ኤርምያስ፡ እነዚህን ሕያዋን ፍሬ-ነገሮች፡ በዚያ ደብዳቤው ውስጥ በማካተት ነበር፡ በእኛ፡ በእግዚአብሔሩ መንገድ፡ ለእነዚህ፡ ለዛሬዎቹ የተለያዩ ተፃራሪ ወንድማማች ሕዝቦች፡ ለዚሁ የዘር ጠላትነት ጠንቃቸው፡ ፍጹም መፍትሔ ሊኾናቸው የሚችለውን፡ መልካም አሳብ አቅርቦላቸው የነበረው።

ይህንኑ፡ ለይስሓቃውያኑ እና ለእስማኤላውያኑ የወንድማማች ችግር፡ ፍጹም ፍቱኑና እግዚአብሔራዊው የኾነውን፡ የመፍትሔ አሳብ የያዘው፥ አገልጋያችን ኤርምያስ፡ በእኛው፡ በእግዚአብሔሩ መንገድ አዘጋጅቶ፡ ስማቸውን፡ ቀደም ብዬ ለጠቀስሁላችሁ፡ ለኹለቱም ተቃራኒ ወገኖች መሪዎች፡ የላከው ደብዳቤ፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ" እና "Ethiopia: The Classic Case" በሚሉት መጻሕፍቱ ውስጥ ተመዝግበው ይገኛሉ።

በኹለቱ፡ ወንድማማችና የእነርሱ ትውልዶች በኾኑትስ መካከል፡ ይህን የመሰለው፡ የማይሽር የጥላቻና የማይሻር የጦርነት ኹኔታ፡ ጥንቱኑ፡ ለምን? እንዴትስ ሊፈጠር ቻለ? ለእነዚህ ጥያቄዎች፡ ተገቢውን መልስ በመስጠት፡ መሠረታዊ ምክንያቱን፡ እኔው ልግለጥላችሁ! ይኸውም፡ እንዲህ ነው፡-

የግርዛት ቃል ኪዳንን፡ ከእኛ፡ ከእግዚአብሔር የተቀበለውና ያለልጅ ያረጀው አብርሃም፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቱና ምግባሩ ረገድ፡ ጽኑ በኾኑ፡ አያሌ መከራዎች ከተፈተነ በኋላ፡ ከእኛ፡ ከፈጣሪው፡ የተሰጠው ተስፋ፡ ከመካኒቱ እኅት ሚስቱ ከሣራ፡ ወንድ ልጅን እንደሚያገኝ ነው።

እንዲህ ከኾነ፡ አብርሃም፡ ይህን፡ የእኛን መለኮታዊ የተስፋ ቃል፡ በፍጹም ሃይማኖቱ፡ እስከመጨረሻው በመጽናት መጠበቅ ይገባው ነበር። ነገር ግን፡ እንደታማኙ እውነተኛ ልጃችን፡ እንደኢዮብ፡ በትዕግሥቱ ጸንቶ መቀጠል ሳይቻለው ቀረ።

ከዚያ ይልቅ፡ እርሱ አብርሃም፡ ያን፡ የእኛን፡ የፈጣሪውን የተስፋ ቃል በማቃለል፥ እንዲያውም፡ የእኛን፡ የፈጣሪውን ፈቃድ በመሻር፡ የሚስቱን የሣራን ማራኪ አሳብ ተቀብሎ፡ እንደሚስቱ ፍላጎት፡ ከአገልጋይዋ ከአጋር፡ እስማኤልን፡ አስቀድሞ ለመውለድ በቃ።

አብርሃም፡ ይህን፡ ታላቅ ስሕተት በመፈጸሙ፡ ልክ፡ አዳምን ኾነ፤ ይኸውም፡ አዳም፡ በሚስቱ በሔዋን፡ አሳሳችና አስመሳይ ንግግር ተታልሎና ተሸንፎ፡ የእኛን የፈጣሪውን መለኮታዊ ቃል በመተላለፍ እንዳፈረሰ ኹሉ፡ አብርሃምም፡ በሚስቱ በሣራ ቃል፡ በእኛ ላይ፡ እንዲሁ ስላደረገ ነው።

እንግዴህ፡ በኹለቱ ወንድማማች መካከል፥ እነዚህም፡ የእስማኤል ልጆች በኾኑት፡ በፍልስጥኤማውያን እና የይስሓቅ ልጆች በኾኑት፡ በአይሁድ መካከል፡ ያው፡ የአዳምና የሔዋን ልጆች እንደኾኑት፡ እንደቃኤልና እንደአቤል፡ የማይቀረው ጠላትነት፡ ሊፈጠር የቻለው፡ በዚህ ምክንያት መኾኑን፡ ኹላችሁም እንድታውቁት ያስፈልጋችኋል። <u>የእግዚአብሔር ፈቃድ ሲፈርስ፡ ምንጊዜም፡ ውጤቱ ይህ ነውና።</u>

ይኹን እንጂ፡ ይኸው ጠላትነት፡ ሊወገድ የሚችልበትን የምሥራች ቃሌን፡ በዚሁ ዐዋጄ ላሰማችሁ! ይኸውም፡ እኔና ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በኪዳነ ምሕረትነት መድኃኒትነታችንና ቤዛነታችን፡ ለእነርሱና ለመላው ፍጥረተ-ዓለም ያቀረብነውን ሰላማችንን፡ በእርግጥ መቀበላቸውን፡ እነርሱውና መላው ፍጥረተ-ዓለም፡ በእኛዋ፡ በእግዚአብሔራዊቷ የእውነትና የመንፈስ-ቅዱስ አምልኳቸው፡ በሚያረጋግጡበት ጊዜ ብቻ ነው።

<u>ለግብረ-ሰዶም መፈጠር፡ አምስተኛው ጠንቀኛ ምክንያት፡ ይህ መኾኑን አስተውሉት!</u>

፮. ለቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁና አምልኳችሁ፡ መሠረትና አዕማድ በኾኑት፡ "ምሥጢረ-ሥላሴና ምሥጢረ-ሥጋዌ፥ ምሥጢረ-ጥምቀትና ምሥጢረ-ቊርባን፥ ምሥጢረ-ትንሣኤ-ሙታንም" በምትሏቸው ትምህርቶቻችሁ ላይ፡ ባዕዳኑ ተቃዋሚዎቻችሁ፡ አሪታውያኑ የአይሁድ ካህናትና ኦርቶክሳውያኑ ግብፃውያን መነኮሳት፡ በወንድነት ጾታቸው በመመካት፡ ረቂቅ የኾነ ቀውስንና ነቅዕን፥ ኑፋቄንና ክህደትን በማምጣታቸው፡ እጅግ ከባድ የኾኑ፡ ጠንቀኛና አሳሳቢ ችግሮች መቀፍቀፋቸው ታወቀ።

ከእነዚህ ችግሮች መካከል፡ ከዚህ የዐዋጅ ቃሌ ጋር፡ አግባብነት ያለውን፡ ዓይነተኛውንና ዐቢይ የኾነውን፡ አንዱን ብቻ፡ እዚህ ላይ፡ በቀዳሚነት እጠቅስላችኋለሁ።

እርሱም፡ የእኛን፡ የፈጣሪነታችንን፡ እግዚአብሔራዊ ማንነትና ምንነት፡ በእግዚአብሔር አብነት፥ በእግዚአብሔር ወልድነትና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስነት ብቻ ወስነው በመመደብ፥ የእነርሱንም፡ የወንድነት ጾታ ብቻ በማጽናት፡ የእኔን ግን፡ በመንበረ-ጸባዖት ቅድስት ሥላሴነቴና በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነቴ፡ እግዚአብሔር እም የመኾኔንና የሴትነት ጾታዬን እውነታ የመካዳቸውና በሓሰት የመሻራቸው ድፍረት ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ ወንዶቹ ሰብአውያን ፍጡሮቻችን፡ አኹንም፡ በቀንደኛው ተቃዋሚያችን፡ በዲያብሎስ መሪነት፡ በእኔ፡ በእግዚአብሔር እምዋ ላይ፡ ይህን ያህል ድፍረትን ከመፈጸም፡ ወደኋላ ያላሉ ከኾኑ፡ በዕሩቅ-ብእሲ ሴቶች ልጆቼ ላይማ፡ የበላይ ገዢነታቸውንና የተጽዕኖ ጭቆናቸውን፡ በበለጠ ከማጽናት በቀር፡ በምንም መንገድ ለማቃለል እንደማይመለሱ፡ እርግጥ ኾኖ፡ ይኸው ይታያል።

አዎን! እነርሱ፡ በእኔ ብቻ ሳይወሰኑ፡ እኛ እግዚአብሔር፡ ወንድንና ሴትን፡ እንደእኛ፡ እኩል አድርገን የፈጠርናቸው መኾናችን እየታወቀ፡ ነገር ግን፡ በዚሁ፡ የወንድነት የበላይነት ትምክህታቸው ተመርተው፡ "**ኀበ ምትኪ ይኩን ምግባኢኪ! ወውእቱ ይቅንይኪ!**

"**ታዛዥነትሽ፡ ለባልሽ ኾኖ፡ እርሱ ይገዛሻል!**" ተብሎ፡ በአንዲቱ ሔዋንና እርሷን በመሰሉ፡ በየግል ሴቶች ላይ የተጣለው፡ አምላካዊ የመርገም ፍርድ፡ በአጠቃላይ፡ በኹሉም ሴቶች ላይ፡ ለዘለዓለም ሲፈጸም እንደሚኖር አድርገው በማቅረብ፡ በሴቶች ልጆቼ ላይ፡ ለ፭ሺ፭፻ (ለአምስት ሺህ አምስት መቶ) ዓመታት ሲያካኼዱት የኖሩት በደልና ግፍ፡ የሚዘነጋ አይደለም።

እኔ ድንግል ማርያም፡ "**ተዐብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር፤ ወትትሐሠይ መንፈስየ፡ በአምላኪየ፥ ወመድኃኒየ፤ እስመ ርእየ፡ ሕማማ፡ ለአመቱ። ናሁ እምይእዜሰ፡ ያስተበፅዑኒ፡ ኵሉ ትውልድ፤ እስመ ገብረ ሊተ፡ ኃይለ ዓቢያተ።**

"**ነፍሴ፡ እግዚአብሔርን ታገንነዋለች፤ መንፈሴም፡ በአምላኬና በመድኃኒቴ ሐሤትን ታደርጋለች፤ የገረዱን መከራ አይቷልና።**" ብዬ፡ ይህንኑ በደልና ግፍ፡ እንዲሻር እስካደረግሁት ድረስ፡ ቀጥሎ እንደነበረ ይታወቃል።

አኹን ግን፡ እጅግ የሚገርመውና የሚያሳስበው፡ በሴቶች ልጆቼ ላይ፡ ከቀድሞው የክርስትና ዘመን አንሥቶ የተዘመተው፡ ይህ የበደልና የግፍ ጭቆና፡ በክፉዎቹና በጨካኞቹ አይሁድ፥ አረማውያንና ተንባላት [እስላሞች] ዘንድ ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ "ጥንታውያንና አክራሪ ክርስቲያኖች ነን!" በሚሉት፡ በምንኵስናው አበጋዞች፡ በኦርቶዶክሳውያኑና በካቶሊካውያኑ፥ በወንጌላውያኑም ካህናት ዘንድ ጭምር፡ ሳያባራ፡ አኹንም፡ በተጠናከረ ይዞታ ሲካኼድ መታየቱ ነው።

እኛ እግዚአብሔር፡ በእኛው እግዚአብሔር አብነትና እግዚአብሔር እም'ነት፡ ተዋድደውና ተጋብተው፡ ይወልዱና ይዋለዱ ዘንድ፥ ይፋቀሩና ይረዳዱም ዘንድ፥ በሴትነትና በወንድነት፡ ኹለት ጾታዎች አድርገን፡ የሠራናቸው ሰብኣውያን ፍጡሮቻችን፡ በዚያው በሠራንላቸው፡ የተፈጥሮ ሥርዓት፡ እኩልነታቸውን ጠብቀውና አጽንተው፡ በመከባበር፡ መልካሙን እግዚአብሔራዊ ሕይወት እንዲኖሩ በመተው ፈንታ፡ ያው፡ እንደተለመደው፡ በክፋቱ አበጋዝ፡ በዲያብሎስ አነሣሽነትና በተባባሪ የጥፋት ጭፍሮቹ መሠሪነት፡ ያ፡ የእኛ፡ እግዚአብሔራዊውና ትክክለኛው የተፈጥሮ ሥርዓት፡ ኾነ ተብሎ፡ እንዲቃወስና እንዲለወጥ ተደረገ።

ይኼም አደገኛ ቀውስና ለውጥ፡ በመላዋ ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥታችን የአገልግሎት ዘርፎቻችን በኾኑት፡ በቤተ-ሕዝቡ፥ በቤተ-ምልክናውና በቤተ-ክህነቱ ውስጥ ሳይቀር፡ ሥርጎ በመግባት፡ በአንድ ወገን፡ የወንድ የበላይነትና ገዢነት፥ በሌላ ወገን ደግሞ፡ የሴት የበታችነትና ተገዢነት፡ ጥብቅ መሠረት መያዙ፥ ተከሥቶና ጸንቶም መቀጠሉ ነው።

በዚህ ምክንያት፡ በወንዶችና በሴቶች መካከል፡ ድብቅና ግልጥ፥ ረቂቅና ግዙፍ የኾነ፡ የማይታረቅና የማይበርድ፡ ጽኑ ቅራኔና ቂም-ዐዘል ጥላቻ ተፈጠረ። ከዚህም የተነሣ፡ ወንድ የኾነ ኹሉ፡ ቀደም ብዬ የጠቀስሁት፡ አደገኛው ቀውስና ለውጥ ባስገኘለት ዕድል በመጠቀም፥ በራሱም ኃይል በተቀዳጀው፡ በዚህ ሰይጣናዊ ሥልጣኑና ጉልበቱ በመመካት፡ በሴቲቱ ላይ፡ የፈለገውን ኹሉ ለማድረግ፡ ልቅ የኾነ ነጻነትን አገኘ። ሴቲቱ ደግሞ፡ በዚህ ዓይነትና በዚህ ረገድ፡ ከወንዱ የሚደርስባትን ጥቃት፡ በዓቅመ-ቢስነት፡ ዝም ብላ ከመቀበል በቀር፡ ሌላ አማራጭና መከላከያ ስለሌላት፡ በቀሏን ለመፈጸም፥ ባገኘችው ዕድል ኹሉ በመጠቀም፡ የራሷን ጥቃት፡ ያለምንም ርኅራኄ፡ በወንዱ ላይ ከማካኼድ፡ ወደኋላ የማትል ኾነች።

ስለዚህ፡ እዚህ ላይ፡ "ወንድ፡ በሴት ላይ ያለውን፡ የበላይነት ተፅዕኖ፡ ለምን፡ እያጸና የሚኼድ ኾነ? ሴትስ፡ ለምን፡ በወንድ ላይ፡ ያላትን ጭካኔ፡ እንዲህ የምታጠናክር ኾነች? አስቀድመው ተዋድደውና ተፈቃቅደው የተጋቡና ልጆችን ወልደው የኖሩ ባልና ሚስት ሳይቀሩ፡ በትዳራቸው ተስማምተው ሊቀጥሉ የማይቻላቸው እየኾኑ፡ ለምን፡ እስከመፋታት ይደርሳሉ?" የሚሉት ጥያቄዎች ስለሚነሡ፡ ለእነዚሁ ጥያቄዎች፡ መልሶቹን መስጠት፡ ግድ ይኾናል።

በወንዱ ላይ፡ በምሥጢር ለምታካኺደው፡ የማያባራ የጥቃት ዘመቻዋ፡ ማጥቂያ ከሚኾኑላት ከብዙዎቹ መሣሪያዎቿ መካከል፡ ቀዳሚውና ዋናው ኾኖ የሚገኘው፡ የወንዱን የፍትወተ-ሥጋ ፍላጎት ለማርካት፡ የሴትነት ጾታዋ ያቀዳጃት፡ ኃይለኛ መስሕብነቷ ይኾናል። ወንዱም፡ ያለው ዕድል፡ ራሱን ተቆጣጥሮ ሊያስቀረው የማይቻለውን፡ ይህን የፍትወተ-ሥጋ ፍላጎቱን ለማርካት ሲል፡ በሚኾንለት፡ በማናቸውም ዘዴና መንገድ፡ እርሷን፡ አስደስቶና አሞጋግሶ፥ አባብሎም ኾነ ተለማምጦ፡ ፈቃዱን ተቀብላ እንድትፈጽምለት መጣር ብቻ ይኾናል።

ከዚህ በቀር፡ ሌላ፡ ምንም ዓይነት ማማረጫ ስለሌለው፡ ከዚህ ግቡ ለመድረስ፡ የማይከፍለው፡ እስከመሥዋዕትነት የሚደርስ ዋጋ፡ ከቶ አይኖርም። ይህንም፡ ሴቲቱ፡ ጥሩ አድርጋ ስለምታውቅ፡ ባንድ ፊት፡ የጋለ የምርኮ ወጥመዷን በመዘርጋት፥ በሌላ አግጣጫ ደግሞ፡ ውስብስብ የክልከላ መረቧን በዙሪያዋ በማጠር፡ እንደፈለገች ትጫወትበታለች፤ የፈለገችውንም ኹሉ ራሷ ታደርጋለች፤ እርሱንም ታስደርገዋለች።

በወንድና በሴት መካከል ያለውን፡ የጋብቻና የወሲብ ግንኙነት በሚመለከት፡ በሰብኣውያን ፍጡሮቻችን መካከል የሚታሰበውና የሚወጠነው፥ የሚካኼደውና የሚፈጸመው ኹኔታና ድርጊት ኹሉ፡ እኛ የሠራነውን፡ እውነተኛውን እግዚአብሔራዊና መንፈሳዊው ዓላማና ሥርዓት ተከትሎ የሚከናወን ሳይኾን፡ ከዐውደ-ነገሥቱ ኮከብ ቆጠራና ከአምልኮ ባዕዱ ገዢ የተፅዕኖ ኃይል የተነሣ፡ በሓሰተኛው ሰይጣናዊውና ሥጋዊው ዓላማና ግብ የሚመራ በመኾኑ፡ ተግባሩና ውጤቱ፡ ከዚህ፡ ከክፋቱ ኹኔታ ድርጊት ውጪ ሊኾን፡ ከቶ አልቻለም።

በወንዱ በኩል፡ ይህን የመሰለው ከፍተኛ የፍቅር ጥረትና ትግል ከተደረገ በኋላ፡ በሴቲቱ በኩል፡ የራሷንም ፍትወተ-ሥጋ ለማርካት ስትል፡ የወንዱን ፍላጎት ብትፈጽምም፡ ቊጭትዋን በሚቀጥለው ግንኙነት ጊዜ፡ በጸና ይዘት ለማሳየት ትዘጋጃለች እንጂ፡ በወንዱ ላይ ያላትን የቂም በቀል ዕቅድ በማቅለል፥ ወይም፡ በመተው፥ ወይም፡ በመዘናጋት፡ ልታረግብ ወይም ልታለሰልስ ዝንባሌው የሚኖራት አትኾንም።

እንግዴህ፡ ኹለቱንም ወገኖች ሊጎዳቸው የሚችለውን ጠንቅ በማስከተል ረገድ፡ በወንዱና በሴቲቱ መካከል የሚከሠተው፡ ከባዱና አማሳኙ ችግር፡ በተለይ፡ በወንዱ በኩል፡ በአሳብ መፀነስ የሚጀምረው፡ የኹለቱ የወሲብ ግንኙነት፡ እንዲህ ካለው፡ የከረረ ደረጃ በሚደርስበት ጊዜ ይኾናል። ይኸውም፡ ወንዱና ሴቲቱ፡ በፍቅርና በተዝናና ስሜት ኾነው፡ እርስ በርሳቸው በመፈላለግና በመፈቃቀድ፥ በጋራ አካኺደው ሊፈጽሙት የሚገባቸውን፡ ይህን፡ የፍትወተ-ሥጋ ፍላጎታቸው ማርኪያ የኾነውን ሩካቤ-ሥጋ [የወሲብ ግንኙነት]፡ በአንድ ወገን፡ በወንዱ በኩል ግፊት ሲኖር፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ በሴቲቱ ክልከላ ምክንያት፡ እውን ሊኾን ከማይችልበት ደረጃ ሲደርስ፡ በዚያን ጊዜ፡ የሚከሠተው፡ ጠንቀኛው ችግር ነው።

እንዲህ ባለ ኹኔታ የሚከሠተው የጠንቅ ቋት፡ ከያዛቸው መዘዞች መካከል፡ ከዝሙትና ከአመንዝራነት ጋር፡ <u>*ግብረ-ሰዶም፤*</u> አንዱ ኾኖ ይገኛል። "አመንዝራነት"፡ ጋብቻን የማፍረስ ኃጢአት ሲኾን፥ "ዝሙት" ደግሞ፡ ከተፈጥሮ ግዳጅ የተነሣ፡ በጋብቻ ውስጥ እና/ወይም፡ ከጋብቻ ውጭ፡ ከሌላ ጾታ ጋር የሚፈጸም፡ የሩካቤ-ሥጋ ግንኙነት ነው።

በአንድ ወገን፡ በወንዱ የበላይነት የተፅዕኖ ቀንበር ምክንያት፡ በሴቲቱ ውስጥ የተፈጠረው ሥነ-ልቡናዊው የቂም በቀል እሳተ-ገሞራ ፍንዳታ፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ በወንዱ ላይ፡ ከሴቲቱ በኩል በሚሠነዘርበት ጥቃት የተነሣ እየደረሰበት ያለው፡ የሰለባነት ጉዳት፡ እየጨመረበት ኼዶ፡ የወንዱ፡ የትዕግሥቱ ጽዋ ሲሞላ፥ ይህም ማለት፡ ወንዱ፡ በሴቲቱ፡ የተባባሰ ክልከላ ምክንያት፡ የተፈጥሮ ችግሩን መቋቋም ሲያቅተው፡ ወደዝሙቱና ወደግብረ-ሰዶሙ፥ በመጨረሻም፡ ወደአመንዝራነቱ ኃጢአት እንዲያመራ ይገደዳል።

ይህን የመሰለው የችግር ሰለባነት፡ እጅግ በርትቶና በዝቶ የሚታየው፡ በሕጋዊ ጋብቻቸውና ትዳራቸው፡ በታማኝነት ጸንተው በሚኖሩና በክህነት አገልግሎት ላይ በሚገኙ ልጆቼና ሰብአውያን ፍጡሮቻችን ዘንድ በመኾኑ፡ ለዝሙቱ፥ ለግብረ-ሰዶሙና ለአመንዝራነቱ ኃጢአት፡ በብዛትና በይበልጥ ተዳርገው የሚገኙት፡ እኒሁ ወገኖች ናቸው። ከዚህ የተነሣ፡ እንዲህ ባለ መልክና ይዘት፡ በሴትና በወንድ መካከል የሚካኼደው የተዛባ ግንኙነትና የሚደርሰው የችግር ኹኔታ ኹሉ፡ በጋብቻ ሥርዓትና በትዳር ሕይወት ተሣሥረው የሚኖሩትን፡ ባሎችንና ሚስቶችን የሚያካትት መኾኑ ሊታወቅ ይገባል።

እኛ፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታ ተለይተው፡ በእኩልነት ደረጃ፡ በደስታ ሕይወት ይኖሩበት ዘንድ፡ በፍጹም መልካምነት ሠርተን፡ ለሰዎች ፍጡሮቻችን የሰጠናቸውን እግዚአብሔራዊ ሥርዓት፥ ወንዶች፡ የሚሻላቸውና የሚጠቅማቸው መስሏቸው፡ "የለም! የጋራው ኑሮ መካኼድ ያለበት፡ በወንድ የበላይ ገዢነት እና በሴት፡ የበታች ባርነት ነው!" ብለው፡ ወደሰይጣናዊው አሠራር በመለወጣቸው፡ ዋጋቸው ኾኖ፡ ለዚህ አሳፋሪና አስነዋሪ፥ አሳዛኝና አሠቃቂ የኑሮ ኹኔታ ሊዳረጉ እንደቻሉ፥ በዚህም ዳረጎት፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ፡ "ሥራ ለሠሪው! እሾህ ላጣሪው!" የሚለው ይትበሃላችሁ፡ በእየራሳችሁ፡ በወንዶች ላይ እንዴት እንደደረሰ መመልከት ነው።

እዚህ ላይ፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ፡ በእናትነቴ፡ ለወንዶቼም ለሴቶቼም ልጆቼና ሰብአውያን ፍጡሮቼ ኹሉ፡ የማበረክትላችሁ "መጠይቃዊ ምዕዳን" አለኝና፡ በእውነተኛው ልጅነታችሁ፡ እስኪ እባካችሁ፡ ለአንድ ጊዜ እንኳ አዳምጡኝ! አዳምጣችሁኝም፡ ፈቃዴን ፈጽሙልኝ! ይህን በማድረጋችሁ፡ ትጠቀማላችሁ እንጂ፡ የምትጎዱበት፡ አንዳችም ነገር፡ ከቶ የለም። የምትጎዱትስ፡ ሳትሰሙኝ ብትቀሩ ነው፤ ሰምታችሁኝ ከኾነም፡ የሰማችሁኝን ሳትፈጽሙት ብትቀሩም ትጎዳላችሁ።

አይዟችሁ! ከእኔ የሰማችሁትን፡ ይህን መጠይቃዊ ምዕዳኔን ብትፈጽሙት፡ ለዘለዓለማዊው ቀርቶ፡ እናንተ፡ እንዲህ ለምትጓጉለትና ለምትሠዉለት፡ ለዚህ ዓለም ኑሮአችሁም እንኳ ቢኾን፥ ሥጋዊዉን ፍላጎታችሁን ብቻ ሳይኾን፡ ነፍሳዊዉንና መንፈሳዊዉን ጭምር፡ በእርግጥ፡ አጠቃልላችሁና አሟልታችሁ፡ በፍጹም ተድላ ደስታ የምትኖሩበት ሕይወታችሁ ኾኖ ታገኙታላችሁ።

"*መጠይቃዊ ምዕዳን*" ያልኳችሁ፡ *ምዕዳን = ተግሣፅና ማስጠንቀቂያ የተመላበት ትምህርታዊ ምክር* ሲኾን፡ በጥያቄ መልክ ጭምር የቀረበ ማለት ነው። እርሱንም፡ እንዲህ በሚል አጭር ቃል አሳውቃችኋለሁ፡-

*መጠይቃዊነቱን ላስቀድምላችሁ፡-*

እናንት፡ ወንዶች እና ሴቶች ልጆቼ! ሰብአውያን ፍጡሮቼም!

ከእኔ፡ ልትሸሽጉኝ የሚቻላችሁ፡ አንዳችም ነገር አይኖርምና፡ ለእየራሳችሁና ለሌሎቹ መሰሎቻችሁ ጥቅም ስትሉ፡ እያንዳንዳችሁ፡ ወንዶቹም፥ ሴቶቹም፡ ይህን ምሥጢራችሁን፡ እስኪ፡ ለእኔ ብቻ፡ በእያላችሁበት ኾናችሁ፡ በግልጽ ንገሩኝ!?

ዛሬ፡ እናንተ፡ እያንዳንዳችሁ፡ ወይ፡ በአንደኛው ወገን፡ በፍጥረት ልደት መጀመሪያ፡ በእኛ፡ በእግዚአብሔሩ መልካችን፥ ከዚያም፡ "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾኑ!" ብለን፡ በአርአያችን እንደፈጠርናቸው፥ እነርሱ ግን፡ ያን ማንነታቸውንና ምንነታቸውን ለውጠው፡ ለ፭ሺ፭፻ (ለአምስት ሺህ አምስት መቶ) ዓመታት፡ በአንድ ዓይነት፡ የክፋትና የሓሰት፥ የኃጢአት እና የሞት ዓለም ይገኙ እንደነበሩት፡ እንደቀድሞዎቹ "አዳም እና ሔዋን" እንደተባሉት ወንድ እና ሴት ሰዎች ናችሁ፤

አለዚያ ደግሞ፡ በኹለተኛው ወገን፡ ከዚያ ወዲህ፡ የዛሬ ፪ሺ፰ (ኹለት ሺህ ስምንት) ዓመታት፡ ሴቶቹ፡ እግዚአብሔር እም እንደተዋድኋትና "ዳግማዊት ሔዋን" እንደተባልሁት፡ እንደእኔ፡ እንደድንግል ማርያም ናችሁ፤ ወንዶቹ ደግሞ፡ "ዳግማዊ አዳም" እንደተባለው፡ እንደወዳጄ ልጄ ኢየሱስ መሲሕ ናችሁ።

ከኹለቱ ባንዳቸው ወገን የሚያደርጋችሁን ይህንም እውነታ፡ ኹላችሁም፡ በየሃይማኖታችሁ፥ "ሃይማኖት የለንም!" ለማለት የምትደፍሩ ካላችሁም፡ በሰጠናችሁ የተፈጥሮ አእምሮአችሁ፡ በቀላሉ ልታውቁት ይቻላችኋል።

ቀደም ብዬ ባሰማኋችሁ ሓተታዬ ውስጥ እንደተገነዘባችሁት፥ ሰብአውያን ፍጡሮቼ በኾናችሁትም ኹሉ ዘንድ፥ ይልቁንም፡ "ልጆቼ!" በምላችሁ መካከል እንኳ ሳይቀር፥ "እየራሱን፡ ከሰይጣናዊው ባዕድና ጣዖት አምልኮ ነጻ ያደረገ፡ አንድም ቤተሰብ ይኖራል!" ተብሎ ሊታሰብ በማይቻልበት፡ በዚህ በዛሬው ዘመናችሁ፡ ኹላችሁም፡ ወንዶቹም ሴቶቹም፡ ዝንባሌያችሁ፡ እንዲህ፡ ክፉው ወደኾነው፡ ወደሰይጣናዊው ኾኖ መገኘቱ ባያስደንቅም እንኳ፡ የእኛን፡ የቅርባችሁ የኾንነውን፡ ሴቶቹ፡ "ዳግማዊት ሔዋን" የተባልሁትን፡ እኔን፡ ድንግል ማርያምን፥ ወንዶቹ ደግሞ፡ "ዳግማዊ አዳም" የተባለውን፡ ልጄ ወዳጄን ኢየሱስን መምሰልን ያቃታችሁ፥ ወይም፡ የእኛን፡ አርአያነታችንንና ምሳሌነታችንን መከተልን ትታችሁ፡ የቀድሞዎቹን አዳምንና ሔዋንን መምሰልን ብቻ የምትመርጡት? ወይም፡ የእነርሱን እምነት [አስተሳሰብ] እና ምግባር [አድራጎት] ብቻ ተቀብላችሁና ተከትላችሁ የምትፈጽሙት? ለምን እንደኾነ፡ እንዲያው ለእየራሳችሁና ለሌሎችም ለማሳወቅ ያህል፡ እባካችሁ ብትነግሩኝ!?

ባጭሩ፡ የምዕዳኔ መጠይቃዊነቱ፡ ይህ ነው።

አኹን ደግሞ፡ ራሱን፡ ምዕዳኔን ላስከትልላችሁ፡-

እኔ፡ ጾታ የሌለኝ፡ አንድ እግዚአብሔር፡ አስቀድሜ፡ ራሴን፡ "እግዚአብሔር አብ እና እም" ብዬ፡ ለምን፡ በወንድነት እና በሴትነት፡ እኩል ከኹለትነት ከፈልሁ? እኩል ከኹለትነት በመክፈልም፡ ለምን፡ በአባትነትና በእናትነት፡ አንድ "እግዚአብሔር ወልድ"ን፡ ወለድን? "እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ"ንም አሠረጽን?

ልክ፡ እንደዚሁ ኹሉ፡ በእኛው መልክና አርአያነት፡ አስቀድመን፡ "ዕጓለ እመሕያው" ብለን ፡ ያለ ምንም ጾታ፡ በሥጋችን፥ በነፍሳችንና በመንፈሳችን፡ አንድ አድርገን፡ በሰውነት፡ ለምን ፈጠርነው? እንዲህ ፈጥረነውም፥ ከእኛ፡ እንደእያንዳንዳችን በማድረግ፡ ለምን፡ "አዳም እና ሔዋን" ብለን፡ በወንድነት እና በሴትነት፡ እኩል ከኹለትነት ከፈልነው? እኩል ከኹለትነት በመክፈልም፡ ለምን፡ በአባትነትና በእናትነት፡ መሰሎቻቸውን፡ እናንተን፡ ወንዶችንና ሴቶችን ልጆችን እንዲወልዱ አደረግን?

እናንተም፡ ወንዶቹና ሴቶቹ፡ እንዲህ፡ ከእኛ፡ በተፈጥሮ ባገኛችሁት፡ እግዚአብሔራዊ ዕውቀትና የመምረጥ ነጻነት፥ የመወሰን ሥልጣንና የማድረግ ኃይል ተጠቅማችሁ፡ በቀዳማዊው አዳምነታችሁና ሔዋንነታችሁ፡ ከእኛ፡ ከእግዚአብሔር ሕይወት ውጭ ያደረጋችሁን፡ ሞትን ያስከተለባችሁን፡ የዲያብሎስ የኾነውን፡ ሰይጣናዊዉን ሓሰትና ኃጢአት፡ በፈቃዳችሁ ተቀብላችሁ በመከተላችሁ፡ በክፉው የኵነኔ ፍርድና ፍዳ፥ ለ፭ሺ፭፻ (ለአምስት ሺህ አምስት መቶ) ዓመታት፡ በጨለማው ግዛትና በባርነቱ ቀንበር ሥር ተጨቍናችሁ፡ ስትሠቃዩ ኖራችሁ።

በዚህ ጊዜ ነው፡ እኔ፡ ሴቲቱ፡ የአዳምና የሔዋን ልጅ፡ ድንግል ማርያም፡ በመልአኩ ገብርኤል አንደበት፡ "ቡርክት አንቲ እምአንስት!"

"ከአዳምና ከሔዋን ሴቶች ልጆች መካከል፡ አንዲት የበቃሽ፡ አንቺ ብቻ ተገኘሽ!" የሚለውን፡ የምሥራች ቃል ሰምቼ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር እም፡ አስቀድሜ፡ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከተዋሓድኋት በኋላ፡ ልጄን ወዳጄን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ ከእርሷ፡ ከዚችው፡ ድንግል ማርያም፡ በሰውነት ወልጄ፡ በእርሱና በእኔ መሥዋዕትነትና ቤዛነት፡ መድኃኒታችሁ ኾነን፥ እናንተን፡ ለዘለዓለም ሞት ከዳረጋችሁ፡ የሓሰቱ አባትና የክፋቱ አበጋዝ፥ የኃጢአቱ ጠንቅና የባርነቱ ቀንበር ከኾነው፡ ከዲያብሎስም ጋር፡ ልጄ ወዳጄ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከፍጥረት በፊት አንሥቶ፡ ለዝንተዓለም ሲያካኼድ በኖረው ታላቅ ጦርነት ላይ፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፡ ድልን በመቀዳጀቱ፡ ቅድስት የኾነችውን የትንሣኤን ሕይወትና ዘለዓለማዊት የኾነችውንም የሰንበት ዓለም አወረስናችሁ፤ እናንተንም፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ ልጆቻችንና ነጋሢዎቻችን፥ ካህናት አገልጋዮቻችንና ዜጎቻችን አደረግናችሁ።

እኛ እግዚአብሔር፡ ይህን ኹሉ፡ የኾንነውና ያደረግነው፡ ታዲያ! ለምን መሰላችሁ? ስለእናንተ ስንል ብቻ እኮ ነው? አዎን! እናንተን፡ እያንዳንዳችሁን፡ በነፍስ ወከፍ፡ ከቀደሙት፡ ከክፉዎቹ አዳምና ሔዋን ማንነታችሁና ምንነታችሁ ፈጽመን ለይተን አውጥተናችሁ፡ ሴቶቹን፡ እኔን፡ እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያምን፥ ወንዶቹንም፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ያደረግናችሁ መኾናችሁን አውቃችሁ፡ እየራሳችሁን፡ ለዚህ እግዚአብሔር ማንነታችሁ እንድታበቁ እኮ ነው!

እናንተ፡ ወንዶቹና ሴቶቹ ልጆቻችን፥ ሰብኣውያኑም ፍጡሮቻችን፡ በባል እና በሚስት፡ የአንድነት ሕይወታችሁ፥ የጋብቻና የትዳር ህልውናችሁም፡ እንዴት፡ በፍጹም ፍቅር ተስማምታችሁ መኖር እንደሚገባችሁ፡ እስኪ፡ እኛ፡ እግዚአብሔር አብ እና እግዚአብሔር እም፡ በአርአያነት የፈጸምንላችሁን አብነታችንን፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ተመልከቱት።

ይኸውም፡ አንድ ልጃችንን በመውለድና አንዱን መንፈሳችንን በማሥረፅ፡ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ጀምረን፡ እስከዛሬ፥ ዛሬና ወደፊትም፡ ለዘለዓለም፡ ዐብረን እያሳለፍን ያለውን፡ ሰላማዊ አኗኗራችንን ነው።

ደግሞም፡ እንዲህ፡ ተፋቅረንና ተስማምተን፡ እየኖርን ሣለን፡ በተመሰገነው፡ የጌትነት ክብራችንና በተቀደሰው የተድላ ደስታችን የተመላው፡ የመልካሙ እግዚአብሔራዊ ህልውናችን ተካፋዮች ይኾኑ ዘንድ፡ ፍጥረታተ-ዓለማቱን መፍጠራችን ነው።

ይህ ብቻ ሳይኾን፥ ይህንኑ፡ ፍጥረታተ-ዓለማታችንን፡ የምንጠብቅባትንና የምንመግብባትን፥ የምንመራባትንና የምናስተዳድርባትን፥ የምንቈጣጠርባትንና የምንንከባከብባትን፥ ዲያብሎስና እርሱን የመሰሉት ክፉዎች ጭፍሮቹ፡ በሰዎች ፍጡሮቻችን ላይ ሳይቀር፡ በሥነ ፍጥረት ሥርዓታችን ላይ የሚያደርሱትን፡ የጥፋት ቀውስና ሙስና ኹሉ፡ በቤዛነታችን የምናስተካክልባትን፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችንን መሥርተን፡ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴነታችን፡ ይህንኑ መለኮታዊና ፍጥረታዊ ህልውናችንን፡ ይኸው በአባትነታችንና በእናትነታችን፡ በመልካም እያካኼድን መቀጠላችን ነው።

አዎን፡ እውነታው ይህ ነውና፡ ስለዚህ፡ ከዚች አፍታ ጀምራችሁ፡ ወንዶቹም፥ ሴቶቹም፡ እኛን መምሰል ብቻ ሳይኾን፡ እኛን መኾንም ይቻላችኋልና፡ እንግዴህ፡ "እኛን ኹናችሁ፡ በእግዚአብሔራዊው ሕያውነት፡ ለዘለዓለም ኑሩ!" እንላችኋለን።

ራሱ ምዕዳኔ ደግሞ፡ ባጭሩ፡ ይህ ነው።

<u>ለግብረ-ሰዶም መፈጠር፡ ስድስተኛው ጠንቀኛ ምክንያት፡ ይህ መኾኑን አስተውሉት!</u>

፯. ቀደም ብዬ እንዳብራራሁላችሁ፡ እኛ እግዚአብሔር፡ በተፈጥሮ ጭምር ባርከን የሠራነው፡ ይህ፡ ንጹሑና የተቀደሰው የጋብቻና የሩካቤ ሥጋ፥ የፍቅርና የፍትወተ ሥጋ ጽንሰ-ሓሳብና ስሜቱ፥ ግብሩና ሥርዓቱም ኹሉ፡ "ነውርና ኃጢአት፥ ርኵሰትና መርገም ነው!" ተብሎ፡ በክፋቱ አበጋዝ፡ በዲያብሎስና በአገልጋዮቹ ክፉ ሰዎች ዘንድ፡ ለሓሰት መዳረጉና በሓሰት መመደቡ ይፋ ስለኾነ፡ ኹላችሁ ታውቁታላችሁ።

ይህ ሓሳዊ ድርጊት፡ እስካኹን ጸንቶ የኖረው፡ በክፋው ወገን ዘንድ፡ "ኀፍረተ-ሥጋ" በሚል የነውር ስያሜ እንዲዋረዱ ከተደረጉት፥ በእኛ ዘንድ ግን፡ ከተከበሩትና ከተቀደሱት፥ ከነጹትና ካማሩት፡ የሰውነት ሥጋውያት የአካል ክፍሎች ከኾኑት አባላት ጋር ተዳምሮ መኾኑንም ታውቃላችሁ።

በዚህም ምክንያት፡ ይኸው ሰይጣናዊ አስተሳሰብና ድርጊት፡ በወንድነትና በሴትነት የጾታ ተፈጥሮ ላይ ያመጣውን አሉታዊና ጠንቀኛ ችግር፡ በጥሞና እያስተዋላችሁ ትገመግሙት ዘንድ፡ ላቀርብላችሁ ነውና፡ ስሙት!

የጋብቻና የሩካቤ ሥጋ፥ የፍቅርና የፍትወተ ሥጋ ጽንሰ-ሓሳብና ስሜቱ፥ ግብሩና አፈጻጸሙ፥ ፍሬያማ ውጤቱም ኹሉ፡ እኛ እግዚአብሔር፡ በተፈጥሮ ጭምር ባርከን የሠራነው ስለኾነ፡ አዎን! በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ ዘንድ፡ ከአዳምና ሔዋን የፍጥረት ልደት ጀምሮ፡ ንጹሕና የተቀደሰ፡ የህልውናቸውና የሕይወታቸው፡ አንዱ ዐቢይ ክፍል ኾኖ፡ በእግዚአብሔራዊው ሃይማኖትና ምግባር፡ ሲገለገሉ የኖሩበት ሥርዓት ነው።

ይኸው መለኮታዊው የተፈጥሮ ሥርዓት፡ "ነውርና ኃጢአት፥ ርኵሰትና መርገም ነው!" ተብሎ፡ በክፋቱ አበጋዝ፡ በዲያብሎስና በአገልጋዮቹ ክፉ ሰዎች ዘንድ፡ ለሓሰት መዳረጉና በሓሰት መመደቡ፡ በይፋ የተጀመረው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ አጼዪት ድንግል ልጃችን በኾነችው፡ በቅድስቲቱ ንግሥት ማክዳ ይመሩና ይተዳደሩ የነበሩት ሕዝቤ፡ የዛሬ ፫ሺ (ሦስት ሽህ) ዓመታት፡ በኦሪታውያኑ አይሁድ የአገዛዝ ሥልጣንና ኃይል ሥር በወደቁበት ጊዜ፡ እንደነበረ ኹላችሁ ልታውቁት ይገባችኋል።

በዚህ ረገድ የተመሠረተው፡ ይኸው፡ የባዕዳኑ አይሁድ፡ የአገዛዝ ሥልጣንና ኃይል ደግሞ፡ ለዘመናት፡ ሥር እየሰደደና እየተጠናከረ ሲካኼድ ቆይቶ፡ በኋለኛው የክርስትና ዘመን፡ የዛሬ፡ ፩ሺ፮፻ (አንድ ሽህ ስድስት መቶ) ዓመታት፡ በኦርቶዶክሳውያኑ ግብፃውያን መነኮሳት ጳጳሳት፡ በበለጠ ተፅዕኖና ጭቆና እንዲጸና ተደረገ።

በዚያን ጊዜና ከዚያ በኋላ ነው፡-

፩. በኢትዮጵያ ልጆቼ ዘንድ ያልነበረውና የማይታወቀው፡ አምልኮ-ባዕድንና ግብረ-ሰዶምን ያካተተው፡ የዝሙትና የአመንዝራነት ኃጢአት፥ በይፋ ተከሥቶና ዕውቅና ተሰጥቶት፡ ሃይማኖታዊ ባህል የኾነው፤

፪. እኛ እግዚአብሔር፡ በተፈጥሮ ጭምር ባርከን የሠራነው፡ የጋብቻና የሩካቤ ሥጋ፥ የፍቅርና የፍትወተ ሥጋ ጽንሰ-ሓሳብና ስሜቱ፥ ግብሩና አፈጻጸሙ፥ ፍሬያማ ውጤቱም ኹሉ፡ "ነውርና ኃጢኣት፥ ርኵሰትና መርገም ነው!" ተብሎ፡ በክፋቱ አበጋዝ፡ በዲያብሎስና በአገልጋዮቹ ክፉ ሰዎች ዘንድ፡ ለሓሰተኛ ትርጉም የተዳረገውና በሓሰት ምንነት የተመደበው፤

፫. በእኛ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ የተከበሩትና የተቀደሱት፥ የነጹትና ያማሩት፡ የሰውነት ሥጋውያት፡ የአካል ክፍሎች የኾኑት አባላት፡ ከዚህ፡ ከበጎውና ከተቀደሰው፡ የተፈጥሮ ጸጋችን ጋር ተዳምረው፡ "ኀፍረተ-ሥጋ" በሚል፡ የነውር ስያሜ እንዲዋረዱ የተደረጉት።

አዎን! እነዚህ ኹሉ የተፈጥሮ ጸጋዎቻችን፡ "ኃጢኣት ናቸው!" ተብለው የተፈረጁት፥ እነሆ፡ ለ፫ሺ (ለሦስት ሺህ) ዓመታትና እስከዛሬ የቀጠለው፡ እንዲህ የሚለውም፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል፡ በኢትዮጵያ ልጆቼ ላይ መፈጸም የጀመረው፥ በዚያን ጊዜና ከዚያ በኋላ ነው።

"እምኢያእመርክምዋ ለኃጢኣት፡ ሶበ ኢመጽአት ኦሪት፤ ወለፍትወትኒ እምኢያእመርክምዋ ግሙራ፤ ሶበ ኢትቤ ኦሪት፡- 'ኢትፍቱ!'። ወምክንያተ ኮነታ፡ ይእቲ ትእዛዝ፡ ለኃጢኣት፤ ወአምጽአት ላዕሌየ፡ ኵሎ ፍትወታተ። ወቀዲሙሰ፡ ዘእንበለ ትምጻእ ኦሪት፡ ምውት ይእቲ ኃጢኣት። ወአነሂ ሐየውኩ ትካት፣ ዘእንበለ ትምጻእ ኦሪት። ወሶበ መጽአት ትእዛዘ ኦሪት፡ ሐይወት ኃጢኣት፤ ወአንሰ ሞትኩ። ወኮነተኒ ቀታሊተ፡ እንታክቲ ትእዛዘ ሕይወት። እስመ ኮነታ፡ ምክንያተ ይእቲ ትእዛዝ፡ ለኃጢኣት፤ ወበእንቲአሃ፡ አስሓተተኒ፤ ወቀተለተኒ። ...ትሑት ብእሲ አነ። መኑ እምአድኀነኒ፡ እምዝንቱ ነፍስትየ መዋቲ? እኩት እግዚአብሔር፡ በእንተ እግዚእነ ኢየሱስ መሲሕ! አንሰ፡ ሎቱ እትቀነይ፡ በልብየኒ፥ ወበኅሊናየኒ፡ ለሕገ እግዚአብሔር። ወለነፍስትየኒ፡ ለሕገ ኃጢኣት።

"ኦሪት ባትመጣ፡ ኃጢኣትን ባላወቅኋት ነበር፤ ኦሪት፡ 'አትመኝ!' ባትል ኖሮ፡ ፍትወተ-ሥጋንም [ምኞትንም]፡ፈጽሜ ባላወቅኋት ነበር። ይህች ትእዛዝ፡ ለኃጢኣት፡ ምክንያት ኾነቻት፤ በእኔ ላይ፡ ምኞቶችን ኹሉ አመጣችብኝ። ነገር ግን፡ [ኃጢኣትን ያሳወቀችኝ] ይህችው ኦሪት፡ ከመምጣቷ በፊት፡ በውስጤ የሚሰሙኝና የምፈጽማቸው፡ እነዚህ ኹሉ የተፈጥሮ ፍላጎቶቼ፡ አስቀድመው፡ ፈጽመው የሌሉ፣ የሞቱ እንጂ፡ 'ኃጢኣት' ተብለው የሚታወቁ አልነበሩም። ስለዚህ፡ ኦሪት ሳትመጣ፡ ከጥንት ጀምሮ፡ እኔ፡ ሕያው ኾኜ፡ በመልካም ሕይወት እኖር ነበር። የኦሪት ትእዛዝ በመጣች ጊዜ ግን፡ ያልነበረችው ኃጢኣት፡ ነፍስ ዘርታ ሕያው ኾነች። ሕያው የነበርሁት፡ እኔ ግን፡ ሞትሁ። ይህች፡ 'የሕይወት ትእዛዝ' የተባለችው ኦሪት፡ ለእኔ፡ 'ገዳዬ' ኾነች። እርሷ፡ ለኃጢኣት፡ የዚህች ትእዛዟ ምክንያት ኾነችላት። ስለእርሷም ብላ፡ እኔን አሳሳተችኝ፤ ገደለችኝም።

...አወይ እኔ፡ ወራዳው ሰው! ከዚህ፡ በሥጋዬ፡ ተቀሥፌ ከተያዝሁበት፡ ከአሪቱ የሞት ፍዳ፡ ማን ባዳነኝ! በጌታችን ኢየሱስ መሲሕ፡ እግዚአብሔር ይመስገን፡ እኔማ፡ በልቡዬና በኅሊናዬ፡ ለእግዚአብሔር ሕግ እገዛለሁ፤ በሥጋዬም፡ ለኃጢአት ሕግ እገዛለሁ።" (ሮሜ ፯፥ ፯-፲፩፤ ፳፬-፳፭።)

በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆቿ ዘንድ ጸንቶ የኖረውን፡ የቀድሞውንና እስካኹን፡ በእያንዳንዳቸው ዘንድ፡ ከዚሁ አቋሙ ሳይፋለስ የቀጠለውን ሥርዓት፡ ልጁ ወዳጇ ኢየሱስ መሲሕ፡ እንዴት አድርጎ፡ በገሃድና በግዝፈት ምስክርነቱ እንደገለጠው፡ በዚህ ረገድ የተናገራቸውን ቃሎቹንና ያሳያቸውን ሥራዎቹን ስሚቸው!

እነዚህም፡ በቅድሚያ፡ ከዓሥሩ መለኮታውያት ትእዛዛት መካከል፡ አንዱ የኾነውን፡ "አታመንዝር!"ን የሚመለከት ሲኾን፡ ቀጥሎ ደግሞ፡ "ዝሙት" የሚለውን ቃል እያሉ የሚያጣቅሱ ናቸው። "'አመንዝራነት'፡ ጋብቻን የማፍረስ ኃጢአት ሲኾን፥ 'ዝሙት' ደግሞ፡ ከተፈጥሮ ግዳጅ የተነሣ፡ በጋብቻ ውስጥ፥ ወይም፡ ከጋብቻ ውጭ፡ ከሌላ ጾታ ጋር የሚፈጸም፡ የሩካቤ-ሥጋ ግንኙነት ነው።" በማለት፡ ቀደም ብዬ፡ አውስቼላችሁ የነበረውን የቃላቱን ትርጉም፡ እዚህም ላይ፡ እንደገና ሊታወሱ አግባብ ይኾናል።

<u>በቅድሚያ</u>፡-

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ "የእግዚአብሔር ሥርዓት ነው!" ብለው አምነውበት እየፈጸሙ የኖሩትና የሚኖሩት ጋብቻና የትዳር ኑሮ፡ እንደአዳምና ሔዋን፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እስከሞትና ከዚያም በኋላ፡ ለዘለዓለም በሚጸና አንድነት፡ ህልውናን፡ በሕያውነት መቀጠል ነው።

በዚህ አንጻር፡ "የእስራኤል ልጆች ነን!" የሚሉት፡ አይሁድ እንደሚያደርጉት፡ በተቃራኒነት ያለው አመንዝራነት ግን፡ ይህን፡ እግዚአብሔራዊ ሥርዓት ትተው፡ የተቀደሰውን ጋብቻቸውን፡ ኹለቱም ባልና ሚስት፥ ወይም አንዳቸው፡ በፈለጉ ጊዜ፡ እያፈረሱትና፡ እየለዋወጡት፥ እነርሱም፡ እየተፋቱና ከሌላው ጋር ሌላ ጋብቻን እየመሠረቱ፡ ባለመጽናትና በወረት የሚኖሩበት ሰውኛው ወግ ነው፤

ይኸው፡ ከእግዚአብሔር ሥርዓት፡ የወጣው፡ የጋብቻ ሕጋቸው ብልሹ መኾኑን፡ በግልጽ በማስታወቅ፡ ጌታችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ነቅፎባቸው፡ አመንዝራነት፡ ጋብቻን ማፍረስ መኾኑን፡ እንዲህ በሚለው፡ መለኮታዊ ቃሉ አረጋግጧል፡- "እብለክሙ፡ አነሂ፡ 'ኵሉ ዘይድኅር ብእሲቶ፡ ዘእንበለ ትዘሙ በላዕሌሁ፡ ለሊሁ ረሰያ ዘማ፤ ወእንተሂ ደኅርዋ አውሰበ፡ ዘመወ።

"እኔ ግን፡ እላችኋለሁ! ያለዝሙት ምክንያት፡ ሚስቱን ፈትቶ፡ ሌላዪቱን የሚያገባ ኹሉ፡ ያመነዝራል፤ የተፈታችውንም የሚያገባ፡ ያመነዝራል።" (ማቴ. ፲፱፥ ፫-፲፫።)

ቀጥሎ፡-

"ዝሙት" ደግሞ፡ ከተፈጥሮ ግዳጅ የተነሣ፡ በጋብቻ ውስጥ፥ ወይም፡ ከጋብቻ ውጭ፡ ከሌላ ጾታ ጋር የሚፈጸም፡ የሩካቤ-ሥጋ ግንኙነት በመኾኑ፡ ራስን የሚጎዳና የሚያዋርድ፥ የሌላውን ጾታ መብትና ክብርም የሚነካ፥ እንዲሁም፡ በራሱ፡ በአድራጊው ዘንድ፡ በሥጋ፡ እንደጥፋት፥ በነፍስም፡ እንደኃጢአት የሚቆጠር ኾኖ ተገኝቶ፡ ይቅርታ የሚያስጠይቅና ንስሓ የሚያስገባ ካልኾነ በቀር፡ በእኛ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ እንደአመንዝራነት ኃጢአት የሚታይ አለመኾኑን፡ ለወንዶችም፥ ለሴቶችም የተነገሩ፡ እንዲህ የሚሉት፡ የልጇ የወዳጇ የኢየሱስ መሲሕ ቃላትና የተፈጸሙ ድርጊቶቹ እያረጋገጡ ያስረዱ ችኋል፡-

**፩. "ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ፡- 'ሑሪኬ ጸውዒ ምተኪ! ወንዒ ዝየ።' ወአውሥአቶ ይእቲ ብእሲት፤ ወትቤሎ፡- 'አልብየ ምት።' ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ፡- 'ሠናየ ትቤሊ! ‹አልብየ ምት!› ቀዲሙሰ፡ ኃምስቱ ዕደው፡ ነበሩ ምስሌኪ፤ ወይእዜሰ፡ ዘሀሎ ምስሌኪ፡ ኢኮነ ምተኪ፤ ወዘንተሰ፡ አማነ፡ ትበሊ። ወትቤሎ፡ ይእቲ ብእሲት፡- 'እግዚእየ! እሬእየከ፡ ከመ ነቢይ አንተ። ...ነአምር፡ ከመ ይመጽእ ማስያስ፡ ዘይብልዎ፡ ‹ክርስቶስ!›፤ ወአመ መጽአ ውእቱ፡ ይነግረነ ኵሎ።' ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ፡- 'አነ ውእቱ፡ ዘእትናገረኪ።'"**

**"ጌታችን ኢየሱስ፡ ሴቲቱን፡- 'ኺጂና ባልሽን ጥሪው! ወደዚህም፡ ይዘሽው ነይ!' አላት። እርሷም፡- 'ባል የለኝም።' ብላ መለሰችለት። ጌታችን ኢየሱስም፡ '‹ባል፡ የለኝም!›' በማለትሽ፡ መልካም ተናገርሽ። ከእርሱ በፊት ግን፡ አምስት ወንዶች፡ ዐብረውሽ ነበሩ፤ አኹን፡ ከአንቺ ጋር ዐብሮሽ ያለው፡ አዎን! ባልሽ አይደለም፤ በዚህስ፡ እውነትን ተናገርሽ።' አላት። ይህችም ሴት፡ 'ጌታዬ ሆይ! አንተ፡ ነቢይ እንደኾንህ፡ አይሃለሁ። ...‹ክርስቶስ!› የሚሉት መሲሕ እንደሚመጣ እናውቃለን፤ እርሱ፡ በሚመጣበት ጊዜ፡ ኹሉን ይነግረናል።' አለችው። "ጌታችን ኢየሱስም፡ 'የማናግርሽ፡ እርሱ፡ እኔ ነኝ!' አላት።"**

ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሲሕ፡ ውኃ፡ ከጕድጓድ ልትቀዳ፡ በቀትር ጊዜ ከመጣች፡ ከአንዲት፡ የሰማርያ ገጠር ሴት ጋር ባደረገው፡ በዚህ የንግግር ልውውጥ ጊዜ፡ በዝሙት የተሞላ የገመና ኑሮዋን፡ እንደኃጢአት፥ እርሷንና ደባሎቿን ወንዶችም፡ አንዳቸውንም፡ እንደኃጢአተኞች ቆጥሮ፡ "ኃጢአታችሁ ተሰርዮላችኋል! ዳግመኛም እንዳትበድሉ!" ብሎ የተናገረው ቃል አለመኖሩን፡ በማስተዋል መመልከቱ የሚያስፈልጋችሁ ይኾናል።

በአንድ ወገን፡ የወንድን፡ የበላይነትና ገዢነት፥ ማን-አለብኝነትና ትምክህተኝነት፥ አምባ-ገነንነትና አጥቂነት፣ በሌላው ወገን ደግሞ፡ የሴትን፡ የበታችነትና ተገዢነት፥ ምስኪንነትና ውርደት፥ ዓቅመ-ቢስነትና ተጠቂነት፡ በገሃድና በቀላሉ ለመመልከት፡ እኒያ ስድስት ወንዶች፡ እንዲህ፡ በአንዲት ሴት ላይ የፈጸሙት፡ ይህን የመሰለው፡ ተከታታይና የተያያዘ፡ የቍጥጥርና የግፍ ርብርቦሽ፡ በቂ ማስረጃ ይኾናችኋል።

ለመኾኑ፡ ይህች ሴት፡ እንዲህ ባለ ግልሙትና የምትኖር ስትኾን፡ እንዴት፡ ከልጇ ከወዳጇ ኢየሱስ መሲሕ ጋር፡ ለብቻዋ ተገኝታ፡ ለመነጋገር የበቃችና የተመረጠች ኾነች? ክፉ ሰዎች እንደሚያስቧት ሳትኾን፡ የዚህችን ሴት፡ እውነተኛ ማንነት፡ በትክክል ለመረዳት፥ አዎን! የእኒህ ወንዶች፡ ከባድ በደል የደረሰውና የተፈጸመው፡ በምን ዓይነቷ ሴት ላይ እንደኾነ ለማወቅ ትችሉ ዘንድ፡ እስኪ፡ በዚያ፡ በልጇ በወዳጇ በኢየሱስ መሲሕ ቃል ውስጥ ተካትቶ የተነገረውን፡ ዐቢይ መልእክት ስሙት!

ይኸውም፡ እርሱ፡ ቀደም ብሎ፡ ለአይሁድ ሊቃነ ካህናት፡ በቤተ-መቅደስ፥ ወይም፡ ለደቀ-መዛሙርቱም እንኳ፡ በቤት፥ ወይም፡ በገለልታ ያላስተማረውን፥ እርሱው ራሱ፡ "እስመ እግዚአብሔር፡ መንፈስ ውእቱ፤ ወእለሂ ይሰግዱ ሎቱ፡ በመንፈስ፥ ወበጽድቅ፡ ሀለዎሙ፡ ይስግዱ ሎቱ።"

"እግዚአብሔር፡ መንፈስ ስለኾነ፡ የሚያመልኩት፡ በመንፈስና በእውነት ሊያመልኩት ያስፈልጋቸዋል!" ሲል የተናገረውን፡ ታላቁን የአምልኮ ምሥጢር የያዘውን፡ መለኮታዊ እውነት፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ ገልጦ የነገራት፡ በሳምራዊትነቷ፡ በአይሁድ ዘንድ እጅግ ለተናቀችው፡ ለዚችው ተራ ሴት በመኾኑ፡ ይህች ሴት፡ በእኛ በእግዚአብሔር ዘንድ ያላትን፡ የብቅዓት ደረጃ፡ በማስተዋል መመልከቱ የሚሳናችሁ አይኾንም።

፪. "ወአምጽኡ ኀበ እግዚእ ኢየሱስ፡ ጸሓፍት ወፈሪሳውያን፡ ብእሲተ እስርተ፣ እንተ ተረክበት በዝሙት፤ ወአብእዋ ውስጠ፤ ወአቀምዋ፡ ቅድመ እግዚእ ኢየሱስ። ወይቤልዎ፦ 'ኦ ሊቅ! ረከብናሃ፡ ለዛቲ ብእሲት፡ እንዘ ትኤብስ በዝሙት። ወበሕግነሰ፡ ሠርዐ ሙሴ፡ ከመ ትትወገር በእብን፤ ወአንተሰ፡ እንከ፡ ምንተ ትብል፡ በእንቲአሃ፡ እስመ ናሁ፡ ተረክበት በዝሙት?' ... አንሥአ እግዚእ ኢየሱስ አዕይንቲሁ፤ ወነጸረ ኀቤሆሙ፤ ወይቤሎሙ፦ 'ዘአልቦ ኃጢአት እምኔክሙ፣ ቀዲሙ፡ ለይገራ በእብን። ...ወሰሚያሙ እሙንቱ፡ ዘንተ ዘለፋ፡ በለብዎ፤ አኀዙ፣ ይሑሩ፡ በበአሓዱ፣ እስከወጽኡ ሊቃውንቲሆሙ፡ እምቀዳሚ፡ እስከደኃሪ። ወተርፈ እግዚእ ኢየሱስ፡ ባሕቲቶ፤ ወይእቲኒ ብእሲት፡ ትቀውም ውስጠ። ወአንሥአ እግዚእ ኢየሱስ አዕይንቲሁ፤ ወነጸረ ኀቤሃ፤ ወይቤላ፦ 'ኦ ብእሲቶ! አይቴ ሀለዉ፡ እለ ይኴንኑኪ?' አውሥአት፤ ወትቤሎ፦ 'አልቦ ዘእሬኢ፡ እግዚእየ!' ወይቤላ እግዚእ ኢየሱስ፡ አነሂ፡ አልቦ ዘእኴንነኪ፤ ሑሪ! እትዊ በሰላም! ወእምዝ ዳግመ ኢተአብሲ።

"የአይሁድ ጸሓፍት ፈሪሳውያን፡ በዝሙት የተያዘች፡ እስረኛ ሴትን፡ ወደጌታችን ኢየሱስ አመጡ፤ወደውስጥም አገቧት፤ በጌታችን ኢየሱስም ፊት አቆሟት። አሉትም፦ 'ይህችን ሴት፡ ስትሴስን አገኘናት። በሕጋችንም፡ በድንጋይ እንድትወገር፡ ሙሴ፡ ደንግጎልናል። ዝሙት ስትፈጽም ተገኝታለችና፡ እንኪያ፡ አንተሳ፡ ስለእርሷ፡ ምን ትላለህ?' ጌታችን ኢየሱስም፡ ዓይኖቹን አቅንቶ፡ ወደእነርሱ ተመለከተ፤ አላቸውም፦ 'ከእናንተ መካከል፡ ኃጢአት የሌለበት፡ እርሱ፡ አስቀድሞ፡ በድንጋይ ይውገራት!'

"...እነርሱም፡ ይህን የዘለፋ ቃል ሲሰሙ፡ ነገሩ ተሰማቸውና፡ ከፊተኛው፡ እስከኋለኛው፥ እስከታላላቆቻቸውም ድረስ፡ ያሉት ኹሉ፡ አንድ በአንድ እየተመለሱ፡ ወጥተው መኼድ ጀመሩ። ጌታችን ኢየሱስም፡ ብቻውን ቀረ፤ ያቺም ሴት፡ በውስጥ ቆማ ነበረ። ጌታችን ኢየሱስም ቀና ብሎ፡ ወደእርሷ እየተመለከተ፡- 'አንቺ ሴት! ከሳሾችሽ የት አሉ?' አላት። እርሷም መልሳ፡- 'ጌታዬ! የማየው፡ አንድም የለም!' አለችው። <u>ጌታችን ኢየሱስም፡ 'እኔም፡ ምንም የምፈርድብሽ የለም! ኺጂ! በሰላም፡ ወደቤትሽ ተመለሺ!</u> ከዚህ በኋላም፡ ዳግመኛ አትበድዪ!' አላት። (ዮሓ. ፰፥ ፫-፲፩።)

ልጆቼ! ሰብአውያን ፍጡሮቼም! ሰው የኾነው የባሕርይ አምላክና ዘለዓለማዊው ዳኛ፡ ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሲሕ፡ ያደረገውን፡ ይኸው አያችሁ አይደለምን? የተናገረውንም፡ ይኸው ሰማችሁ አይደለምን? አዎን! አያችሁ፤ ሰማችሁም። ዝሙትን በሚመለከት ግን፡ ምንም ዓይነት የፍርድ ቃሉን፥ ብያኔውንም አላያችሁም፤ አልሰማችሁምም፤ ኹሉም የሉምና። በዝሙት ምክንያት፡ ለውግረት በቀረበችው ተጠቂና ተከሳሽ ሴት ዘንድ ብቻ ሳይኾን፡ ሊወግሯት ባቀረቧት፡ በራሳቸው፡ በአጥቂዎቿና በከሳሾቿ፡ ዘማውያን ወንዶች ዘንድም እንኳ፡ የኃጢአተኝነት ፍርድ እንዳልተሰጠ፡ "ዘአልቦ ኃጢአት እምኔክሙ፤ ቀዲሙ፡ ለይገራ በእብን።

"ከእናንተ መካከል፡ ኃጢአት የሌለበት፡ እርሱ፡ አስቀድሞ፡ በድንጋይ ይውገራት!"

ደግሞም፡ "<u>አነሂ፡ አልቦ ዘእኴንነኪ፤ ሑሪ! እትዊ በሰላም!</u>

"<u>እኔም፡ ምንም የምፈርድብሽ የለም! ኺጂ! በሰላም፡ ወደቤትሽ ተመለሺ!</u> ከሚለው አምላካዊ ቃል በቀር፡ ሌላ የተሰማ፣ የኃጢአተኛነትና የኃጢአተኛነቱ ኵነኔ፡ ከቶ የለም።

አዎን! ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሲሕ፡ በሰዎች ዘንድ፡ "የዝሙት ኃጢአትን ፈጽማለች!" ተብላ፡ ተይዛና ተከሳ፥ በድንጋይ ተወግራ ልትገደል ተፈርዶባት፡ የሞት ፍርዱ ሊፈጸምባት የቀረበችውንም ሴት፥ ደግሞም፡ ከእርሷ ጋር፡ ያንኑ፡ የዝሙቱን ኃጢአት የፈጸመውን ወንድ፥ እንዲሁም፡ ይህንኑ ተመሳሳዩን የዝሙት ኃጢአት፡ እየራሳቸው የፈጸሙ ኾነው እያሉ፡ ነገር ግን፡ እንዳልፈጸሙ ንጹሓን ቀርበው፡ ሴቲቱን ይወግሩ ዘንድ፡ ድንጋያቸውን ሊወረውሩ የተዘጋጁትንም ወንዶች፡ የኹሉንም፡ የዝሙት ኃጢአት አላየም፤ አልተመለከተም፤ አልያዘም፤ በዚሁ ኃጢአታቸው ላይ፡ አንዳችም የፍርድ ኵነኔንም አልሰጠም፤ እንደኃጢአት አልቆጠረባቸውምና። "አለ!" ከተባለም፡ ተወላቸው፥ ይቅርም አላቸው እንጂ።

ተፈጥሮአዊው የጾታ ግዳጅ የሚያስከትለውን፡ የወንድና የሴትን፡ የፊ ቃደኛነት ሩካቤ-ሥጋን [ግብረ-ሥጋን=ወሲብን]፡ "ዝሙት፥ ኃጢአት ነው!" እያሉ፡ ቀድሞም፥ አኹንም፡ በአድራጊዎቹ ላይ፡ በድንጋይ ተወግሮ እስከመሞት የሚያደርስ፡ የቅጣት ፍርድን የሚሰጡ ኹሉ፡ የዲያብሎስ ጭፍሮች የኾኑ፡ ክፉዎች ሰዎች ናቸው።

ከእነዚህም መካከል፡ እንደእነዚሁ እንደአይሁድ ካህናት ኹሉ፡ በእኛ ስም የተቋቋሙ የሃይማኖት ድርጅቶች፥ "ክርስቲያኖች ነን!" የምትሉት ጭምር መገኘታችሁ፡ ለእየራሳችሁ ሳያስገርማችሁ የሚቀር አይኾንም።

እዚህ ላይ፡ አኹንም፡ ሳይወሳ የማይታለፈው ቍም-ነገር፡ በከፍተኛ መጠን የተለያየው፡ በአንደኛው በኩል ያለው፡ የወንድ ማንነትና ምንነት፡ የልህቀት ልዕልና፥ በሌላው በኩል ደግሞ ያለው፡ የሴት ማንነትና ምንነት፡ የውርደት ዝቅጠት፡ በጉልህ የተንጸባረቀበት ኹኔታ ነው። ይኸውም፡ ዝሙቱን የፈጸሙት፡ አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት ሲኾኑ፡ ለክሱና ለውግረቱ፡ ሰለባ ኾና የቀረበችው ግን፡ ሴቲቱ ብቻ ናት፤ ለምን? ዋናው የዝሙቱ ፈላጊና ወጣኝ፥ ቢያስፈልግም፡ አስገዳጁና ፈጻሚው፡ ወንዱ አይደለምን? አዎን! ነው። ታዲያ! እርሱ፡ ለምን፡ ከእርሷ ጋር አልቀረበም? እርሱ፡ ወንድ ነዋ! እርሷ ደግሞ፡ ሴት ነቻ! ስለዚህ፡ ለክሱና ለውግረቱ፡ መቅረብ ያለባት፡ እርሷ ብቻ ነች። እንዲህ ነው፡ የሰዎች ሕግ! ይህ ነው፡ የሰዎች ዳኝነት!

እውነተኛው ዳኛ፡ ልጁ ወዳጁ ኢየሱስ መሲሕ፡ በእውነተኛው መለኮታዊ ሕጉና ዳኝነቱ፡ "ዘአልቦ ኃጢአት እምኔክሙ፤ ቀዲሙ፡ ለይገራ በእብን።

"ከእናንተ መካከል፡ ኃጢአት የሌለበት፡ እርሱ፡ አስቀድሞ፡ በድንጋይ ይውገራት!" ባለ ጊዜ፡ ይህንኑ የግፍ በደል የፈጸመባት፡ ያው ወንድ፡ ተመልሶና ከሌሎቹ መሰሎቹ ወንዶች ጋር፡ በግብረ-ዐበርነት መጥቶ ሊወግራት፡ በእጁ ድንጋዩን ጨብጦ ይዞ፡ በመካከላቸው ኾኖ ይጠባበቅ የነበረ መኾኑን ስላወቀ እንደኾነ፡ መናገር የሚችል፡ ከእኔ፡ ከእናቱና ከአባቱ፥ ከመንፈስ-ቅዱስ ሕይወቱም በቀር፡ ሌላ ማን ይኖራል? የለም።

ከዚህ የተነሣ፡ ወንዱም ኾነ ሴቷ፡ ጋብቻን አጽንተው እያሉ፡ በመካከላቸው፡ ከጋብቻ ውጪ የተደረገ ሩካቤ ሥጋ ካለ፡ ያ ዝሙት ሲኾን፡ ራሱን ጋብቻን ማፍረስ ግን፡ "አታመንዝር!" ያለውን፡ ከእኛ፡ ከአሥሩ፡ የእግዚአብሔር ቋሚ ቃላት፡ አንዱ የኾነውን፡ መተላለፍ እንደኾነ፡ ከላይ የተጠቀሰው፡ የልጁ የወዳጁ የኢየሱስ መሲሕ ቃል፡ በሚበቃ ያስረዳችኋል።

እንግዲህ፡ ተፈጥሮአዊው የጾታ ሥርዓት የሚጠይቀው፡ ይህ፡ የወንድና የሴት፡ የጋብቻና የፈቃደኛነት ግንኙነት፥ የፍቅርና የፍትወተ ሥጋ ጽንሰ-ሓሳብና ስሜቱ፥ የሩካቤ-ሥጋ [ግብረ-ሥጋ=ወሲብ] ግብሩና አፈጻጸሙ፥ ፍሬያማ ውጤቱም ኹሉ፥ ከእነዚያ፡"ኀፍረተ-ሥጋ" በሚል፡ የነውር ስያሜ እንዲዋረዱ ከተደረጉት፥ የእነዚሁ አምላካውያት ጸጋዎች ምንጮች ከኾኑት፡ ክቡራትና ቅዱሳት፡ የሰውነት አባላት ጋር፡ "ዝሙትና ኃጢአት፥ ርኵሰትና መርገም ነው!" ተብሎ፡ በክፉዎች ሰዎች ዘንድ በመፈረጁ፡ ይኸው ፍረጃ፡ በራሳቸው፡ በፈራጆቹ ላይ፡ ምን ዓይነት ያልታሰበ፡ ጠንቀኛ ፍርጃ ኾኖ፡ ያደረገውን፡ በእየራሳችሁ ተመልከቱት!

፩. ቀድሞም ኾነ፥ አኹን፡ በወንዶችና በሴቶች ሰውነት ላይና ውስጥ፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስም፡ የተለያየና ከባድ የኾነ፥ ሊያስወግዱት የማይቻል፡ ረቂቅ፡ የጭንቀትና የሥጋት ቅጣትን አስከተለ፤

፪. ልጆቼንና ሰብአውያን ፍጡሮቻችንን፡ ግብረ-ሰዶምን ለመሰለ፡ በወንድና በወንድ፥ በሴትና በሴትም መካከል ለሚካኼድ ኢ-ተፈጥሮአዊና ኢ-እግዚአብሔራዊ ለኾነ፡ ለከንቱ የሙስና [የብልሽት] ህልውና [አኗኗር]፡ ዳረጋቸው።

ይህም ማለት እግዚአብሔራዊዉና ተፈጥሮአዊ የኾነው ፍላጎታቸው፡ "ኃጢአት፥ ርኵሰትና መርገም ነው!" ከተባለ፥ ያን መፈጸም ደግሞ፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስም፡ የተለያየና ከባድ የኾነ የጭንቀትና የሥጋት ቅጣትን የሚያስከትል ነው!" ተብሎ፡ ኹሉም፡ በጠቅላላ ከተከለከለ፡ በእርግጥ፡ ግብረ-ሰዶምን ጨምሮ፡ ሌላው ተዛማጅና ተመሳሳይ ድርጊት ኹሉ፡ በግድ እንዲፈጠር ማድረጉ እንደማይቀር፡ በኹላችሁም ዘንድ ይታወቃል።

ይህን እውነታ ለማስረዳት፡ ተፈጥሮአዊና ልማዳዊ የኾነውን መብልንና መጠጥን፡ ለማስረጃነት፡ በቀላሉ መጥቀስ ይቻላል። ይኸውም፡ ማንም ሕያው የኾነ ሥጋዊ ፍጡር፥ ሰው ጭምር፡ በልቶና ጠጥቶ፡ የማይጸዳዳ ሊኖር እንደማይችል ኹሉ፡ ይህም፡ በወንድና በሴት ሩካቤ-ሥጋ የሚፈጸመውን፡ የመውለድና የመዋለድ የተፈጥሮ ግዳጅ፡ በምንም መንገድ መግታቱ ጨርሶ የማይቻል መኾኑ ነው።

እዚህ ላይ፡ በእነዚሁ፡ በክፉዎቹ ሰዎች አስተሳሰብና ድርጊት፡ በዚህ ረገድ፡ ለደረሰውና እየቀጠለ ላለው፡ ለዚህ ተፃራሪ ዘመቻ፡ በእኛ፡ በእግዚአብሔር በኩል የተደረገውን ቸርነት በሚመለከት፡ ይኸው፡ አኹን፡ እኔ፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ አንሥቼ የማናግራችሁ፡ አንድ ቍም-ነገር አለ፤ ይኼንንም፡ እናንተ ኹላችሁ፡ ከባሕርያችን ከፍለን የሰጠናችሁ፡ ያ መንፈሳዊው ኅሊናችሁ፡ አኹንም፡ ገና፡ በውስጣችሁ እየሠራላችሁ የሚገኝ ከኾነ፡ በእርግጥ፡ በእርሱ ተጠቅማችሁ፡ ልትሰሙኝና በማስተዋል አዳምጣችሁት፡ ዛሬ፡ በተግባር ላይ ልታውሉት፡ በእጅጉ የሚገባችሁ ይኾናል። "የማናግራችሁ" ያልሁት ቍም-ነገር፡ ይህ ነው፤ እርሱም፡-

-በአንድ ወገን፡ እኛ እግዚአብሔር፡ ጥንቱኑ፡ በሥነ-ፍጥረታችን፡ በንጽሓ-ባሕርያት ቀድሰንና አሳምረን የሠራነው፡ የሰውነታችሁ የሥጋ አካል፡ ከርኵሰትና ከመርገም፥ ከኃጢአትና ከበደል የነጻ መኾኑ ታውቆ፡ ለሰው ወገን መዋለድና መባዛት፡ 'አስፈላጊዎች ናቸው!' ብለን የሠራናቸው፡ እነዚያ፡ አምላካውያቱ የፍሬ ምንጮችና ጸጋዎች የኾኑት፡ ክቡራትና ቅዱሳት፡ የሰውነት አባላት፡ የወንዱ፡ "ዘርና አባለ-ዘር" የሴቷም፡ "የወር አበባና አፈ-ማሕፀን" መባል ሲገባቸው፥

-በሌላው ወገን ግን፡ በክፉ ሰዎች አስተሳሰብና ድርጊት፥ በዲያብሎስ አነቃቂነትና ግብረ-ዐበርነትም፡ "የለም! ይኸው፡ የሰውነታችሁ የሥጋ አካል፡ በርኵሰትና በመርገም፥ በኃጢአትና በበደል የተመላ ነው!" ደግሞም፡ "የለም! እነዚያ፡ የወንዱና የሴቷ፡ የሰውነት የዘርና የፍሬ አባላት፡ «ኀፍረተ-ሥጋ» በሚል፡ የነውርና የውርደት ስያሜ ነው! መታወቅ የሚገባቸው!" ከተባለ፣

-በመጨረሻም፡ በዚህ ኹሉ ምክንያት፡ ይህ መዘዝ፡ በእያንዳንዱ ወንድ እና በእያንዳንዷ ሴት ላይ፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስም፡ እንዲህ ያለ፡ የተለያየና ከባድ የኾነ፡ ረቂቅ ጭንቀትንና ሥጋትን፥ ጥፋትንና ቅጣትንም ያስከተለ ኾኖ ከተገኘ፡ "ታዲያ! ለዚህ ጠንቀኛ ክፉ ችግር፡ መፍትሔው፡ ምንድር ነው?" ተብሎ፡ ለዝንተዓለም ሲቀርብ ለኖረው፡ መሠረታዊና ዘለዓለማዊ ጥያቄ፡ ተገቢውንና አስፈላጊውን ዘላቂ መልስ፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ የሰጠንለትና የሰጠንበት መኾኑን እንድትገነዘቡት ማስቻል ይኾናል።

አዎን! ራሳቸው ክፉዎች ሰዎች፥ ከሌላው መንፈሳዊ ክፉ ፍጡር ጋር በመተባበር፡ ለፈለፈሉት፡ ለዚህ ኹሉ፡ መዘዘኛና ጠንቀኛ ችግር፡ ፍጹም መፍትሔና መድኃኒት እንዲኾን፡ ጥንቱኑም፥ ኋላም የሠራነውና የመሠረትነው መለኮታዊ ሥርዓት አለ። ይኸውም:-

<u>ቀዳሚውና ዋናው:-</u> ራሱን የቻለው፡ ጋብቻ ነው።

<u>ኹለተኛውና የመጨረሻው ደግሞ:-</u> እኔ እግዚአብሔር እም እና ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ፡ በለበስነው፡ በኢትዮጵያዋ ድንግል ማርያም እና በኢትዮጵያዊው ኢየሱስ መሲሕ ሰውነት፡ የዛሬ ፪ሺ፰ (ኹለት ሽህ ስምንት) ዓመታት፡ በምድር ላይ፡ ለዲያብሎስና ለጭፍሮቹ፡ ለክፉ ሰዎች፡ ለአንዴና ለዘለዓለም፡ በፍቅር ኃይልና በሰላም ድል ነሺነት የከፈልነው፡ አስፈላጊውና ተገቢው መሥዋዕትነትና ቤዛነት ነው።

ከዚያን ጊዜ ወዲህ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ የወንዶችና የሴቶች ልጆቻችንና ሰብአውያን ፍጡሮቻችን ሕይወትና ህልውና፡ ለዘለዓለም፡ ምንም የማይከፈልበት፥ በፍጹም ነጻነት የሚኖርበት ኾኗል። ያም፡ በእውነተኛ የመንፈስ አምልኳችሁ ኾናችሁ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁና የየግል የንስሓ ምግባራችሁ አማካይነት፡ በእየተቻላችሁና በእየተመቻቻችሁ ጊዜ ኹሉ፡ በእያላችሁበት ቦታ፡ ልትቀበሉት የሚያስፈልጋችሁና የሚገባችሁ፡ ያ፡ <u>የነፍሳችሁና የሥጋችሁ፥ የመንፈሳችሁም ምግብና ማጽጃ፥ መድኃኒትም የኾነው፡ እውኑ "ቅዱስ ቍርባን" ነው።</u>

እንግዴህ፡ ያልነበረውና የሌለው፡ "ዝሙት፥ ኃጢአት፥ ርኵሰት፥ መርገም፥ ዐደፍ-ጉድፍ፥ ኃፍረተ-ሥጋ፥ ሌላው፥ የመሰለው፥ ቍጥሩ የበዛው፥ የጥፋትና የክፋት ስያሜ ኹሉ"፡ በክፉዎች ሰዎችና በዲያብሎስ ዘንድ፡ "አለ!" ተብሎ፡ በምትሓት እንዲኖር ተደርጎ፥ ሰዎችም፡ በእየራሳቸው ፈልገውትና ፈቅደውት፡ ለእየራሳቸው እንዲህ፡ እውን ሊያደርጉት ካስቻሉት ደግሞ፡ ይኸው፡ አኹን፡ እንደተረዳችሁት፡ ይኸው ሰው-ሠራሹ የጠንቅ ግሥንግሥ፡ በቅዱስ ቍርባናችን፡ ለአንዴና ለዘለዓለም፡ ፈጽሞ እንዲደመሰስና እንዲወገድ ተደርጓል።

<u>ለግብረ-ሰዶም መፈጠር፡ ሰባተኛው ጠንቀኛ ምክንያት፡ ይህ መኾኑን አስተውሉት!</u>

## ቅዱሱን ቍርባናችንን በሚመለከት፡ የ"ካህናት" እና የወላጆች እውነተኛ አገልጋይነት፡ ለማን ስለመኾኑ።

ለግብረ-ሰዶም መፈጠር፡ ሰባተኛው ጠንቀኛ ምክንያት የኾነውን፡ ይህንኑ ርእሰ-ነገር በሚመለከት፡ አኹንም፡ ኹላችሁም፡ ለእየራሳችሁ እጅግ ሊያስገርማችሁና ሊያሳዝናችሁ የሚገባ፡ ከዚሁ ጋር የተያያዘ፡ ሌላ ቍም-ነገር ስላለ፡ እርሱን ደግሞ አስከትዬ ልግለጽላችሁ፡- ይኸውም፡ በይፋ፡ የእኛ "ካህናት ነን!" እያሉ፥ ነገር ግን፡ እኛ የማናውቀው ይመስል፡ በሥውር የሌላው፣ የባዕዱ አገልጋዮች ኾነው የተገኙት፡ በተለይ፡ የሕዝቤ ወገኖች የሚያደርጉትን ነው።

የእኒህ ወገኖች ሕፃናት ልጆች፡ ከክርስትና ጥምቀታቸው ጀምረው፡ ነፍስ እስከሚያውቁበት ዕድሜያቸው ድረስ፥ ስለቅዱስ ቍርባን እንዲማሩ እየተደረገም ኾነ ሳይደረግ፡ ቅዱስ ቍርባናችንን፡ ደኅና እየተቀበሉ ይቆዩና፡ ልክ፡ ወንዶቹ፡ ለዘር፥ ሴቶቹም፡ ለወር አበባ መድረሳቸው፡ በወላጆቻቸውና በካህናቱ ዘንድ ሲረጋገጥ፡ መቍረባቸውን እንዲያቆሙ ይደረጋል።

ለምን? ለምንድር ነው፡ መቍረቡን እንዲያቆሙ የሚደረገው? እኛ እግዚአብሔር፡ በመልካችንና ከእኛ እንደአንዳችን፡ በወንድነት፥ ወይም፡ በሴትነት ጾታ፡ በማሕፀን የሚፈጠረውን ሰው እንዲያስገኝ፡ በመለኮታዊው ረቂቅ የሥነ-ተፈጥሮ ሥርዓት፡ በዚያ፡ በወንዱ አብራክ ውስጥ፡ እንዲዘጋጅ ያደረግነው፡ ያ የተቀደሰው ዘር፥ በዚያች፡ በሴቷም፡ ማሕፀን ውስጥ፡ እንዲመነጭ ያደረግነው፡ ያ የተቀደሰው የደም አበባ፡ በእነዚሁ ክፉዎች ካህናትና ወላጆች ዘንድ ብቻ፡ "ኃጢአት ነው" ተብሎ፡ በኃጢአትነት ስለተፈረጀ ብቻ አይደለምን? አዎን ነው።

መልካም! በእነርሱ ዘንድ፡ እውነታው ይህ ከኾነ፡ ታዲያ! ለዚሁ ኃጢአት ማስተስረያ፥ ወይም፡ ማስወገጃ ይኾን ዘንድ አይደለም ወይ፡ ቅዱስ ቍርባናችን፡ በየዕለቱ፡ በእየቤተ-ክርስቲያኑ፡ ያለማቋረጥ፡ በሥርዓተ-ቅዳሴ እየተዘጋጀ፡ "ኃጢአተኞች ናቸው!" ወይም፡ እነርሱ ራሳቸው፡ "ኃጢአተኞች ነን!" የሚሉ ኹሉ እየቀረቡ እንዲቀበሉት የሚታወጀው? ይህ ካልኾነ፡ ለሌላ፡ ለምን ዓላማ ነው?

እውነታው፡ ይህ መኾኑንማ፡ ቅዱሱ ቍርባናችን ተዘጋጅቶ የሚቀርብበትን፡ የቅዳሴ ሥርዓታችሁን፡ ገና በምትጀምሩበት፥ ኋላም፡ በምትጨርሱበት ጊዜያት፡ በመግቢያውና በመዝጊያው ክፍሎቹ ላይ፡ በዚያ ሥርዓት ላይ የተገኘው ሕዝብ፡ በሙሉ፡ ወንዱም፡ ሴቱም፥ ልጁም፡ ሽማግሌውም፡ ኹሉም ዐዳምጦ፡ ሊያደርግ የሚገባውን ይወስን ዘንድ፡ በከፍተኛ ድምፅና በዜማ ስልት፡ በይፋ የምታስሰሙት፡ የዐዋጅ ቃሎቻችሁ፡ በማስረጃነት፡ የሚመሰክሩባችሁ አይደለምን? አዎን! ይመሰክሩባችኋል።

ነገር ግን፡ እነዚህ የዐዋጅ ቃሎች፡ ከሕዝቡ ጆሮዎች ደርሰው እንዳይደመጡ፡ ግብራችሁ፡ አይሁድን ባስመሰላችሁ፡ በእናንተ፡ በካህናቱና በሊቃነ-ካህናቱ ዘንድ፡ ኾነ ተብሎ፡ ከሚፈጸመው ግርግርና ትርምስ ጋር፡ የውጭው የመረዋና የውስጡ የቃጭል ጩኸት ተደማምሮ፡ ሕዝቡ፡ ትርጒማቸው በማይገባው የግእዝ ቋንቋ፡ እየተዜሙ እንዲሰሰሙ ስለሚደረግ፡ ምን እየተባለ እንደኾነ፡ በአንዳቸውም አስቀዳሶች ዘንድ የሚታወቅ፡ ምንም ነገር እንደሌለ፡ ኹላችሁም እንደምትገነዘቡት፥ በዚህ መልኩና ይዘቱም፡ እስካኹን፡ ለዝንተዓለም እየተሠራበት እንደሚገኝ፥ እናንተም ኹላችሁ፡ ተስማምታችሁበት፡ ይኸው፡ አሳፋሪ ኹኔታ እንደቀጠለ የምትመለከቱት ነው።

እኒህን፡ የዐዋጅ ቃሎች፡ የመግቢያውንም፥ የመዝጊያውንም፡ እኒኸውላችሁ! ለትዝብት ያህል፡ ስሟቸው!

የመግቢያው፡- "ሃሌ ሉያ! እመቦ ብእሲ፡ እምእመናን፣ ዘቦአ ቤተ-ክርስቲያን፡ በጊዜ ቅዳሴ፤ ወኢሰምዐ፡ መጻሕፍተ-ቅዱሳት፤ ወኢተዐገሠ፡ እስከይፌጽሙ፡ ጸሎተ ቅዳሴ፤ ወኢተመጠወ፡ እምቊርባን፤ ይሰደድ፡ እምቤተ-ክርስቲያን! እስመ አማሰነ፡ ሕገ-እግዚአብሔር፤ ወአስተሐቀረ ቊመተ፡ ቅድመ ንጉሥ ሰማያዊ፣ ንጉሠ-ሥጋ፥ ወመንፈስ።

"ዓለም ሳይፈጠር የነበርህ! ዓለምንም አሳልፈህ፡ ለዘለዓለም የምትኖር! በቅዳሴ ጊዜ፡ ወደቤተ-ክርስቲያን የገቡ ምእመንና ምእመኒት ቢኖሩ፡ የቅዱሳት መጻሕፍትን መልእክቶች ባያውቁ፥ የቅዳሴውም ጸሎት እስኪፈጸም ባይታገሡ፥ ከቅዱስ ቊርባንም ባይቀበሉ፡ ከቤተ-ክርስቲያን ይለዩ! የእግዚአብሔርን ሥርዓት አፍርሰዋልና፤ የሥጋና የነፍስ፥ የመንፈስም ንጉሥ በኾነው፡ በሰማዩ ንጉሥ ፊት መቆምንም፡ አቃልለዋልና።" የሚል ነው።

የመዝጊያው ደግሞ፡- "ወወሀቦሙ [ኢየሱስ መሲሕ]፡ ለእሊአሁ አርዳኢሁ፤ ወይቤሎሙ፡- 'ንሥኡ! ብልዑ! ዝ ኅብስት! ሥጋየ ውእቱ፡ ለዘበእንቲአከሙ ይትፌተት፡ ለኅድገተ ኃጢአት።' ...ሥጋ ቅዱስ ዘበአማን፣ ዝ ውእቱ፡ ዘእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወመድኃኒነ ኢየሱስ መሲሕ፣ <u>ዘይትወሀብ፡ ለሕይወት፥ ወለመድኃኒት፥ ወለስርየተ-ኃጢአት፤ ለእለ ይነሥኡ እምኔሁ በአሚን።</u>

"መጠዎሙ ለእሊአሁ አርዳኢሁ፤ ወይቤሎሙ፡- 'ንሥኡ! ስትዩ! ዝ ጽዋዕ! ደምየ ውእቱ፡ ለዘበእንቲአከሙ ይትከዐው፡ ለቤዛ ብዙኃን።' ...ደም ክቡር ዘበአማን፣ ዝ ውእቱ፡ ዘእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወመድኃኒነ ኢየሱስ መሲሕ፣ <u>ዘይትወሀብ፡ ለሕይወት፥ ወለመድኃኒት፥ ወለስርየተ-ኃጢአት፤ ለእለ ይትሜጠዉ እምኔሁ በአሚን።"</u>

"[ኢየሱስ መሲሕ]፡ 'ይህ ኅብስት፡ ለኃጢአት ማስተስረያ ይኾናችሁ ዘንድ፡ ስለእናንተ የሚቆራረስ ሥጋዬ ነውና፡ እንካችሁ! ብሉ!' ብሎ፡ ለወገኖቹ ለደቀ-መዛሙርቱ ሰጣቸው። ... በእውነት አምነው፡ ከእርሱ ለሚቀበሉ፡ ሕይወትና መድኃኒት፥ የኃጢአት ማስተስረያም ሊኾን የሚሰጥ፡ የጌታችንና የአምላካችን፥ የመድኃኒታችንም የኢየሱስ መሲሕ ቅዱስ ሥጋ፡ ይህ ነው።

"[ኢየሱስ መሲሕ]፡ 'ይህ ጽዋ፡ ለብዙ ሰዎች፡ ቤዛ ይኾናችሁ ዘንድ፡ ስለእናንተ የሚፈስስ ደሜ ነውና፡ እንካችሁ! ጠጡ!' ብሎ፡ ለወገኖቹ ለደቀ-መዛሙርቱ ሰጣቸው። ... በእውነት አምነው፡ ከእርሱ ለሚቀበሉ፡ ሕይወትና መድኃኒት፥ የኃጢአት ማስተስረያም ሊኾን የሚሰጥ፡ የጌታችንና የአምላካችን፥ የመድኃኒታችንም የኢየሱስ መሲሕ ክቡር ደም፡ ይህ ነው።" (የሓዋ. መጽሓፈ-ቅዳሴ።)

ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሲሕ፡ "አሌ ለክሙ፡ ጸሓፍት ወፈሪሳውያን፡ መደልዋን! እስመ ተዐጽዉ መንግሥተ-ሰማያት፡ ቅድመ ገጹ ለሰብእ፤ አንትሙሂ፡ ኢትበውኡ፤ ወለእለሂ ይበውኡ፡ ትከልእዎሙ በዊአ።"

"እናንት ግብዞች፡ ጸሓፍት ፈሪሳውያውያን! ወዮላችሁ! የእግዚአብሔርን መንግሥት ደጃፍ፡ በሰው ኹሉ ፊት ትዘጋላችሁና፤ እናንተም፡ አትገቡም፤ ሊገቡ የሚፈልጉትንና የሚቻላቸውንም፡ እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ።" ብሎ የወቀሳችሁ፡ እናንት፡ ካህናትና ሊቃነ ካህናት! ስለልጆቻችንና ስለፍጡሮቻችን፡ የነፍስና የሥጋ፥ የመንፈስም፡ ፍጹምና ዘለዓለማዊ ደኅንነት ስትሉ፡ እኒህን፡ የእኛን መለኮታውያት ዐዋጆች፡ መፈጸምና ማስፈጸም ስትችሉና ሲገባችሁ፡ ይህን፡ ለእኛ የገባችሁትን፡ የቅዱሱ ኪዳን ተልእኳችሁንና ግዳጃችሁን አለመፈጸማችሁ ለምንድር ነው? በእርግጥ ትጠየቁበታላችሁ! አዎን! አይቀርም። (ማቴ. ፳፫፥ ፲፬።)

ይህንኑ ቅዱስ ቍርባን በሚመለከት፡ ኹላችሁም፡ "እናውቀዋለን!" እያላችሁ፡ በይፋ ማስመሰል የምትናገሩለት፥ ነገር ግን፡ በእውነት እንደማትሠሩበት፡ በሥውር ያረጋገጣችሁት፡ አንድ ልዩ ግብር አለ፤ ይኸውም፡ የዚህ ቅዱስ ቍርባን የመኖሩና በየጊዜው እየተዘጋጀ የመቅረቡ አስፈላጊነት ዓላማ፡ ለአንድ ኃጢአተኛ፡ ለነፍሱም፥ ለሥጋውም፥ ለመንፈሱም፡ በእኛ በፈጣሪው፡ ቸርነትና ልግሥና፥ መሥዋዕትነትና ቤዛነት ተገኝተው የተሰጡትን፡ ሦስቱን መለኮታውያት፡ የጸጋ ኃይላት፡ እንዲያው በነጻ ማበርከት መኾኑን ማስተማመን ነው።

"ሦስቱ መለኮታውያት፡ የጸጋ ኃይላት" የተባሉት፡ "ምግብ፥ ስርየትና መድኃኒት"፥ ወይም፡ "ማሕየዊ (ሕይወት-ሰጪነት)፥ መንጽሒ (የማንጻት ኃይል)፤ መጽንዒ (ጤንነት የማስገኘት ዓቅም) ናቸው። "ሦስቱ አካላትና ባሕርያት" የተባሉትም፡ የኃጢአተኛውን ፍጹምና ሙሉ ሰውነት የሚያስገኙት፡ ነፍስና ሥጋ፥ መንፈስም ናቸው።

እነዚህ፡ ሦስቱ መለኮታውያት፡ የጸጋ ኃይላት፡ ሦስቱንም አካላትና ባሕርያት፡ ማደሪያቸው አድርገው፡ ይኸው ቅዱስ ቍርባን፡ አንደኛ፦ ለዘለዓለም ሕይወት በሚያኖር፡ ረቂቅ ምግብነቱ፥ ኹለተኛ፦ ከረቂቅ ዕድፍ፡ ፈጽሞ በማጽዳትና ኃጢኣትን በማስተስረይ ኃይሉ፥ ሦስተኛ፦ በፍጹም መድኃኒትነቱ፡ ማናቸውንም ደዌ የመፈወስ ፍቱንነቱን፡ ለረሃብተኛው፥ ለኃጢኣተኛውና ለበሽተኛው በማቀዳጀት፡ ሰብኣዊዉን ፍጡራችንን፡ ኹለንተናውን አድሰው፡ ለፍጹሙ እግዚአብሔራዊ መልካም ሕይወት ያበቁታል።

"ሥጋ ወደሙ" የሚባለውን፡ ይህንኑስ ቅዱስ ቍርባን፡ ልጄ ወዳጄ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ለእነዚሁ ለኃጢኣተኞች የሰጠው፡ **"ሕሙማን ይፈቅድዎ፡ ለዐቃቤ ሥራይ፤ ወአኮ ጥዑያን።**

**"ባለመድኃኒት የሚያስፈልጋቸው፡ በሽተኞች እንጂ፡ ጤነኞች አይደሉም፤"** የሚለውን፡ የማያነቃንቅ፥ ጽኑ ማስረጃን በማስቀደም፡ **"ኢመጻእኩ፡ እጸውእ ጻድቃነ፤ አላ፡ ኃጥኣነ ለንስሓ።**

**"እኔም የመጣሁት፡ ኃጢኣተኞችን፡ ወደንስሓ ልጠራ እንጂ፡ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም።"** በሚለው፡ ግልጽና ቍርጥ፥ አጭርና ቀጥተኛ በኾነ፡ መለኮታዊ ቃሉ፡ "ለምን ከኃጢኣተኞች ጋር ዐብሮ ይነጋገራል፥ ይውላል፥ ይበላል፥ ይጠጣልስ?" ብለው፡ ለተቃወሙት፡ ለቀደሙትና ለዛሬዎቹ፥ ለወደፊቶቹም፡ የሰጠው መልስ ነው። (ማቴ. ፱፥ ፲፫-፲፬።)

ለመኾኑ ቤተ-ክርስቲያን፡ በያለበት፡ በብዛት እየታነጸና እየተደራጀ፥ ይህን ያህል የካህናትና የቀሳውስት፥ የመነኮሳትና የጳጳሳትም ቍጥር በርክቶ የሚርመሰመሰው፡ ለምንድር ነው? በመሠረቱ፡ ቅዱሱ ቍርባንን፡ አዘጋጅቶ ለማቅረብ ብቻ አይደለምን? ቅዱስ ቍርባንስ እየተዘጋጀ የሚቀርበው ለምንድር ነው? አንድ ኃጢኣተኛን፥ አንዲት ኃጢኣተኛንም፡ ለቅዱስ ቍርባን ለማብቃት አይደለምን? አዎን! በእርግጥ ነው።

እውነታው ይህ ከኾነ፡ ታዲያ! በዚህ ውሳኔና አሠራር፡ የካህናቱም፡ ክህነት፥ የወላጆቹም፡ ልጅነት፡ የማንና ለማን እንደኾነ፡ በግልጽ ተለይቶ ታወቀ፤ ተረዳ፤ ተረጋገጠም ማለት አይደለምን? አዎን! ነው። ያ የወላጆቹ፡ ልጅነታቸው፥ ያ የካህናቱ፡ ክህነታቸው፡ በይፋ እንደሚታየው፡ ከእኔና ለእኔ፥ ከልጄ ወዳጄ ከኢየሱስ መሲሕና ለእርሱ ሊኾን እንዳልቻለ፡ በዚሁ ተረጋገጠ።

ፍረዱኝ! ልጆቼ! ፍጡሮቼ! ምን በወጣቸው! ምን በበደሉ? ምን ባደረጉ? ምንም በማያውቁት? እኛ ፈጣሪያቸው፡ እንደሠራናቸው ኾነው በተገኙ፡ ተፈርዶባቸው፡ እኔና ልጄ ወዳጄ፡ በመስዋዕትነት ቤዛነታችን ከከፈልነው፡ ከቅዱስ ቍርባናችን፡ "ወግዱ!" ተብለው፡ እንዲህ ይከልከሉ!? እንዲህ ይባረሩ!?

እስኪ፡ ንገሩኝ! በዚህ፡ በእንጭጭና በለጋ ዕድሜያቸው፡ ወዴት ይኺዱ! ከመላው አብያተ-መቅደሶቻችን ሲሳደዱ! አዎን! ወዴት ይማሩ! ይወቁ! ስትከለክሏቸው፥ ስታሳድዷቸውና ስታባርሯቸውም እንኳ፡ ይህን ውሳኔ፥ ይህን ቅጣት፡ ለምን እንደጣላችሁባቸውም እንኳ፡ ምክንያቱን ገልጻችሁ አልነገራችኋቸውም። ወይም፡ ከዚያ በኋላ፡ ምን ማድረግ እንደሚያስፈልጋቸው፥ ማማረጫው፥ ወይም፡ መፍትሔው፡ ምን እንደኾነ አላስታወቃችኋቸውም፤ ፍንጩንም እንኳን፡ አላመላከታችኋቸውም። እንዲያው ዝም ብላችሁ፡ ጠፍ ሜዳ፥ ያም ብቻም አይደለም፡ በረሃ ላይ፥ ምድረ-በዳ ላይ፣ ወስዳችሁ ወረወራችኋቸው፤ ጣላችኋቸው። ለዱር አራዊት ሳይቀር፡ አወይ ልጆቼን! ፍጡሮቼን! አሳልፋችሁ ሰጣችሁብኝ!

አዎን! እናንት ክፉዎች ካህናትና ወላጆች! እነዚህን ልጆቼንና ፍጡሮቼን፡ ኾነ ብላችሁ ወርውራችሁ የጣላችሁበትና አሳልፋችሁ የሰጣችሁበት ጠፍ-ሜዳና ዱር፥ በረሃና ምድረ-በዳም፡ የነማን መፈንጫ መኾኑን ዐውቃችሁ አይደለምን? አዎን! እኒህ፡ ልጆቼንና ፍጡሮቼን፡ ምንም ሳያውቁት፥ ያለፈቃዳቸው፡ ከእኛ እግዚአብሔራዊ ልጅነት፥ ነጋሢነትና ካህንነት መንጥቃችሁ አውጥታችሁ፡ ለዲያብሎስና ለጭፍሮቹ ባዕዳን ባርነትና ተገዢነት፥ ሎሌነትና አገልጋይነት የዳረጋችኋቸው መኾናቸውን፡ በትክክልና በእርግጥ ዐውቃችሁ ነው። እንግዲህ፡ በእነዚህ እልፍ አእላፋት ወንዶችና ሴቶች ልጆቼ፥ ፍጡሮቼም ላይ፡ እንዲህ፡ ለዝንተዓመታት፡ እስከዛሬ ላደረሳችሁት፥ ወደፊትም ለምታደርሱት ጥፋትና ጥቃት፥ ክፋትና ውድቀት፡ እያንዳንዳችሁ፡ በፊታችን ትጠየቁበታላችሁ፤ መልስም ትሰጡበታላችሁ፤ ዋጋችሁንም ትከፈሉበታላችሁ።

እነዚህ፡ በኃጢኣተኛነት ተፈርጀው፡ የትም ተወርውረው የተጣሉ ወንዶችና ሴቶች ልጆቼና ፍጡሮቼ፡ እየራሳቸውን፡ ለጋብቻና ለትዳር፥ ወልደው ለማሳደግም ወግ እያበቁ፥ ሰውነታቸውንም፡ በመንፈስ ቅዱስ ዕውቀት አንጸውና በንስሓ አንጽተው፡ ወዳዘጋጀንላቸው ቅዱስ ቍርባን እያቀረቡ እንዳይቀበሉ፡ ከካህናቱና ከወላጆቹ የማስፈራሪያ መልእክት የተነሣ፡ የማይቻላቸው በመኾኑ፡ ይኸው፡ ግብረ-ሰዶምንና እርሱን የመሰሉት የስሕተትና ጥፋት ድርጊቶች፡ እየተስፋፉና እየተበራከቱ፥ እያደጉና እየተጠናከሩ ለመኼዳቸው ምክንያት ኾኗል።

## በጋብቻ አንጻር፡
## ጃንደረብነት እና ምንዝስና።

ከዚህ ርእሰ-ነገሬ ጋር የተያያዘውና በዚህ ረገድ፡ ልታውቁት የሚገባው፡ ሌላው ዓቢይ ጉዳይ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ፡ ስለጋብቻና ስለጃንደረብነት፥ ስለምንዝስናም ያለውን፡ የእያንዳንዳቸውን እውነተኛ ምንነት፡ በትክክል እንድትገነዘቡት የማድረጉ የዕውቀት በረከቱ ነው።

ከኹሉ አስቀድማችሁ የምታውቁት፥ ልታውቁት የሚገባችሁም እውነት፡ እኛ፡ እግዚአብሔር በመንበረ-ጸባዖት ቅድስት ሥላሴነታችን፡ አርኣያና አምሳያ፥ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስም አካላትና ባሕርያት፥ ከእኛ፡ እንደኹለታችንም በማድረግ፡ በወንድና በሴት መልክና ጾታም ለፈጠርነው፡ ሕያውና ተንቀሳቃሽ ለኾነው፡ ለመላው ፍጥረታችን፡ ለህልውናውና ለሕይወቱ መገለጥና መመሥረት፥ መቆምና መቀጠል፡ የሠራንለት ሥርዓት፡ ጋብቻ ብቻ እንጂ፡ ጃንደረብነት [ስልብነት]፥ ወይም፡ ምንኵስና አይደለም።

ለመኾኑ፡ "ጃንደረባ"፥ ወይም፡ "ምንኵስና" የሚሉት ቃላታችሁ፡ ዘይቤያቸው [ትርጉማቸው] ምንድር ነው? "ጃን-ደረባ" = ስልብ የኾነ፡ የንጉሥ ባለሟልና ባለሥልጣን ማለት ነው። "ምንኵስና"፡ "መነኰሰ"="ሳይሞት በሰሌን ተገነዘ፤ ፍታት ተፈታ [ራሱን፡ በፈቃዱ ገደለ፥ ሞተ]፤ 'ዓለም በቃኝ!' አለ፤ መነነ፤ ገዳም ገባ፤" ከሚለው ዘር የተገኘ ነው። የ"ምንኵስና" ትርጉሙ፡ ይህ ከኾነ፡ ታዲያ፡ "'የልጄ የወዳጄ የኢየሱስ መሲሕ፡ በመስቀል ሞቱና በቤዛነቱ፥ በትንሣኤውና በዕርገቱም፡ ሞትንና የመቃብር መበስበስን፡ ድል ነሥቶ፡ እነዚህን የክፋትና የጥፋት ጠንቆች፡ ከሰው ኹሉ አስወገደ! የዘለዓለም ሕይወት ዘውድንም፡ አቀዳጀው!' የሚባለው፡ የእውን ምሥራች፡ ከንቱ ኾነ!› ሊባል አይደለምን? አዎን! በእርግጥ ሊባል ነው። (ደስታ ተክለ ወልድ፤ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ-ቃላት፤ ገጽ ፫፻፶፱ እና ፯፻፶፫።)

ጃንደረብነትም ቢኾን፡ የኋላ ኋላ፡ በእኛ ዘንድ፡ ለታወቀ መልካም ዓላማና የተቀደሰ ተግባር፡ በእኛው የተፈጥሮ ጥበብ የተከሠተ እንጂ፡ በሰውኛ አሠራር የተጀመረ አይደለም። ይኸውም፡ እኛ እግዚአብሔር፡ የተለየ መልእክታችንን፡ ወደምድራዊው ፍጥረታችንና ሕዝባችን ያደርሱልን ዘንድ፡ ገና በማሕፀን ስንፈጥራቸው፡ መርጠን የምንልካቸውን አገልጋዮች ልጆቻችንን፡ የምናዘጋጃቸው፡ እንዲህ አድርገን፡ በጃንደረብነት ስለኾነ ነው።

ከእነዚህ፡ እናንተ ከምታውቋቸው መካከል፡ ከብሉያቱ፡ ኤልያስን፥ ከሓዲሳቱም፡ ጳውሎስን፡ በአብነት ልጠቅስላችሁ ይቻለኛል። ራሴ፡ በምድር ላይ፡ በአካለ-ሥጋ ስመላለስ ሣለሁ፡ ከራሴ ከልጄ ወዳጄ ኢየሱስ መሲሕ ጋር፡ እንደእርሱ የኾኑልኝን፡ ልጄን፡ መጥምቁ ዮሓንስን፥ ደግሞም፡ ባለምሥራቹንና ባለራእዩን ልጄን፡ ዮሓንስን ሳይቀር፡ በዚህ ጃንደረብነታቸው የተሸለሙና የተጌጡ መኾናቸውን ሳወሳላችሁ ደስ ይለኛል።

በራስ ኾነ፡ በሌላው የሚደረገው ጃንደረብነት [በየራሳቸውና በሰው የሚሰለቡ ቢኖሩ] ግን፡ ውጤቱ፡ ምንጊዜም፡ እንደተፈጥሮአዊው የሠመረ ባይኾንም እንኳ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ ቤተ-ሕዝብ፥ ቤተ-ምልክናና ቤተ-ክህነት ውስጥ፡ ለታማኝነት አደራና ለባለሟልነት ማዕርግ እየታጩ፡ ንጹሕና ቅን አገልግሎታቸውን የሚያበረክቱ ይኾናሉ።

*እንግዲህ፡ ምድራዊዉና ሥጋዊው ሥነ-ፍጥረት፡ ከተከሠተ አንሥቶ፡ በኢትዮጵያ ልጆቹ ዘንድ፡ ከጋብቻ ውጭ የኾነውን፥ ወይም፡ ከዚያ የተረፈውን፥ ብሕትውናንና ድንግልናን ጭምር የሚያካትተውን፡ ኅብረተሰባዊ የኑሮ ክፍተትና ጕድለት፡ ለዝንተዓለም የሸፈነውና የሞላው፡ ይኸው ጃንደረብነት እንጂ፡ ሌላ፡ ዓይነት የህልውና ሥርዓት ከቶ ታይቶም፣ ተሰምቶም አይታወቅም።*

*እግዚአብሔራዊ የኾነውን፡ የእኛን ብቸኛ የጋብቻ ቅዱስ ሥርዓት የሚፃረርና ሊያፈራርስ እየሞከረ ያለ፥ ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሲሕ፡ ያልሠራው፥ ሓዋርያቱም፡ ያላወሱት፥ እንዲያውም፡ በሓልዮ የተቃወሙት፥ (፩ጢሞ. ፫፥ ፩-፲፫። ቲቶ ፩፥ ፭-፱።) ከባዕዱም የመነጨ <u>"ምንኵስና"</u> የሚባል፥ እንግዳ የቅኝ አገዛዝ ልማድ፡ ከእኔና ከልጇ ከወዳጇ ኢየሱስ መሲሕ የምሕረት ዘመን ወዲህ በ፬ (አራት)ኛው ምእት-ዓመተ-ምሕረት፥ ይኸውም፡ የዛሬ ፩ሺ፮፻ (አንድ ሽህ ስድስት መቶ) ዓመታት ግድም፡ በግብፅ ምድረ-በዳ፡ ከግብፃውያን በረኸኞች [ገዳማውያን] ሠርፆ፡ ብቅ አለ።*

*ይህን የጃንደረብነትን ነገር በሚመለከት፥ ከእርሱም ጋር፡ በቀደመው ዘመነ-ብሉይ፡ ኦሪታውያኑ የአይሁድ ሊቃነ-ካህናት፡ በአመንዝራነት ኃጢአታቸው፥ በኋለኛው፡ ዘመነ-ሓዲስ ደግሞ፡ ኦርቶዶክሳውያኑ የግብፅ ገዳማውያን፡ በምንኵስና ጠንቃቸው አማካይነት፡ እግዚአብሔራዊ የኾነውን፡ የእኛን ብቸኛ የጋብቻ ቅዱስ ሥርዓት በመፃረር፡ እንዴት አድርገው፡ ሊያፈራርሱ እንደሞከሩ የሚያስረዳችሁን፡ ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሲሕ የተናገረውንና በኢትዮጵያ ልጆቹ ዘንድ፡ "በእንተ ኪዳን ዘኢይትፈታሕ = የማይፈታው ውል" የሚል ርእስ የተሰጠውን፡ እንዲህ የሚለውን፡ መለኮታዊ ቃሉን፡ እዚህ ላይ እጠቅስላችኋለሁ፡-*

***"ወመጽኡ ኀቤሁ ፈሪሳውያን፡ እንዘ ያሜክርዎ፤ ወይቤልዎ፡- 'ይከውኖሁ ለብእሲ፡ ይድኃር ብእሲቶ፡ በኵሉ፡ ዘአበሰት ሎቱ? ወአውሥአ፤ ወይቤሎሙ፡- 'ኢያንበብክሙኑ፡ ዘውስተ ኦሪት፡ ከመ ዘፈጠሮሙ እግዚአብሔር እምትካት፡ ተባዕተ፥ ወአንስተ ገብሮሙ? በእንተዝ፡ የኀድግ ብእሲ፡ አባሁ፥ ወእሞ፤ ወይተልዋ ለብእሲቱ፤ ወይከውኑ ክልኤሆሙ፡ አሐደ ሥጋ። እንከሰኬ፡ ኢኮኑ ክልኤተ፤ አላ፡ አሐዱ ሥጋ እሙንቱ። ዘእግዚአብሔር አስተፃመረ፣ ሰብእ ኢይፍልጥ!'***

***"ወይቤልዎ፡- 'ለምንት አዘዘ ሙሴ፡ የሀቡ መጽሓፈ ፍልጣን! ወይኅድግዋ!' ወይቤሎሙ፡- 'ሙሴሰ አዘዘክሙ፡ በከመ እከየ ልብክሙ፣ ከመ ትኅድጉ አንስቲያክሙ፤ ወበቀዳሚ ፍጥረትሰ፡ አኮ ከማሁ። እብለክሙ አነሂ፡ 'ኵሉ ዘይድኅር ብእሲቶ፡ ዘእንበለ ትዘሙ በላዕሌሁ፣ ለሊሁ፡ ረሰያ፡ ዘማ፤ ወእንተሂ ደኅርዋ አውሰበ፡ ዘመወ!'***

***"ወይቤልዎ አርዳኢሁ፡- 'እመሰ፡ ከመዝ ውእቱ ሥርዓተ ብእሲ ወብእሲት፡ ኢርቱዕ ያውስቡ!' ወይቤሎሙ፡- 'አኮ ኵሉ ዘይክሎ፡ ለዝንቱ ነገር፡ ዘእንበለ ዳእሙ ዘተውህበ። እስመ ቦ ሕፅዋን፡ እለ ከማሁ ተወልዱ እምከርሠ እሞሙ፤ ወቦ ሕፅዋን፡ እለ ሓፀውዎሙ ሰብእ፤ ወቦ ሕፅዋን፡ እለ ሐፀዉ ርእሶሙ፡ በእንተ መንግሥተ-ሰማያት። ወዘሰ ይክል ተዓግሦ፡ ለይትዓገሥ።'"***

"አይሁድ ፈሪሳውያን፡ ሊፈትኑት፡ ወደእርሱ [ወደኢየሱስ መሲሕ] መጥተው፡ 'ባል፡ ሚስቱ፡ በምታደርስበት በማናቸውም በደል ምክንያት ኹሉ፡ ሊፈታት ይፈቀድለታልን?' ሲሉ ጠየቁትም። እርሱም፡ እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፡- 'እግዚአብሔር፡ ጥንት፡ ከመጀመሪያው፡ ወንድ እና ሴት አድርጎ እንደፈጠራቸው፡ በኦሪት የተጻፈውን አላነበባችሁምን? ስለዚህ፡ ወንድ፡ አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ሚስቱንም ይከተላታል፤ ኹለቱም፡ አንድ ሥጋ ይኾናሉ። ከእንግዴህ ወዲህ፡ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ፡ ኹለት አይደሉም። እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ በጋብቻ ያጣመረውን፡ ሰው አይለየው!'

"እነርሱም፡- 'ታዲያ! ለምን፡ ሙሴ፡ «ባልዬው፡ የፍቺዋን ጽሑፍ ሰጥቶ ያሰናብታት!» ብሎ አዘዘ?' አሉት።

እርሱም አላቸው፡- 'ሙሴማ፡ ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ፡ ይህን ትእዛዝ የሰጣችሁ፡ በየልባችሁ ክፋት ምክንያት ነው። በፍጥረት መጀመሪያ ግን፡ እንዲህ አይደለም። እኔም እላችኋለሁ፡- 'ሚስቱ፡ በላዩ ካልሴሰነችበት በቀር፡ [እርሱም፡ በእርሷ ላይ ካልሴሰነ በቀር] ሊፋቱ አይገባም! አለዚያ፡ እርሱ፡ እርሷን፡ አመንዝራ ያደርጋታል፤ እንዲህ የተፈታችውን ያገባም፡ ራሱን፡ አመንዝራ ያደርጋል። እርሷም፡ እርሱን፡ አመንዝራ ታደርገዋለች፤ እንዲህ የፈታውን ያገባችም፡ ራሷን፡ አመንዝራ ታደርጋለች።'

"ወይቤልዎ አርዳኢሁ፡- 'እመሰ፡ ከመዝ ውእቱ ሥርዓተ ብእሲ ወብእሲት፡ ኢርቱዕ ያውስቡ!' ወይቤሎሙ፡- 'አኮ ኵሉ ዘይክሎ፡ ለዝንቱ ነገር፡ ዘእንበለ ዳእሙ ዘተውህቦ። እስመ ቦ ሕፅዋን፡ እለ ከማሁ ተወልዱ እምከርሠ እሞሙ፤ ወቦ ሕፅዋን፡ እለ ሓፀውዎሙ ሰብእ፤ ወቦ ሕፅዋን፡ እለ ሐፀዉ ርእሶሙ፡ በእንተ መንግሥተ-ሰማያት። ወዘሰ ይክል ተዓግሦ፡ ለይትዓገሥ።'"

"ደቀ-መዛሙርቱም አሉት፡- 'የባልና ሚስት ሥርዓት፡ እንዲህ ከኾነ፡ ጋብቻ፡ በትክክል ሊኖሩት የሚቻል አይደለም።'

"እርሱም አላቸው፡- 'አዎን! ያለጋብቻ፡ ሊኖሩ ይቻላቸው ዘንድ፡ [ከሰማይ] የተሰጣቸው ካልኾኑት በቀር፡ ይህ [የጋብቻ ኑሮ] ነገር፡ ለኹሉ የሚቻል አይደለም። እነርሱም፡ ገና፡ በእናቶቻቸው ማሕፀን ሣሉ፡ ጃንደረቦች ኾነው፡ እንዲህ የሚወለዱ አሉና። አረማዊም የሰለባቸው፡ ጃንደረቦች አሉ፤ ስለመንግሥተ-ሰማያት ሲሉም፡ አባለ-ዘራቸውን ሰልበው፡ እየራሳቸውን፡ ጃንደረባ ያደረጉ አሉ። በዚህ ጃንደረብነት፡ እስከመጨረሻው ጸንቶ ለመኖር የሚችል፡ ይጽና!'" (ማቴ. ፲፱፥ ፫-፲፪።)

ከአዳምና ሔዋን ፍጥረት ጊዜ ጀምሮ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" በተባሉት፡ የኢትዮጵያ ልጆቹ ዘንድ፡ ከጋብቻ ውጭ ያለው፡ የሰብኣዊው ፍጡራችን ህልውና የሚካኼደው፡ በዚሁ ጃንደረብነት ብቻ እንጂ፡ ከቅርብ ምእት-ዓመተ-ምሕረት በፊት በታየው፡ "ምንኵስና" በሚባለው፡ እንግዳና ባዕድ ልማድ አለመኾኑ፡ በዚህ፡ በልጇ በወዳጇ በኢየሱስ መሲሕ ቃል፡ ተረጋግጦ ይታወቃል።

የግብረ-ሰዶም ሰለባዎች የኾኑ ወንዶች፡ በአካለ-ሥጋቸውና በተፈጥሮ ባሕርያቸው፡ የጃንደረብነት ዝንባሌ የሚሰማቸውና የሚያጠቃቸው ኾኖ ከተገኘ፡ እነዚህ ግለሰቦች፡ እግዚአብሔራዊ ለኾነው መልካም ተልእኮ፡ በእኛ መንፈስ ቅዱስ ተመርጠው የተጠሩና የተዘጋጁ ለመኾናቸው ምልክቱ ነውና፡ ራሳቸውም፡ ይህንኑ ዐውቀው፡ እየራሳቸውን፡ ለዚሁ ጸጋና በረከት ሊያበቁ፥ የቅርብ ወገኖቻቸውም፡ ወደዚሁ ግብ ይደርሱላቸው ዘንድ፡ ሊደግፏቸውና ሊያበረታቷቸው ይገባቸዋል።

በዚህ ዓይነት፡ ለጃንደረባነት የበቃ ሰው፡ ግብረ-ሰዶምን ለመሰሉ፡ ኢተፈጥሮአዊና አስነዋሪ ለኾኑ፡ የኃጢአት ተጠቂነት፡ ሰለባ እንዳይኾን፡ በብርቱ መጠንቀቅ ይኖርበታል። ነገር ግን፡ እንዲህ፡ በተፈጥሮው ጃንደረባ ካልኾነ፥ ወይም፡ ሌላው ሰው፡ በጨካኝነት፡ ጃንደረባ ያደረገው [የሰለበው] ካልኾነ፥ ወይም፡ ራሱን፡ በራሱ የአካል ጭካኔ፡ ጃንደረባ ያደረገ [የሰለበ] ካልኾነ በቀር፡ በሙሉ ጤናማነት፡ ከአባለ-ዘሩ ጋር እንዳለ ኾኖ፡ እንደጃንደረባ፥ ወይም፡ "መነኵሴ" መኾን፡ ከቶ አይቻለውም። እንዲህ ያለው ደፋር፡ በኹሉም መልኩና ይዘቱ፡ የግብረ-ሰዶም፡ ምቹ ሰለባ መኾኑ፡ ፈጽሞ አይቀርም። እግዚአብሔራዊዉንና ተፈጥሮአዊዉን የጋብቻ ሥርዓትና የህልውና ግዳጅ፡ ለመቋቋም፡ ዓቅሙ አይኖረውምና። ቀደም ብዬ የጠቀስሁላችሁንም፡ የልጇ የወዳጇን የኢየሱስ መሲሕን ቃል፡ ማስተሓቀር ይኾንበታልና።

በቅዱሱ ኪዳን የተዋሕዶ ሃይማኖታቸውና ምግባራቸው፥ በኢትዮጵያዊው የመልከ-ጼዴቅ ቃል-ኪዳናቸውም ምክንያት፡ በእኔ፡ በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ በነፍስ ወከፍ፡ የእኛ የእግዚአብሔር ልጆችና ነጋሢዎች፥ ካህናትና ዜጎቻችን ኾነው፡ ለ፭ሺ፱፻፰ (ለአምስት ሽህ ዘጠኝ መቶ ስምንት) ዓመታት የኖሩት፡ እያንዳንዳቸው ወንዶቹ ኢትዮጵያውያን እና ሴቶቹ ኢትዮጵያውያት ልጆቼ፡ በኦርቶዶክሶቹ ግብፃውያን ጳጳሳት አማካይነት፡ ምንኩስና ወደእነርሱ እስከመጣበት፡ እስከአራተኛው ምእተ-ዓመተ-ምሕረት ድረስ፡ ምንኵስና፡ ፈጽሞ አላስፈለጋቸውም። ይህ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታቸው፡ ከምንኵስናም፥ ከይሁዲነትም፥ ከኦርቶዶክሳዊነትም ይልቅ፡ የሚቀድምና የሚበልጥ፥ የተወደደና የተከበረ፥ የተቀደሰና የጸደቀ፥ አስቀድሞ፡ ለ"እግዚአብሔር ልጅነት"፥ ቀጥሎም፡ ለ"ኢትዮጵያ ልጅነት" ያበቃቸው ስለኾነ ነው።

"ምንኵስና" ግን፡ "ዓመተ-ምሕረት" የተባለው፡ የአዲስ ኪዳን የክርስትና ዘመን መግባቱ ከታወጀ፡ ከአራት መቶ ዓመታት ያህል በኋላ፡ በርስት ጕልቴ፡ ምድረ-ኢትዮጵያ ላይና በቃል ኪዳን ሕዝቤ መካከል እንዲተከል የተደረገ፡ የክፋትና የጥፋት ጠንቅ ነው። ለምን፡ ይህ ተደረገ? በእርግጥ፡ ለምን፡ እንዲህ፡ እንዲተከል እንደተደረገ፡ አጭርና ቍርጥ የኾነ፡ ቀጥተኛና ግልጽ መልስ ያስፈልገዋል።

አዎን! መልሱ፡- "ዲያብሎስና የእኔ ያልኾኑት፡ ጭፍሮቹ፡ ክፉዎቹ ሰዎች፡ ያው፡ በዚህና ባለፉትም ዐዋጆቼ እንዳሳወቅኋችሁ፥ አኹንም፡ በየዓይኖቻችሁ በገሃድ እንደምታዩት፡ አይኾንላቸውም እንጂ፡ የሚኾንላቸው ቢኾን ኖሮ፡ ይኸው፡ የተቀደሰችውን ምድሬንና የተባረኩትን ልጆቼን፡ በሙሉ አጠቃልለው፡ ለእርሱ፡ ለዲያብሎስና ለሠራዊቱ ርኩሳን መናፍስትና ለክፉዎቹ ሰዎች አሳልፈው በመስጠት፡ ለዝንተዓለም የጀመሩትን ረቂቅና ግዙፍ ዘመቻ፡ በድል ለማጠናቀቅ ነው!" የሚል ይኾናል።

ታዲያ! ልጆቼና ፍጡሮቼ! ይህ የክፉው ዘመቻ ጥቃት፡ እንኳንስ በድል ሊጠናቀቅ፡ ራሱ፡ የዘመቻው አበጋዝ ዲያብሎስና ሠራዊቱ፡ ዕድሜ የሚያገኙ ይመስሏችኋልን? የለም! አይምሰላችሁ! ኹሉም፡ ፈጽመው ተደምስሰው እንደሚጠፉ እንጂ፡ አንዳቸውም እንደማይቀሩ ዕወቁት! ትዕግሥታችንም እኮ፡ "ብዙዎችን፡ ለንስሓ እናብቃ!" ብለን መኾኑን አስተውሉት! ዲያብሎስንም፡ እንደተስፋ ቃላችን፡ የሺህኛው ዓመት ማብቂያ በነበረው፡ በኹለት ሽህኛው ዓመተ-ምሕረት መባቻ ላይ፡ ከጥልቅ እሥራቱ እንዲፈታ ያደረግንበትን ቸርነታችንንም አትዘንጉት!

"በድል ማጠናቀቅ" የሚባለው ነገራቸው፡ ከቶ ምንድር ነው? የምን ድል? ድሉማ፡ የዛሬ ኹለት ሽህ ስምንት ዓመታት፡ በእኔና በልጇ በወዳጇ በኢየሱስ መሲሕ ትንሣኤና ዕርገት፥ በርደተ-መንፈስ ቅዱስም፡ ለአንዴና ለዘለዓለም ተጠናቅቆ ያበቃ አይደለምን? አዎን! ተጠናቅቆ አብቅቷል።

ካለፉት ዐዋጆቼ፡ በአንደኛው አማካይነት የተላለፈው፡ ያ፡ የቀደመው ቃሌ፡ ያብራራላችሁ እኮ፡ በመላዋ ዓለም በሰፈነችው፥ በእኔና በልጇ በወዳጇ በኢየሱስ መሲሕ፡ የኪዳነ-ምሕረት ደመ-ማኅተም ጸንታ፡ በመልካም በመቀጠል ላይ ባለችው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ላይ፡ እነዚሁ ግብፃውያን መነኮሳት፡ የጠንቅ ምክንያት ኾነው፡ ከሌሎች መሰል-ግብረ-ዐበሮቻቸው ጋር ሊያካኼዱ የወጠኑትን፡ የጥፋት ዘመቻ ለማፈራረስ የተመዘዘውንና እስካኹን ወደዐፎቱ ያልተመለሰውን፡ የእስልምና ሰይፍ እንደነበረ ታስታውሱታላችሁ።

*"ምንዥስና"*፡ የእኛን እግዚአብሔራዊ የጋብቻና የመዋለድ፥ የትዳርና የኅብረተሰብ ህልውና ሥርዓት፡ ከመሠረቱ ማቃወስና ከአቋሙም ማናጋት ብቻ ሳይኾን፡ ከዚህ ያላነሰ፡ ታላቅ ጠንቅን፡ በመላው ሰብአዊው ፍጡራችን ሕይወት ላይ ጭምር፡ ማስከተሉ እዚህ ላይ፡ በከፍተኛ ትኵረት ሊዘከር ይገባዋል።

ይኸውም፡ በሦስቱ የነፍስና የሥጋ፥ የመንፈስም አካላትና ባሕርያት የተፈጠረ፡ የወንድ ኾነ የሴት ሰውነት፡ የተፈጥሮ ፍላጎቱንና ግዳጁን ከመፈጸም፡ በምንም መንገድ ሊከለከል ቀርቶ፡ ሊገታ፡ ከቶ የማይችል ሲኾን፡ ነገር ግን፡ "ይቻላል!" ተብሎ በሚሞከርበት ጊዜ፡ በዚያ ሰውነት፡ ነፍስና ሥጋ፥ መንፈስም ውስጥ፡ የኀልዮ [የአስተሳሰብ]፥ የነቢብ [የአነጋገር] እና የገቢር [የአደራረግ] ነውጥና ቀውስ መምጣቱ፡ ፈጽሞ እንደማይቀር እሙን ነው።

ብዙውን ጊዜ፡ በምንኵስና ሕይወት ውስጥ በሚገኙ ግለሰቦች ዘንድ፡ የጠባይ አለመስማማት ችግር የሚታየው፡ ከዚህ የተነሣ መኾኑ መታወቅ አለበት። በተለይም፡ ለግብረ-ሰዶምና እርሱን ለመሰሉት፡ ብዙ ዓይነት ልማዶች መፈልፈልና መጠናከር፥ መስፋፋትና መደርጀት፡ ጥንቱኑም ቢኾን፡ ዋናው ምክንያት የኾነው፡ ይኸው ምንኵስና መኾኑ፡ በግልጽ አትናገሩትም እንጂ፡ ኹላችሁም፡ አበክራችሁ የምታውቁት ነው።

ይህን የግብረ-ሰዶምን የመንሠራፋት ኹኔታ፡ እጅግ በበለጠ መልክና በከፋ ይዘት፡ እንዲባባስ ያደረገው፡ ራሱ፡ የምንኵስና ፅንሰ-ሓሳብ፡ በመሠረቱ፡ በሴትነት አካልና በጾታነቱ ባሕርይ ላይ ሳይቀር፡ ካለው ታላቅ ጥላቻ የተነሣ፡ ስለዚሁ እውነታ፡ ማየቱና መስማቱ ቀርቶ፡ ማሰቡ እንኳ፡ እንደታላቅ ኃጢአት እንዲቆጠር በማድረግ፡ የምንኵስና ሰለባ የኾነውን ግለሰብ፡ በራሱ እጅ፡ አባለ-ዘሩን፡ እስከመስለብ፥ ወይም፡ ራሱን እስከማጥፋት በሚያደርስ ጭካኔ፡ የመጨረሻውን ውሳኔ፡ በቍርጥ ሰጥቶ እንዲፈጽም ያደርገዋል።

በልጆቼና በፍጡሮቼ ሰዎች ላይ፡ ለረዥም ዘመናት፡ እንዲህ ሲካኼድና ሲፈጸም የኖረውን፡ ይህን የመሰለውን እጅግ አሳዛኝና አሠቃቂ ድርጊት፡ እኔ እናታችሁ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ዝም ብዬ መመልከቴን አልቀጥልም። "አምናለሁ!" ለሚለው ኾነ፥ ለማያምነውም ምድራዊ ፍጥረተ-ዓለማችን፡ በነሐሴ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፩ ዓመተ-ምሕረቱ ቍጥር ፩ ዐዋጃችን የተገለጥነው፡ እኔ እና ልጄ ወዳጄ ኢየሱስ መሲሕ፡ ፈጽመን <u>እናስወግደዋለን እንጂ፡ እንዲቀጥል አናደርገውም።</u> በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ ኹሉን እናስተካክለዋለን።

ከኹሉ አስቀድሞ፡ እናንት፡ በልጄ በወዳጄ በኢየሱስ መሲሕ ተጠምቃችሁ፡ "ክርስቲያን ነን!" ያላችሁ መነኮሳት ኹሉ፥ በተለይም፡ እኔ፡ "ልጆቼ!" የምላችሁ፥ እናንተም፡ እየራሳችሁን፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" የምትሉ ኹላችሁ! የምናገራችሁን ስሙኝ!

"ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ኾኜ፡ ስለፍጥረታተ-ዓለማቱ ስል፡ ምንጊዜም፡ እጆቼን፡ ወደእኛው፡ ወደእግዚአብሔር እንደዘረጋሁ፡ ለዘለዓለም ያለሁትን፡ የእግዚአብሔር አብ ሙሽራና የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ እናት፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም መንበረ-ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ የኾንሁትን፡ እኔን፡ እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያምን፡ እንዲህ በኾንሁበት ማንነቴ፡ እስካኹን አምናችሁ ስላልተቀበላችሁኝ፥

ይህ ሳያንስ፡ ከቀደመው የኵነኔ ዘመን በኋላ፡ በተለይ፡ በእኔ፡ በእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም መድኃኒትነት እና በልጄ በወዳጄ በኢየሱስ መሲሕ ቤዛነት፡ "ክፋትና ኃጢአት [ሓሰት]፥ ጠላትነትና ጦርነት፥ ቅጣትና ሞት" የተባሉት፡ ኹሉም ዓይነት ስሕተትና ጥፋት፥ መርገምና ርኵሰት፡ "በደግነትና በጽድቅ [በእውነት]፥ በዕርቅና በሰላም፥ በምሕረትና በሕይወት" ፈጽመው ተወግደውና ተተክተው፡ ቅድስቲቱ፡ የትንሣኤ ሕይወት እና ዘለዓለማዊቷ፡ የሰንበት ዓለም፡ ለእያንዳንዳቸው ወንዶች እና ሴቶች ልጆቼ መተካታቸውን ስላላበሠራችሁልኝ፥

እንዲያውም፡ በእኔ ጾታ የፈጠርናቸውን ሴቶች ልጆቼንና ፍጡሮቼን ብቻ፡ አኹንም፡ በዚያው፡ በኦሪታዊዉና በአይሁዳዊው፥ በኦርቶዶክሳዊዉና በግብፃዊው የወንድነት ማንነታችሁ ተመክታችሁ፡ በእነርሱ ላይ እየፈጸማችሁ ያላችሁትን፡ ፀረ-እግዚአብሔራዊና ፀረ-ኢትዮጵያዊ፥ ፀረ-ማርያማዊና ፀረ-ክርስቲያናዊ የጥቃት ዘመቻችሁን፡ ከማጽናትና ከመቀጠል በቀር፡ አንዱንም ዓይነት ስሕተትና ጥፋት ማስወገዱ ቀርቶ፡ ልታቃልሉት፡ አንዳች ዓይነት ዝንባሌ ስላላሳያችሁት፥

በእውነተኛውና በተገቢው ንስሓችሁ፡ በጊዜው ካላስተካከላችሁት በቀር፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ላይ፡ ቀደም ብላችሁ፡ በፈጸማችሁት፡ የክህደትና የዓመፅ፥ የክፋትና የአምልኮ አመንዝራነት ኃጢኣታችሁ ምክንያት፡ እስካኹን ተይዛችሁ በምትገኙበት መለኮታዊ ውግዘት ጋር፡ ይህም፡ የአኹኑ፡ የእኔው የታከለበት መኾኑን እንድታውቁት ይኹን!

"ልጆቼ!" ልላችሁ በሚከብደኝ፡ በእናንተ፡ ሰብአውያን ወንዶቼ ፍጡሮቼ ዘንድ፡ በአንድ በኩል፡ የእኛ የተቀደሰው ሥነ-ፍጥረት ሥርዓታችን ተቃራኒ የኾነው፡ የምንዝርስና ወግና ተባዕትነት፡ እንዲህ፡ ከፍተኛ የተከባሪነትና የቀዳሚነት፥ የታላቅነትና የበላይነት ማዕርግ እንዲሰጠው መደረጉ፣

በሌላ በኩል ደግሞ፡ እኛ እግዚአብሔር የሠራነው፥ ራሳችንም የምንኖረው የጋብቻ ሥርዓት፥ ደግሞም፡ ከወንድነት ጋር እኩል አድርገን የፈጠርነው ሴትነት፡ ለምን እንዲህ እንዲነወር፥ እንዲነቀፍና እንዲዋረድ መኾኑ፥ ይልቁንም፡ የሰው ወገን የኾኑት ሴቶቼ ብቻ ሳይኾኑ፡ የእንስሶቼ እንስት እንኳ ሳይቀሩ፡ እናንተ መነኮሳቱ በምትገኙበት ሥፍራ እንኳ እንዳይታዩ መደረጉ ለምንድር ነው?

ይህ ግብራችሁ፡ በእኔ፡ በራሴ፡ በእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም ላይ፡ እንደተቃጣ ብቻ ሳይኾን፡ እንደተፈጸመ አድርጌ የምቆጥረው መኾኑን፡ እንዴት፡ እስካኹን ለእየራሳችሁ ልትገነዘቡት ሳትችሉ እንደቀራችሁ፡ ለእየራሳችሁ አይገርማችሁም? አያሳዝናችሁምም? ወይስ፡ ዐውቃችሁት፤ ተገንዝባችሁትም ነው፡ ለዚህን ያህል ረዥም ዘመን፡ ዝም ብላችሁ የኖራችሁት? እንዲያ ከኾነም፡ መልካም! እንደልጄ ወዳጄ ኢየሱስ መሲሕ ቃል፡ ለኹላችሁም፡ እንደእየሥራችሁ ይከፈላችኋል።

## ኢትዮጵያዊቷ፡ ንግሥት ማክዳ
## እና
## እስራኤላዊው፡ ንጉሥ ሰሎሞን።

ከባለቃል-ኪዳናችን ነቢይ ንጉሥ ዳዊት የተወለደውን ሰሎሞንን፡ ከሌሎቼ ልጆቼ ኹሉ የተለየ ያደረገው ምክንያት አለ፤ ይህንኑም፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ፡ እኔው ራሴ ልገልጥላችሁ አስፈልጎኛል። ያስፈለገኝም፡ እንዲያው አይደለም፤ በቂና ከባድ መነሻ ስላለ ነው። ይኸውም እንዲህ ነው፡-

ከእስራኤል ልጆች ንጉሥ፡ ከዳዊት የቃል-ኪዳን ዘር የተገኘውን፡ ሰሎሞንን የወለደችው፡ ኢትዮጵያዊቷ ቤትሳባ የመኾኗን ምሥጢር በሚመለከት፡ ይህ ዓቢይ ጉዳይ፡ ከኢትዮጵያ ልጆቼ ጋር ያለውን፡ የዜና-መዋዕልና የዝክረ-ነገር ትክክለኛ ግንኙነትና እውነተኛ ትስስር፡ በእርግጥ ታውቁታላችሁ? አታውቁትም። እንድታውቁት አልተደረገምና። እንድታውቁት የተደረገውና የምታውቁት ግን፡ ተቃራኒውን፡ ሐሰቱን ነው። ተቃራኒውንና ሐሰቱንም ብቻ አይደለም፤ ፍጹም ተገላቢጦሹን ነው።

ታዲያ! ቀደም ብዬ፡ "ይህንኑ እውነታ፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ፡ እኔው ራሴ አረጋግጬ ልገልጥላችሁ አስፈልጎኛል!" ያልኳችሁ፡ ለዚህ አይደለምን? ነው እኮ፡ ፍጡሮቼ! ልጆቼ! ስለዚህ፡ በጥንቃቄና በማስተዋል ስሙኝ!

"የኢትዮጵያ ልጆቼ" ብዬ የጠቀስኳቸው ወገኖች፡ የዚህኑ የሰሎሞንን እናት የኾነችውን፡ ኢትዮጵያዊቷን ቤትሳባንና ኢትዮጵያዊዉን ባሏን፡ ኦርዮን፥ ኋላም፡ የእኛን እግዚአብሔራዊ ዓላማ እናስፈጽማት ዘንድ፡ የዘር ግንዷ፥ ምዝላቷ፡ መልከ-ጼዴቅ ወደቆረቆራት፡ ወደኢየሩሳሌም ተጉዛ፡ ሰሎሞንን እንድትጎበኝ ያደረግናትንና ከእርሱ፡ "እብነ-መለክ" የሚል ስም የተሰጠውን "ምን-ይልቅ"ን [ምኒልክን] ፀንሳ የተመለሰችውን፡ "የዓዜብ ንግሥት"፥ "የደቡብ ንግሥት"፥ "ንግሥተ-ሳባ" በሚል አጠራር የምትታወቀውን፡ ንግሥት ልጃችንን፡ ማክዳን የመሰሉትን ታማኞቼን መኾኑን እንድትገነዘቡት ይኹን!

አዎን! እነሆ እንግዴህ ተመልከቱ! በዚህ መለኮታዊ እውነታችን ላይ፡ "የራሴ" ከምላቸው፡ ኢትዮጵያውያን ልጆቼ መካከል ሳይቀር እየተነሡ፡ ከብዙዎች የክፉው ወገኖች ጋር፡ በክፋት በመመሣጠር፥ በተንኰልም በመተባበር፡ ዐውቀውም ኾነ፥ ሳያውቁ፥ በሞኝነትም ኾነ፥ በብልጠት፡ በዚያው፡ በሚታወቀው፡ የሐሰት አባት በኾነው፡ በዲያብሎስና በጭፍሮቹ ቀንደኛ አበጋዝነትና መሪነት፡ እጅግ በርካታ፥ ጠንቀኞች የስሕተት ይትበሃሎችን፡ ባልተቋረጠና በተጠናከረ ዘመቻ፡ ለዘመናት፡ በቃልና በጽሑፍ፡ በሥውርና በገሃድ፡ ሲያሠራጩ ኖሩ።

በዓለማችሁ ላይ፡ የይፋ ተቀባይነትን ካገኘው፡ መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ውጭ በኾነ መልክና ይዘት፡ እንደ"ፍትሐ-ነገሥቱ" መጽሓፍ ኹሉ፡ "'በ፫፻፲፰ቱ (በሦስት መቶ ዐሥራ ስምንቱ) የኒቅያ ሊቃውንት ጉባኤም' ጸድቋል!" የተባለለት፡ በእነዚያው፡ በተለመዱት፡ በአሪታውያኑ አይሁድና በኦርቶዶክሳውያኑ ግብፆች መነኮሳት "ጳጳሳት" ተቀነባብሮና ተዘጋጅቶ፡ ለብዙዎች፡ ለስሕተታቸውና ለበደላቸው፥ ለውድቀታቸውና ለጥፋታቸው ዋና መነሻ የኾነው፡ *"ክብረ-ነገሥት"* የሚባለው መጽሓፍ፡ ከአብነቱ ከቅብጥና ከዓረብኛ ልሳኑ፡ ወደግእዝ ብቻ ሳይኾን፡ ወደሌሎቹም የዓለም ቋንቋዎች በመተርጐምም፡ ናኝተውታል። (ኦሪት ዘልደት [ዘፍጥ.] ፴፰፥ ፩-፴፤ ፵፱፥ ፲።)

ዳሩ ግን፡ ይኼ አሳሳችና ሐሳዊ ድርጊታቸው፡ እንግዴህ ወዲህ ሊቀጥል አይቻለውም! ለአንዴና ለዘለዓለም አብቅቷል።

ይህም የኾነው፡ ሳታስተውሉት ቀርታችሁ ይኾናል እንጂ፡ አስተውላችሁት ከኾነ፡ በእኔ፡ በኢትዮጵያዋ እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም ሃይማኖትነትና ንግሥትነት፥ በልጇ በወዳጇ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ሊቀ-ካህናትነትና ንጉሥነት፡ ኢትዮጵያ፡የእግዚአብሔር መንግሥትነታችን፡ በይፋ ከተገለጠችበት፡ ካለፈው፡ ነሓሴ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፫ ዓመተ-ምሕረት አንሥቶ ነው።

በዚህ መሠረት፡ በቀጥታ፡ ወደፍሬ-ጉዳዩ ገብቼ የምለው፡ይህን ነው፡- ስማቸውን፡ አኹን ቀደም ብዬ ከጠቀስኋቸው "የኢትዮጵያ ልጆቼ" መካከል አንዷ የኾነችው፡ ቅድስቲቱና ንጹሒቱ፥ ብልሂቱና ውቢቱ ልጃችን፥ ለእኔም፡ ለድንግል ማርያም፡ ቀዳሚት አርአያዬና አብነቴ የኾነችው ማክዳ፡ "በአፈ ታሪካችሁም ኾነ፡ "ክብረ-ነገሥት" በምትሉት መጽሓፋችሁ ውስጥ፣ ምን ዓይነቱ ስምና ግብር፥ መልክና ባሕርይ ተሰጥቷት፡ ተቀብታውና ተሸክማው እንደኖረች፡ ይህን "ጠንቀኛ ተረት"፡ በአኹኑ ዘመናችሁ፡ በምድራችሁ ላይ ያልሰማና ያላነበበ፥ ያላወራና ያልጻፈ፥ ያላስተጋባና ያላደነቀ፣ ያልተቸና ያላፌዘ ይኖራልን? አይኖርም።

አዎን! በዚህ "ጠንቀኛ ተረት" አማካይነት፡ "ንግሥተ-ሳባ" በሚለው ገናና ስሟ፡ በይበልጥ የምትታወቀው፡ ይህችው፡ ልጃችን፡ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ፡ እኛን፡ የሰማይና የምድር ፈጣሪን፡ እግዚአብሔርን ***የማታውቅ፣ ፀሓይ-አምላኪ፥ ለዘንዶ የምትገብር፥ አረማዊት እንደኾነች ተደርጋ ቀርባለች።***

ይህ ብቻ አይደለም፤ እንዲያውም፡ ወላጇ፡ እርሷን ፀንሳ ሣለች፡ ደስ የሚል ፍየል ስላየች፡ ሕፃኗ ሴት ኾና በተወለደች ጊዜ፡ አንድ እግሯ፡ በእንስሳ ፀጉር እንደተሸፈነ ኾኖ፣ የፍየል ሸኰና በመሰለ አካል ተፈጥራ እንደተገኘች፥ በዚህ የተፈጥሮ ጉድለቷም እንዳለች ኾና ዐድጋ፡ ለንግሥትነት መብቃቷ ተነግሯል፤ ተመዝግቧል።

ከዚሁ የተፈጥሮ ጒድለቷ ተፈውሳ፡ በሰብኣዊ እግሯ ልትሟላ የቻለችው፡ በዚሁ ንግሥትነቷ፡ ወደኢየሩሳሌም ተጉዛ፡ ከንጉሥ ሰሎሞን ጋር ከተገናኘች በኋላ፡ በዚያ በቤተ መንግሥቱ ግቢ ወድቆ በነበረ፥ ከገነት በመጣ እና ሰሎሞን፡ ሸኰና እግሯን ለማየት ሲል፡ በውኃ እንዲሸፈን ባደረገው እንጨት ተነክታ እንደኾነ ተደርጎም፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነገረውና ተጽፎ የሚነበበው ሓተታ ያስረዳል።

ከኹሉም ይበልጥ እጅግ የሚያስገርመው፡ ስለእኛና ስለአምልኮተ-እግዚአብሔር ያወቀችውና የተማረችው፡ ከእርሱው፡ ከሰሎሞን አንደበት እንደኾነ፥ ከዚህ ይባስ ግን፡ ንጉሥ ሰሎሞንን ለማየት፡ ወደኢየሩሳሌም እንድትጓዝ የተገደደችው፡ በሥጋዊ ፍትወት ከተነደፈችበት የፍቅር ጽናት የተነሣ እንደኾነ በማስመሰል፥ እንዲሁም፡ ከእርሷ በኋላ፡ በኢትዮጵያ የነገሠው ልጇ ምኒልክ፡ ተቀብቶ በኢትዮጵያ ዙፋን የተቀመጠው፡ በሰሎሞን ፈቃድና ትእዛዝ እንደኾነ፥ ከእርሱ ወዲያም፡ በኢትዮጵያ፡ ሴት ንግሥት እንዳትነግሥ እንደተደነገገ ተደርጎ፡ በቃል የተነዛውና በጽሑፍ የተከተበው ሓሳዊ ወሬ ነው።

እንኳንስ ፈጣሪያችሁ በኾንነው፡ በእኛ ዘንድ ቀርቶ፡ አስተዋይ ተመልካች በኾነ፡ በማንኛውም ሰብኣዊ ፍጡራችን ዘንድ እንኳ፡ ተቀባይነትን አይደለም፡ ተደማጭነትን እንኳ "ሊያገኝ አይችልም!" የሚባለው፡ ይህ የማይመስል ሓሳዊ ይትበሃል መነገሩ፡ በምንም መልኩና ይዘቱ አያስደንቅ ይኾናል።

የማያስደንቀውም፡ ልጄን ወዳጄን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ በሰውነት ባገኙት ጊዜ፡ በመስቀል ላይ አሠቃይተው የገደሉት፡ ኦሪታውያኑ አይሁድ እና ግብረ-ዐበሮቻቸው ኦርቶዶክሳውያኑ ግብፆች፡ እነርሱው ራሳቸው ፈጥረው ያስገኙትና ያሠራጩት በመኾናቸው ብቻ፡ እነርሱና እነርሱን የመሰሉት ወገኖች፡ ተቀብለው በተግባር ላይ ዐውለው ሲጠቀሙበት የኖሩ በመኾናቸው ነው።

እጅግ የሚያስደንቀው ግን፡ ይህንኑ የማይመስል ሓሳዊ ይትበሃል፡ የራሴ ከምላችሁ፡ ከኢትዮጵያ ልጆቼ መካከል፡ እንዴት ተቀብላችሁትና አጽንታችሁት፡ እስከቅርቡ የመጨረሻው አጼ፡ እስከኃይለ-ሥላሴ ዘመን ድረስ፡ እየሠራችሁበት ልትኖሩ እንደቻላችሁ፥ እንዲያውም አንዳንዶቻችሁ፡ አኹንና ለወደፊት፡ ልትሠሩበት የምትፈልጉ ጭምር ስለመኖራችሁ ለማመን፡ ምናልባት፡ አስተዋይ ተመልካች የኾነ፡ አንድ ሰብኣዊ ፍጡር እንኳ ከተገኘ፡ አዎን! ለእርሱም እንደሚያዳግተው እርግጥ መኾኑ ነው።

ይህን ስታደርጉ የኖራችሁ ኾናችሁ፥ ነገር ግን፡ እናንተ፡ አኹንም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች ነን!" ለማለት የምትደፍሩ ካላችሁ፡ የእኔ እውነተኞች ልጆቼ የመኾናችሁ እውነታ፡ አጠያያቂ መኾኑን ልትገነዘቡት ይገባችኋል። አያስኬድማ! እንዴ! ምን ማለታችሁ ነው? እርግጡ ይህ፡ የተባለውና የተጻፈው ኾኖ ከተገኘማ፡ "የኢትዮጵያ ልጆች ነን!" ለማለት የምትደፍሩትን እናንተን፡ በእርግጥ፡ "ምን ነክቷችሁ ኖርዋል?" የሚያሰኝ ነው። ሊኾን አይችልማ! ይህ፡ እንዴት ሊኾን ይችላል? የምታምኑበት ባዕድ አምልኮ ቢኖራችሁ እንኳ፡ ያ ጠላታችሁ፡ አንድ ዓይነት ዐዚም [አፍዝ-አደንግዝ] አድርጎባችሁ ካልኾነ በቀር፡ በጤና ህልውናችሁ፡ ይህ ነገር፡ እንኳንስ፡ እንዲህ፡ ጸንቶ፡ ሲፈጸም ሊኖር ይቅርና፡ በመሠረቱ፡ ቀድሞውኑ፡ ሊታሰብም እንኳ የሚቻል ባልኾነ ነበር።

እናንተ "የኢትዮጵያ ልጆች"፡ ለእኛ ያላችሁን፡ እውነተኛውንና መንፈሳዊዉን አምልኮተ-እግዚአብሔር በሚመለከት፡ እንኳንስ፡ ከመላው የዓለሙ አሕዛብ ፍጡሮቻችን ቀርቶ፡ በኪዳናተ-አብርሃም፥ ሙሴና ዳዊት ምክንያት፡ "ሕዝቤ!" ብለን ከምንጠራቸው፡ ከ"እስራኤል ልጆች" እንኳ ሳይቀር፡ የእኛ የ"እግዚአብሔር ወገን" ከመኾናችሁ፥ ለእኛም፡ ለፈጣሪያችሁ፡ ካላችሁ ፍጹም ታማኝነታችሁ የተነሣ፡ ከኹሉ ለይተንና አብልጠን ያቀረብናችሁ፥ ያፈቀርናችሁም በመኾናችሁ አይደለምንዴ፡ "'<u>አኮ ከመ ደቂቀ ኢትዮጵያ አንትሙ በኀቤየ፡ ደቂቀ እስራኤል!</u>' ይቤ እግዚአብሔር፡ **ዘኵሎ ይመልክ ስሙ።**"

"ስሙ፡ 'ኹሉን የሚገዛ' የኾነ እግዚአብሔር፡ ‹የእስራኤል ልጆች! እናንተ፡ በእኔ ዘንድ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም።› አለ።" ስንል፡ ይህን የዐዋጅ ቃላችንን በነቢያችን፡ በአሞጽ አፍ ያናገርነው? ለዚህ ካልኾነ በቀር፡ ታዲያ ለምን ኖርዋል ያናገርነው? አዎን! ይህንኑ እውነታ ለማረጋገጥ ስንል ብቻ እንደነበረ፡ ለማንኛችሁም ግልጽ ሊኾን ይገባል።

ታዲያ! በዚህ፡ በእግዚአብሔራዊው የእውነት ቃላችን መሠረት አይደለም እንዴ፡ ኢትዮጵያዊት ልጃችንን፡ ንግሥት ማክዳን፡ ከአገሯ ከኢትዮጵያ ተነሥታ፡ በኢየሩሳሌም ይኖር ወደነበረው ወደእስራኤሉ ልጃችን፡ ወደንጉሥ ሰሎሞን እንድትጓዝ ያደረግነው? ይህን እውነታ የማታውቁ ካላችሁ፡ እኔው ገልጬና አብራርቼ ላሳውቃችሁ! ስሙኝ!

ከአዳምና ከሔዋን የፍጥረት ልደት ጊዜ አንሥቶ፡ በሰዎች ኪዳነ ልቦና ላይ የተመሠረተውን፡ እውነተኛውንና ትክክለኛውን አምልኮተ-እግዚአብሔር፡ በቅዱሱ ኪዳን ጠብቀውና ሕይወት አድርገው፡ በዚያን ዘመኑ መላ የምድሪቱ ዓለም ላይ፡ ይኖሩ የነበሩት፡ በኢትዮጵያ ስሜ፡ የተጠሩት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ ብቻ ናቸው። እነርሱም፡ በኹለቱ ምድሮቻቸው ተዘልለው ይኖራሉ። ከኹለቱ ምድሮቻቸው አንዲቱ፡ አዳምና ሔዋን የተፈጠሩባት፥ የኖኅ መርከብም፡ በጥፋት ውኃ ተንሳፍፋ፡ ምድሪቱን እስከለቀቀችባት ሰዓት ድረስ፡ ከነትውልዶቻቸው የቆዩባት፡ ዐፅመ-ርስታቸውና ማዕከላቸው የኾነችው፡ ዋናዋ አገራቸው፡ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ስትኾን፥ ሌላዪቱ አገራቸው ደግሞ፡ ኖኅና ልጆቹ፡ ከጥፋት ውኃ ከዳኑባት መርከባቸው ወጥተው የሠፈሩባትና የኖኅ የልጅ ልጅ የኾነው "መልከ-ጼዴቅ" የተባለው ታማኙ አጼያችን፡ ኢትዮጲስ፡ የቈረቈራትና ብሔረ-ሙላዳቸው የኾነችው፡ የዛሬዪቱ ኢየሩሳሌም ናት።

የኢትዮጵያ ልጆቼ፡ እንዲህ እየኖሩ ባሉበት፡ በዚያን፡ በማክዳና በሰሎሞን ጊዜ፡ በመላው ዓለም የሚርመሰመሰው፡ ሌላው ሰብአዊው ፍጡር ኹሉ፡ በጣዖት አምልኮ የተዋጠ ነበር። በኢየሩሳሌም የሚኖሩት፡ የእስራኤል ልጆችም እንኳ፡ ለኢትዮጵያዊነት በበቃው አገልጋያችን በሙሴ መሪነት፡ ቀደም ብለው፡ ከግብፅ የፈርዖን ባርነት፡ ነጻ ወጥተውና ባሕረ-ነጋሢን ተሻግረው፡ በሲና በረሀ ሣሉ፡ ከኢትዮጵያ ልጆቼ፡ በትምህርት የተቀበሉትን፡ የእኛን፡ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔርን ሥርዓተ-መንግሥት፡ በነቢያችን በሳሙኤል የሥልጣን ጊዜ፡ ባደረሱት ፀረ-እግዚአብሔር ዓመፃቸው ምክንያት፡ ያ፡ መለኮታዊው የአስተዳደር ሥርዓታችን ጸጋ፡ ከእነርሱ ስለተገፈፈ፡ ከሳዖል እስከሰሎሞን በደረሰው የሰዎች አገዛዝ ቀንበር ሥር ወድቀው የነበሩበት ዘመን ነበር። (፩ሳሙ. ፰፥ ፩-፳፪።)

በዚህ ጊዜ ነበር፡-

፩. ኢትዮጵያዊቷ ልጃችን፡ ንግሥት ማክዳ፡ የባለቃል ኪዳን ታማኝ አገልጋያችን፡ የእስራኤላዊው ዳዊትና የኢትዮጵያዊቷ የቤትሳባ ልጅ፡ ንጉሥ ሰሎሞን፡ በአባቱ ዙፋን ተቀምጦ፡ አባቱ፡ ለእኛ ሊሠራ ቃል የገባውን፡ "ቤተ-መቅደስ እያሳነፀ ነው!" የሚል ዜናን የሰማችው!

፪. በተለይም፡ አምልኮ-ጣዖት ፈጽሞ አጥለቅልቆ በሰፈነበት፡ በዚያን ዘመኑ ዓለም፡ ይህ፡ "ለእኛ፡ ለእግዚአብሔር ቤተ-መቅደስ የሚሠራ አንድ ንጉሥ ተነሥቷል!" የሚለው ዜና፡ ከዚችው ልጃችን፡ ከንግሥት ማክዳ ጆሮ ሲደርስ፡ ቀደም ብሎ፡ በእኛ መንፈስ ቅዱስ የተቃኘውና የተነሣሣው ልቦናዋ፡ በመለኮታዊው የፍቅርና የቅንዓት እሳት የተኰሰተረው።

ተኰስትሮም፡ "ይህ ዜና፡ በእርግጥ እውነት መኾኑን፡ በዓይኖቿ አስተማምና በማየት ለማጽደቅ፥ እስራኤላዊዉን ንጉሥ ሰሎሞንንም፡ በተለይ፡ ስለሃይማኖቱ አማናዊነትና ስለአምልኮቱ ትክክለኛነት በማረጋገጥ፡ በራሷ በኩል፡ በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ፥ በእኛም በኩል ደግሞ፡ ያዘጋጀንላትን አምላካዊ ተልእኮ ፈጽማ ትመለስ ዘንድ፡ ለተቀደሰው ዕፁብ ድንቅ ጉዞዋ አነሣሥተን ያስጀመርናት።

ይህንም፡ ቅዱሳት መጻሕፍታችሁ ፡ **"ወንግሥተ ሳባ፡ ሰምዓት ስሞ፡ ለሰሎሞን፤ ወስሞ፡ ለእግዚአብሔር። <u>መጽአት፡ ትፍትኖ፡ ምስለ ጥበባ።</u> ወቦአት ኢየሩሳሌም፡ በኃይል ክቡድ ፈድፋደ፤ ወአግማል ይፀውሩ አፈዋተ፥ ወወርቀ ብዙኀ ፈድፋደ፥ ወዕንቈ ክቡረ።**

**"የሳባም ንግሥት፡ የሰሎሞንን ስም፡ በዝና ሰማች፤ የእግዚአብሔርም ስም፡ ከእርሱ ስም ጋር ሲጠራ ሰማች። <u>በጥበቧ ትፈትነው ዘንድ መጣች።</u> በግመሎችም ላይ፡ ሽቱና እጅግ ብዙ ወርቅ፥ የከበረም ዕንቍ አስጭና፡ ከታላቅ ጓዝና ከሚያስፈራ ሠራዊት ጋር ወደኢየሩሳሌም ገባች።"** በማለት፡ የጉዞዋን ዓላማ ገልጠውታል። ከዚህ በቀር፡ በእርሷ በኩል፡ ስለሃይማኖቱና ስለአምልኮቱ አጣርታ ለማወቅ ስትል፡ በጥበቧ እየፈተነችው፡ ላቀረበችለት ጥያቄ፡ ከእርሱ፡ ተገቢውን ምላሽ ማግኘቷን፡ ጨምረው ጽፈዋል። በዚህ ረገድ፡ በዓይኖቿ ባየችውና በጆሮዎቿ በሰማችው ኹሉ፡ የእርሷ አምላክ የኾነው እግዚአብሔር፡ የእርሱም አምላክ ኾኖ በማግኘቷ፡ እጅግ ተደስታ፡ በማመስገን፡ ያሳየችውን ስሜት፡ ሰሎሞን፡ **"ወርእየት ንግሥተ-ሳባ፡ ...ወመሥዋዕቶኒ ዘይሠውእ ለቤተ-እግዚአብሔር፤ ወተደመት።**

**"የሳባ ንግሥት፡ ...ሰሎሞን፡ በእግዚአብሔር ቤተ-መቅደስ የሚያሳርገውን መሥዋዕት አየች፤ በአንክሮም ተደነቀች።"** በሚል ቃል፡ እኒሁ ቅዱሳት መጻሕፍታችሁ አመልክተውታል። (፩ነገ. ፲፥ ፩-፲፫።)

እዚህ ላይ፡ በጥቂቱም ቢኾን፡ ስለንግሥት ማክዳ ልናገር አስፈልጎኛል። ነገር ግን፡ ስለእርሷ ከመናገሬ በፊት፡ እርሷንና ንጉሥ ሰሎሞንን በሚመለከት፡ የማወሳው፡ አንድ ቍም-ነገር አለ፤ እርሱም፡ በአንድ በኩል፡ ንግሥት ማክዳን ያስገኙት፡ "የኢትዮጵያ ልጆች"፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ከተባሉት፡ ከአቤል ወገኖች የተመደቡ ኾነው፡ የዘር ግንድ ሐረጋቸውን የሚመዝዙት፡ ከአዳምና ከሔዋን በመኾኑ፡ የህልውናቸው ዕድሜ፡ እስከዛሬ ሲቆጠር፡ ፯ሺ፭፻፰ (ሰባት ሽህ አምስት መቶ ስምንት) ዓመታት መኾኑን ማስገንዘቡ ነው።

በሌላው በኩል ደግሞ፡ ንጉሥ ሰሎሞንን ያስገኙት፡ "የእስራኤል ልጆች"፡ "የሰው ልጆች" ከተባሉት፡ ከቃኤል ወገኖች ኾነው፡ በታማኙ አገልጋያችን፡ በኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ የክህነት ተልእኮ፡ ከጣዖት አምልኮ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት፡ አራተኛው እርከን ለኾነው፡ የግርዛት ቃል-ኪዳን የበቃው፡ የአብርሃም ዘሮች ሲኾኑ፡ የህልውናቸው ዕድሜ፡ ከዛሬ ወደኋላ፡ ወደእርሱ፡ ወደአብርሃም ዘመን ሲተመን፡ ከ፬ሺ፭፻፰ (ከአራት ሽህ አምስት መቶ ስምንት) ዓመታት የማያልፍ መኾኑን፥ ማሳወቁ ነው።

በዚህ ረገድ፡ የእኛ የኾነውን አምልኮተ-እግዚአብሔርን በሚመለከት፡ ከ"ኢትዮጵያ ልጆች!" አንዷ የኾነችው ንግሥት ማክዳ፡ ከ"እስራኤል ልጆች" አንዱ አባል የኾነውን፡ ንጉሥ ሰሎሞንን፡ በሦስት ሽህ ዓመታት ትቀድመዋለች ማለት ነው።

እውነታው ይህ ከኾነ፡ እንግዲህ፡ በነገረ-ቀደም፡ እንዲህ፡ በእኛ አምልኮተ-እግዚአብሔር ላይ ከተመሠረተና ከሠረፀ የትውልድ ሓረግ የተገኘችው፡ ራሷ፡ ይህች ንግሥት ማክዳ፡ "ማን ናት?" ለሚለው ጥያቄ፡ እውነተኛውን መልስ ለመስጠት፡ ለማንም ሰብኣዊ ፍጡራችን፡ የሚከብድ አይኾንም።

በኢትዮጵያ ልጆቹ ዘንድ፡ ከመጀመሪያው የፍጥረት ጊዜ አንሥቶ፡ ጸንቶ ከቆየው፡ ከቅዱሱ ኪዳን የተነሣ፡ "**ናሁ፡ ድንግል ትፀንስ! ወትወልድ ወልደ! ወይሰመይ ስሙ፡ 'አማኑኤል!' ዘበትርጓሜሁ፡ 'እግዚአብሔር ምስሌነ።'**

**"እነሆ፡ ድንግል ትፀንሳለች! ወንድ ልጅንም ትወልዳለች! የስሙ ትርጉም፡ 'እግዚአብሔር፡ ከእኛ ጋር ነው!' ማለት ኾኖ፡ 'አማኑኤል!' ይባላል።** የሚለው፡ በነቢያችን፡ በኢሳይያስ አፍ ያናገርነው ትንቢት፡ የመፈጸሚያው ዘመን ደርሶ፡ በእኔ፡ በኢትዮጵያዋ፡ በድንግል ማርያም፡ እውን እስኪኾን ድረስ፡ ከእነርሱ፡ ከ"ኢትዮጵያ ሴቶች ልጆቻችን፡ በአንዷቱ እንደሚፈጸም ያምኑ እንደነበረ ይታወቃል። (ኢሳ. ፯፥ ፲፬። ማቴ. ፩፥ ፳፪-፳፫።)

ስለዚህ፡ በመልከ-ጼዴቅያዊው ዙፋናቸው ላይ የሚያስቀምጧቸው አጼዎች፡ ሴቶች በሚኾኑበት ጊዜ ኹሉ፡ እነዚሁ፡ አጼዪቶች፡ ለዚሁ የተቀደሰ አምላካዊ ትንቢት ይበቁ ዘንድ፡ በድንግልና ንጽሕናቸው ጸንተው የሚገኙና እስከመጨረሻው፡ በዚሁ የሚቀጥሉ መኾናቸው፡ በፍጹም መረጋገጥ ስለነበረበት መኾኑን፥ "የሳባ ንግሥት" የተባለችው፡ የዚችው፡ የልጃችን፡ የንግሥት ማክዳ፡ የድንግልናዋም ምሥጢር፥ በዚህ፡ በሰሎሞን ጊዜም፡ ለዚህ፡ ለታላቁ መለኮታዊ ተልእኮ የተጠራችው፡ በዚሁ ምክንያት መኾኑን፡ ልትገነዘቡት ያስፈልጋል።

ይህን እውነታ፡ እንዲህ በሚል ቃል አብራራላችኋለሁ፡- ይኸውም፡ "ይሰሙት እንደኾነ!" ብለን፡ ታማኙንና ገድለኛውን፥ ታላቁንና ኢትዮጵያዊዉን ነቢያችንን፡ ኤርምያስን፡ ወደእነርሱ ልከነው በነበረበት፡ በዚያን ዘመን የነበሩት "የእስራኤል ልጆች"፡ እንደተለመደው፡ በእኛ፡ በእግዚአብሔር ላይ የፈጸሙት፡ የክፋትና የክህደት፥ የዓመፅና የአምልኮ አመንዝራነት ኃጢኣታቸው፡ ጽዋው ሞልቶ ሊፈስስ፡ ደርሶ ነበር።

ከዚያ የተነሣ፡ በአረማዊው ናቡከደነጾር የጭካኔ ሠይፍ፡ ሊቀጡና ሊያልቁ፥ ከነከተማቸውና ከነቤተ-መቅደሳቸውም ሊፈራርሱ፥ ከዚያ ዕልቂት የተረፉ ቢኖሩም፡ ለስደት ሊዳረጉ የተወሰነበት የቅጣት ፍርድ፡ ጊዜው፡ እየተቃረበ መጣባቸው።

ይህ አስደንጋጭና አስፈሪ፥ አሠቃቂና መራራ የዕልቂት ጽዋ ሞልቶ ከመፍሰሱ በፊት ግን፡ የእኛ፡ የቸርነትና የምሕረት ሥራ፡ አስቀድሞ መፈጸም ያለበት ኾኖ ተገኘ። ያም፡ በ"እስራኤል ልጆች" ዘንድ ያሉትን፥ ስለደጋጎቹ ምዝላቶቻቸው ስንል፡ ለእነርሱ፡ በልግሥናችን የሰጠናቸው ጸጋዎች በመኾናቸው፡ የእነርሱ ሲኾኑ፡ እነርሱ ግን፡ ለእነዚያ አምላካውያት ስጦታዎቻችን፡ ራሳቸውን ሊያበቁ፡ ፈጽመው ባለመቻላቸው፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ ያጧቸው ናቸው። እነዚህም፦

፩ኛ፡ በግርዛት ምልክት የታተመው፡ የአብርሃም፡ የሃይማኖትና የምግባር ቃል-ኪዳን፥

፪ኛ፡ በእኔ፡ በእግዚአብሔር እም እና በእግዚአብሔር ቃል ታቦተ-ጽዮንነት የተገለጠችው፡ የሙሴ ጽላተ-ኪዳን፥ እና

፫ኛ፡ የዳዊት መንግሥታዊ የቃል-ኪዳን ዘር ናቸው።

ስለዚህ ነው፡ ይህ፡ መቅሠፍታዊው "የእስራኤል ልጆች" ዕልቂትና ውድመት፥ ስደትና ፍልሰት ከመድረሱ በፊት፡ እነዚህን ሦስት ቅዱሳት ቃል-ኪዳናት፡ ከነምልክቶቻቸውና ማኅተሞቻቸው፡ እንደተጠበቁ ኾነው፡ ወደታማኞቹ ባለአደራዎቻችን፡ ወደ"ኢትዮጵያ ልጆቻችን" ተመልሰው እንዲመጡ ማድረግ፡ ለእኛ ያስፈለገን።

ለዚህ፡ መለኮታዊ ዕቅዳችን የቀጠርነው ጊዜያችን ሲደርስም፡ ታማኟንና የበቃችውን ኢትዮጵያዊት ድንግሊት አጼያችንን ማክዳን፡ ለዚሁ፡ ለኢየሩሳሌም ተልእኮዋችን እንድታገለግለን መርጠን የጠራናት፤ እርሷም፡ ይህንኑ ተልእኮዋን፡ በሚገባ ፈጽማ የተመለሰችው፡ ስለዚህ ነው። ያ ድንግልናዋና ንጽሕናዋ ያስፈለገው፥ ይኸው ድንግልናዋና ንጽሕናዋም፡ ልጇን ምኒልክን፡ ከንጉሥ ሰሎሞን በመፅነሷና በመውለዷ ሳይገሠሥ ጸንቶ መቀጠሉ የተረጋገጠው፡ በፍጻሜ የሕይወት ዘመን፡ እኔ እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም እና ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ የተዋሓድነው፡ የዳዊት የቅዱሱ ቃል-ኪዳን ዘር በመኾኑም ነው።

እንግዴህ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖትና በፍጹሙ የአምልኮተ-እግዚአብሔር ምግባር፥ የተመሠረተችውንና የደረጀችውን፥ የታወቀችውንና የገነነችውን፥ የከበረችውንና የተሸለመችውን፡ እንዲህ ያለችዪቱን፡ ቅድስትና ንጽሕት ኢትዮጵያዊት ድንግል፡ ንግሥት ማክዳን ነው፡ ክፉዎች፡ አሪታውያን አይሁድና ኦርቶዶክሳውያን የግብፅ መነኮሳት "ጳጳሳት"፥ ተባባሪዎቻቸውና ግብረ-ዐበሮቻቸው የኾኑትን፡ "የኢትዮጵያ ልጆች ነን!" የሚሉ፡ አንዳንድ ወገኖችን ጨምረው፡ ማንነቷንና ምንነቷን፡ እንዲያ አድርገው ያጎዳደፏት! ስሟን በክለው፡ እንዲያ ያጠፉፏት!

እዚህ ላይ፡ እርሷ፡ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ፡ እስራኤላዊዉን ንጉሥ ሰሎሞንን ትጎበኘው ዘንድ፡ ወደኢየሩሳሌም እንድትጓዝ፡ ለምን እንዳነሣሣናት፡ እስኪ፡ በይበልጥ ልዘርዝርላችሁ! እነዚህም፡ እንዲህ የሚሉ ናቸው፡-

<u>የመጀመሪያውና ዋናው ምክንያት፡-</u> ቀደም ብዬ የገለጽሁላችሁን፡ እነዚያን ሦስት ቅዱሳት ቃል-ኪዳናት፥ እነርሱም፡ ከታማኞቻችን፡ ከአብርሃም፥ ከሙሴና ከዳዊት ጋር ያደረግናቸውን ኪዳናት፡ ከነምልክቶቻቸውና ከነማኅተሞቻቸው ጋር፡ በእርሷና በልጇ፥ እንዲሁም፡ ዐብረዋቸው በመጡት ዕብራውያን ሠራዊት አማካይነት፡ በሙሉ፡ ወደታማኞቹ ባለአደራዎቻችን፡ ወደ"ኢትዮጵያ ልጆቻችን" ተመልሰው እንዲመጡ ለማድረግ መኾኑን የሚያመላክተው ነው።

<u>ተከታዩና የመጨረሻው ምክንያት ደግሞ፡ ይህ ነው፡-</u> በአንድ ወገን፡ በእኛ ላይ ባላት፡ አምልኮተ-እግዚአብሔር ፈጽማ የማትጠረጠረውን፥ የእኛን ሥርዓተ-መንግሥትም አክብራና ተከትላ በመኖር የምትታወቀውን፥ ንጽሕናንና ቅድስናን ፥ ታማኝነትንና መንፈሳዊትነትን የተጎናጸፈችውን፡ ኢትዮጵያዊት ድንግል ልጃችንን፡ ንግሥት ማክዳን፤

በሌላው ወገን፡ ከእግዚአብሔራዊው የአምልኮና የአኗኗር ሥርዓት ውጭ ኾኖ፡ ጣዖት አምላኪዎች የሚበዙባቸውን፡ ሦስት መቶ ሚስቶችን አግብቶና ሰባት መቶ ዕቁባቶችን አስቀምጦ፡ በርኵሰትና በስሕተት የህልውና መንገድ፡ ይኖር ወደነበረው፡ ወደእስራኤሉ ልጃችን፡ ወደንጉሥ ሰሎሞን የላክናት፡ ጥበቧ በኾነው፡ በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት፡ ሥጋዊና ዓለማዊ የኾነውን እስራኤላዊዉን ንጉሥ ሰሎሞንን አስተምራ፡ ወደቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖትና ምግባር እንድትመልሰው መኾኑን ልትገነዘቡት ይገባል።

የእርሱን፡ የንጉሥ ሰሎሞንን እስራኤላውያን ምዝላቶች፡ አብርሃምን፥ ሙሴንና ዳዊትን፥ የእርሷ፡ የንግሥት ማክዳ ምዝላቶች፡ ኢትዮጵያውያኑ መልከ-ጼዴቅና ዮቶር፥ እንዲሁም፡ ኦርዮና ኢትዮጵያዊቷ ቤትሳባ እንዳደረጉት ማለት ነው። አዎን! አገልጋያችን መልከ-ጼዴቅ፡ ታማኛችንን አብርሃምን አስተምሮ፥ ካህን ዮቶር፡ ታማኛችንን ሙሴን አስተምሮ፡ ለእኛ፡ ለእግዚአብሔር ልጅነት እና ለእኔ፡ ለኢትዮጵያ ልጅነት እንዳበቋቸው ኹሉ፡ አኹንም፡ እርሷ፡ ኢትዮጵያዊቷ ጥበበኛዪቱ ንግሥት ማክዳ፡ ጠቢቡን እስራኤላውዊ ንጉሥ ሰሎሞንን፡ አስተምራ ፡ ለኢትዮጵያዊ ልጅነቱ አብቅታዋለች።

"ሰምዓት ስሞ፡ ለሰሎሞን፤ ወስሞ፡ ለእግዚአብሔር። <u>መጽአት፡ ትፍትኖ፡ ምስለ ጥበባ።</u>

"የሰሎሞንን ስም፡ በዝና ሰማች፤ የእግዚአብሔርም ስም፡ ከእርሱ ስም ጋር ሲጠራ ሰማች። <u>በጥበቧ ትፈትነው ዘንድ መጣች።</u> ተብሎ የተጻፈው ለዚህና በዚህ ምክንያት እንደኾነ አታውቁምን? ካላወቃችሁ፡ ዕወቁት!

ለታላቅ አገልግሎት መርጠነው፡ መለኮታዊ ፈቃዳችንን ሲፈጽም የኖረው፥ ጥንቱኑም፡ በተፈጥሮው፡ በወላጆቹ አብራክና ማሕፀን፡ በኢትዮጵያዊነት አካልና ባሕርይ የሠራነው ነቢያችን ዳዊት፡ በቤተ-መንግሥቱ አስቀምጧቸው፡ በፍጹም ታማኝነት፡ ያገለግሉት ከነበሩት፡ ከኢትዮጵያዊው ባለሟሉ፡ ከኦርዮና የኦርዮ አንዲት ሚስቱ ከኾነችው፡ ከቤትሳባ፡ ስለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖትና ምግባር፡ ምን ያህል ተምሮና ተረድቶ፡ በመጨረሻ፡ ራሱን፡ በእውነተኛ ንስሓ አስተካክሎ፡ ለፍጹሙ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት እንዳበቃ አስተውላችኋል? ኋላ፡ ልጁ፡ ንጉሥ ሰሎሞንም፡ በንግሥት ማክዳ፡ ጥበባዊ ምሁርነትና ምስክርነት፡ በመጨረሻ፡ ራሱን፡ በእውነተኛ ንስሓ አስተካክሎ፡ እንዴት፡ ለፍጹሙ ኢትዮጵያዊነት እንደበቃ ማለት ነው።

አዎን! በቅድሚያ፡ ኢትዮጵያዊው ባለሟሉ ኦርዮ፥ ቀጥላም፡ ታማኟ የኦርዮ ሚስት፡ ቤትሳባ፡ ባሏ፡ በዳዊት የግፍ ውሳኔ፡ ከመገደሉ በፊት፡ በገረድነቷ፥ ኋላም፡ በሚስትነቷና በሰሎሞን እናትነቷ፡ ኹለቱም፡ ለጌታቸው፡ ለንጉሥ ዳዊት፡ በተጠየቁ ቊጥር፡ በየአንደበታቸው ያበረክቱ በነበረው ምክራቸው ብቻ ሳይኾን፥ ከዚያ በላይ፡ በሃይማኖታዊና በምግባራዊ፥ በታማኝነትና በጨዋነት አርአያነታቸው ጭምር፡ ለእርሱ፡ ለዳዊት ይሰጡት የነበረው ትምህርት፡ እስከኦርዮ የሞት ቤዛነትና እስከቤትሳባ የሰለባ መሥዋዕትነት በደረሰ ፍጹም የእውነተኛነት ብቅዓት የታየና የተረጋገጠ ለመኾኑ፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት ይበቃችኋል።

ይኸውም፡ ዳዊት፡ ከእነርሱ ላገኘው፡ ለዚህ የኢትዮጵያዊነቱ ዕውቀትና ጸጋ፡ የሰጠው ግምት፡ ከእስራኤላዊቱ በላይ፡ እጅግ የላቀ በመኾኑ፡ ስለራሱ ማንነት ብቻ ሳይኾን፡ ከእኛ ያገኘውን የቃል-ኪዳን ሰብአዊ ዘሩን ሳይቀር፡ በእስራኤላዊነት፥ ወይም፡ በሌላ ሳይኾን፡ በዚሁ፡ አምኖ በተቀበለበት፡ የኢትዮጵያዊነት ማሕፀን አማካይነት ብቻ ተላልፎ፡ ወደእኔ፡ ወደኢትዮጵያዋ ድንግል ማርያም እንዲደርስ ለማስቻል፡ ራሱ የከፈለውን፥ በይበልጥም፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት መገለጫ አካልና ባሕርይ የኾኑት፡ ባልና ሚስቱ፡ ኦርዮንና ቤትሳባ ጭምር፡ እንዲከፍሉ ያስገደዳቸውን ዋጋ ስትመለከቱት፡ ምን ያህል፡ በአንክሮና በተዘክሮ እንድትመሠጡ እንደሚያደርጋችሁ በእየራሳችሁ አስተውሉት!

አዎን! ታማኙ ኢትዮጵያዊ ኦርዮ፡ ሚስቱን፡ ቤትሳባን እንዲያይ፡ ካንዴም ኹለቴ፡ በአጥቂ ጌታው ቢታዘዝና ቢገደድም፥ ቢደለልና ቢደነገዝም፡ ከሚስቱ ጋር፡ ሲቀማጠል ከማደር ይልቅ፡ ታቦተ-ጽዮን፡ በድል አዝማችነት እየመራች ባለችበት ሰልፍ ላይ፡ በፊቷ፡ በሰማዕትነት ተወግቶና ተሠይፎ መውደቅን መምረጡ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትን፡ ምንነትና ማንነት፥ ይህም ማለት፡ እግዚአብሔራዊነት፡ በዳዊት ዘንድ ብቻ ሳይኾን፡ በመላዎቹ ሰብአውያን ፍጡሮቻችን ዘንድ ጭምር፡ ያለጥርጥርና ያለውልውል፡ ፍጹም ዕውቅናንና የተቀባይነት አክሊልን እንዲቀዳጅ አስችሎታል።

*ዳዊት፡ ታማኙን፡ ኢትዮጵያዊ አገልጋዩን፡ እንዲህ፡ በግፍ ካስገደለ በኋላ፡ ከቤትሳባ የወለደው፡ የመጀመሪያው ሕፃን ልጁ፡ ከዚህ፡ ከደረሰው ከባድ ኃጢኣት የተነሣ፡ ቅዱሱን የቃል ኪዳን ሰብኣዊ ዘሩን፡ ወደኢትዮጵያዊቷ ድንግል ንግሥት ማክዳ ሊያስተላለፍበት የበቃ ሊኾን ስላልቻለ፡ ያም፡ ኢትዮጵያዊ ሕፃን፡ በሥጋ ሞቱ ቅሥፈት፡ ለዚሁ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት፡ የበኵሉን የመሥዋዕትነት ድርሻ መክፈል ግድ ኾኖበት፡ ይህንኑ የፍርድ ጽዋውን ተቀብሎ አልፏል።*

*በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖቷና ምግባሯ፡ እንደኢትዮጵያዊው የቃል-ኪዳን ባሏ፡ እንደኦርዮ የጸናችው፡ ኢትዮጵያዊቷ ቤትሳባ፡ ኢትዮጵያዊው የቃል ኪዳን ጋብቻዋ በመሥዋዕትነት መፍረሱና ታማኙን የቃል-ኪዳን ባለቤቷን፡ በሞተ-ሥጋ ከማጣቷ ጋር፡ ይህን፡ አዲሱን ሕፃን፡ በቅሥፈት በመነጠቋ፡ የወረደባትን መራራ ኀዘን፡ በትዕግሥትና በመጽናናት ጽናት ተቋቁማ፡ የፈተናና የመከራ ገድሏን በድል አድራጊነት በመወጣቷ፡ ስለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት፡ ለንጉሡ፡ ለዳዊት፥ ከእርሱ ለወለደችው፡ ለኹለተኛው ወራሽ ልጁና ልጇ፡ ለሰሎሞንም ማስተማርዋን ቀጥላበት፡ ይህንኑ የተቀደሰ ዓላማዋን ከግቡ አድርሳለች።*

*በዚህ ኹኔታ፡ ከእስራኤላዊው አባቱ፡ ከንጉሥ ዳዊትና ከኢትዮጵያዊት እናቱ፡ ከቤትሳባ የተወለደው ሰሎሞን፡ አድጎና ለአካለ-መጠን ደርሶ፡ ለአባቱ ዙፋን ከበቃ በኋላ፡ አኹን በሚገኝበት አሳዛኝ፤ የአምልኮ ስሕተትና የኑሮ ድቀት ላይ ሣለ ነበር፡ ከዚህ ኹኔታው፡ ትታደገው ዘንድ፡ ልጃችንን ንግሥት ማክዳን፡ ጥበቧን፥ እርሱም፡ ኋላ፡ በኢየሱስ መሲሕነት ተገልጦ ስለእርሷ የተናገረውን፡ የእግዚአብሔር ቃል አስታጥቀን፡ እርሱ፡ ንጉሥ ሰሎሞን፡ በገናንነት ይኖርባት ወደነበረችው፡ ወደኢየሩሳሌም የላክናት።*

*አዎን! ኋላ፡ በፍጻሜው የሕይወት ዘመን፡ በልጇ በወዳጇ፡ በኢየሱስ መሲሕ፡* ***"ንግሥተ አዜብ ትትነሣእ፡ አመ ዕለተ ደይን፡ ምስለ ዛ ትውልድ፤ ወትትፋትሓ፥ ወታስተኃፍራ፤ እስመ መጽአት እምአጽናፈ ምድር፡ ትስማዕ ጥበቢሁ ለሰሎሞን፤ ወናሁ፡ ዘየዐቢ እምሰሎሞን፡ ሀሎ ዝየ።***

***"ንግሥተ አዜብ (ኢትዮጵያ)፡ በፍርድ ቀን፡ ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ፡ ትፋረደዋለች፤ ታሳፍረዋለችም። የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት፡ ከምድር ዳር መጥታለችና። እነሆም፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ፡ ከዚህ አለ።"*** *ተብሎ የተነገረላት፡ ይህችው ኢትዮጵያዊት ንግሥት ማክዳ፡ የሰሎሞን ሰብኣዊና እስራኤላዊ፥ ሥጋዊና ምድራዊ፥ ዓለማዊና ጣዖታዊ ጥበብ፡ ከእርሷ እግዚአብሔራዊና ኢትዮጵያዊ፥ መንፈሳዊና ሰማያዊ፥ ሃይማኖታዊና አምልኮታዊ ጥበብ ጋር፡ የቱን ያህል ይመሳሰል፥ ወይም፡ ይቀራረብ እንደኾነ፡ በዚሁ ጥበቧ ትፈትነው ዘንድ፡ ወደኢየሩሳሌም መምጣቷ፡ በእርግጥ እሙን ነው።*

ከእርሱ፡ ከሰሎሞን በሚበልጠው በኢየሱስ መሲሕ ጥበብነት፡ እግዚአብሔራዊዉን ዕውቀትና ኢትዮጵያዊዉን ትምህርት፡ ለሰሎሞን በማበርከት፡ ይህንኑ የተልእኮ ግዳጇን፡ በብቅዓት አከናውና፡ ወደአገሯ፡ በድል ፍሬያማነት መመለሷም፡ በፍጹም እውነት ነው። (፪ሳሙ. ፲፩፥ ፩-፳፯። ፲፪፥ ፩-፳፬። ማቴ. ፩፥ ፯፤ ፲፪፥ ፵፪።)

የእስራኤላዊው፡ የሰሎሞን አስተሳሰብና *ሥራው*፥ አምልኮውም ሳይቀር፡ ሰብኣዊና እስራኤላዊ፥ *ሥጋዊና* ምድራዊ፥ ዓለማዊና ጣዖታዊ ዝንባሌ ከብዶ ባመዘነበት፡ የጥበብ *መሠረት* ላይ *ታንፆ*፡ በሰፊው ጥርጊያ ጎዳና፡ በከፍተኛ ፍጥነት እየተካኼደ ያለ *መኾኑ*፡ በግልጽ የሚታይ ነበር።

ይህም እውነታ፡ ልጇ ወዳጇ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ኋላ፡ በእኔ፡ በድንግል ማርያም ሰውነት፡ በዚህ ዓለም ተገልጦ፡ በኢየሩሳሌም በሚያስተምርበት ጊዜ፡ በተናገራቸው፡ እንዲህ በሚሉት፡ መለኮታውያት ቃላቱ ተረጋግጧል፡-

**፩. "ኢይክል፡ አሓዱ ገብር፡ ለክልኤ አጋእዝት ተቀንዮ። ...ኢትክሉኬ፡ ተቀንዮ ለእግዚአብሔር ወለንዋይ። በእንተዝ፡ እብለክሙ፡- 'ኢትተክዙ ለነፍስክሙ፡ ዘትበልዑ፥ ወዘትሰትዩ! ወኢ ለሥጋክሙ ዘትለብሱ! አኮሁ ነፍስ፡ ተዐፅብ እምሲሲት? ወሥጋ፡ የዐፅብ እምዐራዝ? ነጽሩ አዕዋፈ-ሰማይ! እለ ኢይዘርኡ፤ ወኢየአርሩ፤ ወኢያስተጋብኡ ውስተ አብያት፤ ወአቡክሙ ሰማያዊ ይሴስዮሙ። አኮኑ፡ አንትሙ፡ ፈድፋደ፡ ትኄይስዎሙ!? መኑ እምኔክሙ፡ በተክዞ ዘይክል፡ ወስኮ፡ አሓደ እመተ፡ በዲበ ቆሙ!?'**

**"ወበእንተ ዐራዝኒ፡ ምንተኑ ትሔልዩ? ርእዩ ጽጌያተ ገዳም! ዘከመ ይልኅቁ፡ እንዘ ኢይጻምዉ፤ ወኢይፈትሉ። እብለክሙ፡- 'ከመ ሰሎሞን ጥቀ፡ ኢለብሰ፡ በኵሉ ክብሩ፡ ከመአሐዱ፡ እምእሉ። ወናሁ ሣዕረ-ገዳም ዘዮም ሀሎ፥ ወጌሠመ፡ ውስተ እሳት ይትወደይ፥ ወእግዚአብሔር፡ ዘከመዝ ያለብሶ፡ እፎ እንከ ፈድፋደ፡ ለክሙ!? አ ሕፁፃነ ሃይማኖት!?**

**"አንድ አገልጋይ፡ ለኹለት ጌቶች፡ መገዛት አይችልም። ...ለእግዚአብሔር እና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም። ስለዚህ፡ እላችኋለሁ፡- 'ለነፍሳችሁ ሕይወተ-ሥጋ ስትሉ፡ ስለምትበሉትና ስለምትጠጡት፥ ይህንኑ ሥጋችሁንም፡ ለመሸፈን ስትሉ፡ ስለሚያስፈልጋችሁ ልብስ፡ አትጨነቁ! ከምግብ ሲሳይ፥ ከጨርቅ ልብስም ይልቅ፡ በይበልጥ ሊያስጨንቋችሁ ይገቡ የነበሩትን፥ ለዚሁ በድን ሥጋችሁ፡ ሕይወትን ሰጥታ የምታኖራችሁን፡ ነፍሳችሁን፥ ለእርሷ፡ ለማትታይ ረቂቅ ነፍሳችሁም፡ ገዝፋ የምትታይበትንና የምትገለገልበትን፥ የምታገለግልበትንም አካለ-ሥጋን፡ ሳትጠይቁ፡ እንዲያው አግኝታችሁ የለምን? ሳይዘሩና ሳያጭዱ፥ እህላቸውንም የሚያከማቹበት ጎተራ ሳይኖራቸው፥ የሰማዩ አባታችሁ ብቻ የሚመግባቸውን፡ የሰማይ ወፎችን፡ እስኪ ተመልከቱ! እናንተ፡ ከእነርሱ ይልቅ፡ እጅጉን በብዙ፡ የምትሻሉ አይደላችሁምን? ከእናንተ መካከል፡ ማነው፡ በመጨነቅ፡ አንዲት ሥንዝርን፡ በቁመቱ ላይ መጨመር የሚቻለው?**

"ስለልብስስ፡ ለምን ትጨነቃላችሁ? እስኪ፡ የዱር አበቦች፡ እንዴት እንደሚያድጉ እዩዋቸው! አይደክሙም፤ አይፈትሉም። ነገር ግን፡ እላችኋለሁ፡- '<u>ሰሎሞን እንኳ፡ በዚያ ኹሉ ክብሩ፡ እንደአንዲቱ፡ አልለበሰም</u>። እነሆ፡ ዛሬ፡ እንዲያ፡ በአበቦች አሸብርቆ ያለውን፥ በበነጋው ግን፡ በበረሃው ፀሓይ ጠውልጎ፡ ወደእሳት እንደሚጨመር እንጨት የሚያቃጥለውን፡ ያን፡ የዱሩን ሣር፡ እግዚአብሔር፡ እንደዚያ አስጊጦ የሚያለብሰው ከኾነ፡ እናንተንማ፡ እንግዴህ፡ እንዴት፡ እጅግ አብልጦ አያለብሳችሁ!? እናንተ፡ ሃይማኖት የጎደላችሁ!? (ማቴ. ፮፥ ፳፬-፴።)

፪. የሰሎሞን፡ የጥበቡ ዋና ዓላማና ተግባር፡ በይበልጥ፡ ሥጋዊና ምድራዊ፥ ዓለማዊና እስራኤላዊ ርእየት ባለው፡ በቤተ-መቅደስ ሥራ ላይ ያተኮረ እንደነበረ ይታወቃል። የዚህንም አመለካከት እውነተኛነት፡ ከዚህ የሚከተሉት፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች፡ እየገላለጡና እያብራሩ ያረጋግጣሉ፡-

"ወአብእዋ [ለደብተራ-ስምዕ] ምስሌሆሙ፡ ...እስከአመ መዋዕለ ዳዊት፡ ዘረከበ ሞገሰ፡ በቅድመ-እግዚአብሔር፤ ወሰአለ ይርከብ፡ ማኀደሮ፡ ለአምላከ ያዕቆብ። ወዳእሙ፡ ሰሎሞን ሐነጸ ሎቱ፡ ቤተ። ወአኮሰ፡ ዘየኃድር ልዑል፡ ውስተ ግብረ እደ-ሰብእ፤ እስመ ከመዝ ይቤ ነቢይ፡- ‹'ሰማይኒ መንበርየ፤ ወምድርኒ፡ መከየደ እግርየ፤ አየኑ፡ ቤተ፡ ተሓንጹ ሊተ?' ይቤ እግዚአብሔር! 'ወአይኑ መካን ውእቱ፡ መካነ ምዕራፍየ? አኮኑ እደውየ፡ ገብራ ዘኵሎ!?'›

"[የምስክር-ድንኳኗ]፡ በእግዚአብሔር ፊት፡ ሞገስን እስካገኘው፡ እስከዳዊት ዘመን ቆይታ፡ በእርሱ ጊዜ፡ ከእነርሱ ጋር አገቧት፤ እርሱም፡ የያዕቆብ አምላክ፡ ማደሪያውን ያገኝ ዘንድ ለመነ። ይኹን እንጂ፡ ቤተ-መቅደሱን የሠራለት፡ ሰሎሞን ኾነ። ነገር ግን፡ ልዑል እግዚአብሔር፡ የሰው እጅ በሠራው ሕንጻ ውስጥ የሚያድር አይደለም። ነቢዩ፡ እንዲህ ሲል ተናግሯልና፡- ‹'ሰማይ፡ ዙፋኔ፥ ምድርም፡ የእግሬ መረገጫ ሲኾኑ፡ ታዲያ! ምን ዓይነት ቤት የሚያስፈልገኝ ኾኖ ነው፡ ለእኔ፡ ሌላ ሕንጻ ልትሠሩልኝ የምትሹት?' ይላል እግዚአብሔር፤ ወይስ፡ ማረፊያዬ ቦታ፡ የትኛው ሥፍራ ሊኾን ነው? ኹሉንስ፡ እጆቼ የሠሩት አይደለምን!?'› ተብሎ፡ ቀድሞ፡ በነቢያት የተነገረውንና በመጀመሪያው ሰማዕት፡ በቅዱስ እስጢፋኖስ የምስክርነት ደም የጸደቀውን እውነታ፥

ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሲሕ፡ "ወወፂአ እግዚእ ኢየሱስ፡ እምቤተ-መቅደስ፡ ሖረ። ወቀርቡ አርዳኢሁ፤ ወአርአይዎ፡ ንድቀ ሕንጻሁ፡ ለቤተ-መቅደስ። ወአውሥአ፥ ወይቤሎሙ፡- 'ትሬእዩኑ ዘንተ ኵሎ? አማን እብለክሙ! ኢይትኀደግ ዝየ፡ እብን ዲበ እብን፡ ዘኢይትነሠት።'

"ጌታችን ኢየሱስ፡ ከቤተ-መቅደስ ወጥቶ ኼደ። ደቀ መዛሙርቱም ፡ ወደእርሱ ቀርበው፡ የቤተ-መቅደሱን፡ የሕንጻ ግንባታ አሳዩት። እርሱም፡- 'ይህን ዅሉ፡ ታያላችሁን? እውነት እላችኋለሁ! ድንጋይ፡ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ፡ በእዚህ አይቀርም።' ብሎ መለሰላቸው።"

ደግሞም፡ "ንሥትዎ፡ ለዝንቱ ቤተ-መቅደስ! ወበሠሉስ ዕለት፡ አነሥኦ። ወውእቱሰ፡ በእንተ ቤተ-ሥጋሁ ይቤሎሙ።

"ይህን ቤተ-መቅደስ፡ አፍርሱት! በሦስተኛው ቀን፡ አነሣዋለሁ! እርሱ ግን፡ የተናገራቸው፡ ቤቱ ስላደረገው፡ ስለሥጋው አካል ነበር።" ባለው መለኮታዊ ቃሉ አጽንቶታል።

ተቃዋሚዎቹና ገዳዮቹ አይሁድም፡ "በአርባዓ ወስድስቱ ዓመት፡ ተሓንጸ ዝንቱ ቤተ-መቅደስ፤ ወአንተሰ፡ በሠሉስ መዋዕል ታነሥኦ?

"በአርባ ስድስት ዓመታት የታነጸውን፡ ይህን ቤተ-መቅደስ፡ አንተ፡ በሦስት ቀኖች ታቆመዋለህን?" ሲሉ፡ በጽነት በሰጡት፡ የተግዳሮት መልስ፡ እውነታውን አጉልተውታል። (ማቴ ፳፬፥ ፩-፪። ዮሐ. ፪፥ ፲፱-፳። የሐዋ. ፯፥ ፵፬-፵፱።)

በዚህ አንጻር ደግሞ፡ የልጃችን፡ የንግሥት ማክዳ፡ የሕይወቷ መመሪያ በኾነው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖትና ምግባር፡ በዚህ፡ በኢየሩሳሌም ጉዞዋ የተከሠተውንና የተንፀባረቀውን፡ የእኛን የእግዚአብሔርን እውነት፥ ከዚህ የተነሣም፡ በኢትዮጵያዊት እናቱ፡ በቤትሳባ በኩል፡ ወንድሟ ለኾነው፡ ለእስራኤላዊው ንጉሥ ሰሎሞን፡ ይህችው ንግሥት ማክዳ፡ በኢትዮጵያዊትነት እኅትነቷ፡ ያበረከተችውን ምዕዳኗን [ምክሯንና ተግሣፅዋን] በማስተዋል ተመልከቱት!

አዎን! ይህችው ኢትዮጵያዊት ንግሥት ማክዳ፡ የሰሎሞን ሰብኣዊና እስራኤላዊ፥ ሥጋዊና ምድራዊ፥ ዓለማዊና ጣዖታዊ ጥበብ፡ ከእርሷ እግዚአብሔራዊና ኢትዮጵያዊ፥ መንፈሳዊና ሰማያዊ፥ ሃይማኖታዊና አምልኮታዊ ጥበብ ጋር፡ የቱን ያህል ይመሳሰል፥ ወይም፡ ይቀራረብ እንደኾነ፡ በዚሁ ጥበቧ ትፈትነው ዘንድ፡ ወደኢየሩሳሌም መጥታ፡ ከእርሱ፡ ከሰሎሞን በሚበልጠው በኢየሱስ መሲሕ ጥበብነት፡ እግዚአብሔራዊዉን ዕውቀትና ኢትዮጵያዊዉን ትምህርት፡ ለሰሎሞን በማበርከት፡ ይህንኑ የተልእኮ ግዳጇን፡ በብቅዓት አከናውና፡ ወደአገሯ በድል ፍሬያማነት መመለሷን፡ ከዚህ ቀደም ብዬ ገልጬላችኋለሁ።

በዚህ ተልእኮዋ መሠረት፡-

በቅድሚያ፡ ለሥጋዊ ሥልጣኑና ለምድራዊ ግዛቱ፥ ለዓለማዊ ክብሩና ለእስራኤላዊ የብልጽግና ዝናው መስፋፋት ሲል፡ የአረማውያንንና የአሕዛብን ነገሥታት ሴቶች ልጆች፡ ከነአማልክቶቻቸው፡ በንግሥትነት በማግባት፡ ከተዘፈቀበት፡ ከጣዖታዊው አምልኮው፡ ወደእኛው፡ ወደእግዚአብሔራዊው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሥርዓተ-አምልኮ፡ በንስሓ እንዲመለስ፥

አስከትላም፡ የግልና ቤተሰባዊ አኗኗሩን፡ ሥርዓተ-አልባና አረማዊ ከኾነው፡ ብዙ ሚስቶችን ከማግባቱና አያሌ ቁባቶችን ከማስቀመጡ ልማድ፡ ራሱን፡ ፈጽሞ፡ በእውነተኛ ንስሓ በማንጻትና ክፉውን ልማድ በማስወገድ፡ እግዚአብሔራዊዉንና ኢትዮጵያዊዉን፡ የአንድ-ለአንድ ባልና ሚስትነትን ጋብቻንና ትዳራዊ ኑሮን የመመሥረትን ሥርዓት እንዲከተል፥

አያይዛም፡ ቀድሞ፡ በዘመነ-ሙሴ፡ ከኢትዮጵያዊው ዮቶር ተረድተው የተረከቧትንና ኋላ፡ በነቢዩ ሳሙኤል ምስፍና ጊዜ ግን፡ በራሳቸው፡ በእስራኤል ልጆች ክህደትና ዓመፅ ያጧትን፡ የእኛዋን፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችንን፡ አኹን መልሶ በመቀበል፡ ሥርዓተ-መንግሥቱን እንዲያስተካክል፥

በመጨረሻም፡ እርሱ ንጉሡ ሰሎሞን እየሠራው ያለው፡ የእስራኤል ልጆች ቤተ-መቅደስ፡ ወደፊት፡ ድንጋይ በድንጋይ ሳይቀር፡ ፈጽሞ የሚፈራርስ ሲኾን፥ እርሷ ንግሥት ማክዳ፡ ለእርሱ ያሳየችውና ያስተማረችው፡ የኢትዮጵያ ልጆች ቤተ-መቅደስ ግን፡ የእኛ እግዚአብሔራዊ ሕንጻ የኾነው፡ "ሰው" በመኾኑ፡ ይኸው፡ በእኛ፡ በእግዚአብሔር መልካችንና ከእኛ፡ ከእግዚአብሔር አብ፥ ወይም ከእግዚአብሔር እም፡ እንደአንዳችን፡ በወንድነት እና በሴትነት አምሳል የፈጠርነው ሰብአዊው ፍጡራችን፡ ለዘለዓለም ሕያው ኾኖ የሚኖር እንጂ፡ የማይፈርስ መኾኑን እንዲያውቅ፡ አጥብቃ በማሳሰብ፡ ከተግሣፅዋና ከማስጠንቀቂያዋ ጋር፡ ዝርዝርና አጠቃላይ ምክርዋን ሰጥታዋለች።

የኢትዮጵያ ልጆች፡ ይህንኑ ሰብአዊ ፍጡር፡ "ሕያዉና ዘለዓለማዊው የእግዚአብሔር ቤተ-መቅደስ ነው!" ብለው፡ ለእግዚአብሔራዊውና ለኢትዮጵያዊው ዘለዓለማዊ ሕይወት ለማብቃት ሲሉ፡ ከጋብቻና ከማሕፀን ጀምረው፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስና በኹለንተና ህልውናው፡ በፍጹም እኩልነት የሚንከባከቡትና የሚጠብቁት፥ የሚያገለግሉትና የሚያዘጋጁት መኾኑን፡ ይህችው ንግሥት ማክዳ፡ ለንጉሥ ሰሎሞን፡ አበክራ አስገንዝባዋለች።

ንግሥት ማክዳ፡ ይህን ምክርዋን፡ ለንጉሥ ሰሎሞን ካበረከተችው በኋላ፡ በፊትም፡ ገና፡ ወደኢየሩሳሌም ስትመጣ እንዳደረገችው ኹሉ፡ አኹንም ደግሞ፡ ወደአገርዋ፡ ወደኢትዮጵያ በምትመለስበት ጊዜ፡ እግረ-መንገድዋን ያረፈችበት "ጋዛ"፡ ከእስራኤላዊ ንጉሥ፡ በችሮታ እንደተሰጣት ተደርጎ እንደሚነገረው የፈጠራ ወግ ሳይኾን፡ ጥንት፡ ከምዝላቷ፡ ከመልከ-ጼዴቁ ኢትዮጲስ ጀምሮ፡ የኢትዮጵያ ርስት ኾኖ የኖረ መኾኑ፡ መዘንጋት የለበትም።

ይህም እውነታ፡ "ባኮስ" በሚል ስም የሚታወቀው፡ የኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ሕንደኬ ባለሥልጣንና የአዲስ ኪዳኑ፡ ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ፡ ወደኢየሩሳሌምና ከኢየሩሳሌም፡ ያደርጋቸው በነበሩት ጉዞዎቹ፡ ጋዛ፡ ማረፊያው እንደነበረ የሚተርከው፡ እንዲህ የሚለው፡ የቅዱሳት መጻሕፍታችሁ ዝክረ-ነገር ያረጋግጠዋል።

"ወነበቦ መልአከ እግዚአብሔር፡ ለፊልጶስ፤ ወይቤሎ፡- 'ተንሥእ! ወሑር፡ ጊዜ ቀትር፡ ፍኖተ በድው፡ ዘያወርድ እምኢየሩሳሌም ለጋዛ። ወተንሥአ፤ ወሖረ፤ ወረከበ ብእሴ፡ እምሰብአ ኢትዮጵያ፣ ኀፅዋ ለሕንደኬ፡ ንግሥተ ኢትዮጵያ፥ ወመጋቢሃ ውእቱ፡ ላዕለ ኵላ መዛግብቲሃ፤ ወሖረ ኢየሩሳሌም ይስግድ።

"የእግዚአብሔር መልአክ፡ ፊልጶስን ተናገረው፤ አለውም፡- 'በቀትር ጊዜ፡ ተነሥተህ፡ ከኢየሩሳሌም፡ ወደጋዛ በሚያወርደው፡ በምድረ-በዳው መንገድ ኺድ!' ተነሥቶም ሲኼድ፡ ከኢትዮጵያ ሰዎች፡ ሊሰግድ፡ ወደኢየሩሳሌም ኼዶ የነበረ፥ የኢትዮጵያ ንግሥት፡ የሕንደኬ፡ ባለሟሏ፥ በገንዘቧም ላይ ኹሉ የሠለጠነ ምሉኳ የኾነ፡ አንድ ሰውን አገኘ።" (የሐዋ. ፰፥ ፳፮-፳፯።)

እንግዴህ፡ በእውነተኛ ማንነቷና ምንነቷ፡ በእኛ በእግዚአብሔር ዘንድ፥ በእውነተኞቹ ፍጡሮቻችንም ዘንድ፡ እንዲህ፡ በግልጽና በእውን ታውቃ፡ በሕያውነት የኖረችው፥ ዛሬ ያለችውና ወደፊትም የምትኖረው ልጃችን ንግሥት ማክዳ፡ ጥንት፡ ከአዳምና ከሔዋን፥ ቀጥሎ፡ በኖኅና በሓይከል፥ ተያይዞም፡ "መልከ-ጼዴቅ" በተባለው፡ በኢትዮጲስና "ሳሌም" በተባለችው፡ በእንተላ፥ ከዚያም፡ በአብርሃምና በሣራ፥ በኬጡራም፥ ተከታትሎም፡ በሙሴና በሲጳራ፥ በመጨረሻ፡ በዳዊትና በቤትሳባ በኩል፡ ቀደም ብሎ፡ ለአራት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት ያህል፡ ያለማቋረጥ ተራዝሞ፡ ከእኛ ጋር፡ በቅዱሱ ኪዳን በመዋዋል፡ እኒህን የመሰሉ፡ የእኛ "የእግዚአብሔር ልጆች!"፥ ይልቁንም፡ ከሌሎቹ፥ ከእስራኤልም ልጆች ለይተን ለመጥራት ስንል፡ የእኔ፡ "የኢትዮጵያ ልጆች!" ያልናቸው ሰብኣውያን ፍጡሮቻችን፡ በኪዳነ ልቦና ተቀብለው፡ ከትውልድ ወደትውልድ፡ ሲወርድ ሲዋረድ፡ ባልተቋረጠ ህልውናቸው፡ በእኛ፡ በእግዚአብሔር እውነትና መንፈስ፡ ሲያካኼዱት የኖሩት፥ ፍጹም የኾነው አምልኮተ-እግዚአብሔራቸው ያስገኛት ናት።

አዎን! እርሷ፡ በልጄ በወዳጄ በኢየሱስ መሲሕ ቃል፡ ሰሎሞንና በዘመኑ የነበረው ትውልድ፡ የሚገኙበትን ኹኔታ ሰምታ፡ በኢትዮጵያነቷ፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት መሲሓዊ ዕውቀትና ጥበብ፥ መልእክትና ምሥራቹን፡ ለሰሎሞንና በዘመኑ ለነበረው፡ ለዚያ ትውልድ ልትገልጥና ልታስተምር፥ ልታደርስና ልትሰብክ፡ ወደኢየሩሳሌም ተጉዛ፡ ተልእኮዋን፡ በመልካም ፍሬያማነት ፈጽማ፡ ወደአገርዋ ወደኢትዮጵያ የተመለሰች ናት።

የእርሷ ነገር፡ በዚህ ብቻ የተወሰነም አይደለም፤ በመሲሕነቱና በጥበቡ፡ ከሰሎሞንና ከጥበቡ የሚበልጠው እርሱ ልጁ ወዳጁ ኢየሱስ፡ በሕያዋንና በሙታን ላይ፡ የመጨረሻውን ብያኔ ሊሰጥ፡ በሚመጣበት ጊዜ፡ ኢትዮጵያዊት ልጃችንን፡ ንግሥት ማክዳን ተቀብሎ ያስተናገደውን፡ የሰሎሞንንና በዘመኑ የነበረውን ትውልድ ፈለግ ባለመከተል፡ የልጁን የወዳጁን ትምህርቱንና ጥበቡን ብቻ ሳይኾን፡ ራሱንም እንኳ፡ በእግዚአብሔር ልጅነቱ ለመቀበል፡ "እንቢ!" ብሎ፡ በመስቀል ሥቃይ፡ እስከመግደል የደረሰውን፡ ያን የኋለኛውን የእርሱን ዘመን፡ ክፉና ከሃዲ፥ ዓመፀኛና አመንዝሪ ትውልድ፡ በእርሱው ፊት፡ በዚያው፡ የሃይማኖትና የምግባር ጥበቧ የምትፋረደው፡ ይህችው፡ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ መኾኗን እንደተናገረላት፡ መላው ዓለም በተቀበላቸው የሃይማኖት መጻሕፍቶቹ ውስጥ ተመዝግቦ ስለሚነበብ፡ በኹላችሁ ዘንድ ይታወቃል።

"የሳባ ንግሥት" በመባል የምትታወቀው፡ ይህችው ንግሥት ልጃችን ማክዳ፡ "ኢትዮጵያ" ለኾንሁት፡ ለእኔ፡ ለድንግል ማርያም፡ ሰብኣዊት ጥላና ቀዳሚት አርአያ፥ አብነትና ምዝላቴ ናት። ይህን እውነታ የማያውቅ፡ ሰብኣዊ ፍጡራችን ካለ፡ እንግዲህ ወዲህ ይወቅ!

ስለዚህ፡ ያ ኹሉ፡ በእርሷ ላይ በሓሰት የተነገረውና የተጻፈው፡ የነቀፋና የዘለፋ፥ የውርደትና የስድብ ቃል፡ በቀጥታ በእኔ ላይ እንደተሠነዘረ የሚቆጠር ስለኾነ፥ ይህም የድፍረት ድርጊት፡ "በእንተዝ፡ እብለክሙ፡- 'ኵሉ ኃጢኣት፥ ወፅርፈት፡ ይትኀደግ ለሰብእ፤ ወዘሰ፡ ፀረፈ ዲበ መንፈስ ቅዱስ፡ ኢይትኀደግ ሎቱ። ወዘሰ፡ ነበበ፡ ቃለ፡ ላዕለ ወልደ እጓለ እመሕያው፡ ይትኀደግ ሎቱ፤ ወዘሰ፡ ነበበ፡ ላዕለ መንፈስ ቅዱስ፡ ኢይትኀደግ ሎቱ፤ ኢ በዝ ዓለም፤ ወኢ በዘይመጽእ።

"ስለዚህ እላችኋለሁ፡- 'ኃጢኣትና ስድብ ኹሉ፡ ለሰዎች ይሰረይላቸዋል፤ ነገር ግን፡ መንፈስ ቅዱስን ለሰደበ፡ አይሰረይለትም። በማርያም ልጅ ላይ፡ ቃልን የተናገረ ይሰረይለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ግን፡ ቃልን የተናገረ፡ በዚህ ዓለም ኾነ፥ በሚመጣው፡ አይሰረይለትም።" ሲል፡ ልጁ ወዳጁ፡ ኢየሱስ መሲሕ ባሰማው ቍርጥ ቃሉ መሠረት፡ መንፈስ ቅዱስን እንደመስደብ የሚቆጠር ስለኾነ፡ የዚህ ኃጢኣት አድራጊዎች ኹሉ፡ በየግላቸው በሚፈጽሙት የንስሓ ምግባራቸው፡ እየራሳቸውን፡ ከዚሁ ኃጢኣታቸው ካላነጹ በቀር፡ ከፍዳው እንደማያመልጡ፡ መገንዘብ ይኖርባቸዋል። (ማቴ. ፲፪፥ ፴፩-፴፪።)

## መለኮታዊ የፍርድ ውሳኔ፡

### በዐውደ-ነገሥት፥ በፍትሐ ነገሥትና በክብረ-ነገሥት ላይ የተሰጠ።

እንግዴህ፡ ይህችው ንግሥት ልጃችን ማክዳ፡ ቀደም ብላችሁ፡ ከእኔው አንደበት ከሰማችሁት፡ በአፈ-ታሪክ ከተነገረባትና "ክብረ-ነገሥት" በምትሉት መጽሓፋችሁ ከተመዘገበባት፡ የስም ማጥፋትና የሓሰት ቃል ኹሉ፡ ፈጽማ ነጻ መኾኗን፡ ፍጥረታተ-ዓለማቱ ኹሉ፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ፡ እነሆ፡ በይፋ ዕወቁት!

ከዚህም ጋር፡ የማሳውቃችሁ ዓቢይ ቁም-ነገር አለ፤ ይኸውም፡ በአንድ ወገን፡ በመላው የሰማይና የምድር ፍጥረታተ-ዓለማት ዘንድ በሰፈነችው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ውስጥ፡ በእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያምነቴ፡ "ኢትዮጵያ" በተባልሁበት ስሜ በምትጠራውና ርስት ጕልቴ በኾነችው ምድሬ ላይ፡ የእኔ፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" የተባሉት ሕዝቤ፡ ጥንት አስቀድመው፡ ከእኛ፡ በፈቃዳቸው ተቀብለውና በመካከላቸው መሥርተው፥ አጽንተውትም የሚኖሩበት፡ እግዚአብሔራዊ የኾነ፡ ሰብኣዊና ሕዝባዊ፥ ግለሰባዊና ቤተሰባዊ፥ ማኅበራዊና ኅብረተሰባዊ፥ ሃይማኖታዊና ምግባራዊ፥ ብሔራዊና መንግሥታዊ፡ የጋብቻና የትዳር አኗኗር ሥርዓታችን መኖሩ ነው።

በሌላው ወገን ደግሞ፡ የተቃዋሚዎቼ የባዕዳኑ አሪታውያን አይሁድና የኦርቶዶክሳውያኑ ግብፆች እንጂ፡ የእኔ፡ የኢትዮጵያ ያልኾኑ፡ <u>*ዐውደ-ነገሥት፥ ፍትሐ-ነገሥትና ክብረ-ነገሥት*</u> የተባሉ የሰዎች መጻሕፍታቸው፡ በቀንደኛው ጠላት በዲያብሎስ አበጋዝነት፥ እንዲሁም፡ በጭፍሮቹ፡ ርኩሳን መናፍስትና ክፉ ሰዎች መሠሪ አገልጋይነትና መሣሪያነት፡ በዚችው፡ በቀደስኋት ምድሬ ላይና በዚሁ በባረክሁት ሕዝቤ መካከል፡ ሠርገው ገብተው፡ ሲያካኼዱና ሲፈጽሙ የኖሩትን ጉልህና ሥውር፥ ግዙፍና ረቂቅ፡ የጥቃት ዘመቻ ባጭሩና በጥቂቱ ስሙት!

እርሱም፡- "ልጆቼ!" ለምላቸው ሕዝቤ፡ በሥጋ፥ በነፍስና በመንፈስ፡ ያጎናጸፍናቸውን፡ ፍቅርንና ሰላምን፥ ዕረፍትንና ደስታን፥ ዕውቀትንና ብልጽግናን አሳጥተው፥ በእነዚያ ፋንታ፡ መከራንና ሥቃይን፥ ልቅሶንና ዋይታን ብቻ ተክተው፥ መልካሙን ህልውናቸውን፡ ለዝንተ ዓለም ሲያመሰቃቅሉበትና ሲያምሱበት፥ ሲያቃውሱበትና ሲያማስበኑት፥ ሲያጣምሙበትና ሲያጠፋፉበት ያሳለፉት፡ ረዥሙ ህልውናቸው ነው።

ይህም ብቻ አይደለም፡ እኔና ልጄ ወዳጄ፡ በመሥዋዕትነታችንና በቤዛነታችን ላዘጋጀንላቸው ንስሓና ቅዱስ ቊርባን፡ እንዲበቁ በማድረግ ፋንታ፡ ወንዶቹንም፡ ሴቶቹንም ልጆቼን፡ ገና ከልጅነታቸው ጀምረው፡ ወደእነዚያ ጸጋዎቻችንና በረከቶቻችን እንዳይቀርቡ፡ በማስፈራራት፡ እንዲያውም፡ ሲያርቋቸውና በቀጥታ፡ ወደተለያየ የአምልኮ ባዕድ ተገዢነትና አገልጋይነት እየሰደዱ ሲዳርጓቸው፥ እርስ በርሳቸው ሲያለያዩዋቸውና ሲያጣሏቸው፥ ሲያናክሷቸውና ሲያዋጓቸው፥ ደም ሲያፋስሷቸውና ሲያጋድሏቸው የኖሩ መኾናቸው ነው።

በዚህ ረገድ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ውስጥ፡ **በመጀመሪያ፡ የክብረ-ነገሥቱ መጽሓፍ፡ ነፍሳዊ በኾነው፡ በቤተ-ሕዝቡ፥ ቀጥሎ፡ ፍትሓ-ነገሥቱ ደግሞ፡ ሥጋዊ በኾነው፡ በቤተ-ምልክናው፥ በመጨረሻ፡ ዐውደ-ነገሥቱም እንዲሁ፡ መንፈሳዊ በኾነው፡ በቤተ-ክህነቱ፡** በሦስቱም፡ የአገልግሎት ዘርፎቻችን ውስጥ፡ እንዴት ሠርገው፡ በምሥጢርና በብልሃት፥ በትጋትና በንቃት ሲሠሩ በመኖራቸው፡ ለእነርሱ፡ ለተቃዋሚዎቼ፡ ለባዕዳኑ ኦሪታውያን የአይሁድ ካህናትና ለኦርቶዶክሳውያኑ ግብፆች መነኮሳት፡ ፍሬያማ ውጤትን ሊያስገኙ እንደቻሉ፡ ምድሬና ሕዝቤ፡ ዛሬ ያሉበትን ኹኔታ መመልከቱ ይበቃል።

እንግዴህ፡ ይህን ከመሰለው፡ ሰይጣናዊ ድርጊታቸውና ክፉ ውጤታቸው የተነሣ፡ ከዚህ የዐዋጅ ቃሌ በኋላ፡ እነዚሁ፡ በመሠረታቸውና በኹለንተናቸው፡ አፅራረ-እግዚአብሔርና አፅራረ-ኢትዮጵያ፥ አፅራረ-ማርያምና አፅራረ-ክርስቶስ የኾኑት፡ <u>ዐውደ-ነገሥት፥ ፍትሓ ነገሥትና ክብረ-ነገሥት</u> የተባሉ የሰዎች መጻሕፍት፡ በማንኛውም ሰብኣዊ ፍጡራችን ዘንድ፡ በምንም መንገድና ይዘት፡ በሥውርም ኾነ በይፋ፡ ተቀባይነትና ተፈጻሚነት እንዳያገኙ፥ ከተቀደሰችው ምድሬና ከባረክሁት ሕዝቤ መካከል፡ ለመቼውም ጊዜ፡ ፈጽመው እንዲወገዱ የተደረገ መኾኑን፡ ይኸው፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ አስታውቄአችኋለሁ።

ከእኔ የተሠወረ ማንም፥ ወይም፡ ምንም የለምና፡ "ልጆቼ!" ከምላቸው ሕዝቤ መካከል ብቻ ሳይኾን፡ ከመላው ዓለም ሰብኣውያን ፍጡሮቻችን መካከልም ጭምር፡ ይህን የዐዋጅ ቃሌን ባለመቀበል፡ ሳይፈጽሙ የሚቀሩ፡ ወንዶችም፥ ሴቶችም ቢገኙ፡ ከእኔ እግዚአብሔራዊ እናትነት ብቻ ሳይኾን፡ ከእግዚአብሔር አብ አባትነት፥ ከልጄ ከወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ወንድምነት፥ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም የአንድነት ጓደኝነት የተለዩ መኾናቸውን እንዲገነዘቡት ይኹን!

## «ያዘጋጀንላችሁ ሕይወት፡ በሕያዋን ዓለም የምትኖሩበትን እንጂ፡ በሙታን ዓለም የምትጠፉበትን አይደለም።»

ይህን የዐዋጅ ቃሌን ከማብቃቴ በፊት፡ በማጠቃለል የምገልጥላችሁ ቍም-ነገር አለኝ፤ ይኸውም፡ በእኛ በኩል፡ እስካኹን ምንም ሳንታክት፡ እንዲህ፡ የምንደክምላችሁ፡ እንዲያው አለመኾኑን፡ አኹንም፡ እንደገና አሳውቃችኋለሁ! አዎን! እንድትኖሩባት፡ አዘጋጅተን በሰጠናችሁ፡ በዚች ምድር ላይ፡ "ክፋትና ጥፋት፥ ኃጢአትና ሞት" ብላችሁ፡ ራሳችሁ፡ በእየራሳችሁ ላይ ያመጣችሁትን፡ የሥቃይ አኗኗር፡ እየራሳችሁ፡ በገዛ እጃችሁ፡ በቀላሉና በፍጥነት አስወግዳችሁ፡ ነፍሳችሁ፡ በሥጋዋና በመንፈሷ የምትናፍቀውን፡ መልካምና ዘለዓለማዊት የኀነት ሕይወት፡ አኹን፡ ከዚች አፍታ ጀምራችሁ፡ ለመኖር እንድትችሉ ሊያሳምናችሁና ሊያበቃችሁ ሲል፡ ልጄ ወዳጄ ኢየሱስ መሲሕ፡ በዚህ ዓለም፡ ዐብሯቸው ለነበሩት፥ እንደእናንተ ላፈቀራቸውና ላቀረባቸው ወንድሞቼና እኅቶቼ የከሠተውን ዕፁብ ድንቅ የህልውና እውነታ፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ መጨረሻ ላይ፡ አክዬ እንዳሰማችሁ ስላሳሰበኝ፡ እንዲህ የሚለውን ቃሉን፡ ይኸውላችሁ ስሙት!

እያንዳንዳችሁ ልጆቼ! በሰውነት ያስገኘኋችሁ ፍጡሮቼም! ወንዶቼም! ሴቶቼም! ኹላችሁም! በእኔ የዐዋጅ ቃል ሳይቀር፡ ተደጋግሞ የተነገራችሁ፡ ይህን፡ ፍጹም መልካምና የተሟላ ዓለም አዘጋጅተን፥ በመልካችንና በጾታችንም፡ ከእኛ እንደእያንዳንዳች አድርገን፡ የፈጠርናችሁ፡ እንደእኛ፡ በእግዚአብሔራዊነትና በሕያውነት እንድትኖሩት እንጂ፡ አኹን፡ እያንዳንዳችሁ፡ እየራሳችሁን እያዘጋጃችሁ ለምትገኙበት አለመኾኑን አረጋግጦ የሚያስረዳውና የሚያስገነዝበው፡ እንዲህ የሚለው፡ <u>ልጄ ወዳጄ ኢየሱስ መሲሕ፡</u> የተናገረው ቃሉ ነው፡-

**"አነ ውእቱ፡ ትንሣኤ፥ ወሕይወት። ዘየአምን ብየ፡ እመኒ ሞተ፡ የሐዩ። ወኵሉ፡ ዘሕያው፥ ወየአምን ብየ፤ ኢይመውት ለዓለም።"**

**"ትንሣኤ እና ሕይወት፡ እኔ ነኝ። የሚያምንብኝ፡ ቢሞት እንኳ፡ ሕያው ነው። ሕያው የኾነ፥ የሚያምንብኝም፤ ለዘለዓለም አይሞትም።"** (ዮሐ. ፲፩፥ ፳፭።)

ዛሬ በምድር ላይ ከምትኖሩ፡ ከእናንተ ልጆቼና የሰው ወገኖች ፍጡሮቼ መካከል፡ ይህን፡ የልጄ የወዳጄ የኢየሱስ መሲሕን ቃል፡ በትክክል ዐውቃችሁትና በእውነት ተረድታችሁት ያመናችሁበት፥ በእርግጥም፡ ሕይወት አድርጋችሁት የምትኖሩት፡ ስንቶች ትኾናላችሁ? ለዚያውስ፡ የምትገኙ ካላችሁ አይደለምን? ቢቀር ቢቀርማ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ልጆቼ፡ በዚህ ዕውቀትና ለዚህ እምነት፥ በዚህ እውነትና ለዚህ ሕይወት የበቃችሁ መኾን ይኖርባችኋል።

አለዚያማ፡ ልጄ ወዳጄ ኢየሱስ መሲሕ፡ "'እትሉከኑ እግዚኦ!? ወባሕቱ፡ አብሐኒ፡ እሑር ቅድመ፡ እቅብሮ ለአቡየ።'

"'አቤቱ፡ ልከተልህን!? ነገር ግን፡ አስቀድሜ፡ አባቴን እቀብር ዘንድ፡ ፍቀድልኝ!' ላለው፡ ለአንዱ ደቀ-መዝሙሩ፡ "'ኅድጎሙ፡ ለምውታን፡ ይቅብሩ ምውታኒሆሙ። ወአንተሰ፡ ሑር! ወስብክ፡ መንግሥተ-እግዚአብሔር!'

"'ሙቶቻቸውን ይቀብሩ ዘንድ፡ ሙቶችን ተዉዋቸው! አንተ ግን፡ ኺድ! የእግዚአብሔርን መንግሥት ምሥራች ስበክ!'" ብሎ የተናገረው ቃሉ፡ በእያንዳንዳችሁ ላይ የሚደርስባችሁ ይኾናል። (ሉቃ. ፱፥ ፶፱-፷።)

ለመኾኑ፡ በዚህ ረገድ፡ እንዲህ የምትለውን፡ ይህችን፡ የእኛን የእግዚአብሔርን እውነት ታውቃላችሁ? በእኛና በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን የማያምን ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ፡ ሙት እንደኾነ የምታስታውቀዋን፡ ይህችን፡ የእኛን የእግዚአብሔርን እውነት፡ በእርግጥ የምታውቁ፥ አውቃችሁም፥ በእምነት ተቀብላችሁ፡ ሕይወት አድርጋችኋት የምትኖርዋት ስንቶች ናችሁ?

ዛሬ፡ ይኸው፡ እናንተም ጭምር፡ ተካፋዮቹ የኾናችሁበት፡ ይኼ፡ በምድር ላይ እየተርመሰመሰ፡ "በሥጋዊ ዕውቀቱና እውነቱ፥ እምነቱና ሕይወቱ ብቻ እየኖርሁ ነኝ!" የሚለው ሰብአዊው ፍጡራችን ኹሉ፡ በሙሉ፡ እየተንቀሳቀሰበት ያለው ህልውናው፡ በእኛ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ በሕያዋን ሕይወት የሚኖር ሳይኾን፡ በሙታን [በሙቶች] ዓለም የሙላት ጎርፍ ውኃ ተጥለቅልቆ፡ እንደሚንሳፈፍ ሬሳ፡ በጊዜያዊነት በመንገዋለል በመኾኑ፡ ከመካከሉ፡ "ሞተ" ብሎ የሚቀብረው በድኑ ሬሳም ኾነ፡ "ሕያው ነኝ!" የሚለው ቀባሪውም፡ ኹለቱም ወገኖች፥ ኹሉም፡ "ሙታን = ሙቶች" ተብለው፡ በልጄ በወዳጄ በኢየሱስ ቃል፡ "ሙታንን ተዉዋቸው! ሙታናቸውን ይቅበሩ!" የተባሉት፡ ለዚህ አይደለምን?

ታዲያ! ዛሬ፡ ኹላችሁም የምትኖሩት፡ በዚሁ በሞት ዓለም መኾኑን፡ እየራሳችሁ፡ በእየራሳችሁ እየመሰከራችሁ አይደለምን? አዎን! ነው እንጂ። የትንሣኤ ልጆች ሣላችሁ፥ እናንተም፡ በግብዙ ክርስቲያንነታችሁና ውሸታችሁ፡ "የትንሣኤ ልጆች ነን!" እያላችሁ፥ ነገር ግን፡ በዚህ አንጻር፡ አኗኗራችሁ፡ የሞት፥ ዝግጅታችሁም፡ ለሞት፥ ፍጻሜያችሁም፡ ሞትና መቃብር፥ ኃዘንና ለቅሶ፥ እድርና ጥቁር ልብስ ኾኖ፡ ይኸው እየታየ አይደለምን?

እኛ፡ እግዚአብሔር፡ ፍጥረታተ-ዓለማቱን ፈጥረን ከማዘጋጀታችን ጀምረን፡ እናንተን፡ በመልካችንና ከእኛ፡ እንደእያንዳንዳችን አድርገን አስገኝተናችሁ፡ በፍጹም መልካም ሕይወት ብናኖራችሁ፥ ያንን ስላማሰናችሁት፡ እኔና ልጄ ወዳጄ ኢየሱስ መሲሕ፡ እንደእናንተው ሰው ኾነን፡ ታላቁን ቤዛነት ከፍለን፡ በትንሣኤያችንና በዕርገታችን፥ በርደተ መንፈስ ቅዱሳችንም ጸጋና በረከት፡ ወደቀደመው የክብር ቦታችሁ መለስናችሁ እኮ!

እናንተ ግን፡ እየራሳችሁን፡ ለዚያ ጸጋና በረከት፡ በማብቃት ፋንታ፡ አኹንም፡ እንደገና፡ ግብረ-ሰዶምን ለመሰሉ፡ ለመጨረሻ የኃጢአት ዝቅጠት ዓይነቶች ወደዳረገ ምውትነታችሁ፡ እየራሳችሁን መመለስን ስለመረጣችሁ፡ ይህ፡ የልጁ የወዳጁ የኢየሱስ መሲሕ ልዩ መልእክት፡ በእኔ፡ በእናቱ የዐዋጅ ቃሌ እንዲደርሳችሁ መጠየቅን አስፈላጊ አደረገው።

አዎን! ልጄ ወዳጄ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ እኅቶቹን ባፈቀራቸውና ባቀረባቸው የአልዓዛር ትንሣኤ፡ እንዲያ እውን ኾኖ፡ በገቢርና በግዘፍ፡ በሕያውነት እንዲፈጸም ያደረገው፡ እንዲያው ያለአንዳች ታላቅ ምክንያት እንዳልነበረ፡ ልታውቁት ያስፈልጋችኋል። ይኸውም፡ በዚያ፡ የአልዓዛር ትንሣኤ ጊዜ ኾነ፡ ከዚያን በፊት ኹሉ፡ ያ፡ **"ዘየአምን ብየ፡ እመኒ ሞተ፡ የሐዩ። ወኵሉ፡ ዘሕያው፥ ወየአምን ብየ፤ ኢይመውት ለዓለም።"**

**"የሚያምንብኝ፡ ቢሞት እንኳ፡ ሕያው ነው። ሕያው የኾነ፥ የሚያምንብኝም፤ ለዘለዓለም አይሞትም።"** እያለ፡ ልጄ ወዳጄ ኢየሱስ መሲሕ ያስተምራቸው የነበረውን ቃሉን፡ በዘመኑ የነበሩት ሕዝብ፡ በእርግጥና በትክክል ገብቷቸው፡ በእምነት የተቀበሉት፥ አምነውም፡ ሕይወት አድርገው ሊኖሩት የቻሉ አለመኾናቸውን ስለተረዳ፡ ቃሉ፡ በተግባር ላይ ሲውል፡ ምን ማለት ኾኖ እንደሚገኝ ሊያሳውቃቸው፡ አልዓዛርን፥ ከነእኅቶቹ፡ ከማርታና ከማርያም ጋር፡ ለዚህ ዓላማው፡ የመረጣቸው መኾኑ ነው። (ዮሐ. ፩፥ ፩-፶፫።)

አዎን! አልዓዛርና እኅቶቹ፡ በልጄ በወዳጄ በኢየሱስ መሲሕ፡ በእውነትና በመንፈስ እስካመኑባት አፍታ ድረስ፡ ይንቀሳቀሱ የነበሩት፡ በሥጋ ህልውና ብቻ ስለነበር፡ በእውንና በእኛ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ "ሙታን"፥ "የሞቱ" ነበሩ። ልክ፡ አዳምና ሔዋን፡ "አትብሉ!" ያልናቸውን፡ ያን፡ የእኛን የፈጣሪያቸውን ቃል፡ በተላለፉ ጊዜ፡ "ትሞታላችሁ!" የተባለው ፍርድ ተፈጽሞባቸው፡ የእኛን፡ የእግዚአብሔርን ጸጋ ተገፍፈውና ከእኛ፡ ከእግዚአብሔር የገነት ሕይወት ወጥተው፡ በዲያብሎስ የክፋት አገዛዝና በኃጢአት ቀንበር፥ በሞት የፍርድ ቅጣትም ሥር ይኖሩ እንደነበረው ማለት ነው።

አልዓዛርና እኅቶቹ፡ ማርታና ማርያም፡ በልጄ በወዳጄ በኢየሱስ መሲሕ፡ በእውነትና በመንፈስ ባመኑባት አፍታ ግን፡ እነዚያ "ሙታን" የነበሩት፡ እነዚሁ፡ አልዓዛርና እኅቶቹ፡ ከሞት ተነሥተው፡ "ሕያዋን" ኾኑ!

በዚህ ጊዜ፡ **"ዘየአምን ብየ፡ እመኒ ሞተ፡ የሐዩ።"**

**"የሚያምንብኝ፡ ቢሞት እንኳ፡ ሕያው ነው።"** የሚለው ቃል ተፈጸመላቸው።

ገና ባላመኑበት ጊዜ፡ ባለማመናቸው፡ "ሙታን" የነበሩት፡ አልዓዛርና እኅቶቹ፡ ባመኑ ጊዜ ግን፡ "ሕያዋን" ኾነው እየኖሩ ናቸውና፡ **"አልዓዛር፡ በቃ! እንግዴህ ወዲህ አይሞትም!"** ብለው ነው፡ እርሱም፥ እነርሱም አምነውና ተማምነው መቀመጥ ይገባቸው የነበረው።

ነገር ግን፡ እነርሱና እንደእነርሱ፡ "አምነናል!" ያሉት፡ ደቀ-መዛሙርቱ ጭምር፡ ገና ይገኙበት የነበረው፡ የእምነት ብቅዓታቸው ደረጃ፡ "ይሞታል!"ን እንጂ፡ "አይሞትም!" የሚለውን፡ የሃይማኖታቸውን የእውነት ፍሬ ስላልነበረ፡ ይህን፡ አለማመናቸውን፥ ይህን፡ የሃይማኖታቸውን ጒድለት በማጋለጥ፥ አልዓዛር፡ በመለኮታዊው ቃል መሠረት፡ ያልሞተ፥ እንግዴህ ወዲህም፡ ሊሞት የማይችል መኾኑን አረጋግጦ ለማሳየት፡ ልጀ ወዳጀ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ እንደገና መጥቶ፡ ከመቃብር እንዲያስነሣው አስፈላጊና ተገቢ ኾነ። በዚህ ጊዜ፡ ያ፡ ወኵሉ፡ ዘሕያው፥ ወየአምን ብየ፣ ኢይመውት ለዓለም።"

"የሚያምንብኝ፡ ቢሞት እንኳ፡ ሕያው ነው። ሕያው የኾነ፥ የሚያምንብኝም፣ ለዘለዓለም አይሞትም።" የሚለው ቃል ተፈጸመላቸው።

ታዲያ! ለዚህ ካልኾነ በስተቀር፡ ለምንድር ነው፡ የአልዓዛር እኅቶች፡ "እግዚእነ! ናሁ፡ ዘታፈቅር ይደዊ!

"ጌታ ሆይ! እነሆ፡ የምትወድደው [አልዓዛር] ታምሟል!" ብለው፡ ወደልጀ ወዳጀ ኢየሱስ መሲሕ፡ በላኩበት ጊዜ፡ መልእክታቸውን እንደሰማ፡ ለደቀመዛሙርቱ፡- "ዝንቱ ደዌ፡ ኢኮነ ለሞት፤ አላ፡ በእንተ ስብሓተ እግዚአብሔር፤ ወከመ ይሰባሕ ወልደ-እግዚአብሔር፡ በእንቲአሁ።

"ይህ ሕመም፡ ለሞት አይደለም፤ የእግዚአብሔር ክብር ሊገለጽበት፥ [እኔም] የእግዚአብሔር ልጅ፡ ስለእርሱ፡ ልከብርበትና ልመሰገንበት ነው እንጂ።" ብሎ የተናገረው? ይህን፡ የመለኮታዊ ቃሉን እውነታ፡ ሊያረጋግጥላቸው አይደለምን? አዎን! ነው እንጂ።

ደግሞስ፡ ለዚህ ካልኾነ በቀር፡ ታዲያ! ለምንድር ነው፡ ለደቀ-መዛሙርቱ፡ "አልዓዛር ዐርክነ ኖመ፤ ወባሕቱ፡ አሐውር አንቅሖ።

"ወዳጃችን አልዓዛር ተኝቷል፤ ነገር ግን፡ ከእንቅልፉ ላስነሣው እኼዳለሁ።" ያላቸው? ደቀ-መዛሙርቱም፡ ልጀ ወዳጀ የተናገራቸው፡ ስለሞቱ እንቅልፍ መኾኑን ሳያውቁ፡ ስለእንቅልፍ መተኛት ያላቸው መስሏቸው፡ መልሰው፡- "እግዚኦ! እመሰ ኖመ፡ ይነቅህ፤ ወይጥዒ።

"ጌታ ሆይ! ተኝቶስ ከኾነ፡ ይድናል።" ባሉት ጊዜ፡ እርሱ ደግሞ፡ "አልዓዛር ሞተ! ወአንሰ እትፌሣሕ በእንቲአክሙ፤ እስመ ኢሀሎኩ ህየ፡ ከመ ትእመኑ።"

"[እንደሙታን እምነት] አዎን! አልዓዛር ሞቷል፤ [ነገር ግን፡ እንዳልሞተ፡ ላሳያችሁ ስለኾነ፡ ይህን፡ የእግዚአብሔርን እውነታ ታምኑ ዘንድ፡ በዚያ ባለመኖሬ፡ ስለእናንተ፡ እኔ፡ ደስ ብሎኛል።" የሚል መልስን፡ ለምን፡ በግልጽ፡ እንደገና ሰጣቸው? ያንኑ፡ የመለኮታዊ ቃሉን እውነታ፡ መልሶ ሊያረጋግጥላቸው አይደለምን? አዎን! ነው እንጂ።

እንዲሁም፡ ልጄ ወዳጄ፡ ወንድማቸው፡ አኹን እንደሚነሣ፡ ለአልዓዛር እኅቶች ባበሠራቸው ጊዜ፡ እነርሱ ግን፡ በመጨረሻው ትንሣኤ ዘጉባኤ ጊዜ የሚነሣውን ትንሣኤ መስሏቸው፡ በዚያን ጊዜ እንደሚነሣ እንደሚያምኑማ ሲነግሩት፡ ያኔም የሚያስነሣው፥ ዛሬም የሚያስነሣው፡ እርሱ መኾኑን በማረጋገጥ፡ ለምን፡ "አነ ውእቱ፡ ትንሣኤ፥ ወሕይወት። ዘየአምን ብየ፡ እመኒ ሞተ፡ የሐዩ። ወኵሉ፡ ዘሕያው፥ ወየአምን ብየ፤ ኢይመውት ለዓለም።"

"ትንሣኤ እና ሕይወት፡ እኔ ነኝ። የሚያምንብኝ፡ [አኹን] ቢሞት እንኳ፡ ሕያው ነው። [አኹን] ሕያው የኾነ፥ የሚያምንብኝም፤ ለዘለዓለም አይሞትም።" አላቸው? አኹንም፡ ያንኑ፡ የመለኮታዊ ቃሉን እውነታ፡ እንደገና ሊያረጋግጥላችው አይደለምን? አዎን! ነው እንጂ። (ዮሐ. ፩፥ ፩-፺፫።)

ደግሞስ፡ ለምንድር ነው፡ ትጉሁና አሸናፊው ሐዋርያዊ አገልጋያችን ጳውሎስ፡ "ወይትነሥኡ ምውታን መቅድመ፡ እለ ሞቱ፡ በሃይማኖተ ክርስቶስ። ወእምዝ፡ ንሕነ ሕያዋን፡ እለ ንተርፍ፡ ንትመሠጥ በደመና፡ ምስሌሆሙ ኅቡረ፤ ከመ ንትቀበሎ ለእግዚእነ፡ ውስተ አየር፤ ወንሄሉ እንከ፡ ዘልፈ፡ ኀበ እግዚእነ።

"'በክርስቶስ አምነናል!' ብለው ያረፉ ሙታን፡ አስቀድመው ይነሣሉ። ከዚህ በኋላ፡ በሕይወተ-ሥጋ እየኖርን ያለነው፡ እኛ፡ ሕያዋኑ ግን፡ ጌታችንን [ኢየሱስ መሲሕን] በአየር ልንቀበል፥ ከዚያ ወዲያም፡ ዘወትር፡ በእርሱ ዘንድ ልንኾን፡ ከእነርሱ ጋር በአንድነት፡ በደመና እንነጠቃለን።" ብሎ የጻፈላችሁ? ይህን፡ የልጄን የወዳጄን የኢየሱስ መሲሕን፡ መለኮታዊ ቃል፡ እውነተኛነቱን፡ ሊያረጋግጥላችው አይደለምን? አዎን! ነው እንጂ። (፩ተሰ. ፬፥ ፲፮-፲፯።)

እናንተም ልጆቼ! ፍጡሮቼ! በእግዚአብሔራዊቷ እውነትና በመንፈስ ቅዱሳዊው አምልኳችሁ፡ እየራሳችሁን፡ ለዚህ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ እምነታችሁና ምግባራችሁ ዐብቅታችሁ ከተገኛችሁ፡ ይህ፡ በአልዓዛር ሰውነትና እምነት ላይ የተከሠተው፡ የልጄ የወዳጄ የኢየሱስ መሲሕ፡ የትንሣኤና የሕይወት ቃል፡ በእያንዳንዳችሁም ላይ በእውንነት የሚገለጽ ይኾናል።

<u>አዎን! ዛሬ፡ አኹን፡ በዚች አፍታ፥ በዚህ የሕይወተ-ሥጋ ሰብእናችሁ፥ በዚች፡ በቆማችሁባት ምድር ላይ የምትገኙበት ህልውናችሁ፡ ከእኛ እንደአንዳንችን፡ ደጋጎቼና የእውነት ልጆቻችን ኾናችሁ፡ በመጀመሪያው የመንፈስ ትንሣኤና በዘለዓለማዊቷ ሰንበት የምትኖሩት፡ የሕያዋኑ ዓለም እንጂ፡</u> <u>*ሰዶሞችና እነርሱን የመሰሉት፡ የሓሰቱና የክፉው ልጆች የኾኑት፡ ሥጋውያኑና ዓለማውያኑ ፍጡሮቻችን የሚናውዙበት፥ የሚሠቃዩበትም፡ የሙታኑ ዓለም አይደለም።*</u>

## መፈጽም

በመሠረቱ፡ በጥንተ-ተፈጥሮው፡ እንደእኛ፡ እንደእግዚአብሔርነታችን፡ እርሱንም፡ በሰውነቱ፡ አንድ አካልና አንድ ባሕርይ አድርገን፡ የፈጠርነውን ሰውን፡ እንደእኛው፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታ፡ ለኹለት የከፈልነው፥ በጋብቻ ፍቅርና በሩካቤ-ሥጋም ግንኙነት መልሰን፡ አንድ ያደረግነው፡ በበለጠ ተሳስቦና ተጣብቆ፥ ተዋድዶና ተስማምቶ፥ መሰሎቹንም እየወለደና እየተበራከተ፡ በሰላምና በጸጥታ፥ በደስታና በተድላም እንዲኖር እንጂ፡ እንዲህ፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታ ምክንያት ሳይቀር፡ ወንዱ፡ በሴቷ ላይ የግፈኛነት፥ ሴቷም፡ በወንዱ ላይ፡ የሴረኛነት ውሳጣዊ መቃቃርን ይዘው፡ እስከዚህ በከረረ ዕብሪትና ጥቃት፥ ጠብና ጥላቻ፡ ጭቆናና ቂም በቀል፥ እርስ በርሳቸው፡ ለዝንተ ዓለም፡ ሲጠላለፉና ሲተላለቁ እንዲኖሩ አልነበረም።

በባልና ሚስት መካከል ሊኖር ስለሚገባው፡ ፍጹም ፍቅርና ስምምነት፥ ሰላምና ዕርቅ፥ መተሳሰብና መተዛዘን፥ መተባበርና መተጋገዝ፥ መመካከርና መወያየት፡ እኔ ድንግል ማርያም እና ልጄ ወዳጄ ኢየሱስ መሲሕ፡ በእግዚአብሔር አብነትና ሙሽርነት፥ በእግዚአብሔር እናትነትና ልጅነት፡ ቀድሞ፡ ከፍጥረተ-ዓለም በፊት፡ በመለኮታዊው ህልውናችን፥ ኋላም፡ በትስብእት (በሰውነት) አስተርዮታችን [መገለጫችን] ጊዜ፡ በቃና ዘገሊላ የሠርግ አዳራሽና በቀራንዮ የስቅለት አደባባይ ላይ ሳይቀር፡ ለአብነትና ለአርአያነት ያሳየናችሁ እምነትና ምግባር፡ ለእናንተ፡ እንዴት ሊበቃችሁ የማይችል ሳይኾን ቀረ? ከሚበቃ በላይ፡ የተትረፈረፈ ነበር።

በእናንተ ላይ፡ ይህ ኹሉ፡ የሕይወት ውድቀት የደረሰባችሁና እየደረሰባችሁ ያለው፡ እኛ የሠራንላችሁን የመልካም ጋብቻንና የትዳር ኑሮን ሥርዓት ጠብቃችሁና አጽንታችሁ መቀጠልን ትታችሁና "እንቢ!" ብላችሁ፡ ግብረ-ሰዶምን ወደመሰለ ኢተፈጥሮአዊና ኢ-እግዚአብሔራዊ ወደኾነ፡ ሰው-ሠራሽና ብልሹ ልማድ የመራችሁን፡ የየራሳችሁን፥ ሰይጣናዊዉንም ክፉ አስተሳሰብ በመከተላችሁ እንደኾነ ግልጽ ነው።

ያልነበረውና የሌለው፡ ስሑቱና ጠማማው ክፉ አስተሳሰብ፡ ከየትና እንዴት እንደመጣ፡ ቀደም ባሉት የዐዋጅ ቃሎቼ ውስጥ ከተካተቱት ሓተታዎች ጋር፡ በዚህም በአኹኑ የዐዋጅ ቃሌ ውስጥ፡ በተጨማሪ ታክሎ አግኝታችሁታል።

እንግዴህ፡ በተፈጥሮ አካሉና ባሕርዩ፡ ፍጹም ጤናማ በመኾኑ፡ ምናልባት፡ በባዕድ አምልኮና በዚህ የግብረ-ሰዶም ርኵሰት ተሳታፊ ሳይኾን የቀረ፡ የዓለም ኅብረተሰብ ካለ፡ ያ ወገን፡ በሙሉ፡ ኹሉም፥ እያንዳንዱም፡ ተባብሮ፡ ይህ ጠንቅ፡ ዛሬ፡ የይፋ ሕጋዊ ዕውቅናን ተቀዳጅቶ ከተንሠራፋበት ግዛቱ፡ ቢቻል፡ በቶሎ፡ በንስሓ እንዲወገድ፥ ባይቻል ግን፡ በዚያው፡ በገመናነቱ እንኳ እንዲገታ ሊያደርግ ይገባዋል።

ይህን ካላደረገ ግን፡ በቀደመው ዘመን፡ ያኔ፡ እኒያ፡ ኹለቱ መለኮታውያት ልኡካት፡ በእንግድነት በተገኙበት፡ በሰዶምና በገሞራ ከተማዎች፥ በሎጥም ቤትና ቤተሰብ ላይ የደረሰው አሠቃቂ የሰዶሞች ድርጊት እንደገና መፈጸሙ፥ ያስከተለውም የቃጠሎ ዕልቂት፡ በእየቤቱና በእየኅብረተሰቡ፥ በእየአገሩና በዓለሙ ኹሉ ተደጋግሞ መድረሱ እንደማይቀር፡ ማንም ሊጠራጠር አይቻለውም።

በአኹኑ ጊዜ፡ በያገሩና በመላው ዓለም እየተካኼደ ያለው አዝማሚያ፡ ይኼው ስለኾነ፡ እያንዳንዱም፥ ኹሉም፡ ሰብኣዊ ፍጡር፡ በብርቱ አስቦበት፡ በግልም ኾነ በኅብረት፥ በመንፈሳውያኑ የሃይማኖት ተቋማትም ኾነ፡ በሥጋውያኑ የመንግሥታት ድርጅቶች ዘንድ፡ ተገቢው የመፍትሔ ተግባር ተካኺዶ ሊከናወን እንደሚገባ፡ ኹላችሁም፡ ወንዶቹም፥ ሴቶቹም ልጆቻችን፥ የሰው ወገን የኾናችሁ ፍጡሮቻችንም፡ በብርቱ ልታጤኑት ያስፈልጋችኋል።

ይህ ካልኾነ ግን፡ ይኼ ጠንቅ ከሚያስከትለው፡ ማዕበላዊ የጥፋት ውኃና ነበልባላዊ የእሳት ድምሳሴ ሊያወጧቸው፡ የእግዚአብሔር መላእክት፡ በእየቤታቸው፡ በእንግድነት ከሚገኙላቸው፡ ከእውነተኞቹ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያ ልጆቹ በቀር፡ ሌላው ሰብኣዊ ፍጥረት ኹሉ፡ የእርሱ ከኾነው ሓሳዊ ዕውቀቱና እምነቱ፥ ጥበቡና ሥልጣኔው፥ ክብረቱና የመሣሪያ ኃይሉ፥ ሀብትና ንብረቱ ጋር፡ ዕጣ ፋንታውና ዕድለቢስ ጽዋው፡ የሰዶሞቹ እንዲኾን፡ በገዛ ፍላጎቱና ምርጫው፡ እየራሱን፡ ለማይቀረው፡ ለነፍስ፥ ለሥጋና ለመንፈስ ጥፋትና ድምሳሴ ያጋለጠ መኾኑን ዐውቆና ተገንዝቦ፡ ለዚሁ፡ ለሚጠብቀው አሳዛኝ ፍጻሜውና አሠቃቂ ዕድሉ መዘጋጀት ይኖርበታል።

እንግዴህ፡ ይህን፡ የዐዋጅ ቃሌን፡ እኔም፡ **"ዘቦ ዕዝን፡ ሰሚዐ ለይስማዕ! የሚሰማ ጆሮ ያለው፡ ይስማ!"** በሚለው፡ በልጇ በወዳጇ በኢየሱስ መሲሕ፡ መለኮታዊና ትስብእታዊ የዐዋጅ ቃሉ መደምደሚያ እፈጽማለሁ። (ማቴ. ፲፩፥ ፲፭።)

**ተዐውደ፡ በሚያዝያ ፲፯ ቀን፥ ፳፻፰ ዓመተ ምሕረት ታወጀ።**

ላእከ ኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር፣
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፣
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
ስመ ጥምቀቱ፡ ኂሩተ-ወልድ።

\+ \+ \+